# አሻራ

ቁጥር 2

ሰኔ 2007



## ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም

የአረቡ ዓለም መቆራቆስ
ቀይ ባህርን
ይሻጋገር ይሆን ?
ዩሱፍ ያሲን

"ጠፍአት ሃገርነ"
ትናንት ማታ ጨረቃዋንም
አዋልደናል!
ጸጋዬ ገብረመድህን አርአያ

ቆም በል!
ህዝብ ከሚያልቅ ህዝብ
ቢያልቅ ይሻላል!
ደረጀ ደስታ

በሁሉም የዝግጅት አይነቶች ብቃትና ልምድ ያለው






አቢሲኒያ የኢትዮጵያዊያን ሬስቶራንት፡-ሲድኒ

ስልክ ቁጥራችን 0470087645



# አሻራ


ጥቂት . . . ከዝግጅት ክፍሉ ብዕር 4



ቆይታ ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር 5

ጸጋዬ ገመድህን አርአያ 8
“ጠፍአት አገርነ”
ትናንት ማታ ጨረቃዋንም አዋልደናል!

ዩሱፍ ያሲን 16
የአረቡ ዓለም መቆራቆስ ቀይ ባህርን ይሻገር ይሆን?

ደረጀ ደስታ 21
ቆም በል!
ህዝብ ከሚያልቅ ህዝብ ቢያልቅ ይሻላል!

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ 25
በካድሬዎች የተወረረ ዩኒቨርሲቲ ሆኗል ነው የምልህ፤ አለቀ!

ዳንኤል ድርሻ 31
አደጋን ‹ንቀው› ፣ ሞትን ለሚተናነቁ ዜጎቻችን ስደት :- የአገዛዙ ሚና

እዮብ ሳህሌ 33
አይ ኤስ ማነው? ኢራኖች እንደሚሉት እውን “ሜድ ኢን አሜሪካ” ነውን?

ዶ/ር መቅደስ መስፍን 11
.. መንግስቱ ኃይለማሪያምን ውረድ ባለበት ወቅት የተፈጠረው ነገር አሁንም ድረስ ሳስበው ይገርመኛል። በጊዜው እኔ እዚሁ አሜሪካን ሃገር ነበርኩ። ይህ በሆነበት ዕለት ወይም ማግስት አንድ ለሱም ለኔም ወዳጅ የሆነ ሰው ደውሎ ....

ወንድማገኝ ጋሹ 13
...ፕሮፌሰር መስፍንን ቀርበህ ስትረዳቸው፣ ጀሮህን ከፍተህ ስታደምጣቸው በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ ንጉስ ዳዊት ለልጁ ለሰለሞን “ሰው ሁን!” ያለው ቃል ነፍስህን የዳሰሳት ይመስልሀል። ...

ያሬድ ኃይለማሪያም 15
...ፕ/ር መስፍን ለድሆች መቆርቆር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ድሃ ገበሬዎች ህይወት ለመለወጥ የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችንም እያካሂዱ (ሰሚ ጠፋ እንጂ) ጠቃሚ ሃሳቦችንና ምክሮችን በማፍለቅ ይታወቃሉ። ...

ፕ/ር መስፍን በኔ ዕይታ 27
ጋሽ መስፍን ቂመኛ አይደሉም። ላመኑት ነገር በጽናት ይቆማሉ። ዕምነታቸውን ይኖሩታል። የመብት ነገር የነፍሳቸው ጩኸት ነው። **(መስፍን ገብረ ሥላሴ ሲድኒ)**

...... ፕ/ር ማይክሮፎኑን ከያዙ በኋላ ግን ሁለንተናችን ጆሮ ብቻ ሆነ። በተለመደው ብቃት አዳራሽን ተቆጣጠሩት። ታሪክ ራሱ ስጋ ለብሶ የመጣ ያህል የሁሉም ሰው ቀልብ ዕንግዳችን ላይ ሆኖ አመሸ።(**አያሌው ሁንዴሳ - ሲድኒ**)



አዘጋጆች
- ሳምሶን አሰፋው
- አቢይ አፈወርቅ

asharamagazine@gmail.com

# ጥቂት . . . ከዝግጅት ክፍሉ ብዕር

እኛ ባሰብነው የጊዜ ቀመር ባይሆንም፤ እንሆ! አሻራ ቁጥር ሁለት ለንባብ በቅታለች። ለመዘግየቷ ምክንያት የሆኑ በርካታ ያልተጠበቁ ክስተቶች ነበሩ። በዋናነት የምንጠቅሰው ግን በየመን፤ በደቡብ አፍሪካና በሊቢያ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን አስቃቂ የግፍ ግድያ ነው። ከዚያም ጋር ተያይዞ በሃዘንና በቁጭት የተብከነከነው ኢትዮጵያዊ በሚገኝባቸው የዓለም ጥጋግ ሁሉ ይከናወኑ የነበሩ እንቅስቃሴዎች እኛም ዘንድ ነበሩና ለአሻራ መዘግየት ተጠቃሽ ምክንያት ናቸው ። "ጥቁር ሳምንት"።

እንሆም! አሻራ ቁጥር ሁለትን በግፍ ላለቁት ወገኖቻችን መታሰቢያ ትሆን ዘንድ ሰይመናል።

ለአሻራ ቁጥር ሁለት ግብዓት የሆኑ አንዳዶቹን ጽሁፎች የተቀበልነው ቀደም ብለን ነው።እናም ከላይ በጠቀስነው ምክንያት መዘግየታችን የጽሁፎቹን ወቅታዊነት ሊያደበዝዝ ይችላል የሚል ሥስ ስጋት ሳያሳድርብን አልቀረም። ይሁንና በክለሳ መልክ ባደረግነው ግምገማ፤ በመጀመሪያ አሻራ ቁጥር ሁለት ልትዘክራቸው በተነሳቺው ታላቁ ኢትዮጵያዊ ምሁር ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም ዙሪያ የቀረቡ ዝግጅቶች በሙሉ ዝክረ-ታሪክ ናቸውና ወቅታዊነት ከሚለው ጊዜ-ወለድ ችግር የጸዱ መሆናቸው አበረታታን።

አሻራ አንጋፋውን ምሁርና የሰብአዊ መብት ተሟጋች መዘከር የምትጀምረው ከራሳቸው ጋር ባደረገቺው ቆይታ ነው። በመቀጠልም ከበኩር ልጃቸው ከዶክተር መቅደስ መስፍን ወልደማሪያም ጋር ለአፍታም ቢሆን ተወያይታለች።

ፕ/ር መስፍን በመሰረቱት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ አባል ሆነው ከሳቸው ባገኙት ስልጠናና ልምድ ዛሬም ድረስ በሰብአዊ መብት ተሟጋችነት የዘለቁት ወንድማገኝ ጋሹና ያሬድ ኃይለማሪያም ስለ ፕ/ር መስፍን የየግላቸውን ምልከታ አቅርበዋል።

ከወደ ሲድኒም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞው የተማሪዎች ማህበር ዋና ጸሃፊ መስፍን ገብረስላሴ ከ14 ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ፕ/ርን ለመጀመሪያ ግዜ ያገኘበት አጋጣሚ እንደነበር አስታውሶ ዛሬ ከ14 ዓመት በኋላ በሲድኒ ሲያገኛቸው የተሰማውን ስሜት ይገልጽልናል። እንደ መስፍን ሁሉ ከዛው ከሲድኒ አያሌው ሁንዴሳ ከ20 አመት በፊት ከሚያውቃቸው ታላቅ ሰው ጋር በሲድኒ የነበረውን ቆይታ ያስቃኘናል።በአካል እንጂ በመንፈስ ዛሬም ጠንካራ ናቸው ይለናል። በፕ/ር መስፍን ዙሪያ እነኚህን አካተናል። ይሁንና ያካተትናቸው ዝግጅቶች የእኝህን ታላቅ ሰው ድንቅ ስብዕናና ገድል በበቂ ይዘክራሉ የሚል እምነት የለንም። እንደ መነሻ ይሆኑ እንደሁ እንጂ።

ወደ ሌላው የመጽሄታችን ቅርቅብ ስናልፍ ፦ ከ20 አመት በፊት የጻፉቸውን ዘመን ተሻጋሪ ጽሁፎች ዛሬም ድረስ ከጦቢያ መጽሄት ማህደር እያወጣን የምናነብለት የጸጋዬ ገብረመድህን አርአያ ጽሁፍንም የተቀበልነው ቀደም ብለን ቢሆንም "ወቅታዊነት..?" የሚል ስጋት ሲያልፍም እንደማይነካው ግን እርግጠኞች ነበርን። በዚህ እትም ለንባብ ካቀረበልን "ትናት ማታ ጨረቃዋንም አዋልደናል" ከሚለው ጽሁፉም ያስተዋልነው ይህንኑ ነው። ዛሬ ላይ ሆኖ ነገንም የሚዋጅ የብዕር ፍሬ መሆኑን።

ጋዜጠኛ ደረጀ ደስታ "ቆም በል! ህዝብ ከሚያልቅ ህዝብ ቢያልቅ ይሻላል" የሚል ርዕስ የሰጠው ጽሁፉ፤ ከርዕሱ ጀምሮ ጥያቄ አጭሮ እስከ ድምዳሜው በለዛ ሲፈስ፤ አንባቢም እንዳያልቅ የተሳሳለት ሕዝብ የትኛው ነው? እንዲያልቅ የተፈረደበትስ..? የሚሉትን ጥያቄዎች ሰንቆ አብሮ በንባብ እንዲፈስ የማድረግ ልዩ አቅም አለው። በኛ እይታ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር የነበሩት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ "ዩኒቨርሲቲው በካድሬዎች ተወሯል" ይላሉ።ከሳቸው ጋር በነበረን ጊዜ ሌሎችም ጉዳዮችን አንስተናል።

የዘወትር ተባባሪያችን ዩሱፍ ያሲን " የአረቡ ዓለም መቆራቆስ ቀይ ባህርን ይሸጋገር ይሆን?" ሲል ይጠይቅና ለጥያቄው ቀጥተኛ መልስ ሳይሰጥ የቀይ ባህር ራስጌና ግርጌ አገራትን ወቅታዊ የፖለቲካ ጡዘት እየገላለጠ በርዕስነት ለወረወረው ጥያቄ የራሳችንን መልስ እንድንፈልግ ያግዘናል። በዚህ አጋጣሚ የዩሱፍ ያሲን ጽሁፍም የተላከልን "ከጥቁር ሳምንት" ቀደም ብሎ መሆኑን መግለጽ አግባብ ይመስለናል። ምናልባት በጽሁፉ ውስጥ የቅርብ ክስተቶች ካለመጠቀሳቸው ጋር በተያያዘ የሚነሳ ጥያቄ ካለ ማለታችን ነው።

የወያኔ መንግስት ከጥቂት ወራት በፊት ከሃገር እንዲሰደዱ ምክንያት ከሆናቸው በኬንያ ከሚገኙ የነጻው ፕሬስ ባልደረቦች መሃል፤ ጋዜጠኛ ዳንኤል ድርሻ ፤ ማቆሚያ ላጣው የወገኖቻችን ስደትና ስቃይ ትልቁ ባለድርሻ ተጠያቂ አገዛዙ መሆኑን ዋቢ እየጠቀሰ ያስነብበናል።

እዮብ ሳህሌ አረመኔው አይ ኤስ እውን የአሜሪካን ስሪት "ሜድ ኢን አሜሪካ ነውን? በሚል ጥያቄያዊ ርዕስ ሥር የአይ ኤስን እንቅስቃሴ የቃኝ ጽሁፍ አቅርበዋል።

ውድ አንባቢያን በአሻራ ቁጥር ሁለት እነኚህ ዝግጅቶች አቅርበናል። ጊዜ ወስዳችሁ እንደምታነቧቸው እምነታችን ነው። ከመሰነባበታችን በፊት ግን ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ለአሻራ ግብዓት የሆኑ፤ በሳልና አስተማሪ ጽሁፎቻቸውን ላቀረቡልን ወገኖቻችን እጅግ ከፍ ያለ ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን።

የአሻራ ቁጥር 3 ሰው ይበለን!

አዘጋጆች ሳምሶን አሰፋውና ዓቢይ አፈወርቅ

ታለቁ የሰብአዊ መብት ተሚጋች

# ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም

ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም ዛሬ የ85 ዓመት አዛውንት ናቸው። ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚያከብራቸው፤ ከወጣት እስከ አዛውንት የሚያደንቃቸው አንጋፋ ምሁርና የሰብአዊ መብት ተሚጋች። በስራቸው ዓለም አቀፍ ዕውቅና ቢያካብቱም እንደ አብዛኛው ምሁር ያፈራቸውን ምድር ለቀው መሄድ አልፈቀዱም። ህይወትና እጣ ክፍላቸውን ከድሃው ወገናቸው ጋር እንዲሆን መርጠው፤ ግፉንም አብረው ተገፍተዋል፤ ስቃዩንም አብረው ተሰቃይተዋል። አሻራ እኝህን ታላቅ ሰው ለመዘከር ዕድል በማግኘቷ ክብር ይሰማታል።

ፕ/ር ሶስት መንግስታትን የዘለቁ ከወርቅ ጸዳል የሚያበሩ አንጸባራቂ ገድሎች ባለቤት ቢሆኑም፤ ሙገሳና አድናቆት፤ ምስጋናና ከፍ ከፍ ማለትን አይወዱም። ስለሳቸው እንዲወራም አይሹም። ይሁንና ታሪክ ነውና ከወጣትነት ዕድሚያቸው ጀምሮ ከሰሯቸው ስራዎች በጣም ጥቂቶቹን ብቻ እንደ መግቢያ እንጠቃቅሳለን።

### ፕ/ር ገንቢ ሃሳቦችን ለባለስልጣናት አቅርበዋል

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የአንድ ዓመት ብሔራዊ አገልግሎት የሚሰጡበትን ሃሳብ አመንጭተው በግዜው የአአዩ ፕሬዚዳንት ለነበሩት ለልጅ ካሣ ወ/ማርያም በዝርዝር የተሠራ እቅድ አቅርበው ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በተግባር ሲውል እሳቸው ለገጠሬው ያሰቡትን ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ ሳይሆን በየከተማው ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ከማስተማር አላለፈም።

እንደገና በ60 ዎቹ ዕድሜ ውስጥ ሆነው ኮ/ል መንግስቱ ቢሮ ቀጠሮ አስይዘው ለሁለት ሰአት ያመኑበትን ሁሉ ሳይሸሽጉ አስረድተዋቸዋል፡፡ ብእራችውን አውጥተው ማስታወሻ ሲይዙ የነበሩት ኮ/ል መንግስቱ ምንም የረባ ነገር ሳይፈይዱ አመታት ተቆጠሩ። በመጨረሻም አመሻሽ ላይ የወንድ በር በማሳየት ከስልጣንህ ውረድ ቢሉት ምክራቸውን አጣጣለ። ጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ አገሪቷንም ጥሎ ፈረጠጠ።

### ንጹሃን ወገኖችን ከአንባ ገነን ባለስልጣናትና አሽከሮቻቸው ታድገዋል

በደርግ ጊዜ በተለይ በሰባዎቹ መጨረሻና ሰማኒያዎቹ መጀመሪያ ደርግ አንዳንድ የትግራይና የኤርትራ ተወላጆች ላይ ጀምሮት የነበረውን ግድያ እና አፈና ባለስልጣናቱን በግል በማነጋገር የበርካታ ሰዎችን ህይወት ታድገዋል ።

በኢህአዴግ ዘመን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤን በማቋቋም በአገዛዙ ባለስልጣናትና የደህንነት ስራተኞች በህዘቡ ላይ የሚፈጸመውን ግድያ ፤ማሰቃየት(ሰቆቃ) እስር ፤እንግልት በተጨባጭ ማስረጃ በማረጋገጥ ለኢትዮጵያ ህዝብ ፤ ለአለም ህዝብ እንዲሁም ለራሳቸው ለኢህአዴግ ባለስልጣነት ሳይቀር አጋልጠዋል። በልዩ ልዩ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጉባኤዎች ላይ በመገኘት(የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ) ይህንኑ በደልና ግፍ አጋልጠዋል፤ መስክረዋል። በሃገር ውስጥ ስለሰብአዊ መብት ምንነት አስተምረዋል ሰብከዋል፤ ይህን ሲያደርጉ በኢህአዴግ መንግስት ታስረዋል፤ ማስፈራሪያና ዛቻ ደርሶባቸዋል። በሳቢያውም ሰው ሁሉ ፈርቶ ሸሽቷቸዋል።

ኢሰመጉ ሲመሰርቱና ሲመሩ በነበረበት ወቀት በቂ የገንዘብ ድጋፍ ባለመኖሩ ለጡረታ ዘመን የቆጠቡትን የግል ገንዘባችውን የሰብአዊ መብት ጥሰቱን ለማጋለጥ በየሃገሩ ሲዘዋወሩ ለአውሮፕላን ትኬትና የጉዞ ወጭ በማዋል ጥሪታችውን አሟጠዋል።



### ጥናትና ምርምር ለተሻለች ኢትዮጵያ

ፕ/ር በሳይንሳዊ ጥናት የተደገፈ ድምዳሜ አዋጭ ነው ብለው ያምናሉ። ለብዙ ሥራዎቻቸው መሠረት የሚያደርጉትም ይህንን ነው። ይህንንም መሠረት አድርገው የወደፊትን አደጋ በግልጽ እያዩ የማይሰሟቸውን መሪዎች ሲመክሩ ኖረዋል። የሚያሳዝነው የሰማቸው አለመኖሩና የፈሩት ሁሉ መድረሱ ነው።

የችጋር መንስኤ ብልሹ አስተዳደር ያለው መንግስት እንጂ የዝናብ እጥረት ወይም የበረዶ መዝነብ አልያም የአንበጣ መንጋ ወዘተ አለመሆኑን አስረግጠው ገልጸዋል። የችጋርና የፍጹም ድህነት ምክንያቶች ብልሹ ስርአቶች መሆናችውን ፕ/ር በጥናት ያረጋገጡት ከ1984 እኤአ በፊት ነበር፡፡የዚህ ጥናታቸው ውጤት የሆነው መጽሃፍ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ማስተማሪያና ማጣቀሻ ሆኖ ይጠቀሙበታል።

ይህንን ጥናት እነዲያደርጉ ለፕ/ር የገንዘብ ድጋፍ ሲሰጣችው የነበረው ሁለተኛ ዲግሪያችውን የተማሩበት ዩኒቨርሲቲ ጥናቱንና መደምደሚያውን ከገመገመ በኋላ የክብር (HONORARY) DOCTORATE OF HUMANE LETTERS ሰጥቷቸዋል።

የሚገርመው ፕ/ር መጽሃፋቸው ከደራሲውና አሳታሚው እውቅና ውጭ በድጋሚ በሌሎች ታትሞ በለንደን ጥቁር ገበያ ሲሸጥ እንኳን ለመሞገት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡


### ለወገን ስለመድረስ - ከርሃብ ጋር ግብግብ

በ1951 ዓ.ም በትግራይ ሀይለኛ ርሃብ ገብቶ ህዝብ በችጋር በጅምላ ያልቅ ነበር ፡፡ ምንም እንኳን ረሃቡ በንጉሰ ነገስቱ ባይታወቅም ለትግራይ መኳንንትና ለሌሎችም ባለስልጣናት ድብቅ አልነበረም፡፡ በዚህ ግዜ ፕ/ር ገና የ29 አመት ወጣት ነበሩ፡፡ ወጣቱ መስፍን በትግራይ ርሃብ ገበቶ ሰዎች በችጋር እያለቁ መሆኑን ከአንድ ባለጸጋ ወይዘሮ ይሰማሉ ፡፡፡ ነገሩን እነደሰሙም በራሳችው ወጭ አዲግራት ድረስ ሄደው ችግሩን ከተመለከቱ በኋላ ህዝብ እንዲያውቅና እርዳታ መሰብሰብ እንዲቻል ለጋዜጣ ጹሁፍ አዘጋጅተው ይልካሉ፤ ነገር ግን ጽሁፉን በጋዜጣ ማውጣት አልተቻለም፡፡ በእንደራሴዎች በኩል ለፓርላማ ለማቅረብ ሞከሩ፤ ይህም አልተቻለም፣ በሚያውቁዋቸው ባለስልጣናት በኩል ነገሩ መፍትሄ እንዲገኝለት ጣሩ፤ አልተሳካም፡፡

በመጨረሻ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አብሯቸው የተማረውና የጃንሆይ ልዩ ጸሃፊ ሆኖ የሚያገለግል ወዳጃቸውን በስፍራው ተገኝተው ያነሱትን የርሃብተኞቹን ሰቆቃ የሚያሳይ ሁለት ፎቶግራፍና ደብዳቤ ለጃንሆይ እነዲሰጥላቸው ይጠይቁታል። ወዳጃቸውም መልዕክቱን ለጃንሆይ ያደርሳል፡፡ ጃንሆይ መልዕክቱ እንደደረሳቸው ለተጎጂው ህዝብ እርዳታ ባስቸኳይ እንዲሰጥና ወጣቱ መስፍንም የኮሚቴ አባል ሆኖ እርዳታ እነዲያከፋፍል አዘዙ።

በ1964/65 ዓ.ም ችጋር ለሁለተኛ ግዜ በተለይ በወሎ ብዙ ህዝብ መፍጀት ይጀምራል፡፡የሄኛውም ችጋር እንደ 1951 የትግራይ ችጋር ሁሉ ከንጉሱና ከህዝቡ ይደበቃል፡፡ ፕ/ር በድጋሚ የህዝብን ሰቆቃ ለማየት ብርታት አጡ። እናም ሁኔታውን ለባልደረቦቻቸው(ጌታቸው ኃይሌ፤ አብረሃም ደሞዝ እና ሌሎችም)ካስረዱ በኋላ፤ በስፍራው ተገኝተው ሰቆቃውን በፎቶግራፎችና በመቅረጸ ድምጽ ቀርጸው እንዲያመጡላችው ያደርጋሉ ፡፡አሁን ፕ/ር እንደ 1951 የትግራይ ችጋር በየባለስለጣናቱ ደጃፍ ደጅ አልጠኑም፡፡

በቀጥታ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ባለው ቢሯቸው ውስጥ አውደ ርእይ (ኤግዚቢሽን) አዘጋጅተው የርሃብተኞቹን ፎቶና የጣር ድምጽ ለተማሪዎችና ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አቀረቡት ፡፡ ተማሪዎች ሌሊቱን አምጸው አደሩ፡፡በዚህ መልክ ለመጀመሪያ ግዜ የወሎ ረሃብ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም ተጋለጠ፡፡



ከብዙ በጥቂቱ ይህን ከጠቃቀስን አሁን ወደ ቃለ ምልልሱ እንለፍ። ⇨



# የአሻራ ቆይታ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጋር



**<u>አሻራ፡-</u> ሰላም ጤና ይስጥልን ፕሮፌሰር፤ በቅድሚያ ግብዣችንን ተቀብለው ለዚህ ቃለ መጠይቅ በመቅረብዎ በአንባቢያንና በመጽሄታችን ዝግጅት ክፍል ስም ከፍ ያለ ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን።**

**አስከትለንም በቅርቡ 85ኛ ዓመት የልደት በዓልዎን እንዳከበሩ ከማህበራዊ ድህረ ገጾች ተረድተናልና እንኳን አደረስዎ እያልን ረዥም እድሜና ጤና ይሰጥዎ ዘንድ በጸሎት የሚታገዝ መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን።**


**ወደ ዋናው ውይይታችን ከመግባታችን በፊት እስኪ እንደ መነሻ ስለጤንነትዎ በመግለጽ ቢጀምሩሉን! እንዴት ነዎት?**

<u>ፕ/ር፡-</u>በጣም ደህና ነኝ። የ85 ዓመቱ ጭነት እየከበደ፤ እየከበደ የመሄድ ስሜት አለው። እኔም ደግሞ ዝም ብዬ እቤት ቁጭ ማለት በመሆኑ ብዙም ስለማልንቀሳቀስ፤ ያ ነው እንጂ እግዚአብሄር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ።ምንም የማማርርበት የጤና ችግር የለብኝም። ጓደኞቼ ሁሉ የሉም እኮ! እንዲያውም ለጉድ የጎለተኝ አይነት ስሜት ነው የሚሰማኝ። እናም እግዚአብሄር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ።

**<u>አሻራ፡-</u>ሃገራችን በሶስት የተለያዩ መንግስታት ውስጥ የነበራትንና ያላትን የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊና የፖለቲካ ገጽታ በንፅፅር ለማየት የሚያስችል ግዙፍ ልምድና ዕውቀት እንዳዳበሩ ይታወቃል። አሁን ላነሳ የፈለኩት ጥያቄም በሶስት መንግስታት ውስጥ ያለፉትን ትውልዶች እንዴት ያነጻጽሯቸዋል? የትውልድ መከፋፈያ እርከንስ በውል የሚታወቅ አሃዝ አለው ወይ የሚል ነው?**

<u>ፕ/ር፡-</u>በመሰረቱ ትውልድ በየ20 ዓመት የሚከፈል ይመስለኛል። ለምሳሌ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት አዛውንት የነበረው ክፍል አንድ ትውልድ ቢሆን ከዚያ የሚቀጥለው የኔ ትውልድ ነው። ከኔ ትውልድ ቀጥሎ ደግሞ አመጸኛው ትውልድ ነው(ሳቅ)። ኢ.ህ.አ.ፓ ፤ መ.ኢ.ሶ.ን ፤ ወያኔ ፤ ሻቢያ፤ ደርግ እነኚህ በሙሉ አንድ ትውልድ ናቸው። ሲጣሉ፤ ሲበጣበጡ፤ ሲገሉ፤ ሲጋደሉ፤ ቆይተው ለህዝቡ ምንም የበጀ ነገር ሳይሰሩ ቀሩ። አሁንም ድረስ ስልጣን ለመያዝ የሚታገሉትም ሆኑ ስልጣኑን ጨብጠው አንለቅም እያሉ ያሉት የዚሁ ትውልድ አካሎች ናቸው። የዚህ ትውልድ አካሎች አሁን ከ55 እስከ 75 ባለው የእድሜ ክልል ይገኛሉ። ከዚህ እድሜ በላይ ያለው አብዛኛው ሞቷል ያለውም በጣም አርጅቷል።

ከዚያ የሚቀጥለው አሁን በ35 እና 55 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ትውልድ ነው። ይሄ ትውልድ በደርግ ስርአት ትምህርት ለብ ለብ ከሆነ በኋላ ትምህርት ቤት በመግባቱ እንደ ኃይለስላሴ ጊዜ ተማሪ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያዳበረ አይደለም። በመሆኑም የማህበራዊም ሆነ የፖለቲካ አቋሙ የላላ ነው። በአብዛኛው የግል ሕይወቱን ለማሳካት አስፈላጊውን መስዋእትነት በመክፈል የሚባዝን እንጂ ለሃገርና ለወገን ሙብት በመታገልና በመቆም ረገድ ምንም ፍላጎታ ያላሳየ ትውልድ ነው ከ35 እስከ 55 ያለው ። የትውልድን ጉዳይ እንዲህ አድርጌ ነው የማየው።



**<u>አሻራ፡-</u>ከ35 በታች ያለውስ ትውልድ?**

<u>ፕ/ር፡-</u>ከ35 በታች ያለው ትውልድማ ገና ነው። በልምድም በዕውቀትም ገና አልዳበረም። ብዙም ሊታማ አይችልም። በእውነቱ ካየነው ደግሞ ይህ ትውልድ መሪም ያላገኘ ትውልድ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ደረጃ ይህን ወጣት ትውልድ እንዲህ ነው እንዲያነው ማለት ይከብደኛል።

**<u>አሻራ፡-</u>ሃገራችን በአሁኑ ወቅት ለምትገኝበት ውስብስብ የፖለቲካ አጣብቂኝ ዛሬ ከ55 እስከ 75 ዕድሜ ክልል የሚገኘውን ትውልድ ተጠያቂ የሚያደርጉ አሉ። ምን ያህል እውነት ነው?**

<u>ፕ/ር፡-</u>ትክክል ነው። ላለፉት 40 ዓመታት በሃገራችን የታየውና እየታየ ያለው የፖለቲካ ችግር ይህ ትውልድ የፈጠረው ችግር ነው። አሁንም ድረስ ይኸው ትውልድ ነው ስልጣን ለመያዝም ሆነ ላለመልቀቅ የሚሯሯጠው፡፡ ወያኔ፤ ሻቢያ፤ ደርግ ፤ ኢህአፓና መኢሶን ሁሉም ማርክሲስት ሌኒንስት ነን ብለው አንድ ርዕዮት ይዘው ቢነሱም አብረው መስራት አልቻሉም። ምክንያቱም የሁሉም ፍላጎት ስልጣን ነበር።

ባለፉት አርባ ዓመታት የሆኑት መጥፎ ነገሮች ሁሉ በነዚህ በአምስት ቡድኖች የሆኑ ናቸው። በትምህርት ረገድ በአንጻራዊነት ስናያቸው ኢ.ህ.አ.ፓና መ.ኢ.ሶ.ን ከሌሎቹ የተማሩ ናቸው። በኋላ የመጣው ደርግ፤ ወያኔና ሻቢያ ደግሞ አልተማሩም። ትምህርት ጠልተው አገር ለመምራት የተነሱ ናቸው። ከአርባ አመት ወዲህ ነገሩ ሁሉ የኋሊዮሽ ነው የሄደው። አሁን ደግሞ ያው እንደምታየው የወያኔ አገዛዝ ድንቁርና የነገሰበት ጊዜ ነው። ከ8ኛ ክፍል ፒ ኤች ዲ እና ማስተርስ እየያዙ ሲጋለጡ እየተመለከትን ነው። በደርግ ጊዜ ትዝ ይለኛል አንድ ባለስልጣን እንዲሁ በሃሰት የትምህርት ማስረጃ ሲያጭበረብር ተደርሶበት ተዋርዶ በኋላም ራሱን ከፎቅ ወርውሮ ገድሏል። ከነኚህ መሃል ግን እስካሁን ይህን ለማድረግ የደፈረ አልሰማሁም።

**<u>አሻራ፡-</u>መከሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በሚለው መጽሃፍዎ ላይ የታሪክን አጻጻፍ በሁለት መልክ አስቀምጠውታል። ታሪክን ለባለታሪኩ መጻፍና ታሪክን ዕውቀት ለሚሻ አንባቢ መጻፍ የተለያዩ ናቸው ይላሉ። ታሪክን ለባለታሪክ መጻፍ ከፍተኛ ሃላፊነት የሚጠይቅ ስራ ነውም ይላሉ።ይህን እንደ መነሻ እንያዝና በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ችግር አለን የሚሉ ወገኖች የሚያነሱትን ነጥብ ስንመለከት፡- በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ መቶ አመት ይሸመቅቁታል። የታሪክ አጻጻፉንም የገዢውን መደብ ዱካ እየተከተለ የተጻፈ ታሪክ እንጂ የህዝብ ታሪክ አይደለም ሲሉ አድማሱን ያጠቡታል ። እነኚህ ወገኖች እንደሚሉት ታሪካችን ችግር አለው ወይስ ታሪክን ላለመቀበል**

**ሲባል የሚነሳ ተጨባጭ ያልሆነ ምክንያት ነው እያጠቀሱ ያሉት? ችግር ካለውስ ችግሩ ምን ላይ ነው?**

<u>ቲ/ር፦</u> መቶ አመት የሚሉት ቀደም ሲል እንደገለጽኩት የድንቁርና ችግር ነው፡፡ አንድ ፈረንሳዊ ጸሃፊ እንዳለው የኢትዮጵያ ታሪክ በብራናና በመጽሃፍ የነበረው ሁሉ ቢጠፋም በድንጋይ ላይ ተጽፎ ይገኛል። ለዚያውም በጣም ጠንካራ በሆነ ድንጋይ ላይ ተጽፎ ያለ ታሪክ ነው። በመሆኑም ማንም ሊያስተባብለውም ሆነ ሊያጠፋው አይችልም። በምንም አይነት።

ለባለታሪኩ የሚጻፍ ታሪክ ስለሚለው፦- የአንድ ታሪክ ባለቤቱ ማነው የሚለው ጥያቄ እኛ ጋ ሲመጣ ችግሩ ሕዝብ የሃገሩ ባለቤት ሆኖ አለማወቁ ነው። ይህንን መቀበል አለብን። የአገሪቷ ባለቤቶች ንጉሳዊያን ቤተሰቦች፤ ደጃዝማቾቹ፤ ግንጥራሮቹ፤ ጀነራሎቹ፤.... ነበሩ። ታሪካቸው እነሱ በፈለጉት መሰረት ይጻፋል። የኢትዮጵያን ታሪክ የነሱ ታሪክ ያደርጉታል። እዚህ ላይ ነው ችግሩ። ለምሳሌ የየነገስታቱን ዜና መዋዕሎች ብናይ ምንም ተከታታይነት አታይባቸውም። የእያንዳንዱ ንጉስ ዜና መዋዕል ያለፈውን ወቅሶ (ራሱን)አዲሱን አወድሶ ከመጻፍ ውጭ አዲሱን ከቀዳሚው አያይዞ አይጻፍም። ስለዚህ ዕውነቱን ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው።

የሁሉም የኢትዮጵያ ነገስታቶች ታሪክ በእንግሊዘኛ ፤ በፈረንሳይኛ፤ በጀርመንኛ፤ በፖርቱጊዝ፤ በስፓኒሽ፤ በሂብሩ ተተርጉመዋል። ያልተተረጎሙት በአማርኛ ብቻ ነው። ለምን? ቢባል አዲሱ ንጉሥ ከሱ በፊት የነበረውን ንጉሥ ታሪክ አስተርጉሞ የራሱን ዝናና ክብር ሊያሳንስበት የሚችል ባለታሪክ ማስተዋወቅ አይሻም፡፡ ወይም እውነቱን ማሳወቅ አይፈልግም።

ለዚህ ለምለው ነገር አንድ ጥሩ ምሳሌ አለ፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ፐ/ር ስርገው ሃብለ ስላሴ የአጼ ምኒሊክን 50ኛ ሙት ዓመት ምክንያት አድርጎ አንድ አነስ ያለች መጽሃፍ ጽፎ ነበር። በዚህ መጽሃፍ አጼ ምኒሊክን በጣም አሞግሶ፤ ለሃብት ምንም ግድ የሌላቸው ፤ ‹ኢትዮጵያ ሁሉ ሃብቴ ነው› የሚሉ ሰው ነበሩ ብሎ ነው የጻፈው።

በኋላ ኃይለ ስላሴ አስጠሩትና “አጼ ምኒሊክን የት ታውቃቸዋለህ?” ብለው ጠየቁት። እሱም “አይ እኔ የታሪክ ተመራማሪ ነኝ፡ ካነበብኩትና ተጽፎ ካለው ተነስቼ እንጂ እሳቸውንማ የት አግኝቼ አውቃቸዋለሁ።” ብሎ ሲላቸው፤ “ታዲያ የማታውቀውን ታሪክ ነው የምትጽፈው?” ብለው መጽሃፉን እንዳይሸጥ አስደረጉ። ይህ እንግዲህ አጼ ምኒሊክ ለሃብት ግድ የላቸውም መባሉ እኔን ያሳንሰኛል ከሚል ስጋት በመነጨ ያደረጉት ነው።

ሌላ ምሣሌ ልስጥህ፦ ይሄ በኔም መጽሃፍ ውስጥ የተገለጸ ታሪክ ነው፡፡ በአምስት አመቱ ጦርነት ከጣሊያን ጋር በዱር በገደሉ ሲዋጉ የነበሩ አርበኞች በአጼ ኃይለሥላሴ ተገፍተዋል። አጼ ኃይለሥላሴ ከስደት ተመልሰው መንበረ ስልጣናቸውን ሲይዙ፤ እንቢኝ ለሃገሬ ብለው በዱር በገደሉ ይዋጉ የነበሩት አርበኞች ለስልጣናቸው ስጋት ሆኑባቸው። ስለዚህ ምን አደረጉ? ባንዳውንና እንደሳቸው የተሰደደውን ያዙ፤ አርበኛውን ደቆሱት። ይሄ ዶክመንትድ የሆነ ነገር ነው የምነግርህ።

መሳፍንትና ሹማምቶቻቸውን ብትመለከት ከራስ አበበ አረጋይና ከደጃዝማቾች በላይ ዘለቀ ሌላ አብዛኞቹ ባንዳና ስደተኛ የነበሩ ናቸው ። ከራስ ስዩም የትግራዩ ጀምረህ፤ ራስ ኃይሉ የጎጃሙ፤ ራስ ጌታቸው … ባንዳ ነበሩ።ደጃዝማቾች በላይ ዘለቀም በኋላ ተገደለ። ላገሩ የሞተን እንደገና የሚገድል እንደኛ ያለ ህዝብ ያለ አይመስለኝም። እንዲህ እያደረግን ነው ታሪካችንን እያኮላሸን የሄድነው። መክሸፍ የምለው እኔ ይሄንን ነው፡፡ አከሸፍነው።


ለመጣው ሁሉ መስገድ ነው ታሪካችን። ጣሊያን መጣ መስገድ፤ ለኃይለሥላሴ መስገድ፤ ለደርግ መስገድ፤ አሁንም ወያኔ መጣ መስገድ። ለክብራችን የምንቆም፤ እንደሰው ጥቅማችንን እና መብታችንን የምናስከብር ሕዝቦች አይደለንም። ታሪካችንን የምንፈልግ ለታሪካችን የምንዋጋ አይደለንም። የድሮ አባቶቻችን እንደዚህ አልነበሩም። በተለይ ከጣሊያን በኋላ የመጣው ትውልድ ወደ መሸጦነት የተጠጋ ትውልድ ሆነ።

**<u>አሻራ፦</u>ወደ እርስዎ ልመለስና፤ የህይወት መመሪያ ፍልስፍና አለዎት? ካለዎትስ ምንድነው?**

<u>ቲ/ር፦</u> የሚገርምህ ሕንድ ሃገር እያለሁ የምማረው ፍልስፍና ነበር። ሕንድ በዛ ጊዜ ብዙም የሚመች ሃገር አልነበረም። እናም ጊዜዬን የማሳልፈው ቁጭ ብዬ በማንበብ ነበር። መጽሃፍ ደግሞ ባጣም እርካሽ ስለነበር እየገዛሁ ማንበብ ነበር ስራዬ። በሳምንት ቢያንስ ሁለት መጽሃፍ አነባለሁ። ከኮሚኒዝም ጋር የተዋወቅኩት ያኔ ነው። እማርበት በነበረው ዩኒቨርሲቲ ውስጥም የኮሚኒስት ፓርቲ ነበር። በምማረው ፍልስፍና ውስጥም ስለኮሚኒዝም እማር ነበርና ይሄ ይሄ ተደማምሮ ይመስለኛል፤ ለድሃ ማሰብ፤ ለተበደለ መቆም፤ ወደሚል ሃሳብ መራኝ። እኔም በጊዜው ድሃ ከሚባል ቤተሰብ የመጣሁ ስለነበርኩ ወደዚህ ማለትም ‹ለተበደለ መቆም› ወደሚለው የህይወት መመሪያ ለመምጣት ቀሎኝ ነበር።

ሁሌም ለድሃውና ለሚበደለው የህብረተሰብ ክፍል አስባለሁ። ለምን ይሄ ይደረጋል? የሚል ጥያቄ ዘወትር በአይምሮዬ ይመላለስ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ በጣም ሃይማኖተኛ ነበርኩ። ክርስቶስ ለድሃ ማሰብ አስፈላጊ ስለመሆኑ የሚለውን ሁሉ አያይዤ ፤ ለድሃው፤ ለተበደለው፤ ለተጨቆነው ለመቆም ለራሴ ቃል ገባሁ። ያኔ ገና 21 ዓመት ቢሆነኝ ነው። ከዚያ በኋላ አሜሪካንም ሄጄ ስመለስ ይህ የህይወት መመሪያ ውስጤ ነበርና በመንግስት መስሪያ ቤት ገብቼ የአገዛዙ አሻንጉሊት መሆን አልፈለኩም። የመንግስት ባለስልጣን መሆን ድሃውን ለመርዳት ለነበረኝ ፍላጎት ምንም እንደማይጠቅም ስለተረዳሁ አልፈልግም አልኩ። በዚህ አቋሜ ከጓደኞቼ ብዙ ሙግት ገጥሞኝ ነበር።

በኋላም አስተማሪነት መረጥኩና ማስተማር ጀመርኩ። ይህንኑ የህይወት መመሪያዬንና አስተሳሰቤን ለተማሪዎቼ የማስተላለፍ እድሉን አገኘሁ። በዚህም በጣም በጣም ደስተኛ ነኝ። ጥሩ ውጤትም አግኝቼበታለሁ ብዬ አስባለሁ።



*ወደ ገጽ 18 ዞሯል*

> **የኢትዮጵያ ወጣቶች በሜዲቴራንያንና በቀይ ባሕር፣ በየበረሃውና በየእስር ቤቱ የሚቀበሉትን አበሳ በቆራጥነትና በመተባበር መንፈስ ተነሳሥተው አገራቸው እንድትመቻቸው ለማድረግ ወደሚያስችል ዓላማ ቢለውጡት የተሻለ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።**

# "ጠፍአት አገርነ"
# ትናንት ማታ ጨረቃዋንም አዋልደናል

ጽጋዬ ገብረመድህን አርአያ

ዋላስ ጆንሰን በ1930ዎቹ ከዩናይትድ ስቴትስ ወደ እንግሊዝና ወደ ሞስኮ (ሶቭየት ህብረት) . . . ሌላ ጊዜ ከምዕራብ አፍሪካ - ጎልድ ኮስት፣ ወደ ካይሮና ወደ ፓሪ፣ ጄኔቭ . . . እየተሽከረከረ የነጻነትን ፖለቲካ ሲዘራ የቆየ የሴራሊዮን ተወላጅ ነበር። ጆንሰን በትምህርት ቤት ደረጃ በሚሰጥ መደበኛ ትምህርት በዲፕሎማና በዲግሪ የማይተመን (የማይለካ) ላቅ ያለ እውቀትና ብስለት ያዳበረ ምሁር ወጣት ነበር። በዚህም በዘመኑ ለጥቁር ህዝብ መብትና ነጻነት በቆራጥነት ቆመው የትግል መርሐዎችን ሲያስፋፉ ከፍተኛ አድናቆትን ከተቀዳጁት ከ W.E.B Du Bois እና ከ Frantz Fanon እኩል ፍቅርና አክብሮትን ማግኘት ላይ የሚገኝ ሆኗል። ( በ1960ዎቹ እየተሻማን እናነባቸው የነበሩትን የ W.E.B Du Bois 'The Sons of Black Folk' እና የ Frantz Fanonን 'The Wretched Of The Earth' ዛሬም ባዝዝላችሁ የሚጠቅሙ ይመስለኛል።)

ጆንሰን የጎልድ ኮስትን (ዛሬ ጋና) ወጣቶች (West African Youth) በማለት በአንድ የአርበኝነት አርማ ስር አሰባስቦ - Liberty or Death (ነጻነት ወይም ሞት ) በተሰኘ አጠቃላይ መርህ ሲያራምድ በመቆየቱ ለቅኝ ገዢዋ እንግሊዝ የጎን ውጋት ሆኖባታል። ስለዚህ በምዕራብ አፍሪካ የእንግሊዝ አገዛዝ እንደራሴዎች "የቦልሼቪኮች ስሎግና ምንደኛ" በማለት ስሙን ለማከፋት ሞክረዋል። ይህ ፕሮፖጋንዳ ለዋላስ ጆንሰን የበለጠ የህዝብ ወገንነቱን ከማረጋገጡም በላይ በወቅቱ በፓሪስና በለንደን የታወቁ ተራማጅ ጋዜጦች "ጆንሰን በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ልብ ውስጥ መርዘኛ ጩቤ እየተከለ ነው" ብለውታል።

1935 ዓ.ም. የፋሺዝም ፈጣሪና በአንድ ወቅትም እንግሊዝም፣ ፈረንሳይም፣ አሜሪካም (ፍራንክሊን ዲ. ሩዝቬልት) እጅግ ያወደሱትና የሃያኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓ ልዩ ፈላስፉ ያደረጉት የቤኒቶ ሙሶሊኒ ሰራዊት ኢትዮጵያን መውረሩን ድምጹን ከፍ አድርጎ ያሰማበት ነበር። ያበዱ ፋሽስቶች ከተሞቻቸውን "በአቫንቲ" (ወደፊት) መፈክር ያተረማመሱበት፣ ሥራ አጥ ኢጣልያውያን ለወዶ ዘማችነት በአያሌ ሺዎች የወጡበት ክፉ ጊዜ - የዘመንም እብድ ዘመን ነበር። ከሮማው ባሲሊካ ደወል እንኳ ባይሆን ፊሽካዎች እየተነፉ ከተማውን የበጠበጡበት፣ ሃይማኖት የሌላቸውን "ባርባሮች" የማሰልጠን ተልእኮ የተባለውን የወረራ ሽፋን የካቶሊክ መሪዎች (ፓየስ 12ኛን ይጠቅሷል) ሳይቀሩ የደገፉበት ሆነ።

የእንግሊዙ ሰር ሳሙኤል ሆርና የፈረንሳዩ ፒየር ላቫል ከሙሶሊኒ ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ከጀርባዋ የወጉበት አሳፋሪ ፖለቲካ የአውሮፓን አየር የበከለበት ነበር። የመንግስታቱ ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) ከፋሽስቶች ጋር ተመሳጥሮ ወረራውን በምስጢር የደገፈበት - የዓለም ቀይ መስቀል ማህበር ሳይቀር ኢትዮጵያን አሳልፎ የሰጠበት ወቅት ነበር። የወቅትም እብድ ወቅት ነበር። የኢኮኖሚ ማዕቀብ አልሰራም። የሙሶሊኒ መርከቦች በሺህ ቤት የሚቆጠሩ ሶልዳቶዎችና የጦር መሳሪያዎች፣ ነዳጅና የመሳሰለውን እየጫኑ ሲሄዱ የስዊስ ቦይ ለእነሱ ምንም ዓይነት እግድ አልነበረበትም። ይህንን የተመለከተ አንድ እንግሊዛዊ The Rape of Abyssinia (የኢትዮጵያ መደፈር። ህገ ወጥ የክብርና መገሰስ) ብሎ ጽፎአል።

አዎን የኤድዋርድ ጊቦንን አገላለጥ ለወጥ አድርገን ስንመለከተው ኢትዮጵያ በዓለም የተረሳችበት . . . ዓለምም ያደመባትና ለፋሽዝም እንደምርቃት የሰጣት አገር ሆናለች። ጄኔራል ባዶልዮ ከአስመራ ቶሎ ቶሎ አያሌ ወታደሮችና በሙቶዎች የሚቆጠሩ የመርዝ ጋዝ በርሜሎች፣ በምብና ዘመናዊ መሳሪያ እንዲላክለት ሲጠይቅ ኢል ዱቼ ገፋ አድርጎ መላክን በሚወድበት ቋንቋ "አሳነስህ ተብዬ ከምወነጀል በርከትከት አድርጌ የመላክን ስህተት መፈጸም እፈልጋለሁ" ይል ነበር። አቶ አዲስ ዓለማየሁ "ትዝታ" በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጡት ሰውና እንስሳት እኩል ተረፈረፉ። በሰውና በእንስሳቱ ደም የተሞላው ወንዝ ራሱ የደም ጅረት ሆነ። ተከዜ የትካዜ ወንዝ ነው። ዘወትር።

በአጭሩ ለመግለጥ በከባድ ጦርነቶች ጊዜ እንደሚከሰተው ሁሉ ሴቲቱ ለወንድሞችዋ እህት፣ ለልጆችዋ እናት፣ ላባልዋ ሚስት፣ ለወላጆችዋ ልጅ የመሆንን ክብር የተገፈፈችበት ቀን መጣ። ባልዋ በፊት ለፊቷ በጥይት ሲወድቅ፣ እርፍ ለመያዝ ያልደፈረ ልጅዋ ያለርኅራኄ ሲታረድ፣ የንስሐ አባትዋ የገመድ ሲሳይ ሲሆን፣ ወንድ ወንዱ እየታደነ ሲጨፈጨፍ . . .የቀትር ጋኔንና የገሐነም ዘበኞች የሚመሳሰሉ "አስካሪሶች" (ይህንን ቃል ስሰማው በጥሬ እንግሊዘኛው ሽቅብ ሽቅብ ይለኛል) ቤትህን በርግደው በመግባት እንስሳዊ የወሲብ ረሃባቸውን በልጅህና በሚስትህ ላይ ሲወጡ . . . ምን ይሰማሃል? እኔ በመጠኑም ቢሆን ጦርነትን አይቻለሁ። አውቃለሁ። ሰው ብቻ ሳይሆን በሰላሙ ጊዜ ሬሳን የዕለት ሲሳያቸው የሚያደርጉ አእዋፍና እንደ ጅብ ወዘተ ያሉ አራዊት ሳይቀሩ ከአገሩ ነቅለው የሚጠፉበት ጊዜ ነው። የዜናሁ ለጋላ መጽሐፍ ደራሲ አባ ባሕርይ አንድ መፈክር ነበራቸው - "ጠፍአት አገርነ" (አገሬ ጠፋች! ) ያንን ዘመን ካላወቃችሁት ዛሬ ተደግሞላችኋል!

የእብሪት ወረራውን፣ ዓለም አቀፍ ሴራውንና በኢትዮጵያዊው ጀግና ዜጋ ላይ እየወረደ ያለውን ጥቃትና ጥፋት ሲከታተል የነበረው ዋላስ ጆንሰን መጽሐፍ ቅዱስንም ያውቃል። "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች!" የሚለውን በትንቢት ወስዶታል። ስለሆነም ከዓለምም፣ ከዓለማውያን መንግስትም፣ ከሰውም ከተፈጥሮም "ፍትሕ ያጣች" አገር መሆንዋን ያጤናል። ይህን ፍትሕ ደግሞ "ከራሱ ከእግዚአብሄር ጭምር" ማጣትዋን ያሰላስላል። በልቡ "አንተም ጌታ ሆይ?" ሳይል አልቀረም። ለእኔ ይኸ ዛሬ መተከዣዬና አዝማቼ ነው።

በዚያን ሰዓት ጆንሰን The African Morning Post የተባለ የምዕራብ አፍሪካ (ጎልድ ኮስት) ጋዜጣ መደበኛ የፖለቲካ ሒሰኛ ነበር። የጋዜጣው አዘጋጅ ደግሞ በኋላ የናይጄሪያ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት የሆኑት Nnandi Azikiwe ነበሩ። ጆንሰን በአብዛኛው የሚጽፈው በምዕራብ አፍሪካ የነጻነት ተጋድሎ ላይ ቢሆንም በዚያን ሰሞን ግን "ዚክ" እየተባሉ ይጠቀሱ የነበሩትን አዚኪዌን በምር ሊያናግራቸው ቀጠሮ ይዞ ይገናኛሉ። የኢትዮጵያን ጉዳይ - የዓለምን ክህደት - የሩዝቬልትንና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን የኮርደን ሐልን ማሾፍና ወረራውን በስውር መደገፍ - የዚችን አገር ታሪካዊ ተጋድሎና በአንድ ወቅትም የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የትግልና የድል ምልክትነት አወሱ። ከዚያ በኋላ ጆንሰን የጽሑፉን ርእስ "Does Ethiopia have a God?" ለማለት ፈለገ። በጽሁፉ ውስጥም "አውሮፓውያኑ በአፍሪካ ውስጥ ባቋቋሟቸው አብያተ ክርስቲያናት የሚመለክ አምላክ እንዳላቸው አውቃለሁ። የዚህ አምላክ መመሪያ ህግ 'እናንተ ጠንካራ አውሮፓውያን እነዚያን ደካሞች አፍሪካውያንን የበለጠ አድክሙ። ሸክማቸው ለከበዳቸው ሸክም ጨምሩባቸው። እናንተ ሥልጡን አውሮፓውያን ከኋላ ቀርነት ያልወጡትን አፍሪካውያን በመድፍና በመትረየስ እየጨፈጨፋችሁ አሰልጥኗቸው። እናንት ክርስቲያን አውሮፓውያን ሃይማኖት የሌላቸውን ኢትዮጵያውያን በቦምብ፣ በመርዝ ጋዝ፣ በክላስተር ፈንጅ ክርስትና አንኗቸው' እንደሚልና ይህም አምላክ Mr. Deceit (አወናባጅ) በሚል ስም ቢጠቀስ ትክክል እንደሆነ ይስማማሉ። በውይይታቸው ፍጻሜ ላይ አዚክዌ ጽሁፉ በአብዛኛው የኢትዮጵያን ክብር መደፈርና የነጻነትዋን መገሰስ መግለጡ እንደተፈለገው ሆኖ ርእሱ Has the African a God? እንዲል መጠነኛ ጭንት አደረጉ። በአጭሩ ግን "በአንተው መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ እጆችዋን . . . (ለፍትህና ለርትዕ) ወደ አንተ ትዘረጋለች . . . እንዳልተባለ ሁሉ ከዚህ የበለጠ ፍትህ የሚጠየቅበት ምን ቀን . . . ምን ፍዳ . . . ምን የመዓት ወቅት . . . ምን ዓይነት ፍርደ ገምድልነት ይምጣ?" የሚል ትርጉም አለው። ከእግዚአብሄር ጋር የተደረገ ጭቅጭቅ ውስጥ የገባ አንድ "ፍቅረ ኢትዮጵያ" ሮሮ ሆኖ ሊታይ ይችላል። "ወይ ውረድ ወይ ፍረድ!" የዛሬው የእኔና የእናንተ የተሰበረ ድምፅና አዝማችም ሆኖአል። የአቡነ ጴጥሮስ ሮሮ "አምላክ ምሕረት አገርህን ኢትዮጵያን ምነው የረሳሃት?"

"ድል እልፍ አእላፍ አባት አላት" ይባላል። ባለድልና ባለጊዜ ስትሆን የሚከብብህ፣ የሚያደንቅህና ዝናህንም የሚያገንነው ሥፍር ቁጥር የለውም። ፈረንጆቹ እንደሚሉትም "ሳቅ ዓለምም አብሮህ ይስቃል። አልቅስ - ብቻህን ታለቅሳለህ" ምሥጢሩ እዚያ ላይ ነው። የእኛኑ ታሪክ እጠቅሳለሁ። በአድዋው ጦርነት ጊዜ ራስ መኮንን የሚመሩት ጦር አምባላጌ ላይ ወራሪውን ሠራዊት ድል ሲመታ አውሮፓውያን መንግሥታትና ጋዜጠኞቻቸው "ይቺ ምንድናት ጣልያን እንዳሸነፈ ይቆጠራል። ዋናው አድዋ ላይ ነው። . . .እስቲ የመቀሌውን ጦርነት እንየው" ሲሉ ምንም እንኳ ብዙ መስዋዕትነት ቢፈጅብንም አሁንም ጣልያን እጆችዋን በምህረት ልመና መልክ ወደ ሰማይ እየዘረጋች ከምኒልክና ከጦር አዛዦቻቸው ፊት በእንብርክክ ብትሄድም በመቀሌም ላይ አሸናፊነታችን ለፈረንጆቹ አልተዋጠላቸውም። አድዋ ላይ ሞትን በኢጣልያ ሠራዊት ላይ አዝንበን ጄኔራሎቹን ገድለንና ማርከን ወደ ጽርሐ አርያም እምስጋና ስንመለከት የእግዜሩንም ፍትሕና ድል ተቀዳጀን። ያን ጊዜ ምኒልክንና ሠራዊቱን፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን . . . የመላው አውሮፓ ጋዜጦች የሚያወድሱበት ቋንቋ ተቸግረው ነበር።

> " ሦስት ሚሊዮን አማራ መጥፋቱን የስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ቀጠራ አረጋግጧል። ሒትለር ዘደውን ከመለስ ቢጠይቅ የአይሑድ ዘር ባልተረፈም ነበር። (እንደሚባለው የአገዳደልን ስልትና ውጤቱን በተመለከተ ሒትለር በስታሊን ይቀና ነበር።) የመለስ ሲነሣ ደግሞ እመኑኝ ሁሉንም ያስከነዳል። "

ኢትዮጵያውያንን Super-human ብለው የምስጋና ካብ ገነቡልን። የአድዋው ምኒልክ በኡምቤርቶ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ፍርድ ሲሰጡና የጦር መላ ሲያወጡ የሚያሳዩ ምስሎች (ካርቱኖች) የኢጣሊያንን ጋዜጦች፣ ታዋቂ የሆኑ የፍሊት ስትሪትን እትሞች . . . የነ ዴርሽፒግልን (ጀርመን) . . . መጽሄቶችና ጋዜጦችሞሏቸው።የዓለም ጋዜጦች አሻሻጭ ሆንን። ድል ስታደርግ ዓለምም የሚሰግድልህ ይመስላል። ስትሸነፍ የአሸናፊዎችን እምነትና ተጽእኖ ተንበርክከህ ለመጨለጥ የምትገደድበት አጋጣሚ ብዙ ነው። እዚያ ደረጃ ላይ የደረሱና የጦርነትን ፍትሐዊ ሕግጋት ለመቀበል የማይሹ ያጋጣሚ ባለድሎች በሕዝብ ላይ የሚፈጽሙትን ባለጌ ስራ ሁሉ እነሆ ባዛሬው ልምዳችን አውቀነዋል። የወገኖቻችን ጭካኔና የዓለምም ፍርድ ይህን ተከትሎ የመጣ ነው።

ድል አድራጊነትህ ዋጋ የሚኖረውና በከፍተኛ የሞራል አሸናፊነት የሚረጋገጠው ለባላንጣህ(ጠላትህ) በምትሰጠው አክብሮትና እንክብካቤም ነው። ሟች ጠላትህ "ውኃ ውኃ" እያለ በመጨረሻ ትንፋሹ ሲለምንህ "ያንተ ፍላጎት ከኔ ፍላጎት ይበልጣል" ብለህ ኮዳህን ስታቀርብለት ነው። የወታደራዊ ሳይንስም ሰብአዊ ባህርይ መላበስ አንዱ ማስረጃ ይኸ ነው። ምናልባትም ከእኛው የአጤ ምኒልክ ሁለት ጦርነቶች ማስረጃ ማቅረብ አግባብ ይመስለኛል። የአጤ ምኒልክን ሠራዊት መቀሌ ውስጥ መሽጐ ለብዙ ቀናት ሲዋጋ የቆየው ማጆር ቶሲሊ ምህረት ጠይቆ እጁን ሲሰጥ ጄኔራል ባራቲየሪ ወደሚገኝበት ከመረብ ምላሽ እንዲሄድ ማለፊያ በቅሎና ለተረፈው መሳሪያ መጫኛ በርከት ያሉ አጋሰሶች እንደሰጡት የታሪክ ምስክርነት አለ። የሥልጡን ህዝብ ድል አድራጊነት ይህን ይመስላል። ሞራላዊ አሸናፊነትን የሚያህልና የሚያስከብር ነገር የለም።

ይኸ ብቻ አይደለም። የሸዋው ጦርና የጎጃሙ ሠራዊት እምባቦ ላይ በተዋጉ ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ቆስለው መያዛቸው ይታወሳል። አጤ ምኒልክ በጊዜው የነበረውን የቁስል መድኃኒት፣ ፋሻና ሙቅ ውኃ አስቀርበው የተክለኃይማኖትን እግር እያጠቡና እያከሙ አርአያነት ያለው እንክብካቤ እንዳደረጉላቸው ከዓይን ምስክሮች ሪፖርት አንብበነዋል። ይህንኑ የታላቅነት ተግባር በጦርነቱ ላይ ለቆሰሉ ኢጣላውያን አድዋ ላይ እንዳሳዩ ይታወቃል። እንዲህ ያለውን አርአያነት ያመጣ ነው አሸናፊ፣ የድሉን ሓቀኛነት በሰብዓዊነትና በርኅራኄ ማሳየት እንደሚገባ ያመነ ፤ የሚያምንና ያንንም በድርጊት የሚያሳይ መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህንን ታላቅ የጦር ሰዎች የክብር ተግባር ከማንም ይልቅ የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች እንዲያጤኑት እፈልጋለሁ። እነሆ ሃያ አራት ዓመት ሙሉ በወገኖቻችን አስከሬን ላይ እየቆሙ ፍከራቸውን አላቆሙም። ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ። - ቀንም ሌሊትም ድንፋታቸው እንደቀጠለ ነው። አንደኛ እኛ ሳንሆን እነሱ ራሳቸው ማሸነፋቸውን አላመኑትም። በርግጥም መታመን የሌለበት ነው። የአሸናፊነት ክብርና ትሁት ባሕርይ ስለሌላቸው፣ ራሳቸውንም በዚህ ረገድ ለማወቅ ስላልቻሉ እስካሁን እጁን ሰጥቶ ወደ ሰላማዊ ሕይወት የተሸጋገረውን ሠራዊት ወኔ እየቀሰቀሱ ይገኛሉ። እንደገና ፍልሚያ ይለምናሉ። እንደ ልብነ ድንግል "ጦር አውርድ" እያሉ ነው። ያ ሠራዊት በአካላዊ ጉስቁልናና

በዕድሜ ምክንያት አፈር ልሶ ወደ ሕልው ዓለም ለመመለስ እንኳ ባይችል ባለጊዜዎቹ በሚፈጽሟቸው ብሔራዊ ወንጀሎች ምክንያት ይህን ትውልድ ለአርበኝነቱ ተጋድሎ እየቀሰቀሱ ይገኛሉ። አገሩ በመያዣና በግዥ የተሰጠበት፣ ታሪኩና ማንነቱ የተረገጠበት፣ ነጻነቱና ክብሩ የጎደፈበት፣ ወጥቶ ለመግባት - ገብቶ ለመውጣት መብት ያጣ ሕዝብ ፤ እየተከፋፈለ እንዲጫረስ የተፈረደበት ኅብረተሰብ - ዘላለም ቀስቃሽ አያስፈልገውም። ይህ ሁሉ የአገር ውርደት ይህን ትውልድ አልቀሰቀሰውም ማለት ዘበት ነው። ከዚህ ሁሉ ውርደት መውጣት ፋይዳ የለውም ትላላችሁ? ለአንተ ወጣቱ ትውልድ፣ ለአንቺ ወላድ ኢትዮጵያዊትና ለእኔም ወደ ጸጥታው ዓለም በመሸጋገር ላለሁት ጀግንነትን የማውቅ ዜጋ የቀረበ ፍልሚያ ነው።

ባለፉት ዘመናት በኢትዮጵያ ውስጥ እኩልነትንና ዲሞክራሲን ለማምጣት በሰላማዊ መንገድ ልንታገል የምንችልባቸው አያሌ የትግል ፈርጆች እንዳሉ በመገመት የተከናወኑ ጥረቶች ነበሩ። ይህ ትግል ደግሞ ፋሽስት ኢጣልያ በአምስት ዓመት ቆይታዋ ከጨረሰችብን ወጣት ትውልድ ይልቅ ወያኔ የጨፈጨፋቸው ሰላማዊ ዜጎች ቁጥር ከአምስት እጥፍ ይበልጣል። ከቶውንም አንዳንዱ መግለጫ የማንንም ሰብአዊ ፍጡር ደም የሚበጠብጥ ነው። እስኪ እነዚህን በየጊዜው የምንሰማቸውን መረጃዎች እንጥቀሳቸው። :-

" ወያኔ በመላው ኢትዮጵያ ባቋቋማቸው እሥር ቤቶች መነጋገሪያው ቋንቋ ኦሮምኛ ሆኗል። - 50 በመቶ የሚሆነው እሥረኛ ኦሮሞ ነው ማለት ነው።

" ሦስት ሚሊዮን አማራ መጥፋቱን የስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ቆጠራ አረጋግጧል። ሒትለር ዘዴውን ከመለስ ቢጠይቅ የአይሑድ ዘር ባልተረፈም ነበር። (እንደሚባለው የአገዳደልን ስልትና ውጤቱን በተመለከተ ሒትለር በስታሊን ይቀና ነበር።) የመለስ ሲነሣ ደግሞ እመኑኝ ሁሉንም ያስከነዳል።

" በብድርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተገኘው ገቢ ከ15 ቢሊዮን ዶላር በላይ በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች አማካይነት ተመዝብሯል።

" ሕዝብን ከሕዝብ የማጫረስ እቅዱ እየተስፋፋ ነው። ይልቁንም በአማራውና በኦሮሞው መካከል የርስ በርስ መጨፋጨፍ እንዲስፋፋ ፕሮፖጋንዳው ደርቷል። እግዚአብሔር ይመስገን ሁላችንም ተዋውቀናል። መርዙ ግን ሊጠፋ የሚችለው ነገ በሚመጣው የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ነው። መንግስት በኢትዮጵያ ልጆች እጅ ስትገባ!

" ኦሮሞው፣ አማራው፣ ጋምቤላው፣ ጉሙዙና አኙዋኩ፣ ሶማሌውና - ሃይማኖቶቻቸው - ክርስትናና እስልምና ጦርነት ተከፍቶባቸዋል።

" የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ማስከበር የሚችል፣ የሕዝቡን ሰላም የሚጠብቅ፣ ሠርቶ ለመኖር የሚያስችል . . . ሥርዓት የለም። መንግስት ደግሞ በኢትዮጵያውያን ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት የሌለውና የተጠላ ሆኖአል።

" ዜጎች በሰላማዊ መንገድ ታግለው ለአገራቸው ደግ ቀን ለማምጣት የሚያደርጉት ሙከራ ሁሉ ከንቱ ሆኗል። የፖለቲካ አክቲቪስቶች በዘፈቀደና በግፍ እየተገደሉ፣ ወደ እሥር ቤት እየተወረወሩ ናቸው። ጋዜጠኞችና ብሎገሮች እንደ አውሬ እየታደኑ እየታሰሩ በፈጠራ ወንጀል እየተከሰሱና ወህኒ ቤቶችን የዘላለም ቤታቸው (ካልቀረ) እያደረጉ ናቸው።

" የጥንቱ የሶቪየት ኢምፓየር የተነወረበትና ዓለምም የትግል ግንባር የከፈተበት በኮሌክቲቫይዜሽንና በቪሌጃይዜሽን ነው። ወያኔ ያንን ፕሮግራም ተፈጻሚ ለማድረግ የአካባቢዎቹን ሕዝብ እያፈናቀለ ከሌሎች አካባቢዎች ያመጣቸውን ግለሰቦች እያሰፈረ ነው። በዚህ ፕሮግራም ብቻ ከ5 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ተጠቂ ሆኗል።

" ባለፉት ሁለት ዓመታት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ብሶታቸውን ለማሰማት፣ አቋማቸውን ግልጽ ለማድረግ የወጡ በሺ የሚቆጠሩ ዜጎች ተጨፍጭፈዋል፤ አካለ ጎዶሎ ሆነዋል። ሽባና አእምሮ ስንኩላን ሆነው ቀርተዋል።

" አብያተ ሃይማኖቶቻችንና መሪዎቹ ተደፍረዋል። ታስረዋል። የደረሱበት ያልታወቀ ብዙዎች ናቸው።ደብሮች፣ ጥንታዊ አብያተ ሃይማኖቶች . . . ተመዝብረዋል። . . .የአምልኮ ቤቶች በግሬደሮች እየፈራረሱ ናቸው። መካነ መቃብሮች ያለኃፍረት ተፈነቃቅለዋል።

" በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች አገሪቱን እየጣሉ በመሰደድ ላይ ናቸው።

አይበቃም? በአጭሩና በአጠቃላይ ለመግለጥ ይኸ አይበቃም? በእኔ በኩል እንደ አባ ባሕርይ "ጠፍአት አገርነ" ያሰኛል። የጠፋችውስ ዛሬ ነው።


ማርከስ ጋርቪ (1887 - 1940) ጥቁሩ ናፖሊዮን እየተባለ ሲጠራ የነበረ ታጋይ - ራስ ተፈሪ መኰንን ወደ ኢትዮጵያ ዙፋን አልጋ ወራሽነት ሲመጡ "ራስ ተፈሪ" የተባለውን ንቅናቄ ካወቁ የጃማይካ ልጆች ግንባር ቀደም የነበረ ነው። ስለ ራስ ተፈሪ እንቅስቃሴ በርከት ያሉ ጽሑፎች ያቀረበና በዘመኑ የጥቁር ሕዝብን የነጻነት ተጋድሎ ችቦ አንስቶ ለሚሊዮኖች ያስተላለፈ ጀግና ነበር። ማርከስ ጋርቪ በሁለተኛው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ (በሓርለም፣ ኒውዮርክ ከተማ) ባደረገው ታሪካዊ ንግግር "እኛ ለሠላሳ አንድ ቀናትና ለሠላሳ አንድ ሌሊቶች እዚህ ሥፍራ የተገኘነው 400 ሚሊዮን ሕዝብ (ጥቁር) በመወከል ነው። ከደረስንበት ውጤት ስንነሳ ይህ ሕዝብ ከዛሬ ጀምሮ ነጻ ሕዝብ የመሆኑን ሐቅ መዝገብ አለብን። ትግሉ የፖለቲካ፣ በተጨማሪም በፍልሚያው መስክ የጨበጣና ማናቸውንም (ሕይወትን የሚሻ) መስዋዕትነት የሚጠይቅ ነው። ይሁንና ሁላችሁም ከእኔ ጋር ልታነብቡት የምትችሉት ጽሑፍ አለ። ጽሑፉን ከግድግዳው ላይ አንብቡት፣ ‹The writing is on the wall› ብሎአል። አማራጭ የሌለው - ጊዜ የማይሰጠው ነገር ነው። አለዚያ የፍትህ ውዝፍና የጦርነት ቀጠሮ ድንቁ የፊደል ሰው ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ እንዳሉት "ቱሞሮ ወለደት ቱሞሮ ነው"። ዛሬ በግድግዳው ላይ የተጻፈው ምንድነው? እንግዲህ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩ ተበጣጥሶ ስትቀር፣ ትውልድ በየሰበቡ ለዳግመኛ ጊዜ - በአርባ ዓመታት . . .ሞትን ሲጋትና መመኪያ አገራዊ ዋሻ ሲያጣ በትከሻው ላይ የወደቀውን ኃላፊነት አልተረዳም አይባልም። ይህን ያስተውላል። ምክንያቱም በግድግዳው ላይ በግልጽ የተጻፈው የሚከተለውን ይመስላል።

የኢትዮጵያ አንድነት በአምባገነኖች የጥላቻና የንቀት መሰዊያ ( altar of prejudice) ላይ መስዋዕት እየሆነ ነው። ሰላማችንና ብሔራዊ እሴታችን በዘረኞች መሰዊያ ላይ ተሰቅሎ ይታያል። ብሔራዊና ግለሰባዊ ክብራችን በውርደት መሰዊያ ላይ እየጋየ ነው። ዴሞክራሲና የዴሞክራሲ አራማጅ ሕዝብ በወያኔዎች መሰዊያ እቶን ላይ ፍዳቸውን እየተቀበሉ ናቸው። ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ አጤ ምኒልክ በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ያረጋገጡት የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በወያኔ መሰውያ ላይ ከድርድር በላይ ሆኖአል። "ጠፍአት አገርነ!" አለን ፓተን "እሪ በይ አገሬ" (Cry the Beloved Country) ብሎ ስለደቡብ አፍሪካ ከጻፈው ጋር የሚመሳሰል ነው።

ኢትዮጵያውያን የአሸናፊነት ታሪካችን በአብዛኛው የአንድ ቀን ጦርነት ነው። ዶግአሊ ላይ አሉላ አባነጋ 500 የጣሊያን ሰልዳቶ ጠራረገ። *ወደ ገጽ 24 ዞሯል*



# አንድ አፍታ
# ከዶ/ር መቅደስ መስፍን ወልደማሪያም ጋር



**አሻራ፡-** ራስሽን ለአንባቢ በማስተዋወቅ ውይይታችንን ብትጀምሪልን ?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** ስሜ መቅደስ መስፍን ይባላል። የፕሮፌሰር መስፍን የመጀመሪያ ልጅ ነኝ። የምኖረውም አሜሪካን አገር ማሳቹቴስ ግዛት ነው። ወደ አሜሪካ ከመጣሁ ከ20 ዓመት በላይ ሆኖኛል፡፡

በኢትዮጵያ እያለሁ የሁለተኛ ደርጃ ትምህርቴን የተከታተልኩት በናዝሬት ትምህርት ቤት ሲሆን በከፍተኛ ትምህርት ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ፋክሊቲ ምሩቅ ነኝ። አሜሪካን ሃገር ከመጣሁ በኋላም በቦስተን ዩኒቨርሲቲ በ Public Health የማስተርስ ዲግሪ አግኝቻለሁ።በዚሁ ሙያ ከኢሚግራንቱ ጋር በተገናኘና በኤቼ አይ ቪ መከላከል (HIV Prevention) ለረዥም ጊዜ ሥሰራ ቆይቻለሁ ። አሁን ደግሞ በግል አንዳንድ ስራ ለመጀመር እየተዘጋጀሁ ነው።

**አሻራ፡-** በቅርቡ በአንድ አጋጣሚ “EforAll 2015 Finalists” በሚል ከተዘረዘሩት 18 ሰዎች ውስጥ ስምሽን አይቻለሁ። ለመሆኑ ይህ EforAll የተሰኘው ድርጅት ምን እየሰራ ያለ ድርጅት ነው። ያንቺ ስም በ Finalists ዝርዝር ውስጥ የሰፈረው ምን ሰርተሽ ነው?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** (Entrepreneurship for All ) ወይም በአጭሩ (EforAll) የተሰኘው ድርጅት አንስተኛ የቢዝነስ ሃሳቦችን የሚያበረታታ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ነው።ይህ ተቋም ሰዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የቢዝነስ ሃሳብ አፍልቀው ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያደርጉትን ጥረት የሚያበረታታ ድርጅት ነው። አሰራሩም በመጀመሪያ ወደ ተግባር የሚለወጥ የቢዝነስ ሃሳብ አለን የሚሉ ሰዎችን ሃሳባቸውን ዘርዝረው በማመልከቻ መልክ ያቀርባሉ። ድርጅቱም የቀረቡለትን ማመልከቻዎች በተለያዩ መመዘኛዎች አወዳድሮ የበለጠ አሳማኝ ሆነው ያገኛቸውን ተቀብሎ ዕቅዳቸውን ወደ ተግባር የሚለውጡበትን መንገድ በተለያየ መልክ ያግዛል። እኔም እንዲሁ አንድ ያሰብኩትን ነገር ለመሞከር ጥናት እያደረኩ ባለሁበት ወቅት ነበር ድንገት ከዚህ ድርጅት የተደወለልኝ። ከዚያ በፊት ስለዚህ ድርጅት ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም። ደውለው “እያደረግሽ ያለውን ሙከራ እያየን ነው። እኛ እንዲህ አይነቱን በግል ተነሳሽነት የሚደረጉ ጥረቶችን የምናበረታታ መንግስታዊ ያልሆንን ድርጅት ነን።” ብለው ራሳቸውን ካስተዋወቁኝ በኋላ፤ ለምን ሃሳብሽን በዝርዝር ገልጸሽ ማመልከቻ አታስገቢም? በርግጥ ያመለከተ ሁሉ ላንቀበል እንችላለን፤፡ ውድድሩ ጠንካራ ነው። ግን መሞከርሽ አይከፋም” ብለው ምክር ሰጡኝ። እኔም ሃሳባቸውን ተቀብዬ እንደተባልኩት አደረግኩ። በኋላም ከ80 ያህል አመልካቾች መካከል አስራ ስምንታችንን ብቻ ተቀበሉን፡፡እንዳሉትም ውድድሩ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ማመልከቻ አስገብቶ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በየግዜው እየጠሩ ሃሳብክን በባለሙያ ፊት እንድታስረዳ ያደርጉሃል። ለሚቀርብልህ ጥያቄ ሁሉ አሳማኝ መልስ መስጠት አለብህ። ምክንያቱም እነሱን ካላሳመንክ ሌላውንም ማሳመን አትችልም ከሚል እምነት ነው። ትክክልም ይመስለኛል። አንዴ ከተቀበሉ ግን ራስህን ችለህ እስክትቆም ድረስ በሁሉም መልክ ያግዙሃል ይረዱሃል። ብዙ ልፋት ያለው ነገር ነበር። ሆኖም ግን ከ18 ተመራጮች መካከል ሆኜ ቀጣዩን ማለትም ወደ ተግባር የሚገባበትን ጎዳና ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነኝ፡፤ EforAll 2015 Finalists ስም ዝርዝር ውስጥ ስሜ የተጠቀሰው በዚህ ምክንያት ነው። ከመነሻዬ በደፈናው በግል አንዳንድ ስራ ለመጀመር እየተዘጋጀሁ ነው ያልኩትም ይህንኑ ነበር።

**አሻራ፡-** ወደ ፕ/ር መስፍን እንመለስ፤ ፕሮፌሰርን እንደ አባት እንዴት ትገልጫቸዋለሽ? አሁን ላለሽ ማንነት የሳቸው አስተዋጾ ምን ያህል ነው? ፕሮፌሰር በትምህርት ላይ ባላቸው ጠንካራ አቋም ይታወቃሉና በዚህ ረገድ በልጅነት ዘመን በጥሩም በመጥፎም የተከሰተ ትዝታም ካለ?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** እንዳልከው በትምህርት ላይ ያለው አቋም ጠንካራ ነው። ያም ሊሆን ይችላል እኛም ብዙ አላሳቸገርንም። የሚፈለገውን ውጤት ስለምናመጣ ብዙም በቁጣም ሆነ ውጤት ከማጣት ጋር በተያያዘ የማስታውሰው ነገር የለም።ከሱ ይልቅ ትዝ የሚለኝ በሃይ ስኩል እያለን የነበረበት የስራ ውጥረት ነው፡፡ ከስራ ወጥቶ ትምህርት ቤት መጥቶ ነው ወደ ቤት የሚውስደን፤ አንዳንዴ ግን ስለሚቆይብን ብቻችንን ትምህርት ቤት ውስጥ የመቆየት ነገር ነበር(ሳቅ)።

**አሻራ፡-** ሌላስ እንደ አባት የሚገለጽ ባህሪ የላቸውም? ቁጡ! የሚፈሩ? ..

**ዶ/ር መቅደስ፡-** ብዙ ጊዜ ጓደኞቼ አባቴ ይቆጣል! አባቴን እፈራዋለሁ.. ሲሉ ይገርመኝ ነበር። እኛ ጋ እንደዚህ አይነት ነገር የለም። ከአፉ አውጥቶ ካልተናገረ በስተቀር ምንም የምናውቀው ነገር አልነበረም። የሚነግረን ነገር ካለም ረጋ ብሎ ነው የሚነግረን።ግርፊያ፤ ዱላ፤ቁጣ ... የሚባል ነገር የለም።ጥፋት እንኳ ብታጠፋ ቁጭ አድርጎ የሚነግርህ ነገር ማጥፋትክን እንድትጠላው ነው የሚያደርግህ። እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ደግሞ ብዙም አልነበረም ።

ሌላው ልነግርህ የምፈልገው “ቅድሚያ ለእንስት” (Ladies First) በሚለው መርህ ላይ ያለውን እምነት ነው። እኔ ልጅም ሆኜ አሁን ጓደኞቼ አብዛኞቹ ወንዶች ናቸው፤ ብዙ ግዜ “ቅድሚያ ለእንስት” (Ladies First) በሚለው መርህ ላይ እንከራከራለን፤ ለምንድነው ቅድሚያ ለሴት የሚሰጠው አይነት ክርክር ማለቴ ነው፤ ይህ መርህ ግን ለአባባ አፋዊ ሳይሆን የውስጥ እምነቱ ነው። ለሴት ልጅ ክብር አለው።

አንድ አጋጣሚ ልንገርህ፡- ወደ አሜሪካ ልመጣ ስል፤ ኢሚግሬሽን ለፓስፖርት ይሁን አሜሪካ ኤንባሴ ለቪዛ ይሁን አሁን ዘንግቼዋለሁ፤ ከሱ ጋር አብረን ሄደን ነበር። በቀኑ በጣም ብዙ ባለ ጉዳይ ስለነበር መቀመጫም አልተገኘም። በኋላ ቀደም ብለው መጥተው ወንበር አግኝተው ከተቀመጡት ሰዎች መካከል እሱን የሚያውቁ ሰዎች እንዲቀመጥ ተነሱሉት፡፡ እሱ ደግሞ “አንቺ ተቀመጪ አለኝ”። እንዴ..? የተነሱት ላንተ ነው እኔ አልቀመጥም አልኩ፡፡ እሱ ግን “አንቺ ቆመሽ እኔ አልቀመጥም” ብሎ አስቀምጦኛል።ይህ የሚያሳየው ለሴት ልጅ ያለውን ክብር ነው።

እኔና እህቴን አስቀምጦ ሲመክረን ብዙ ግዜ ሴት ልጅ ከጾታዋ ጋር በተያያዘ ሊደርስባት የሚችለውን ችግር ካስረዳን በኋላ መፍትሄው

ደግሞ ትምህርት እንደሆነ አያይዞ ነበር የሚነግረን። በዚህ መልኩ ነበር የትምህርትን ወሳኝነት ውስጣችን የሚያስቀምጠው።

**አሻራ፡-** ፕ/ር ብዙ የሚታወቁባቸው ጠንካራ የስብዕና መገለጫዎችና ተያይዞም ችሎታዎች አሏዋቸው። ወዳንቺ የመጣው የትኛው ነው?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** (ሳቅ) በልጅነቴም ብዙ ሰዎች በመልክ ትመስይዋለሽ ነው የሚሉት ። ሌላ ሌላው ባብዛኛው ለሌላ ሰው የሚታይ ወይም ሌላው ሊናገረው የሚችል እንጂ ራስህ ስትናገረው ይከብዳል። ከሱ የተማርኩት የሚመስለኝ አንድ ነገር ፦ አልችለውም ብሎ ተስፋ መቁረጥ የሚባል ነገር የለብኝም። ማድረግ እችላለሁ (I can do it!)" ብዬ ነው የምነሳው! ። የጀመኩትን ግብ ሳላደርስ ተስፋ ቆርጦ ያለመቆም ዕልህ አለብኝ፡፡ ይህም ከሱ የመጣ ይመስለኛል። እሱ በዚህ እድሜው እንኳ አንድ ነገር ከጀመረ ጫፍ ሳያደርስ ምንምና ማንም አያቆመውም።

ሌላው ከሱ ወሰድኩ የምለው ጥቃትን በይሁንታ ወይም በያልፋል አይነት ትዕግስት አለመቀበልን ነው።አሁን ለምሳሌ እሱ የታሰረ ጊዜ እንደኔው ቤተሰባቸው ወይም አባታቸው የታሰሩባቸው ጓደኞቼ የሆነውን ተቀብሎ የማለፍን ነገር ሲያወሩ ለኔ በፍጹም አይዋጥልኝም ነበር። የኔ ጥያቄ በመጀመሪያስ ለምን ይሆናል? ለምን ይታሰራል? ነው፤ አግባብ ያልሆነ ነገር ሲፈጸምብህ ወይም መብትህ ሲነካ ታግለህ መብትን ማስከበር እንጂ ስለ ምህረትና ስለመሳሰሉት ነገሮች ማሰብ ትክክል አይመስለኝም። ይህም እምነቴ ከሱ የተገኘ ይመስለኛል።


**አሻራ፡-** ከፕ/ር የምታደንቂላቸው ችሎታና ባህሪያዎች አንድ አንዱን ልትጠቅሺልኝ ትችያለሽ...? .

**ዶ/ር መቅደስ፡-** በመጀመሪያ የተፈጥሮ ስጦታ በመሆኑ ክሬዲት የሚሰጠው ባይሆንም የሱ ጭንቅላት የተለየና በጣም የሚደንቅ ነው። በትንሽ ጊዜ ውስጥ አንድን ነገር ከተለያየ አቅጣጫ አይቶ ላንተ የማይታይህን ነገር አይቶ የሚያቀርብበት ችሎታው ሁሌም ያስገርመኛል።አንድ አወያይ ሃሳብ ከተነሳ ያ ሃሳብ ብትንትኑ ወጥቶ ካልቀረበ አይረካም። የሰው ሃሳብ በትዕግስት ያደምጣል። እሱም ያለመሰልቸት ያስረዳል። ባጠቃላይ ሃሳብን የመመርመር ችሎታና ትዕግስቱን አደንቃለሁ። ሌላው ደግሞ ያመነበትን ነገር ፊት ለፊት ከመናገር የሚያቆመው የለም።

አሁን ባለንበት ሕብረተሰብ አንድን ሃሳብ ተቃውመህ አልያም ወጣ ያለና የተለየ ሃሳብ ይዘህ ስትቀርብ እንደ ጠላት ወይም እንደ ድፍረት የመውሰድ ነገር እየተለመደ ነው። የታየህን ነገር በግልጽ ስትናገር ሃሳብክን እንደ ተለየ ሃሳብ ተቀብሎ በዛው ስሜት ከመመዘን ይልቅ ከጥላቻ እንደ መነጨ ተደርጎ ይወሰዳል። እንዲህ አይነት ልምድ እየገዘፈ በሄደበት ህብረተሰብ ውስጥ እንደ አባባ አይነት ሃሳቡን በግልጽ የሚናገር ሰው ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ይገጥሙታል።

**አሻራ፡-** በሶስት መንግስታት ውስጥ ሲያልፉ በተለያየ አጋጣሚ በትረ ስልጣኑን ከያዙት አካሎች ጋር በነበራቸው አለመግባባት ቤተሰባችሁ ስጋት ውስጥ የወደቀበት የምታስታውሺው ትዝታ ካለ? በተለይ መንግስቱን ውረድ ባሉበት ወቅት ምን ተሰማሽ?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** በመጀመሪያ የታሰረው እኔ ገና የ 11 ወይም የ12 አመት ልጅ ሆኜ ይመስለኛል፡፡ የረብሻው ምክንያት በጊዜው ባይገባኝም አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተረበሸ ተብሎ እሱም ታስሮ ቤት ውስጥ የነበረው ግርግር ትዝ ይለኛል፡፡ ያኔ ደግሞ አዋቂ ሲያወራ ልጅ ወደ ውጭ ወይም ወደ ጓዳ የሚባልበት ዘመን ነበርና ስለታስረበትና ስለረብሻው ምክንያት ብዙም የማስታውሰው ነገር ባይኖርም እንዲሁ ብቻ መታሰሩ ቤተሰቡን እንዳሳሰበ ትዝ ይለኛል።



ሌላው እንዳልከው መንግስቱ ኃይለማሪያምን ውረድ ባለበት ወቅት የተፈጠረው ነው። ያን ሁኔታ አሁንም ድረስ ሳስበው ይገርመኛል። በጊዜው እኔ እዚሁ አሜሪካን ሃገር ነበርኩ። ይህ በሆነበት ዕለት ወይም ማግስት ይመስለኛል አንድ ለሱም ለኔም ወዳጅ የሆነ ሰው ደውሎ "መስፍንን ሰሞኑን አግኝተሸዋል? "ሲል ጠየቀኝ። አይ ሰሞኑን አላገኘሁትም ብዬ ከመለስኩ በኋላ ነገሩ ስለከነከነኝ ምነው? ምን የተፈጠረ ነገር አለ? ብዬ ጠየቅኩት።

"አይ አሁንማ በቃ መንግስቱን ውረድ ብሎት አሁን ያለበት አይታወቅም፤ (He is in hiding) " አለኝ። በመጀመሪያ በጣም ደነገጥኩ፤ ተደብቋል የሚለው ነገር ከአባባ ተፈጥሮና ባህሪ ጋር በፍጹም የሚስማማ አልሆነልኝም። ልቀበልው አልፈለኩም።

በመሆኑም ወዲያው ደውዬ ለማረጋገጥ ፈለኩ። ላገኘው አልቻልኩም። ይህ በእንዲህ እያለ ያው ወዳጃችን መልሶ ደወሎ "ተድብቋል ያልኩሽ ቀልዴን ነው። መንግስቱን ግን ውረድ ብሎት መንግስቱ ሳይበሰጫጭ አልቀረም" አለኝ፡፡የጉዳዩ ክብደት ቀልዱን ባይገባኝም ተደበቀ የሚለው ነገር እውነት አለመሆኑን ይህን መቀበል አልከበደኝም።

በኋላም ደውዬ ሳገኘው ተረጋጋሁ፡፡ እንደተፈራው አልሆነም መንግስቱም አገር ጥሎ ጠፋ ሁሉም በዚሁ አበቃ። እንደ ሰማሁ ግን በጣም በጣም ነበር የደነገጥኩት።

**አሻራ፡-** የሳቸው ልጅ በመሆንሽ ምን ይሰማሻል?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** ይሄ ምን ያጠያይቃል ብለህ ነው? (ሳቅ) የሱ ልጅ በመሆኔ በጣም! በጣም ነው የምኮራው። በነገራችን ላይ እናቴም ያልተዘመረላት ጀግና እንደሚባሉት አይነት ነች። ከነዚህ ሰዎች መፈጠሬ ለኔ ክብሬም ኩራቴም ነው።


እኔ ብቻ ሳልሆን ሁላችንም ኢትዮጵያዊያኖች እዚህ የደረስነው ብዙ ዋጋ ተከፍሎ ነው። ለሃገራቸው ድንቅ ስራ ሰርተው፤ ግዙፍ መስዋዕትነት ከፍለው ለዛሬው ማንነታችን ያበቁንን አባትና እናቶቻችንን ውለታ ተሸክመን ነው የምንኖረው። እኔም ከሱ በመፈጠሬ ደስታዬ ወሰን የለውም።

**አሻራ፡-** ፕ/ር 85ኛ ዓመታቸውን በቅርቡ አክብረዋልና የመልካም ምኞት መልዕክት ካለሽ?

**ዶ/ር መቅደስ፡-** እሺ! እግዚአብሄር ደግ ነው። አባባ እኛ ጠብቀነው ደግፈነው እዚህ የደረሰ አይደለም።ከዚህ ሁሉ እንግልት በኋላ የተመኘውን ሁሉ አድርጎ ያሰበውን ሁሉ ሰርቶ ለ85 ዓመት የእድሜ ባለጸግነት መብቃት የእግዚአብሄር ስጦታ ነው። አሁንም ደግሞ ያሰበውን ሁሉ ማሳካት እንዲችል እድሜና ጤና እንዲሰጠው የዘወትር ጸሎቴ ነው።

**አሻራ፡-** ስለ ጊዜሽ በጣም እናመሰግናለን

**ዶ/ር መቅደስ፡-** እኔም ለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ።



# የሰብአዊ መብቶች አረኛ ፕሮፍ!

ወንድማገኘ ጋሹ

የህይወት አጋጣሚ ሆኖ ከታላቁ ኢትዮጵያዊ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ጋር አብሮ የመስራት እድል አጋጥሞኝ ስለነበር የአሻራ መጽሄት አዘጋጆች ትውስታዬን እንድከትብ ጋበዙኝ። ስለ ፕሮፌሰር የዘመናት ተጋድሎ ብዙ ለማለት አልደፍርም። አቅሙም የለኝምና። ግና ኢሰመጉን በአባልነት ከተቀላቀልኩበት ጊዜ ጀምሮ ፕሮፍ ከሰፊ ልምዳቸውና ዕውቀታቸው እያካፈሉ ከኮተኮቷቸው አንዱ ነኝና በስራ ሂደት በቅርበት ሆኜ ካየኋቸውና ከታዘብኳቸው መሀል ጥቂት ትውስቶቼን ላካፍላችሁ ወደድኩ።

እስቲ ፕሮፍን በምናብ ለመሳል እንዲረዳን በሚከተሉት ስንኞች እንንደርደር፡-

**"...እኔ ሰው ነኝ፣**
**እኔ ሰው ነኝ፣**
**ኢትዮጵያዊ!**
**መብቴን የማውቅ፣ ነጻነቴም ታሪካዊ!**
**እናቶቼ በደማቸው፣**
**አባቶቼ በአጥንታቸው፣**
**ያቆዩልኝ ያስረከቡኝ፣**
**የነገሩኝ ያስተማሩኝ፣**
**ጭቆና እምቢ አሻፈረኝ፤**
**አላስነካም ነጻነቴን፣**
**አላስደፍርም መብቴን፣**
**አልመነዘርም በጎሳ፣**
**አልሸጥም በቤሳ።**
**እኔ ሰው ነኝ፣**
**እኔ ሰው ነኝ**
**ኢትዮጵያዊ!**
**መብቴን የማውቅ፣ ነጻነቴም ታሪካዊ። ..."**

ይህ ግጥም የኢሰመጉ መዝሙር ነው። አባላቱ በፍጹም ስሜትና ቁርጠኝነት ስናዜመው የሚፈጥረው ስሜት ኃያል ነበር። የግጥሙ ባለቤት ፕሮፌሰር ናቸው። በነዚህ ስንኞች ውስጥ ሁለት ጉልህ ነጥቦች ማስተዋል የሚቻል ይመስለኛል። ሰው የመሆንን የባህሪ ምስጢር ታያለህ። በኢትዮጵያውያን ፍልስፍና ሰው ከሰባቱ ባህርያት ተፈጥሯል። ሦስቱ ባህርያተ ነፍሱ (ሀሳቢነቱ፣ ተናጋሪነቱና ሕያውነቱ) ከእንስሳት የሚለዩት የሰው ልጅ ብቻ የሆኑ ተፈጥሯዊ ፀጋ ናቸው ይልሀል። እነዚህን ስጦታዎቹን በወጉ መጠቀም ከቻለ የሰው ልጅ እራሱንም አካባቢውንም ለመለወጥ የሚያስችል ጠንካራ መሰረት ይኖረዋል። ሀሳቡን በነጻነት መግለጽና ማስተላለፍ መቻሉ ወሳኝ ነው። ይህ ደግሞ በንግግርም በጽሁፍም የሚሆን ነው። ሰብአዊነቱ የሚገለጠውም መብቶቹን አውቆ ላለማስነካት ሲቆርጥ ነው። ለጭቆና የማይንበረከክ ትውልድ እንዲመጣ፣ ሁሉም ለመብቱ እንዲቆም የቀረበ ጥሪም ይመስላል። ይህ መዝሙር የኢትዮጵያ ታሪክ በአባቶቻችን ደም የቀለመ የእምቢተኝነት ውጤት መሆኑንም ያስታውሳል። አይበገሬነትን ጎልቶ ያወጣል። ባጭሩ "እኔ ሰው ነኝ" በሚል ‹ማንነት ወይም ሰውነት ክቡር ነው፣ ተፈጥሯዊ ነጻነትህን ለሆድ ብለህ አሳልፈህ አትስጠው! ከሰውነት ተራ አትውረድ! ‹ሰው ነኝ!› ለማለት ብቃ!" የሚል ጠንካራ መልዕክት ያስተላልፋል። ለዚህም ነው በኢሰመጉ አባላት በቃልኪዳናቸው የመጀመርያው መስመር ላይ " ከእንግዲህ ወዲያ የኢትዮጵያ ህዝብ ለኃይል አገዛዝ ስርዓትና ለጠብመንጃ አፈሙዝ አይንበረከክም!" የሚል ሀሳብ የተገለጠው። ይህም ለአባላቱ ጽናትና ትጋት መሰረት ነው።

የዚህ፡- ሰው መሆንን መሰረቱ ያደረገ፣ ለሰብአዊ መብቶች ጥብቅና የቆመ አካል አስኳሉ ደግሞ ሊቁ ፕሮፍ ናቸው። ፕሮፌሰር መስፍንን ቀርበህ ስትረዳቸው፣ ጆሮህን ከፍተህ ስታደምጣቸው በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ ንጉስ ዳዊት ለልጁ ለሰለሞን "ሰው ሁን!" ያለው ቃል ነፍስህን የዳሰሳት ይመስልሀል። ሰው የመሆን ምስጢሩም በቁመና የማይለካ በአምስቱ የስሜት ህዋሳት የማይገደብ መሆኑ ጠልቆ ይሰማሀል። በፕሮፍ አንደበት የንጉስ ዳዊትን ድምጽ የሰማህ ሊመስልህ ይችላል። ኢሰመጉን መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም. የወለደውና የኢትዮጵያውያን መብትና ነጻነት እንዲከበር ነጋሪቱን የጎሰመው ይኸው ሰው የመሆን ትርጉምና የተቆርቋሪነት መንፈስ ነው።

ካልተሳሳትኩ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስለሰብዓዊ መብቶች በአደባባይ ማስተማርና በይፋ መሟገት የጀመሩት ፕሮፌሰር መስፍን ይመስሉኛል።ኢሰመጉን መስርተው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን እያስተረጎሙ በስፋትና በብዛት ለማሰራጨት የበቁ፣ የሰብአዊ መብቶች መከበርን፣ የህግ የበላይነትንና የዲሞክራሲ ስርዓት መረጋገጥን ቀዳማይ ዓላማቸው አድርገው ያለመታከት የደከሙ ሰው ናቸው ። ዜጎች በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች በግፍ ሲገደሉ፣ ያለህግ ሲታሰሩና ሰቆቃ ሲደረሰባቸው የፕሮፍ ልብ ትቆስላለች። አዝነው ግን ዝም አይሉም። ሁሌም ከሰለባዎች ጎን ይቆማሉ። አጋርነታቸውን በተግባር ያሳያሉ። መንግስታዊ ግድያዎችን በማጋለጥና ገዳዮች ለፍርድ እንዲቀርቡ በመሟገት፣ ታፍነው የደረሱበት ያልታወቁትን በማፈላለግና ነጻ ይሆኑ ዘንድ በመትጋት፣ ግፍን በሚቻለው ሁሉ በማጋለጥና በመጋፈጥ ነፍሱን ለሌሎች አሳልፎ የሰጠ የኢትዮጵያ ውድ ልጅ፤ (የተወዳጁን ብዕረኛ የጸጋዬ ገ/መድህን አርአያን ቃል ልዋስና) የኢትዮጵያ ልዩ አፈር ናቸው - ፕሮፍ። ታላቁ ሰው ስንት የነጻነት፣ የፍትህ፣ የሰብአዊ መብት፣ የፕሬስ ነጻነት ታጋዮችን አፈሩ?. . . ስንት ደቀ መዝሙሮች አስከተሉ? . . .ስንት ትንታግ እምቢ ባዮችን ፈጠሩ? . . . አትጠራጠሩ አእላፍ ናቸው። የነገይቷ ኢትዮጵያ ተስፋዎች።

## ጥቂት ትውስቶች - ከኢሰመጉ ቆይታዬ

በኢሰመጉ ዓላማዎች ተማርኬ ከአባልነት እስከ ሰራተኛነት በቆየሁበት ከ10 በላይ ዓመታት የታላቁን ምሁር ዐዋቂነትና ብስለት፣ ድፍረትና ቁርጠኝነት፣ ንዴትና አይበገሬነት፣ ቀጥተኛነትና ቀናዒነት፣ ለሌሎች ሀሳቢነትና ተቆርቋሪነት . . . በቅርበት ለማየት ዕድል አግኝቻለሁ። ለአብነቱ ያህል እንሆ ከትውስቶቼ ጥቂቱን አቀርባለሁ፡-

ኢሰመጉ በሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራና ማጣራት ክፍል ከመግባቴ በፊት በአባልነት በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በበጎ ፍቃድ እሰራ ነበር። የኢሰመጉ ስራ አስፈጻሚ 7 ወጣቶችን መርጦ ስልጠና እንዲሰጠን አደረገ። በወቅቱ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

⇨

የነበሩና ታላላቅ ስም የነበራቸው ምሁራን ኮርሶቹን ተከፋፍለው ያስተምሩን ነበር። ፐ/ር መስፍን፣ ፐ/ር አንዳርጋቸው፣ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ፣ አቶ ንጋቱና ሊሎችም ነበሩ። ሰባቱ ሰልጣኞች ደግሞ ፦ ያሬድ፣ ቸርነት፣ ዓይንአዲስ፣ ሮማን፣ ሰለሞን፣ ነጻነት እና እኔ ነበርን። Research and Methodology የሚሰጡን ፐ/ር መስፍን ነበሩ። ፕሮፍ በወቅቱ በአንድ ጉዳይ ድምዳሜ (conclusion) ላይ ከመድረሳችን በፊት እንዴት ከስሩ ማጥናት እንዳለብን፣ በማስረጃ ማስደገፍና ሌሎችም መሰረታዊ ነጥቦችን እያነሱ ያስተምሩን ፣ በቤት ስራም ያጣድፉን ነበር። ሰልጣኞቹ በሙሉ በ20ዎቹ መጀመርያ ዕድሜ ላይ የምንገኝ ወጣቶች ስንሆን ለብዙ ርዕሰ ጉዳዮችም እንግዳ ነበርን። ፕሮፍ ደግሞ በማፋጠጥ፣ በጥያቄና መልስ፣ በክርክር አእምሯችንን ይሞርዱታል። የሳቸው ክፍለ ጊዜ ሁሌም ቢሆን የተጋጋለ ነው። የሀሳብ ሙግቱ ይደራል። ያለማስረጃ ፕሮፍን ማለፍ አይሞከርም። በአራዳ ቋንቋ መሸወድ አይታሰብም። ክፍሉ ውስጥ የማይዳሰስ ርዕስ የለም። ባህል፣ ሀይማኖት፣ ታሪክ፣ ድህነት፣ ሥልጣን . . . ወዘተ። የህብረተሰቡ አንኳር ጉዳዮች ሁሉ ይነሱ ነበር ብል ማጋነን አይሆንም።

አንድ ቀን እንዲህ ሆነ። ስለባህልና የነጻነት ጉዳይ ተነስቶ እንወያይ ጀመር። በመሀሉ በማህበረሰቡ ያልተለመዱ ዓይነት አለባበሶችን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች ተነሱ። ፕሮፍ ከነጻነት አኳያ ሲያዩት ኃይማኖት፣ አስተዳደግና ባህል ጨምድዶ የያዘኝ እኔ ደግሞ ሙግት ቢጤ ሞካከረኝ። የህብረተሰቡን ሞራላዊ ዕሴቶች የሚጋፉ ተግባሮች ክልክል ይገባቸዋል በሚል ‹ጸያፍ› ያልኳቸውን ዓይነት አለባበሶች ተቃወምኩኝ። ፕሮፍ ታዲያ በመርህ ደረጃ ነበር መልስ ያሳጡኝ። ሰዎች የሌላውን መብት እስካልተጋፉ ድረስ ወድደው የሚያደርጉትን ነገር ለምን ትከለክላቸዋለህ? የፈቀዳቸውን የማድረግ ግለሰባዊ ነጻነታቸውን ለምን ትገድበዋለህ? መብቱስ አለህ ወይ? አሉኝ። እዚያው ቢሮ ውስጥ የነበረ የጆርጅ ኦርዌል መጽሀፍ አውጥተውም ሁሌም የማይረሳኝን ጥቅስ አስነበቡኝ። “ሌሎች አንተ የምትፈልገውን ብቻ ሳይሆን የማትፈልገውንም ሲናገሩ ለመስማት ሞክር” የሚል። በርግጥም ያቺ ሙግት ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙርያ እንዳምሰለስል ያገዘችኝ ዓይነተኛ ቁም ነገር ሆነች። የማንወዳቸውን ነገሮች ስለሚወዱ፣ መጥፎ የምንላቸውን ጉዳዮች ጥሩ ስለሚሉ ሁሉ ማሰቡ አይከፋም። “እንደኔ ብቻ እዩ፣ እንደኔ ብቻ አስብ . . .” አይበጅም። “እንደኔ ብቻ” ለአንድ የመብት ተሚጋች አይሰራም። “እንደኔ ብቻ” ለአንድ ፖለቲከኛም አይሆንም። ነጥቡ ሌሎች ኃሳቦችን ለመመርመርም በር ከፍቶልኛል። የክርስትና ዕምነት ተከታይ ብሆንም ቁርአንንም አነበብኩ። የኮንፈሽየስን ጨምሮ የተለያዩ ፍልስፍናዎችን ለጠቅላላ ዕውቀት እንዳነብ ግፊት ሆነኝ። ከራሴ ባህልና ሀይማኖት ምህዋር ወጥቼ ሌሎችንም ለመስማትና ለመረዳት እንድሞክር አነሳሳኝ። . . . አንዳንዴ ፕሮፍን ያህል የዕውቀት ማህደር በብሄራዊ ደረጃ በሚተላለፉ መገናኛ ብዙሀን እየቀረቡ ህዝቡን የሚያስተምሩበት ዕድል ቢኖር ምንኛ ጥሩ ነበር እያልኩ እመኛለሁ። ችግሩ ግን አምባገነን ስርአቶች ይህን ቢፈቅዱ የስልጣን ዕድሜያቸው እንደሚያጥር ስለሚያውቁት የማያደርጉት መሆኑ ነው።

## ሕገ - አራዊት


“ሕገ- አራዊት” በ1997 ዓ.ም. የምርጫ ክርክር ወቅት ፕሮፍ የአፈና ስርአትን ለመግለጽ የተጠቀሙባት ቃል ናት። መለስና በረከትን እንዴት ስታንጨረጭራቸው እንደቆየችም አስታውሳለሁ።

እሁድ መጋቢት 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ኢሰመጉ ‹የአካዳሚክ ነጻነት መብቶች› በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች የአንድ ቀን አውደ ጥናት አዘጋጅቶ ነበር። ተናጋሪዎቹ እነ ፐ/ር መስፍን ወልደ ማርያም እና ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ናቸው። ተሜ የብሄራዊ ሎቶሪን አዳራሽ የሞላው ከሰአቱ ቀደም ብሎ ነበር። በዕለቱ ተናጋሪዎቹ ስለሰው ልጆች መብትና ነጻነት፣ ስለዩንቨርሲቲ ተማሪዎች የመማር መብት . . . በስፋት ተነተኑ። ተማሪዎቹ ውስጥ ውስጡን ሲያበግናቸው የቆየውን ችግር ተናጋሪዎቹ በይፋ መድረክ ላይ ያለፍርሀት ሲገልጹት መመልከት ቻሉ። ይህም ፍርሀትን የማስወገድ፣ ዕውነትን በጽናት የመፈለግ ስሜትን ለማሳደግ የበቃ ሆነ።

በማግስቱ ተሜ 6ኪሎ ላይ ተመመ። ‹በጽልመት ውስጥ ዘላለም ከመኖር፣ ብርሀን ውስጥ በነጻነት ለአንድ ሰዓት በስቃይ ማሳለፍ ታላቅነት ነው› እያለ። “የአካዳሚክ ነጻነት ይከበር!” “መብታችን አሁኑኑ!” የሚሉና ሌሎችም ጥሪዎች 6ኪሎን አቋርጠው፤ 5ኪሎንና 4ኪሎን አዳርሰው፤ ኮተቤን፣ ናዝሬትን፣ ባህር ዳርን፣ ጂማና ሐረርን ለማራድ ጊዜ አልፈጀባቸውም። የተማሪዎቹን ጥያቄ ተከትሎ ህዝቡም አጋርነቱን አሳየ። ‹ትንሸዬ አብዮት ተነሳ› ማለት ይቻላል። ከጦር መሳርያ ውጪ ምላሽ የሌላቸው የአገዛዙ ታጣቂዎች ግን አፈሙዛቸውን በሰላማዊ ዜጎች ላይ አዞሩ። 42 ንጹሀንንም ገደሉ። በርካታ ዜጎች በግፈኞች አረር ቆሰሉ፤ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎችም ታፈኑ፣ ተጋዙ፣ ተቀጠቀጡ . . .። በወቅቱ ትንታግ የነበሩ የኢዴፓ አመራርና አባላት ጭምር ወደ ዝዋይና ሸዋ ሮቢት ተጋዙ።

ፕሮፍና ዶ/ር ብርሀኑ ነጋም ዋጋ መክፈላቸው አልቀረም። ሚያዚያ 30 ቀን 1993ዓ.ም. በቁጥጥር ስር ውለው ለ28 ቀናት በዝነኛው ማዕከላዊ ማሰቃያ በእስራት ቆዩ። በዚህ ንቅናቄ የተማሪዎቹ ፕሬዘዳንት የነበረው ተክለ ሚካኤል አበበ (አሁን ካናዳ) እና ዋና ጸሀፊ የነበረው መስፍን ወልደ ስላሴ (አሁን አውስትራሊያ) ከሌሎች በርካታ ተማሪዎች ጋር ወደ ኬንያ ለመሰደድ መገደዳቸው ይታወሳል።

በተከታዩ ሳምንት የህወሀት የደህንነት ሰዎች ከፖሊሶች ጋር በመሆን እስረኛውን ፕሮፌሰር ይዘው ወደ እኛ ቢሮ መጥተው ነበር። ከአንዴም ሶስቴ። ግንቦት3፣ 4 እና 9 ቀን 1993ዓ.ም. ቢሯችንን በረበሯት። በወቅቱ ፕሮፍ ግፉን አውግዘው የረሀብ አድማ ላይ ነበሩ። ታጣቂዎቹ የእኔንና የስራ ባልደረቦቼን ጠረጴዛዎች እየከፋፈቱ የሚፈልጉትን ሁሉ ይወስዱ ነበር። ከእኔ ዴስክ መሳቢያ ኪስ ውስጥ የመንግስት ታጣቂዎች የፈጸሙትን ህገ ወጥ ግድያ ስንመረምር በማስረጃነት ተወስዶ የነበረ አንድ የጥይት ቀለህ መገኘቱ ትዝ ይለኛል። አንድ የህወሀት ደህንነት አባል ቀልሀዋን ይዞ አፈጠጠብኝ። “ከየት አመጣኸው” ሲልም ጮኸ። ይሄኔ ፕሮፍ መቼም የማይረሳኝ ምላሽ ሰጡ። በሞራል ከፍታ ላይ ቆመው “አትጮህ!“ አሉት። “ እነዚህ ወጣቶች የሚሰሩትን የሚያውቁ የህግ ባለሙያዎች ናቸው። ከቶም በአንተ የሚደነፋባቸው ልጆች አይደሉም “ ብለው አስደነገጡት። በእውነቱ በፕሮፍ ላይ የሚታየው በራስ መተማመንና የሞራል የበላይነት አፋኞቹን ሳይቀር የማርበድበድ ሀይል እንደነበረው ሳይ ገረመኝ። ፕሮፍ በአሳሪዎቻቸው እጅ ይውደቁ እንጂ በመንፈስ ተጽዕኖ ስር የታሰሩት ግን ራሳቸው አሳሪዎቹ ይመስሉ ነበር። ያ ታላቅ ሀይል ከምን መነጨ? . . . ዕውነትን ይዞ ከመቆም፣ ከዓላማ ጽናትና



ወደ ገጽ 39 ዞሯል

# የማውቀውን ያህል
# ስለ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም

ያሬድ ኃይለማሪያም (ከቤልጂየም)

ስለ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም መልካም ሥራዎች የማውቀውን ያህል እንድመሰክር እድሉን ስለሰጣችሁኝና እኚህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ ምሁር ለሚወዷት አገራቸውና ለሚያከብሩት ሕዝብ ያበረከቱትን አስተዋጽዖ በህይወት እያሉ ለመዘከር በማሰባችሁ ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ፕ/ር መስፍን ከልጅነት እስከ አሁን ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉና ተስፋም ሳይቆርጡ ኢትዮጵያና ሕዝቧን ለዘመናት ከተጫኗቸው መከራዎች ለመታደግ እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን ያለ አንዳች ስስት ሲገብሩ የኖሩ ሰው ናቸው። ዛሬም በእስተርጅና እድሜን ተከትሎ ከመጣ የጤና መታወክ ጋር እየታገሉ ለአገርና ለወገን ይበጃል ያሉትን ከማድረግ አልተቆጠቡም።

እኔ ፕ/ር መስፍንን የማውቃቸው ቀደም ሲል በተለያዩ ህዝባዊ መድረኮች ላይ እየተጋበዙ አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ትምህርት ሲሰጡና በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶችም በሚታተሙ ጽሑፎቻቸው ነበር። ከዚያም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ተባባሪ አባል በሆንኩኝ ጊዜ እኚህን ታላቅ ሰው በቅርበት ለማወቅ ቻልኩ። ኢሰመጉ ለአባላቱ በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች፣ የስነ-ዜጋ ትምህርቶችና አመታዊ ጉባኤዎች ላይ ፕ/ር መስፍን በሰብአዊ መብቶች፣ በሕግ ልዕልና እና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዙሪያ ይሰጡት የነበረው ትምህርትና ያደርጓቸው የነበሩት ንግግሮች የኢሰመጉ አባላት በሆንነው ወጣቶች አዕምሮ ውስጥ ታትመው ዛሬ ያለንን ስብዕና እንድንላበስ አድርጎናል። እኔና የተወሰንን ወጣቶች ከኢሰመጉ ጋር የነበረን ቆይታ ከተባባሪ አባልነት አልፎ ወደ ሠራተኝነት በማደጉም ፕ/ር መስፍንን እጅግ እንድንቀርባቸውና ከአደባባይ እውቂያም አልፎ በሥራና በትግል መሪነት እንድናውቃቸው እድል ፈጥሮልናል። ኢሰመጉ ውስጥ ለሰባት አመታት ያህል በሰብአዊ መብቶች ጥሰት መርማሪነት ባገለገልኩበት ጊዜ ውስጥ የድርጅቱን አላማ ለማሳካት የሚያስችለውን የመርማሪነት ክህሎትና የሙያ ጽናትን፤ እንዲሁም ስለ ሰብአዊ መብቶች ጥልቅ የሆነ ግንዛቤንና እውቀትን ያገኘነው ከፕ/ር መስፍን ነው።

ፕ/ር መስፍን እሩህሩህ፣ አዛኝና ፈሪሃ እግዚያብሄር ያደረባቸው ሰው በመሆናቸው የተገፉና በደል የደረሰባቸውን ሰዎች ህመምና ስቃይ ቶሎ ብሎ የመረዳት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ከጎናቸውም በጽናት በመቆም ግንባር ቀደም ናቸው። እንደ በርካታዎቹ የአገራችን ምሁራን የወገኖቻቸውን ስቃይ ከንፈር በመምጠጥ ወይም ልሂቃዊ ትንታኔ በመስጠት አያልፉም። የዘር፣ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ ምልከታ ወይም ሌሎች መስፈርቶች ሳይወስኗቸው ለሰው ልጆች ሁሉ፤ በተለይም ለድሆች፣ የመብት ጥሰትና የግፍ ተግባር ሰለባ ለሆኑ፣ መድልአና መገለል ለደረሰባቸው ሁሉ በድፍረትና በሙሉ ልብ አደባባይ ቆመው ድምጻቸውን የሚያሰሙ የሕዝብና የአገር ኩራት ናቸው።

በአብሮ ቆይታችን ውስጥ ከፕ/ር መስፍን የተማርናቸው እጅግ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም ጥቂቶቹን ለማውሳት እወዳለሁ። አንዱ ለሰው ልጆች ሁሉ ያላቸው እኩል አክብሮትና ሚዛን ለፍትህና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ያላቸውን ተቆርቋሪነትና ጽናት በምንም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን እንዳይዛነፍ ያደረገው መሆኑን ነው። ለዚህም የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት ተከትሎ በኤርትራዊያን ከኢትዮጵያ በግዳጅ መባረር ላይ የነበራቸው ጠንካራ አቋም አንዱ ጥሩ ማሳያ ነው። በርካታ የሕግ ባለሙያዎች፣ ፖለቲከኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ሳይቀሩ በዚህ ሁኔታ ላይ ሚዛን የሳተ አቋም ሲይዙ ፕ/ር መስፍን ግን መንግስት የፈጸመውን የመብት ጥሰት ኢሰመጉም እንዲያወግዘው ከማድረጋቸውም ባሻገር በግላቸውም አደባባይ ላይ ወጥተው ድርጊቱን አውግዘዋል። በዚህም ከተለያዩ አካላት ጠንካራ ነቀፌታዎች ተሰንዝረውባቸዋል። በኢሰመጉ የአባላትና የሰራተኞች ስብሰባዎችም ላይ ጉዳዩ በተደጋጋሚ ተነስቶ አንዳንድ ሰዎች የኤርትራዊያኑን በዚያ መንገድ መባረር እንደትክክለኛ እርምጃ ሲቆጥሩት ተስተውሏል። ይሁንና ፕ/ር መስፍን አንድ የሰብአዊ መብት ተሟጋች እንዲህ ባሉ ጉዳዮች ላይ ሊላበስ ስለሚገባው ስብዕና፣ ነገሩን የሚመዝንበትን ፍትሃዊ የሆነ ሚዛንና ከሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችና መርሆዎች አንጻር ያለውን እንድምታ በጥልቀት በማስረዳት ብዙዎች የተንሻፈፈ አመለካከታቸውን እንዲያርቁ አድርገዋል።

ሌላው ትውስታ በአዲስ አበባ የምሽት ጭፈራ ቤቶች ውስጥ ሰዎች እርቃናቸውን ሲጨፍሩ ተገኙ በሚል በርካታ ሰዎች ለእስር ከመዳረጋቸው ጋር የተያያዘ ነው። ይህን ዜና ተከትሎ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች መንግስት የወሰደውን እርምጃ የሚደግፉ ድምጾች ይሰሙ ነበር። በኢሰመጉ የምርመራ ክፍልም ሆነ በጽ/ቤቱ ውስጥ በወቅቱ የነበሩ ኃላፊዎች ከጠቅላላው ማኅበረሰብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ምልከታ ስለነበረንና ድርጊቱንም እንደ ነውር የመቁጠር አዝማሚያ ስለነበር ጉዳዩን ከሰብአዊ መብት አንጻር ለማየት አቅሙ አልነበረንም። በመሆኑም ሁኔታውን ሳንከታተለውና በግለሰቦቹ መታሰርም ዙሪያ ምርመራ ሳናካሂድ ቆየን። ይህን የታዘቡት ፕ/ር መስፍን የኢሰመጉ ጽ/ቤት ድረስ በመምጣት ከሰበሰቡን በኋላ ይህን ጉዳዩ ለምን ችላ እንዳልነው ጠየቁን። እኛም የተሰማንን ገለጽን። ፕ/ር መስፍንም በባህል፣ በኃይማኖትና በሌሎች አገራዊ ወጎች የተተበተበውን አስተሳሰባችንን ቆም ብለን እንድንፈትሽ በሚያደርግ መልኩ ጉዳዩን ከአገሪቱና ከአለም አቀፍ ሕግ አንጻር ያለውን እንድምታ በማሳየት እነዚህ ሰዎች እራቁታቸውን የጨፈሩት ባደባባይ እስካልሆነ ድረስና ታዳሚያቸውም ያሉበትን ቦታ ፈልጎና ከፍ ያለ ገንዘብም ከፍሎ እስከታደመ ድረስ የቀሪው ሕዝብ መብትም ሆነ ጥቅም የተነካ መሆኑን የሚያሳይ ምንም ነገር የለም። ስለዚህ ባህላችንን አጉድፈዋል፣ ወዘተ... የሚሉ ምክንያቶች ደርድሮ ግለሰቦቹን እና ታዳሚዎቻቸውን ከየጭፈራ ቤቱ ሄዶ በማሰር መንግሥት የሰብአዊ መብታቸውን ያለአግባቡ የጣሰ መሆኑንና ቀሪውም ሕዝብ፤ እኛም "የሰብአዊ መብት ተሟጋች" ነን የምንለው ሰዎች ሳንቀር እርምጃውን መደገፋችን አግባብ እንዳልሆነ አስተምረውናል። ሃሳባቸውንም በግል ጋዜጦች በኩል በአደባባይ አሳይተዋል። ስንቶቻችን ከዚህ ክስተት ትምህርት እንደወሰድን አፍ ሞልቶ መናገር ይከብዳል። ምክንያቱም ዛሬም በነጻነት እንዳናስብ፣ ነገሮችን በጥልቀት መርምረን ሚዛን ያለው አስተሳሰብ እንዳንይዝ ተብትበው የያዙን ባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና ሌሎች ስንክሳሮች እንዳሉ ናቸውና።

ፕ/ር መስፍን ስለ ሃብትና ንብረትም፣ እንዲሁም በማህበራዊ ፍትህ ዙሪያ ያላቸው አቋምና ሲያስተምሩን የኖሩትም ከዚሁ ጥልቅ ከሆነው የሰውን ልጅ ስብእና እና የሞራል ልዕልና ከሚመዝኑበት ሚዛን ጋር የተቆራኘ ነው። በድህነትና በባለሃብትነት መካከል ያለውን ቁርኝት

ወደ ገጽ 23 ዞሯል

# የዓረቡ ዓለም መቆራቆስ ቀይ ባሕርን ይሻጋገር ይሆን?

ዩሱፍ ያሲን

የየመን ጉዳይ ዛሬ የደረሰባት ምስቅልቅል ሁኔታ ላይ ሳይደርስ እውቁ የዶቼቬለው ጋዜጠኛ ነጋሽ መሐመድ ባንድ አጭር ቃለ መጠይቅ ውስጥ "ይህ ውጥንቅጥ ቀይ ባሕርን ይሻጋገር ይሆን ወይ?" ብሎ እንደ ቀልድ ማሳረጊያው ላይ ጥያቄ ወረወረልኝ። እኔም በቀልድ ነበር "የት ይቀራል!" ያልኩት በዚያን ጊዜ። ስለ ጥያቄው በጥሞናና በጥልቀት ሳላስብበት ነበር የመለስኩለት። በደመ-ነፍስ ማለቱ ሳይቀል አይቀርም። በኋላ ላይ ግን በጥሞና አሰብኩበት።በተለይ የየመን ጉዳይ አሁን ወደ ደረሰበት የእርስ-በርስ ጦርነት መሰል ሁኔታ ከደረሰ በኋላ የአካባቢያችን ትርምስምሶች ቀይ ባሕርን ተሻግረው እኛን ሊያተረማምሱን ይችላሉን? የሚለውን ጥያቄ በምር አሰብኩበት፤ አሳሰበኝም። ትርምሱ፣ ምስቅልቅሉና ቁሩቁሱ ጠባቡን የባብ-አል-መንደብ መሻገሩ ብቻ አልነበረም አሳሳቢው። ዛሬ ሁሉም የየመን ውጥንቅጥ ሁኔታ አካባቢውን ከማተረማመስ አልፎ "ለዓለማችን ሰላምና ደህንነት አናጊ የስጋት ምንጭ" ይሆናል እያሉ ናቸው። ልብ በሉ ይቺ ባንድ ጉዳይ የተ.መ. ድ. የፀጥታ ምክር ቤት ጣልቃ እንዲገባ ሲፈለግ የምትመዘዝ ሓረግ ነች። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በፀጥታ ምክር ቤቱ ሓላፊነት መዘዘኛው ሰባተኛው አንቀጽ ተጠቅሶ ሰላም አስከባሪ ኃይል እንዲሰማራ ምክንያት (ካልተገኘም) ሰበብ ሲፈለግ ነው። ሰበብም መገኘቱ አይቀርም! የዛሬ 15 ዓመት ገደማ በ1998 አሜሪካና ሸሪኮቿ የኅስላቪያን ለ78 ቀን በቦምብ የደበደቡት "ሰብአዊ ጣልቃ ገብነት" በሚል ሰበብ ነበር። ድብደባውም "ሰብአዊ ድብደባ" መሆኑ ነው።

የሳዑዲ አየር ድብድባ የተጀመረው በዓብዱ ራቦ ማንሱር ሃዲ የሚመራው ሕጋዊ የየመን መንግሥት ባቀረበላቸው ጥያቄ መሠረት ነው ተብሏል። ባሁኑ የሣዑዲና ተቀጻላዎቿ ደብደባ ከገልፍ 4 ሃገራት በተጨማሪ 6 ሃገርት እየተሳተፉበት ነው ተባለ። ግብፅም፣ ሱዳንም ጆርዳንም አሉበት። አለንበት ብለዋልና። ፓኪስታንና አፍጋን ስታንም አለንበት ብለዋል። ከቅርቦቹ ዖማን ሡልጣኔት ብቻ ናት 'እኔን እለፉኝ' ያለችው። ከሁሉም የሚገርመው ግን አፍጋኒስታን ሳትቀር ከሣዑዲ ዓረቢያ ጎን መቆሟን አሳታውቃለች መባሉ ነው። በዚህ ዜና እየተገረምኩ የሱዳኑ መሪ አልበሺር ሃገራቸው ከሣዑዱ ጎን ስለመሰለፏ አስፈላጊነት ያቀረቡት ምክንያት ከማስገርም አልፎ ፈገግ አሰኝቶኛል። " በሣዑዲ ዓረቢያ ያሉት ሁለት ቅዱሳን የሙስሊም ሙክራቦች ላይ የሚቃጣውን ወረራ ለመከላከል ነው" ያሉትን አስቂኝ ምክንያት ማለቴ ነው። ሁለቱ የሓበሻ መንግሥታት ፈራ ተባ እያሉ ዝምታን ከመረጡ በኋላ ኤርትራ ለንጉሡ መልእክት ልካለች ተባለ። ኢትዮጵያ ደግሞ "ሕጋዊውን መንግሥት እቦታው ማስመለሱን " እንደምትደግፍ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሚኒስትሯ እንደበት"የመን የኢትዮጵያ የቅርብ ወዳጅ" በመሆኗ ሃገሪቷ የተረጋጋች እንድትሆን፣ ይህም ለአካባቢ ሰላምና ልማት በተለይም "የቀይ ባሕርን ዙሪያ ሰላም በማድረጉ" ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አስታውቃለች። ሟቹ ጠቅላይ ሚንስትር "ምንን ነበረ፣ ማንን ምን ያገባዋል" ያሉት? የቀይ ባሕር ሰላም ኢትዮጵያን እንደሚያገባት አሁን ከተከሰተላቸው "ማል ጎዳኒ" ነው ለእኛ። እንኳን ለዚህ በቁ! አዲሱ የደብዳቢዎች ስብስብ ከዚህ በፊት በጆርጅ ቡሽ ዘመን ሳዳም ሁሴንን ለመደብደብ ከተሰባሰቡት በጎ ፈቃጅ ወዶ-ዘማቾች (The Coalition of the Willing) ጋር እየተመሳሰለ ነው የመጣው ። በአየር ድብደባ ብቻ እልባት ያስመዘገበ የጦር ውሎ እምብዛም ባለመታወቁ ሑቲ አማፅያኑን ወደ ተነሱበት ሣዕዳ አውራጃ መስመለስ መቻሉ ግን ከወዲሁ ብዙዎችን አጠራጥሯል። ወደ ውይይት ክብ ጠረጴዛ እንዲመለሱና ከቀሪዎቹ የሃገሪቷ ባለድርሻ ወገኖች ጋር እንዲነጋገሩ ማስገደድ ግን ይቻል ይሆናል። ጦርነቱን ወደ ራሷ ወደ ሣዑዲ ዓረቢያ ማዛመታቸው ሳይቀላቸው አይቀርም የሚሉ የአካባቢ ታዛቢዎችም አሉ። ሑቲዎቹ በተገላቢጦሹ የቆየ ሒሳብ ለማወራረድ ሣዑዲ ዓረቢያ ከየመን በጉልበት የጠረነፈችውን መሬት ገና እንስመልሳለን እያሉ እየዛቱ ናቸውና።

ለሁሉም የመንግሥታት ወይም ሃገራት ከውስጥ የመዘለፍለፍ ሂደት "Balkanization" የሚል ስም የተሰጠው ከአንደኛ የዓለም ጦርነት በኋላ በባልካን ሃገራት የተከሰተውን የሃገራት ወደ ታናናሽ ክፍልፋዮች የመሸንሸን ክስተት ተከትሎ ነበር። በዚያን ጊዜ ባልካኒዜሽን የተሰኘው የባልካኑ ሃገራት መዝለፍለፍ ወይም "መበልከን" ነው። እንደ ባልካን ሃገራት ተዝለፍልፎ የመፈረካከስ ሂደትን ለማመልከት። ስያሜው ለመቶዎቹ ዓመታት በዑስማን ቱርኮች ይገዙ የነበሩት የባልካን ባሕረ-ሥላጤ ሃገሮች ወደ ታናናሽ መንግሥታት የመከፋፈላቸውን ሂደት ገላጭ ነው። ቃሉ የተወሰነ አሉታዊ ቃና ወይም ቅላፄ አያጣውም። ከእዚያ ልምድ በመነሳት ባንዱ ሃገር የሚከሰተው አፍረክራኪ ቀውስ በዚያው ሃገር ስም ይወጣለት ገባ። ለምሳሌ የሶማሌ አፈረካከስ ክስተት "ሶማሊዜዬሽን" የሚል አገር ጠቀስ ስም ወጣለት። ከዚያም በፊት በዓረቡ ዓለም "ሊባናኒዜዩሽን" የሚባል የመፍረክረክ ደዌ ከ1975 እስከ 2008 ዓ.ም. ድረሰ ሃገሪቷን ላመሰቃቀለው የእርስ-በርስ ጦርነት የተሰጠ ስም ነው ። ከዚያም በኋላ በየተራ የተዘመተበት ቁርቁስና መፍረክረክ ሁሉ በተፈርክራኪዋ ሃገር ስም ዳቦ ይቆረስለት ገባ ። ዛሬ ባለተራ ለሆነው የየመኑ የእርስ በርስ ምስቅልቅል ገና ምን ስም እንደሚወጣለት አላውቅም። በሌላ አባባል የየመኑ ውጥንቅጥ ምን ስም ይሰጠው ነው። ምክንያቱ እያንዳንዱ መፍረክረክና መመሰቃቀል መቼም የራሱ የሆኑ ገላጭ ባሕርያት አሉትና። " የመኒዜሽንም " እንደ ማንኛውም የአእምሮ ውጤት (Intellectual Property) ለስም-አውጪ የኮፒራይት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ይሆናል።

የዓረቡ ፀደይ እንቅስቃሴ በርካታ ዓረብ ሃገራትን ባዳረሰበት ወቅት በርካታ ኢትዮጵያውያን ሁኔታዎችን በጉጉትና በቅርበት ይከታተሉ ገቡ። ሕዝባዊ መነሳስቱ የቆዩ የአካባቢ አምባገነኖችን ተራ በተራ እየኀበኘ፤ በቱኒስ፣ በሊቢያና በግብፅ መሪዎችን ያሽቀነጠረበትን ሂደት ከቅርበት ብቻ ሳይሆን እንደ አብነትም ይመለከቱት ጀመር። አልፎ ተርፎ እንደ ድሮ ከምዕራባውያኑ ወይም ፈረንጆቹ የዜና ማዕከላት ዋቢነትና ማጣቀሻነት ሳይሆን ቀጥታ ቅርበት ካላቸው ከባለቤቶቹ ምንጮች፣ ከእነ አል-ጀዚራና አል-ዓራቢያ ዓይነቱ የዜና ምንጮች መጎንጨት መለማመድ እያዘወተሩ ነበር። በ2011ዓ.ም. ሕዝባዊ መነሳሳትና እንቢተኛነት የመንን ከዳር እስከዳር አዳርሶ (የገለፍ ሃገራት ተነሳሽነት በጎደለው የመፍትሔ ሓሳብ) የ32 ዓመቱን ወታደራዊ ፈላጭ-ቆራጭ መሪ ከሥልጣን አስወገደ። ልክ

⇨

በግብፅ፣ በሶሪያና ሊቢያ በቅልበሳ ኃይሎች እንደተደረገው ሁሉ ይህ ሕዝባዊ መነሳሳትን የመቀልበሱ ሂደት በየመንም ተጀመረ። በተለያዩ በሥልጣን የሚራኮቱ ሚሊሺያ ኃይሎች አማኻኝነት። በዓረቡ ዓለም የተቀጣጠለው የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄ አገራቱን ተራ በተራ እንዳዳረሰው ሁሉ ቅልበሳውም በዚያኑ መጠን ተራ በተራ ያዳርስ ገባ ማለቱ ይቀላል። ሊቢያ፣ ሶሪያ አሁን ደግሞ የመን እየወደሙ ናቸው። በየመን የምንመለከተው ይኽ በሃይማኖታዊ ማሊሺያና ሌሎች ኃይሎች መካካል የሚካሄደው የመተራመስ ሂደት የራሱ መገለጫዎች ቢኖሩትም ቅልበሳው ይዘቱ ያው ነው።

ዛሬም ቢሆን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የመካከለኛው ምሥራቅን ምስቅልቅል ከቀይ ባሕር ባሻገር ከመከታተል አልፎ ‹ምስቅልቅሉና ትርምሱ እኛን ይመለከተን ይሆን?› ‹ምስቅልቅሉ ቀይ ባሕርን ተሸጋግሮ እኛኑ ያተረማምሰን ይሆን?› እያለ ማሳቡ የግድ ነው። የኤርትራ 60 ኪሎሚትር ጠረፍ ኢትዮጵያን ከአደጋ ተጋላጭነት ሊከላከላት ብቃት ሊኖረው አይችልምና። ወደድንም፣ጠላንም ሃገራችን በቀጠናው ተካታች ሃገር ናት።ከዚህ እውነታ ጋር መለማመድ ይኖርብናል።ከዚህ በተጨማሪ በሞቶ ሺዎች የሚገመቱ የኢትዮጵያና የኤርትራ ዜጎች እርስ-በርስ ጦርነት እያላጋት ባለችው የመን ፍዳቸውን እያዩ ናቸው። መሸሸጊያ እየጠፋ ከሸሹበት፣ መሸሸጊያ ፍለጋ ዳግም ሽሽት እንበለው!

በዓረቡ ዓለም በጥቅል፣ በዚሁ በቀጠናችን በተለይ፣ የቆዩ ቃል ኪዳኖቹ እየፈራረሱና በአዳዲስ ትስስሮች እየተተኩ ናቸው ብለናል። የእሳቱ ወላፈን እየተስፈነጠረ የቅርቡንም የሩቁንም ሊያዳርስ ነው። ከየመን ጋር የቆየ ትስስር አለን። የቅርብም የሩቅም። እስቲ በቅርቦቹ ጥምረቶች እንጀመር! የሳንዓ የትብብር መድረክ ተብሎ በ 2002 ዓ.ም. መጨረሻ ‹አካባቢያው ደህንነትና ንግድ የማሳደግ› ዓላማ አንግቦ የተቋቋመው፤ የመንን፣ ኢትዮጵያንና ሱዳንን ያጣመረው (በኋላ ላይ ጂቡቲና ሶማሊያ የተቀላቀሉት) ጥምረት የመጨረሻው ነው። ምንም እንኳን ኤርትራ ትብብሩ እሷን የማናጋት ዓላማ እንዳለው ብታምንም ድርጅቱ እምብዛም የተቋቋመበትን ዋና ዓላማዎች ግብ ማስመታቱ አጠራጣሪ ነው። ከዚያ በፊት ከሙዓመር አል -ጋዳፊ ጎን ሆኖ የጃዕፋር አል-ኑሜሪን ሱዳን ለመከበብ - የደርግ መንግሥት የሌላ ጥምረት አባል ሆኖ ነበር። ሶማሊያ የ1977ቱን ወረራ ከማፋፋሟ ቀደም ብሎ የኩባ መሪ ፊደል ካስትሮ ሶማሊያን፣ ኢትዮጵያንና የዚያን ጊዜው ደቡብ የመንን ያጣመረ ኮንፌደሬሽን በመፍትሔ ሓሳብነት አቅርበው እንደነበር ይታወሳል። ያ ጥምረት ባይተገበርም ቅሉ፤ ደርግ የዓረቡን ዓለም በሁለት ከፍሎ - ተራማጅና አድሓሪ በሚል ፈርጆ ስለነበር ደቡብ የመን ከሃገራችን ጎን ተሰልፋ ተዋግታልናለች። እንዲያውም በመጀመሪያ በዓሰብ በኩል የደረሱት የዚያን ጊዜ የደቡብ የመንና የኩባ ወታደሮች ናቸው። በ1986ዓ.ም. ላይ በደቡብ የመን ሶሻሊስት ፓርቲ አመራር " ጓዶች" መካከል በተጧጧፈው ደም አፋሳሽ ፍጥጫ የመንግሥቱ ኃይለማሪያም መንግሥት የፕሬዝዳንት ዓሊ ናስርን ወገን ለመደገፍ በባሕር ከዓሰብ ሠራዊት ልኮ ነበር። ሠራዊቱ መዳረሻው ሳይደረስ በሩሲያው አየር ድብደባ አማኻኝነት ፍልሚያው እልባት አገኘ እንጂ። ብዙ ያልተነገረለት የጀብደኛነት ታሪክ ነው። ምናልበት በቅርቡ ለሕትመት ይበቃል ተብሎ በሚገመተው የሸለቃ ፍስሓ ደስታ መጽሓፍ ስለዚህ የ1986ዓ.ም. ዐቢይ ዘመቻ ይነግሩን እንደሆነ መጠበቅ ነው። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ሳንዓ ድረስ ተጉዘው ከዓሊ ዓብዳል ሣሊሕ ጋር ጓድ ዓሊ ናስርን ወደ ሥልጣን የማስመለሱን ዘመቻ መርሓ ግብር የተነጋገሩት እሳቸው ነበሩና። ባልሳሳት ዘመቻው "ዘመቻ ካሌብ " ነበር የተሰኘው። የዚያ ዘመቻ አብራሃ አል-አሽረም የሆኑት ግን ሁለት የሓራሪ (አደሬ) የጦር መኮንኖች ናቸው። ዘመቻውን የመሩት ብርጋዴር ጄኔራል ዓሊ ሓጂ ሲሆኑ በጦሩ ኮሚሳርነት የዘመቱት ሚቼ ሻምበል (አምባሳደር) ፋይሳል ዩሱፍ ነበሩ።

ትናንትም ዛሬም ይህንን ጠባብ ወሽመጥ በሁለቱም አቅጣጫ መሸጋገሩ አይሞከሬ ተግባር አልነበረም። ዛሬም ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ይህቺ 18 ኪሎ ሚትር የማትሞላው ጠባብ መተላለፊያ አፍሪካና ኤሺያን ታለያያለች ብትባልም በታሪክ የተሰነዱና ያልተሰነዱ የሕዝብ ዝውውሮች ነበሩ። ገሚሱ የማስገበር ዘመቻዎች ናቸው። የነቢዩ መሓመድ (ሳ.ቢ.ይ) ተከታዮች ወደዚህ መሻገራቸው በሚገባ የተሰነደ ታሪክ ነው። ከዚያ 40 ዓመት ገደማ በፊት በአብራህ አል-ሓበሺ (አል-አሽረም-ፊተ ገጣባው) ዘማችነት ከዛሬዪቷ ሳንዓ፣ ካባን ለማውደም ወደ መካ የተደረገው ዘመቻም በቁርአንም ሳይቀር በ"ዝሆን ባለቤቶች" አንቀጽ ተወስቷል። አብራሃ አል-ሓበሺ የካሌብ ባሕር ተሻጋሪ ጦር አዝማች ነበሩ። ምንም እንኳን በተለያዩ ምክንያቶች የቀይ ባሕር-ሻገር ትስስር የማይዋጥላቸው ወገኖች ካፍሪካ ጠርዝ ተደረጉ የተባሉትን ሽግግሮችን እምብዛም አይቃወሙም። በሚገባ ካልተሰነዱት ውስጥ የማኣረብ ግድብ (ሰድ ማኣረብ (سدمأرب ተደርምሶ አካባቢው በውሃ ሙላት ተጥለቀለቀ በሚባልለት ዘመን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ አፍሪካዊ ጠረፍ የተሻገረበት አብነት አለ። በነገራችን ላይ 400 ዓመት እስልምና በመካ ከመሰበኩ በፊት የመን ላይ የነበሩት ሕዝቦች በየአቅጣጫ ተበትነዋል፤ በወሃ ሙላቱ ምክንያት። የመኖቹ እስከ ሰሜን አፍሪካ፣ ሶርያና ኢራቅ ድረስ ፈልሰው የተሰደዱት በዚያን ወቅት ነው ተብሎ ይነገራል። በዓለም እንደ የመኖች የተበተነ ሕዝብ የለም ቢባል እምብዛም ማጋነን የለበትም። በኢንዶነዢያና በቹካን ከሰፈሩ ቆየትየት ብለዋል። በተመሳሰዩ ምክንያት ቀይ ባሕርን ተሻግረው ወደ ዛሬይቱ ኤርትራና ኢትዮጵያ መፍለሳቸውም ብዙ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። የሓበሻና አጋዚያን ፍልሰትም ከዚህ ጋር በምን መልኩ እንደሚያያዝ ግልፅ አይደለም፣ እስካሁን። ወደ ኋሊ....ት.....ወደ ኋሊት...የሉሲ የልጅ ልጆችም በዚሁ በቀይ ባሕር መስመር በኩል ይሆናል የተሻገሩትና በአራቱ የዓለም ማዕዘናት "የሰው ልጅ" ተብለው "በዝተው የተባዙት"። ያን ጊዜ ቀይ ባሕር ሳይጎረጉድ መሬቱ የብስ-ገጠም ነበር ካልተባለ በስተቀር። አንዷት ያነበብኳትና ባዲሱ መጽሓፌ (አሰባሳቢ ማንነት ባንድ ሃገር ልጅነት ገጽ16) ያሰፈርኳትን ታሪክ ብጤ ልመርቅላችሁ መሰለኝ። ከዛሬዋ የሞሮኮ ጣንጂር ከተማ ተነስቶ አህጉራትን ያካለለው ኢብን-ባጡጣ (1304-1369) "አል-ሪህላ" በተባለው የጉዞ ዘገባው ቀይ ባሕርን "ባሕር አል-ሓበሽ" ተብሎ ሲጠራ እንደነበረ የሚገልጸውን ታሪክ ማለቴ ነው። ዛሬም ባሕሩ እንደ ገና "ባሕር አል-ሓበሽ" ይባል ብለን ብንከራከር አያምርብንም ትላላችሁ?! በሓኒሽ ደሴት ባለቤትነት ከመወዛገብ በባሕሩ ስያሜ ላይ መነታርኩ ሳይሻል አይቀርም። ልክ ዓረቦቹና ፋሪሶች በመሃላቸው ባለው ወሽመጥ አጠራር ላይ እሰጣ-አገባ እንደሚለዋወጡት ማለት ነው። ምናልባት የኢትዮጵያና ኤርትራ መንግሥታትና ሕዝቦች አንድ የሚስማሙበት ተጨማሪ ጉዳይ ያገኙ ነበር። ሓበሻ ነን ከሚሉት ስያሜ በተጨማሪ ማለቴ ነው።

ኢራን፣ ቱርክና እስራኤል በመካከለኛ ምሥራቅ ቀጠና የሚካተቱ ነገር ግን ዓረብ ያልሆኑ ወይም በዓረቦች አፈራረጅ "ዓጀም" የሚሰኙ ናቸው ብለናል። በዚህ አፈራረጅ በዚህ ቀጠናችን ሌሎች ዓረብ ያልሆኑ ሃገራት አሉ። አይሁዳዊቷ እስራኤል ሌለኛዋ ዓረብ ያለ ሆነች "ፀጉረ

ወደ ገጽ 29 ዞሯል



## የአሻራ ቆይታ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጋር



*ከገጽ 7 የዞረ*

ይህ ነው እንግዲህ የኔ የህይወት መመሪያ ፍልስፍናዬ። ያኔ የጀመርኩት ዓላማ ነው እስከዛሬ ይዞኝ የቆየው።

**<u>አሻራ፡-</u> በህይወት ዘመንዎ በርካታ ግዙፍ ውጤት ያስመዘገቡ ስራዎችን እንደሰሩ እሙን ነው፤ ከነዛ ውስጥ ይህን በማድረጌ በጣም ረክቻለሁ! ብለው በስኬት ከሚያነሷቸው ነገሮች ለአብነት ቢገልጹልንና በአንጻሩ ደግሞ ይህን ባደረኩ ኖሮ ብለው በቁጭት የሚያስቡት ነገር ካለ ቢያካፍሉን?**

**<u>ፕ/ር፡-</u>** ሠርቻለሁ ከምላቸው ነገሮች ለኔ ጉልህ ቦታ የምሰጣቸው፤ አንደኛ በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት በመምህርነት የሰራሁት ስራ ነው። የወጣት ሴት ተማሪዎችን መንፈስ ያነቃቃሁ ይመስለኛል። የራሴ የግል ተልዕኮ አድርጌ ወስጄው ብዙ ነገር ሰርቻለሁ። ልጆቹን አዲስና ጠንካራ መንፈስ የዘራሁባቸው ይመስለኛል። ከዚያ በኋላ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባደረኩት ሁሉ በጣም ደስተኛ ነኝ። የዛን ጊዜ ተማሪዎቹም እውቀት የሚፈልጉ ብሩህ አይምሮ የነበራቸው ስለነበሩ ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ ነበር። በኋላ ከራሳቸው በላይ ሆነው ሲባዝኑ የማይሆን ነገር መሆኑ እንጂ ሃገሪቷ ያፈራቻቸው እንዴት እንዴት ያሉ ተማሪዎች ነበሩ። አሁንም ድረስ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ አሉ። እኔም በምችለው ነገር በዚህ ውስጥ መሳተፌ በጣም የሚያስደስተኝ ነገር ነው።

ሌላው የተሳተፍኩበት ደርግ ስልጣን እንደያዘ ባቋቋመው የመርማሪ ኮሚሲዮን ውስጥ ነው። በመርማሪ ኮሚሲዮኑ ውስጥ ለሁለት አመት ያህል ነው የሰራሁት። 15 ሰዎች ያህል ነበርን። በእውነቱ በኮሚሲዮኑ ውስጥ ከአንድ ሶስት ወይም አራቱ በስተቀር እንዴት ያሉ የሃገሪቷ እንቁ የሆኑ ሰዎች ነበሩ። ግሩም ህሊና ያላቸው፤ ለሰው የሚጨነቁ፤ ለሃገር የሚያስቡ፤ ከሲቪሉም ከወታደሩም ክፍል የተውጣጡ ነበሩ። በኋላም ከጥቂት ሰዎች በስተቀር ደርግ መርማሪ ኮሚሲዮኑን የግድያው መሳሪያ ሊያደርግ ሲፈልግ አሻፈረኝ ብለን ተውነው።

**<u>አሻራ፡-</u>ታሪክ ነውና በስም የሚያስታውሷቸውን ቢጠቅሱልን፡?**

**<u>ፕ/ር፡-</u>**ከማስታውሳቸው መካከል ኮማንደር ለማ ጉተማ (በኋላ እኔ አልሰራም ስል እኔን ተክቶ የኮሚሲዮኑ ሊቀመንበር ሆኗል)፤ በረከተ አብ ወልደስላሴ የሚባል ዋና መሰሪ ነበር (በኋላ ሻቢያ ሊገባ ሞክሮ ሆይ ሆይ ሲል የነበረ እዛም ስልጣን ሳያገኝ ቀርቶ አሁን ወጥቷል መሰለኝ)፤ ባሮ ቱምሳ ነበር። ደሃድ የሚባል የጅማ ልጅም ነበር። እነኚህ ከደርግ ጋር መጠጋት ይፈልጉ የነበሩ ናቸው። አቶ ጌታቸው(ከኦዲት መስሪያ ቤት)፤ ሻለቃ አለማየሁ የሚባል(በኋላ ጀኔራል ሆኗል መሰለኝ፤ ከክብር ዘበኛ እንዴት ያለ ለሰው የሚጨነቅ ጥሩ ሰው።) እነኚህን አስታውሳለሁ። በመርማሪ ኮሚሲዮኑ ውስጥ እነኚህን ከመሰሉ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን ጋር በመስራቴ ደስተኛ ነኝ።

ባደረኩ ኖሮ ብለህ በቁጭት የምታስበው ስላልከው፡- ይሄ መቼም አስቸጋሪ ነገር ነው። ቢሆን ኖሮ ብሎ ነገር የቂል አስተሳሰብ ነው። ቢሆንም ግን እንዲያው አንዳንዴ በአይምሮዬ የምትመጣብኝ ቁጭትም ባልላት ጥያቄ ቢጤ አለች። መንግስቱ ኃይለማሪያም መርማሪ ኮሚሲዮኑን ወደሱ ለማስጠጋት ፈልጎ ኑና አብረን እንስራ ብሎ ጠይቆኝ ነበር። እኔ ከናንተ ጋር በምንም መንገድ ልሰራ አልችልም! እኛ የማልንበት ሌላ ጉዳይ ነው። እናንተ ደግሞ አልማላችሁም። ስለዚህ እኔ በማልኩበት ለመጽናት ነው የምሻው ብዬ ገለጽኩለት። ቆይቶ ይህንኑ ጥያቄ ደግሞ አነሳብኝ፤ እኔም መልሼ፡- አይ የራሴን ሃሳብ ነግሬሃለሁ። ኮሚሲዮኑ አፈሻል መልስ እንዲሰጥህ ከፈለክ ሃሳቡን አነሳላቸውና መልሳቸውን አሳውቅሃለሁ አልኩት። እሱም ጥሩ እንደሱ አድርግና አሳውቀኝ አለኝ። ሰበሰብኳቸውና ሰውየው አብረን እንስራ እያለ ነው ሃሳባችሁ ምንድነው? ብዬ ጠየቅኩ። ቀደም ብዬ ስማቸውን ከገለጽኳቸው የኮሚሲዮኑ አባላት ውስጥ ባሮ ቱምሳና በረከት ከደርግ ተጠግቶ መስራት ፈልገው ነበር። ሌሎቹ ግን በፍጹም አብረን አንሰራም አሉ። ይህንኑ ለመንግስቱ ነገርኩና በዚሁ አበቃ።

ከዚያ በኋላ የህዝብ ድርጅት ብሎ እነ መኢሶንን ሰበሰበና የሆነው ሁሉ ሆነ። በኋላ ይህን ነገር ቆይቼ ሳስበው ምናልባት እኛ እዛ ውስጥ ብንገባ ጥሩ ምክር ሰጥተን የሆነው ሁሉ እንዳይሆን ፤ ተከትሎ የመጣው የቁልቁለት መንገድ ሁሉ እንዲቀር ማድረግ እንችል ነበር? ወይስ እኛንም ይበላን ነበር? አላውቅም። እንዳልኩህ ቢሆን ኖሮ....ብሎ ነገር የጅል ሃሳብ ነው። አንዳንዴ ግን ያኔ እሺ ብንል ኖሮ ...? አይነት ሃሳብ ብቅ ይልብኛል።

**<u>አሻራ፡-</u>እስኪ ሶስቱን መንግስታት በንፅፅር ይመልከቱልንና እያይዘው አሁን ወደምንገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ይውሰዱን?**

**<u>ፕ/ር፡-</u>** የኃይለሥላሴ መንግስት ተቋርጦ እንደገና የቀጠለ መንግስት ነው። የድሮውን ባህላዊ አገዛዝ ጣሊያን ለ5 ዓመታት በቆየበት ጊዜ አቋርጦታል። ስለዚህ ተቋረጦ ከቀጠለበት ልጀምር። አጼ ኃይለሥላሴ ከስደት ሲመለሱ ባንዳና ስደተኛውን አቅፈው አርበኛውን መደቆሳቸውን ቀደም ሲል የታሪካችንን መክሸፍ በጠቀስኩበት ላይ የገለጽኩ ይመስለኛል።

አጼ ኃይለሥላሴ ለሃገሩ ነጻነት በዱር በገደል የተዋደቀን አርበኛ ገድለው ባንዳውንና ስደተኛውን መሾምና መሸለማቸው፤ የመንግስታቸው አስከፊ ገጽታ ነው። ሌላው ገጽታቸው አውሮፓ በቆዩበት አምስት አመት ስለትምህርት ጥቅም በደንብ ተገንዝበው በመምጣታቸው ሁላችንንም የድሃ ልጆች ሰብስበው አዳሪ ትምህርት ቤት ከተው አስተማሩን። በትምህርት በኩል ከፍተኛ እድገትና ውጤት አስመዝግበዋል።

ደስ ያለኝ ደግሞ ጄኔቭ በሊግ ኦፍ ኔሽንስ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ስም ማትረፋቸው ነው። ትልቅም የአለም ፖለቲከኛ ሆኑ። ይህ ዝናቸው ደግሞ ኢትዮጵያን በጣም ጠቅሟል። ብዙ እርዳታዎችን አገኘች። ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ወደፊት ገሰገሰች። በጊዜው በአፍሪካ ሌላም መሪ አልነበር ፤እሳቸው ብቻ ነበሩ። ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ ነበር።

በኋላም ትምህርቱም እየተስፋፋ ሄደ። ወደ አውሮፓና አሜሪካ እየተላኩ ብዙዎች ተምረው መጡ። በህብረተሰቡ ውስጥም የአስተሳሰብ ለውጥ እያደገ መጣ። እሳቸው ግን መለወጥ አቃታቸው። የሃገራችን ችግር የጀመረው እዚህ ጋ ይመስለኛል። ራሳቸው ያስፋፉት ትምህርትና እውቀት ያመጣውን የአስተሳሰብ እድገትና ለውጥ ራሳቸው መቀበል አቃታቸው። የትምህርት መስፋፋትና የዕውቀት ዕድገት ያመጣውን ያስተሳሰብ ለውጥ ተቀብለው መንግስታቸውን ለህገ መንግስት ወደሚገዛ የዘውድ ስርዓት (**Constitutional monarchy)** ቢለውጡትና ቀስ በቀስም ህዝብ የፈለገውን

እንዲመርጥ መንገዱን ቢያመቻቹ አሁን የምንገኝበት ችግር ውስጥ ባልገባን ነበር። እሳቸው ግን ሙጭጭ ብለው ሁሉን ጨምድደው መቆየትን መረጡ። በኋላም በመንግስቱ ነዋይ ተሞክሮ ያልተሳካው ለውጥ ከ13 ዓመት በኋላ ፈንድቶ እሳቸውንም አገዛዛቸውንም ጠራረጋቸው።

ወደ ደርግ ስንመጣ፤ ደርግ የማያውቀውን ነገር አምናለሁ ብሎ የተነሳ፣ የሚሄድበትን የማያውቅ ነበር። በሃይማኖቱ ጽናት የሚታወቀውን ህዝብ እግዚአብሄር የለም ብሎ ለመግዛት መነሳቱ ብቻ የደርግን ምንነት የሚያሳይ ይመስለኛል። ለሰፊው ህዝብ ቆሚያለሁ እያለ ሰፊውን ህዝብ እየረገጠ፤ አንድ ሰው ብቻ ስልጣን ነክሶ የፈለገውን ሲያደርግ ቆየ። ከ17 አመት በኋላ ፍጻሜው ሆነና ሻቢያና ወያኔ አገሪቷን ለሁለት ተካፍለው ተቆጣጠሩ። ኢትዮጵያን የያዙት ወያኔዎች ህሊና የሌለበት፤ ህግ የሌለበት፤ እግዚአብሄር የሌለበት፤ ባህል የሌለበት፤ አገዛዝ አቋቁመው እስካሁንም ህዝቡን እያስለቀሱ ይገኛሉ።

የነኚህ (ወያኔዎች) ከየትኛውም አገዛዝ የሚነጻጸር አይደለም። ፍጹም የተበላሹ፤ ወራዳ የሆኑ፤ ከእውቀት ጋር የተጣሉ፤ እውቀት የማይወዱ፤ ኢትዮጵያን ቁልቁል ይዘው ለመውረድ የተነሱ ናቸው። በአጭሩ ከአጼ ኃይለስላሴ መንግስት አሁን እስከምንገኝበት ድረስ የተጓዝነው የቁልቁለት መንገድ ይሄ ይመስለኛል።

***<u>አሻራ፡-</u> ስለ ቀጣዩስ ዕጣ ፈንታችን ምን ይታይዎታል? ከአዘቅቱ የሚያወጣን መንገድስ የቱ ነው ይላሉ?***

<u>ፕ/ር፡-</u> በኢንተርኔት ላይ የተለቀቀ አንድ የአዲስ አበባን ትራፊክ ትርምስምስ የሚያሳይ ቪዲዮ ክሊፕ አይተሃል? አራትና አምስት መንገዶች በሚገናኙበት ደሴት (intersection) ውስጥ የሚገቡ መኪኖችን በአግባቡ የሚያስተናብር ስርዓት ስለሌለ አንዱ የአንዱን መንገድ ሲዘጋ ሌላውም የሌላውን ሲዘጋ እንዲሁ ሲተረማመስ ነው የሚታየው። አሁንም በወያኔ ባለስልጣኖች መሃል የሚታየው ይኸው ነው። አንዱ ከመሃላቸው አይሎ ወጥቶ ሊመራ አልቻለም። ሁሉም በፈቀደው መንገድ እየተጓዘ ነው። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ሥርዓት አልበኝነት አይቀሬ መሆኑን ነው። እነሱ ገንዘብም መሳሪያም ስለያዙ ላይጎዱ ይችላሉ። ቀሪው ህዝብ ግን...

ከዚህ አዘቅት የሚያወጣን መንገድ ላልከው፤ የህብረተሰቡን 70% ያህል የሚሸፍኑት የኦሮሞኛና አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ክፍሎች አደጋው ታይቷቸው አንድ አይነት ስምምነት ላይ መድረስ ከቻሉ መድህን ማምጣት አይከብዳቸውም የሚል እምነት አለኝ።ነገር ግን አማርኛ ተናጋሪው የተከፋፈለ፤ ኦሮሞኛ ተናጋሪው የተከፋፈለ፤ ሁለቱ ደግሞ እርስ በርስ የሚቆራቆሱ ከሆነ የከፋ ነገር እንደሚመጣ ጥርጥር የለኝም። እንዴት አድርገን እንደምንወጣው አላውቅም። ባጠቃላይ ግን የሃገሪቷ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በነኚህ የሃገሪቱን ህዝብ ቁጥር 70% ያህል በሚሸፍኑ ክፍሎች እንቅስቃሴ የሚወሰን ይመስለኛል።

<u>አሻራ፡-</u>ከረዥም አመታት በፊት የሱማሌን መበታተን ተንብየው ጽፈው ነበር። በጊዜው ይህንኑ ትንበያዎን የተቃወመ አንድ ሱማሌያዊ ፕሮፌሰር "መስፍን እኛን አያውቀንም!" የሚል የተቃውሞ ጽሁፍ ጽፎ እንደነበርና በኋላም የሱማሌ መበታተን ዕውን ሲሆን "መስፍን ከኛ በላይ እኛን ያውቀናል" በሚል ይቅርታ የጠየቀበትን ጽሁፍ እንደጻፈ ሰምቻለሁ። እውነት ነው?

<u>ፕ/ር፡-</u> እውነት ነው። ሱማሌ ኢትዮጵያን የወረረች ጊዜ ነው። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ስሜት ረዥም እድሜ ያለው በመሆኑ በቀላሉ ሊጠፋና ሊዳፈን የሚችል አይደለም። የኢትዮጵያን ብሄራዊ ስሜት በማንቋሸሽ የሱማሌን ብሄራዊ ስሜት መገንባት አይቻልም። ይህ የደረጀው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ስሜት አንድ ቀን ሲነሳ ለወጣቱ የሱማሌ ብሄራዊ ስሜት አደጋ ይዞ መምጣቱ አይቀርም። ያኔ ሱማሌን የመበታተን አደጋ ይጠብቃታል ብዬ ነበር የጻፍኩት።

ይህ ሱማሌያዊ ፕሮፌሰር ወዳጄ (አሁንም በአሜሪካ አንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ያስተምራል፡) ሃሳቤን ተቃውሞ ጽፎ ነበር። በኋላም እንዳልኩት ሱማሌ ስትበታተን " ይቅርታ ለፕ/ር መስፍን" ብሎ ጽፏል። ይኸው ነው ታሪኩ።


***<u>አሻራ፡-</u> አዲስ መንገድ ላይ ያለ መጽሃፍም እንዳለዎት ሰምተናልና ይዘቱን በጥቂቱ ሊነግሩን ይችላሉ?***

<u>ፕ/ር፡-</u> አንድ መጽሃፍ በቅርቡ ለንባብ አበቃለሁ። ርዕሱን "አዳፍኔ" ብየዋለሁ። "መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" የሚለው መጽሃፌ ተከታይ ነው ማለት ይቻላል። መክሸፍ የሚለው ቃል አልገባ ያላቸው አዳፍኔ ይገባቸው እንደሁ ብዬ ነው(ሳቅ)። ይዘቱም ሁሉንም አዳፍኖ የሚጓዘውን የአምባገነንነት አካሄድን አመላካች ነው። ጭቆናን፤ ኋላ ቀርነትን፤ የንዋይና የስልጣን ፍቅርን፤ ክህደትን .... የሚያሳይ ነው።

***<u>አሻራ፡-</u>ኢ.ሠ.መ.ጉን አቋቁመው በሰሩበት ግዚያት ውስጥ ካጋለጧቸው የግፍ ተግባራት መካከል ለርስዎም ሆነ ለኢሰመጉ አባላት ፈታኝና ውጤቱም ትልቅ እርካታ የሰጣችሁን ለአብነት ያህል ቢገልጹልን።***

<u>ፕ/ር፡-</u> ብዙ ሰዎች ግፍን ለማበላለጥ ይሻሉ፤ አንድ ጊዜ ፕሬዚደንት ካርተር በሂልተን ሰብስቦን ሲደሰኩር የደርግ አገዛዝ በጣም ግፈኛ ነበር ሰዎችን ይጨፈጭፍ ነበር፤ አሁን ደህና ሆኖአል ብሎ ሲናገር፣ ከምን ተነሥተህ ነው ይህንን ለማለት የምትችለው? በደርግ ዘመን ልጅዋ የሞተባትን እናት ብታነጋግር እንደደርግ ግፈኛ አገዛዝ የለም ትልሃለች፤ በወያኔ ዘመን ልጅዋ የተገደለባትም እንደወያኔ አገዛዝ ግፈኛ የለም ትልሃለች፤ እነዚህን እናቶች እንዴት ብለህ ልትሞግታቸው ትችላለህ? ሌላው ነገር ደርግ በዓመት 1000 ሰዎችን ቢገድልና ወያኔ ደግሞ በዓመት 100 ሰዎችን ይገድላል ብለህ መደመደሚያህ ወያኔ አሥር ጊዜ ይሻላል ማለት ሊሆን አይችልም፤ እያንዳንዱ ሕይወት ለብቻው እንጂ በመደመርና በመቀነስ ውስጥ የሚገባ አይደለም፤ አልሁትና በአደባባይ ስሕተቱን አረመ፡፡

በሰብአዊ መብት ጉዳይ ግፍን ማበላለጥ ያስቸግራል፤ ግፍን ሰጪው ምናልባት ለግፉ ደረጃ ይሰጠው ይሆናል፤ በግፍ ተቀባዩ በኩል ሆነን ስናየው ግን እያንዳንዱ ግፍ ተቀባይ የግሉ የሆነና ከሌላ ግፍ ተቀባይ የሚለየው ነገር አለው፤ ለምሳሌ ሁለት እናቶች ባንድ ቦታ በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ልጆቻቸውን አጥተዋል እንበል፤ አንድዋ እናት ሌሎች ልጆች ይኖርዋታል፤ አንደኛዋ እናት ደግሞ አንድ ልጅ ብቻ አላት፤ ከዚያም በላይ የአንድ ልጅዋ ጥገኛ የነበረችና ልጅዋ የስዋ ጥገኛ የነበረ የተለየ የሐዘን ሁኔታን ሊፈጥሩ ይችላሉ፤ ስለዚህ በግፍ ተቀባዩ በኩል ሆነን ስናየው ማናቸውም ግፍ ፈታኝ ነው፤ ማናቸውም ማጋለጥና ውጤት ማስገኘት እርካታን የሚሰጥ ነው ለማለት ይቻላል፤ ለምሳሌ መጀመሪያው ላይ የመውጫ ቪዛ ለማግኘት የሚጠየቀውን አጉል ነገር ሁሉ ማስቀረት ለብዙ ሰዎች በሩን ከፍቶአል፤ በሌላ በኩል በዚያኑ ጊዜ ሰው እየገደሉ በየመንገዱ ላይ መጣል እንዲቀር ተደርጓል፤ የተዘረፈ ንብረታቸው የተመለሰላቸው ሰዎች ነበሩ፤ አካልን ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚለውን ሕግ



እያስተማርን (habeas corpus) ብዙ ሰዎች ከእስር እንዲፈቱ ተደርገዋል፤ በኋላም የኤርትራ ተወላጆችን ከአገር ማስወጣት ሲጀመር ኢሰመጉ ጥቂት ሰዎችን፣ ማለት ለአቤቱታ የመጡትን ማስወጣቱ ሕጋዊ እንዳልሆነ እያስረዳን ለማስቀረት ተችሏል፤ . . .

በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶችን ጉዳይ መከታተልና ውጤት ማስገኘት ለኢሰመጉ ሁሌም ፈታኝ ነበረ፤ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ባለሥልጣኖች ከሕግ ይልቅ በጡንቻ የሚያምኑ ስለሆኑ ነበር፤ አሁን የባሰ ነው፤ ኢሰመጉ ትግሉ ተሳክቶለት አንድ ሰውም ሆነ ብዙ ሰዎች ሕጋዊ ዳኝነትን አግኝተው ማየት በጣም ያስደስት ነበር።

**<u>አሻራ፡-</u>በመጨረሻም፡ ለወጣቱ ትውልድ ምን ይመክራሉ? ለጎልማሳውስ ?**

**ፕ/ር፡-** ምክር የተባለውን ልተወው፤ ያለንበት ዘመን ምክር የማይጠየቅበት፣ ሁሉም አዋቂና የፈለገውን የሚያደርግበት ዘመን ነው።

የዛሬው ወጣት ብዙ ችግሮች አሉበት፤ ዋናውና የመጀመሪያው የትምህርት ጥራት እየወደቀ መሄዱ የወጣቱን የወደፊት ተስፋ በዚያው መጠን የሚያጨልመው ይመስለኛል፤ ይህ እንዳይሆን ወጣቶች ለራሳቸው ኑሮ የበለጠ ኃላፊነትን መውሰድና ትምህርታቸውን በንባብ ማጎልበት የሚጠቅማቸው ይመስለኛል፤ ወጣቶች በቤተሰብ ተገርተው እንዳያድጉም ስምንተኛ ክፍል የሚባል የመሀይምነት ማጠናከሪያ አገሩን ሰላፈነው ወላጆች በስምንተኛ ክፍል ስላላለፉ አላዋቂዎች ተብለው ልጆቻቸውን ለመግራት አይችሉም፤ አገዛዙም አላዋቂ ታዛዥ በገፍ ስለሚፈልግ የሚገራው ለሎሌነት እንጂ ለነጻ የዜግነት እንቅስቃሴ አይደለም፤ ስለዚህ ወጣቶች ዘመናቸው የሚነባቸውን ሁሉ በራሳቸው ኃይልና በግዳቸው ተገንዝበው ዳገቱን ለመውጣት መምረጡ ይበጃቸዋል፤ በግዳቸው የምለው ከቁልቁለቱ ኃይል የሚያመልጡበት ከውስጣቸው የሚወጣውን የመንፈስ አሸናፊነት ለማግለጽ ነው።

አገር የሚለማውና የሚበለጽገው በሰዎቹ ነው፤ አገር የሚታፈረውና የሚከበረው በሰዎቹ ነው፤ የዛሬ ወጣቶች ለዚህ ዓይነት አገር የታደሉ አይመስለኝም፤ በሁሉም ረገድ የኢትዮጵያን መልክ መለወጥና የሕጋዊ ሥርዓት፣ የመሥራት ክብር፣ የማደግና የመሻሻል ዕድል የሚታይባት አገር እንድትሆን ትጋትንና መተባበርን ተቀዳሚ ተግባራቸው ቢያደርጉ ለተደላደለ ኑሮ ራሳቸውን ለማዘጋጀት የሚችሉ ይመስለኛል፤ በአንጻሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሽሽትን ወይም መሰደድን እንደመፍትሔ እያደረጉ በየባሕሩ መስጠምና በያገሩ ስቃይን መቀበል የሚያዋጣ አይመስለኝም።

አንድ ነገር በግል እንዲረዱ የሚያሻው የትም ቢሄዱ በማናቸውም መስክ ስኬታማ ውጤትን ማስመዝገብ የሚቻለው በመንፈሰ-ጠንካራነትና በማያቋርጥ ልፋትና ጥረት መሆኑን ነው፤ የተፈጠሩበትን መብት ጥሎ ሌላ ቦታ ሌላ መብት ለመመሥረት እጥፍ ልፋትን ይጠይቃል፤ የኢትዮጵያ ወጣቶች በሜዲቴራንያንና በቀይ ባሕር፣ በየበረሃውና በየእስር ቤቱ የሚቀበሉትን አበሳ በቆራጥነትና በመተባበር መንፈስ ተነሳሥተው አገራቸው እንድትመቻቸው ለማድረግ ወደሚያስችል ዓላማ ቢለውጡት የተሻለ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

◇ ◇ ◇





# ቆም በል!

## ህዝብ ከሚያልቅ ህዝብ ቢያልቅ ይሻላል!?

ደረጀ ደስታ (ጋዜጠኛ)

ቢጻፍ፣ ያለ ዓላማ ቢጻፍ፣ ቃላት ቢዘንቡ፣ ሀሳብ እንደ አሸን ቢፈላ፣ ፍልስፍናው ቢተረተር፣ እውቀት ቢንቆረቆር፣ የግርዶሽ መጋረጃ ተገልጦ ብርሃን ከጨለማው ተፈልቅቆ ቢብለቀለቅ ምን ነበረበት?

ግን ምን ያደርጋል፣ ነገር ሁሉ ጨለማን የመግፈፍ ትግል ብቻ ሆኖ ቀረ። ህይወት ትግል፣ የአገር ጉዳይ ትግል፣ ስደት ትግል፣ ሬዲዮ ቢያደምጡ፣ ጋዜጣ ቢገልጡ ፣ ኮምፒተር ላይ ቢወጡ፣ ቲቪ ላይ ቢያፈጡ፣ እዚህም እዚያም እኛም ቤት ...ትግል! እልቂት! ፍጅት!....

አንተ ግን በግልህ የድርሻህን ምን ታደርጋለህ? ማንን ትታገላለህ? ማንን ትወነጅላለህ? ለትግልህ ሥጋ አበጅተህ ሰዉን አንድ ባንድ ነጥለህ ዒላማህ አድርገህ ካልሄድክ ማንን ትተህ፣ ማንን ወግተህ፣ ማንን ድል ትነሳለህ? የምትከሰው፣ የምትወቅሰው ማንን ነው? "ይህ ሰው ባይኖር ይህ ነገር አይኖርም ነበር!" ብለህ ሰበብ ካላገኘህ፣ ወደ የትም በሚተኮስ ጥይት መትህ የምትጥለው ባይጠፋም፣ ልታጠፋው የፈለግከው ነገር ግን አይጠፋም።

ጠላቴን ነጥዬ አውቄዋለሁ እሱኑ ሌት ተቀን ታግዬ አጠፋዋለሁ ብትል እንኳ አይሆንልህም። ቢሆንልህም ምልክቱን እንጂ ነገርየውን፣ ፍሬውን እንጂ ብቅሉን፣ ጠብታውን እንጂ ምንጩን አታገኘውም። ነገርን ከሥሩ ካላገኘህ፣ ጠላትህን ከሥር ከመሠረቱ ካልደረስክበት ምንም የሚሆንልህ ነገር አይደለም፡፡ ጠላት ጠላት ጠላት.....!

***ማን ይሆን ጠላትህ?***

እግዜር ዓለምና አገርን ከጠላት ጋር ሰጥቶናል። እኛም በአገራችን ወንድማማችነትና ጠላትነትን እያፈራረቅን በመተቃቀፍና በመተናነቅ ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያ ውስጥ እንኖራለን። በስጋት እያዘገምን ነው። ሳናውቀው አንዳችን የሌላኛችን የስጋት ምንጭ ሆነናል። ከስጋት የምንላቀቀው የሚያሰጋንን ድል ነስተን ተሸናንፈን እፎይ ስንል መሆኑም ገብቶናል። ስለዚህ ለእፎይታው መታገል አለብን። ትግላችንም እንደየአሰላለፋችን ለማሸነፍ ነው።

አሰላለፋችን ግን እዚህም እዚያም ሆኗል። በሃይማኖታችን አንደኛው ሰልፍ ላይ ነን። በብሄር ሌላኛው ዘንድ ነን። በፖለቲካ ደግሞ ሰልፋችን ከሌላ ነው። ስለዚህ እዚህጋ እምንቧደንበት እዚያጋ እምንለያይበት ሆኗል። በዚህ ተወዳጅተን በዚህኛው ተጠላልተን..."ከጠላቶቻችን" እንተጋገዳለን። የጠላት መምጫው ግን አይታወቅም። ጠላት ከጉያ ከብብት ፈልቆ የሚያድርበት አጋጣሚ ሞልቷል። ጠላት ብዙ ነው። የዚህ ሁሉ የጠላት የባላንጣ ደረጃ ይለያያል። ደረጃው ተለይቶ አንደኛ ደረጃ ጠላት፣ ሁለተኛ ደረጃ ጠላት ተብሎ ቀመር( ስታንዳርድ) ቢወጣለት ደግ ነበር። እግዜር በፀጉርህ ልክ ጠላት ሰጥቶህ ከሆነ ግን ፣ ፀጉር ተነቅሎ ጠላት ተገድሎ አያልቅምና "ቆም በል!"፣ የሚል መጽሐፍ ወደፊት ይወጣ ይሆናል።

የዚህኛው ሃይማኖት ተከታይ ከሆንክ የዚያኛው እምነት ተከታዮች የሙብት ጥያቄ ያስጠላሃል። የዚህኛው ብሔረሰብ አባል ከሆንክ የዚያኛው ብሔረሰብ ጥያቄና ንጭንጭ እንልቅፍ ይነሳሃል። የዚህኛው አገር ሰው ከሆንክ የዚያኛው አገር ደባና ጠላትነት ወኔህን ይፈታተንሃል። ጥቁር ከሆንክ የነጩ፣ ነጭ ከሆንክ የጥቁሩ ነገር ያበግንሃል። ይሄ ሁሉ ሄዶ ሄዶ ምን ሊሆን ነው ያስብልሃል.... ጠላቶችህ ግን በየጊዜው እንደ ቼዝ ጨዋታ ባልተጠበቀ አቅጣጫና ሰዓት እየመጡ "ቼክ!" ይሉሃል!

አሁን አሁንማ ጠላት አይኑረኝ ብትል እንኳ አትችልም። አንዱ ድንገት ብድግ አድርጎህ ጠላቴ ነህ ይልሃል፡፡ ያልኖርክበትን ታሪክ ጠቅሶ፣ ዘርህን ነቅሶ፣ ያሻውን ንጉሥ ወቅሶ ካልተበቀልኩህ እኔን አያድርገኝ ይልሃል። ወይም አንተን የሚመስል፣ አንተን የሚወክል ሰው በስምህ ተገድሎ ደሙ ከባህር ሲደፋ ትመለከታለህ። ቁጣህን ትገልጽ በቀልም ያምርህ ይሆናል። ግን ማንን ትቆጣለህ? ማንን ትበቀላለህ? ጠላት ይኖርሃል ዒላማ ግን የለህም። እግዚኦ! ያንት ያለህ! ብለህ ዝም ነው። ዝምታህ ግን ምን ቀብሮብህ እንደሚሄድ አታውቅም። አንድ ቀን ሲበዛ ዝምብሎ መፈንዳት ያምርሃል። ያበጠ ይፈንዳ ትላለህ። ፍንዳታውን ግን በሌሎች አይተኸዋልና ውጤትና መዘዙ ያሰጋሃል። ካልደፈረሰ አይጠራም ይሁን ምን አባቱ ማለትም ያምርሃል። ግን ልቦናህ ገና ድሮ ነግሮሃል - ነገረ ዓለሙ ደፍርሷል። አብሮ ያኗኗረህ እምነትህ፣ ብሄር ብሔረሰብነትህ፣ ዓለም- አፍሪካ- ኢትዮጵያዊነትህ ሁሉም ደፍርሷል። ስለዚህ ችግሩ አለመደፍረሱ አይደለም የደፈረሰው አለመጥራቱ ነው ብለህ ቆም ትላለህ!

ስለሆነም አንተም ጠላት ነህ - ጠላትም አለብህ። ወዳጄ ሆይ በጠላት ተንበሽብሸሃል። ያደለውና የተንቀባረረው የአገርህ ሰውማ በማንቼስተር ቸልሲና አርሴናል ቲፎዞነት ተጠላልቶ ይደባደባል እየተባለ ነው። እሱ እንኳ የወዳጅነት ጠላትነት ይሆናል ብለህ ታልፈዋለህ። ድብድቧ ግን ምን ያባውን ምን አውጥቶ እንደሁ ምን ታውቃለህ? ብቻ ጥጋብ ነው ብለህ እንዳታልፈው ድህነትም ጠላት ሆኗል። ጠላት ያነሰን ይመስል ወይም ነገሮችን በጠላትነት ካልሰየምን የማንታገላቸው ይመስል አብሮን የኖረውን ድህነት እንኳ "ጠላታችን ነው" ብለን በአቶ መለስ ዜናዊ አሳውጀናል። ስለዚህ ድህነትን በልማት ልንወጋ፣ ልማትንም በግፍና አፈና ልናመጣት፣ የገዛ ራሳችን ራዕይ ጠላቶች ሆነን አርፈነዋል!

እና- ስለዚህ- ስለሆነም- በዚህ የተነሳም...ነገራችን ጨዋታ ቁምነገራችን ሁሉ የጠላት ነገር ሆኖ ቀርቷል። እኛ ተቃዋሚዎች የመንግሥት ጠላት ነን። እኛ ደጋፊዎች የተቃዋሚዎች ጠላት ነን። ተቃዋሚዎችም ለተቃዋሚዎች አንተኛም። ወያኔዉም ላይ ላዩን ነው እንጂ ውስጡ ውስጡን እንደለመደው ሊተራረድ ቀን ይጠባበቃል። እንገንጠል የሚሉት እንኳ የመገንጠላቸው ራዕይ እስኪገለጥ መቆየት ሰልችቷቸው፣ እንኳን አገር ድርጅት መሆን አቅቷቸው፣ ከወዲሁ አራትና አምስት ቦታ ተገነጣጥለው ሊያልቁ ነው። ኢትዮጵያውያን "አንድ መሆን አለብን" በሚለው አልተግባባንም። "አንድ መሆን የለብንም እንገንጣጠል" በሚለውም የተሰልፍነው እንዲሁ አልተግባባንም። ፍሬ ነገሩ ሁሉ አለመግባባት ሆኗል። አንዱ ያንዱ ጠላት ሆኗልና ሰው ከጠላቱ እንዴት ይግባባል?! ታዲያ ያ የመን ላይ፣ ያ ሊቢያ ሶርያ ላይ የምናየው፣ እኛም አገር ከመጣ...ማን ተናግሮ ማን ሊደመጥ ነው ያሰኝሃል?

በዚያ ላይ በጠላቶች መካከል ገብቶ የሚሸመግለን፣ አንተም ተው አንተም ተው የሚለን አንድ ስንኳ የለንም። ከመንግሥት ሰዎች አብሮ ሻይ የጠጣ ከዳተኛ ሆዳም ነው። ከተቃዋሚ ሰዎች አብሮ የበላ አሸባሪ ነው። ይህ ለተቃዋሚዎችም ለደጋፊዎችም ፖለቲካ አጋፋሪዎች ተመችቷል። ለባለሥልጣኖች ግን ወርቅ እድል ነው። ባለሥልጣኖች ሀሳብ በነጻነት እንዲዘዋወር አይፈቅዱም። ባልሥልጣኖች ሰው እንዲዋደድ አይወዱም። ወያኔዎች ናቸው የምንላቸው ባለሥልጣኖች የሥልጣን መሠረታቸውም ሆነ አመጣጣቸው ጠላትነት ነው። ለትግል ጽናትና ድል ያበቃቸውም ለሌላው ያላቸው የጠላትነት ልክ ነው። ከነሱ የተለየውን አምረው ይጠላሉ። ችግሩ አንተስ ትጠላቸዋለህ ወይ የሚለው ነው? ጠልተሃቸው ከሆነ ጥላቻህስ የትድረስ ይነዳሃል?

አንድ ሰሞን ዋሽንግተን ውስጥ "ወያኔ ጠላት ነው አይደለም?" የሚል ክርክር ተነስቶ

ነበር። አቶ መለስ ዜናዊ ባንድ ወቅት ወደ አንድነትና ተቃዋሚ የፖለቲካ ሰዎች ተጠግተዋል ያሏቸውን እነ አቶ ስዬንና ገብሩ አስራትን መቀሌ ላይ ባደረጉት ንግግር ሲከሱ "ወደ ጠላቶቻችን ጎራ ሄደው የተቀላቀሉ" ብለው ነበር። ስለዚህ አቶ መለስ ከራሳቸው ህዝብና ድርጅት ውጭ የሆነውን ሁሉ የሚያዩት እንደ ተቃዋሚና ተቀናቃኝ ሳይሆን እንደ "ጠላት" ነበር ማለት ነው አስብሎ ብዙዎችን አወያይቷል። ወያኔዎቹ የጠላት ነው ያሉትን አገራዊ ወታደራዊ ኃይልና ተቋም ሁሉ ማፍረሳቸው ግልጽ ነው። ስለዚህ እኛ ባዮቹ - እነሱ - መጥላት ብቻ ሳይሆን እንደጠላት አይተውናል ለማለት የሚያበቃህ በርካታ ምሳሌዎችን ልታገኝ ትችላለህ። አስተዳደራቸውንም ተመልክተህ ሰው የሚጠላውን እንጂ የሚወደወን አገርና ህዝብ እንዲህ አድርጎ ሊያስተዳድር አይችልም ብለህ ልትንጨረጨር ትችላለህ። ከዚህ ከዚህ ተነስተህ እነሱስ ይጠሉናል ፣ እኛስ እንጠላቸው ይሆን ብለህ መጠየቅ ትችላለህ።ችግሩ መጥላት መውደደህ ሳይሆን ከደረስክበት ድምዳሜ አንጻር "ምን ማድረግ ይገባኛል?" የሚለውን ነገር አጥርተህ አለማወቅህ ነው። እነሱንም በሥልጣን ላይ ለተራዘመ ጊዜ ያቆያቸው ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አለመኖሩ እንደሆነ ይሰማሃል። ጥያቄው በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ሁል ቀን የሚነሳ ቢሆንም የሚገኘው መልስ ግን እንደልዩነታችን ብዛት እጅግ የተለያየ መስሏል።

አንዳንዱ ሲናገር "በኢትዮጵያ ላይ ሥልጣኑን በኃይል ጨብጦ፣ ሰብዓዊ መብት ረግጦ፣ በርካታ ዜጎችን ለእስርና ስደት ዳርጎ፣ የኔ ወገኖች ናቸው ያላቸውን ብቻ መርጦ፣ አገርን ለመበታተን አደጋ ጋርጧታል" የሚለውን መንግሥት ከሥልጣን ለማውረድ መታገል ይኖርብናል ይላል። ከፊሉ ደግሞ "ይህን መንግሥት ለሥልጣን ያበቃውን የጎሳና የማንነት ፖለቲካ መንገድ በመጠቀም፣ ከታቻለ ተገንጥለው፣ ካልተቻለ የራሳቸውን ወገን ብቻ ባለሥልጣንና ተጠቃሚ አድርገውና አስቀድመው ለመሄድ የሚታገሉ ተቃዋሚዎችን፣ በሌላው እጃችን መታገል ይኖርብናል" የሚል ነገር ያሰማል። "በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ጭምር ሆን ተብሎ እንዲቀጣጠል የተደረገው የኃይማኖት አክራሪነት እንቅስቃሴ ሄዶ ሄዶ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ስለማናውቅ ምልክቱን ከሥር ከሥር እየተከታተልን ካልተዋጋነው ውሎ ሲያድር ቀውሱ ያስፈራናል ማተኮር ያለብን ይልቅ እሱ ላይ ነው!" የሚልም አለ። ሌላው ደግሞ ተጨማሪ ይልና - "በደቡብ አፍሪካ፣ በየመን፣ በሊቢያ፣ በሳዑዲ አረብያና በሌሎችም አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለው ፍጅትና እንግልት፣ መፍትሔ ስለሚያስፈልገው፣ እሱንም በቅርብ መከታተልና መልክ የማስያዝ ትግል ይጠብቀናል" ይላል። "ጎበዝ! ትግልን አፍጥኖ ለፍሬ በማብቃት በኩል፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች እያሳዩ ያሉት ድክመትና የተበታተነ አቅጣጫ፣ መልክ ይዞ፣ የእርስ በርስ ጠላትነታቸው ቀርቶ፣ አብይ ወደ ሆነው አገራዊ ጠላት ፊታቸውን እንዲያዞሩ ካላደረግን፣ ምንም ነገር አይሰምርልንም" የሚልም አለ። "ሁላችሁም ያላችሁት ልክ ነው፣ ዋናው ጉዳይ ግን የዚህ ሁሉ ትግል መሠረቱ፣ በኢትዮጵያ አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲፈጠር ፣ ሥልጣን ያለውን ጎሰኛና አምባገነን መንግሥት ማስወገድ መሆኑ ግልጽ በመሆኑ፣ እንደ ቁጥር አንድ ችግር ተመልክቶ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው!" በማለት አመራር ይሰጣል ። "እኔ ግን ዜጎችን በእኩል ዓይን የሚያይ ሥርዓትን ህግመንግሥት ተቀርጾ፣ የሕግ የበላይነት ካልሰፈነ፣ እሱን ሊያረጋግጥ የሚችል የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞ አዲስ ሥርዓት ካልተገነባ ይህ ሁሉ ፉርሽ ነው!" የሚለው ደግሞ ሌላኛው ተናጋሪ ይሆናል።

እነዚህን የመሳሰሉ ጣፋጭ አመራሮች በየስብሰባው አዳራሾች ይሰጣሉ። ከየስብሰባዎቹ የማይጠፉት የመደምደሚያ ቃላት አለበት- አለባቸው- አለብን- ይኖርብናል- ያስፈልጋል- ያስፈልገናል- የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ቃላት ኃላፊነትን አንድ ባልታወቀ አካል ላይ የሚጭኑ ናቸው። "እሺ እንዳላችሁት አደርጋለሁ!" ብሎ ማስታወሻ ወስዶ፣ ኃላፊነቱን በባለቤትነት የሚወጣ ሰው እስከዛሬ ብቅ አላለም። መድረክ ላይ የተቀመጠውም፣ አዳራሽ ውስጥ ያለውም፣ በየሚዲያው በየፌስቡኩ የሚጽፈውም ሁሉ እየተነሳ አመራር ይሰጣል። ይመክራል ያስጠነቅቃል። ግን የሚሆን ነገር የለም። ዛሬም ነገም ትናንትም የተባለው የሚባለው ይኸው ነው።

ገዝፎ ገዝፎ ጠላት ነው ወይስ አይደለም ከሚል ጥያቄ ላይ የደረሰው ችግር በእነዚህ ቃላት አይሸነፍም። ትግል ባመረ ንግግር ወይም ትንተና ብቻ አይሰምርም። ባለቤት ይፈልጋል። ባለቤት ብቻ ሳይሆን፣ ንግግሩ በጊዜና በቦታ ተዘርዝሮ ታቅዶ ያ የተነጋገርንበት ነገር ምን ደረሰ ተብሎ ውጤቱ ይገመገማል። ለሚቀጥለው ደግሞ ምን እናድርግ ተብሎ ታቅዶና ታልሞ ጥይትም ከሆነ ጥይቱ ድርጊትም ከሆነ ድርጊቱ ይተኮሳል እንጂ እንዲሁ በብላሽ መንጣጣት ጠላትን ለሽንፈት ወገንን ለድል አያበቃም። ሰላማዊ ትግል ይሻላል ወይስ የትጥቅ ትግል እያሉ መንገዱን ቢያማርጡም አካዳሚክ እንጂ የተግባር አይሆንም። የሚደረገው ነገር ታውቆ፣ አድራጊው ተገኝቶ ፣መታገያው መንገድ የጠፋ ማስመስል እንዲሁ ዝምብሎ ራስን መሸንገል ነው። ገና መንገድ የሚያማርጡት ቀርቶ ፣ ይኸኛው መንገድ ይሻለናል ብለው የመረጡትም ወገኖች ርቀው አልሄዱም። ምክንያቱም የተመረጠውም መንገድ ቢሆን የሚሄድበት መንገደኛ ወይም ባለቤት ይፈልጋል። ካለበለዚያ ጥቂቶች ብቻ የሚጓዙበት ወይም ማንም የማይታይበት ባዶ መንገድ ይሆንና ማንንም የትም አያደርሰም። እነሆ እኛም አልደረሰንም።

እርግጥ ነው በሚሆነው ሁሉ ተቃጥለናል። ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ ላለማለት እንደማንመለስ ልቦናችን ቢያውቀውም የሚደረገው ጠፍቶን የተቀመጥን ሞልተናል። ጠላትነትን በጠላትነት ክፋትን በክፋት ጎሰኝነትን በጎሰኝነት መውጋት እየደበረን የጨዋታው ህግ እያስጠላን፣ ጠልተን ተጠልተን የተቀመጥን እልፍ ነን። እግዜር መንገዱን እስኪያመላክተን ለሚጠሉንና ለሚያውኩን ሁሉ ጸሎትም ሆነ እንጉርጉሯችን እንዲህ ይላል፦

እነሆ ባህላችን፣ አብሮ ኗሪነታችን፣ ወንድማማችነታችን፣ ጠላትነታችሁን እየቀነሰብን ልባችንን አለዘቦ አውኮብናል። አንዳንዶች እንደሚያስቡት ብሶት አንሶን ግፋችሁ ጣፍጦን አይደለም። በሏቸው! ፍጇቸው! አቃጥሏቸው! አለማለታችን ጥላቻ ጎድሎን ንዴት አንሶን አይደለም። ሥልጣኔያችን ነው ፍርሃታችን። ሰው ሰውን አስብቶ አለማረዱ፣ ወንድም ወንድሙ ላይ አለመደራጀቱ ነው ነውራችን። ነውር ነው እንደናንተ በጎሳ አንደራጅባችሁም። በልሳን አንነጋገርባችሁም። ካዱን፣ ግፈፉን፣ ጨፍጭፉን፣ ፎከሩብን፣ ጀግኑብን፣ ተማከሩብን፣ ተደራጁብን፣ ተንሸኳሾኩብን፣ በቀን አስራ አስምት ጊዜ ድል ንሱን፣ ጨፍሩብን፣ አቅራሩብን... ግን የእናት አገሩ ልባችን ለእናት አገር ልጅ መቸም ቢሆን ልስልስና ልፍስፍስ ነው! እንዲያው ቢጨንቀን ብሶት ግልፍ ቢልብን ነው እንጂ እኛ የናንተ ጠላት ልንሆን እንችላለን፣ እናንተ ግን የኛ ጠላት አይደላችሁም። መቸም መቸም አትሆኑም! የጥላቻ፣ የበቀል፣ የቁረጥ ስቀል ንግግራችን ሁሉ ገና ከአፋችን ሳይወጣ እዚያው ሟምቶ የሚቀርብን፣ እንደሬት እየመረረን ወዲያው የምንጉመጠመጠው እንዲያው እንደነገሩ...ስለሆነብን ነው። እናንተም ይህን አሳምራችሁ ታውቃላችሁ። ይሉኝታም አዜነታም ከበሬታም የላችሁምና በዚህም ትነግዳላችሁ። ግን ከኛ መካከል የበቃው ፈንድቶ ያፈነዳችሁ ቀን፣ እኛም አናንተም አገርም ተያይዘን እንፈነዳለን። ህዝብ በእንግልት፣ በእስርና በስደት እያለቀ ከባህር እየጠለቀ መሆኑን እናውቃለን። ብንነሳም እልቂት ዝም ብንልም እልቂት ሆኗል። የህዝብ ትንሽ የለውምና- ህዝብ ከሚያልቅ ህዝብ ቢያልቅ ይሻላል- ከሚል ጭንቅ የህሊና ሙግት፣ አምላካችን ይጠብቀን። እግዜአብሔር አምላክ አሁንም መንገዱን ያመላክተን። "ሺ ጠላት ከቦሃል ቢለው ግድ የለም አንድ እግዜር ብቻ አይክበበኝ እንጂ ችግር የለም" እንዳለው እሱ ብቻ አይክበብን! ይልቁንስ እኔና ጠላቶቼን ቆም የሚያስደርግ ማስታወል ይስጠን- አሜን!

◇ ◇ ◇

አስተያየት ካለዎት!

asharamagazine@gmail.com

# የማውቀውን ያህል
## ስለ ፐ/ር መስፍን ወልደማርያም

ያሬድ ኃይለማሪያም (ከቤልጂየም)

ከገጽ 15 የዞረ

ባጭሩ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፤ "ድሃ ባይኖር ኖሮ ሃብታም ጠግቦ አያድርም ነበር"። ይህ አባባል እንደ ብዙ ምሰጢራዊ አገላለጾች በአርምሞ የሚታለፍ አይደለም። ማኅበራዊ ፍትሕ ባልሰፈነበትና የብዙዎችን ሃብት እና ድርሻ ጥቂቶች ጠቅለው በመያዛቸው ሚሊዮኖች በከፋ ድህነት ውስጥ ሆነው እንዲማቅቁ በሚደረግበት አለም፤ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር ውስጥ፤ ይህ የፐ/ር አገላለጽ ሰፊ መልዕክት ያዘለ ነው። ታሪክንም ያየን እንደሆነ የቀድሞዎቹ መሳፍንቶች፣ መኳንንቶችና ባለጸጎች የሃብታችውም ሆነ የድሎት ኑሮዋቸው መሰረቱ የተጣለው በሚያስገብሩዋቸው ጭሰኞችና አገልጋይ ባደረጉዋቸው ሰዎች ትከሻና ወዝ ነው። አንድም በባርነት የሚፈነገል ወይም በጭሰኝነት የሚያገለግል ድሃ ባይኖር እነ ጌቶች ማን የሰራውን በልተው ያድሩ ነበር? በማንስ ጉልበት ያንን ሁሉ ሃብት ያፈሩ ነበር? በዚህ ባለንበት ዘመንም ቢሆን ሌላውን አለም ትተን የገዛ አገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ በቅጡ ብንፈትሽ ይህን የፐ/ር መስፍንን አገላለጽ ቁልጭ ያለ ዕውነት ሆኖ እናየዋለን። ዛሬም የጥቂቶች ሃብት ምንጩ የብዙ ድሆች ስቃይና እርሃብ ለመሆኑ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል።


ፐ/ር መስፍን ለድሆች መቆርቆር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ድሃ ገበሬዎች ህይወት ለመለወጥ የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችንም እያካሄዱ (ሰሚ ጠፋ እንጂ) ጠቃሚ ሃሳቦችንና ምክሮችን በማፍለቅ ይታወቃሉ። ይህ የዜግነትና ሙያዊ ድርሻቸው ቢሆንም በሰውነታቸው ደግሞ ድህነትን የሚያዩበት መነጽር እጅግ የተለየ ነው። ደጋግመው ድህነትን በተመለከተ ሲያጫውቱን እንዲህ ይሉ ነበር።

*"እንደ ድህነት ቶሎ የሚረሳ ነገር የለም። ብዙ ሰዎች ድህነታቸውን ወይም ድሃ እንደነበሩ ትንሽ ያገኙ ዕለት ቶሎ ይረሱታል። ስለ ድሃም ሆነ ድህነት ማሰብን ያቆማሉ። እራሳቸውን እና በነሱ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችን ብቻ ነው የሚያስቡት። እኔ ድህነቴን ላለመርሳት ስል ሁሌም የምኖረውና ለመኖሪያነት የምመርጠውም ብዙ ድሆች የሚኖሩበትን ሰፈራ ነው። ምክንያቱም ከቤቴ በገባሁና በወጣሁ ቁጥር ስለማያቸው ድህነቴን እንዳስታውስ ያድርጉኛል። በድህነት ለሚኖሩ ሰዎችም እለት ተዕለት እንዳስብ ያደርጉኛል።"*

በርግጥም ፐ/ር መስፍን የመዲናዋ እምብርት በሆነውና በርካታ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የከተማዋ ነዋሪዎች በሚኖሩበት በፒያሳና በቴዎድሮስ አደባባይ መካከል ባለ መንደር ውስጥ ነው የሚኖሩት። አንዲት እድሜ ጠገብ በሆነች ህንጻ ውስጥ በሚገኝ ጠባብ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ባሸበረቁና ውድ በሆኑ የቤት እቃዎች ሳይሆን እጅግ በርካታ በሆኑ መጽሐፎችና የምርምር ሰነዶች ተከበው ነው የሚኖሩት። መተዳደሪያቸውም በየወሩ የሚያገኙት የጡረታ ገንዘብ ነው። በዚህ አነስተኛ ገቢያቸውም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በኑሮው ውድነቱ የተነሳ የገጠመውን የከፋ የኑሮ ፈተና አብረው ተጋፍጠው እየኖሩ ነው።

ሌላው በሥራ አጋጣሚ ከፐ/ር መስፍን የተማርኩት አንድ ታላቅ ነገር በምርምር ስራ ላይ መረጃዎችን የማሰባሰብና በእያንዳንዱ ፍሬ ጉዳይ ላይ ለማስረጃ የሚሰጡት ክብደት ነው። በምንም ጉዳይ ላይ ቢሆን ፐ/ር መስፍን ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ በመረጃ ላይ ሳይሆን በማስረጃ ላይ ተመርኩዘው ነው። ማስረጃ በሌለው ጉዳይ ላይ ምንም እንኳን ነገሩ የከበደ፣ አንገብጋቢ ወይም አጣዳፊ ቢሆንም፤ በቂ ሊባል በሚችል ማስረጃ እስካልተደገፈ ድረስ ፐ/ር በጉዳዩ ላይ ምርምራቸውን ይቀጥላሉ እንጂ ባደባባይ በጉዳዩ ላይ አይተቹም። ይሄ በእሳቸው ደረጃ ላይ ላለ የምርምር ሰው እንደ አንድ የሙያ ብቃት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ነገር ግን የፐ/ር መስፍን በማስረጃ ላይ ያላቸው ጥንቃቄ ከዚህም አንድ ደረጃ ከፍ ያለ በመሆኑ በሚጽፏቸውም ሆነ በሚናገሯቸ ጉዳዮች ላይ ብዙ ጊዜ ነቀፌታ የሚሰነዝሩባቸው ሰዎች የትችት ትኩረታቸው ፍሬ ጉዳዩ ሳይሆን በግል እሳቸው ላይ ያነጣጠረ ነው። ምክንያቱም ግልጽ ነው። ባደባባይ የሚናገሩበት ፍሬ ጉዳይ በበቂ ማስረጃ ላይ ወይም አመክንዮ ባለው አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ብቻ ነው። ይህ ብቃታቸው የኢሰመጉንም የምርመራ ሥራ ከፍ ወዳለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ስላደረገው ድርጅቱ የሚያውጣቸው መግለጫዎች ከማስረጃ ስህተቶች የጸዱና ለትችትና ነቀፌታ የማይመቹ ለመሆን ችለዋል። አንድም ቀን የወያኔ መንግስት ኢሰመጉ አጣርቶ ባወጣው መግለጫ ላይ ሃሰት ነው የሚል ማስተባበያ ሰጥቶ አያውቅም። ይልቅስ ልክ በፐ/ር መስፍን ስብዕና ላይ ያተኮረ ስድብ እንደሚሰነዝረው ሁሉ ኢሰመጉን እንደ ተቋም የሚሰድቡ ተደጋጋሚ መግለጫዎችም በመንግስት ተሰጥተዋል። ከዚህ ጋር የተያያዙ አንድ ሁለት ነጥቦች ልጥቀስ።

በአንድ ወቅት ከተለያዩ አካላት ለኢሰመጉ ከሚቀርቡት አቤቱታዎችና ጥቆማዎች መካከል አንዱ ‹በመንግሥት መዋቅር ውስጥ አብዛኛውና ቁልፍ የሆኑ የሥራ ኃላፊነቶች በአንድ ጎሣ (በትግራይ) አባላት ተይዘዋልና ፍትሐዊ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል የለም› የሚል ነበር። ጉዳዩ አሳሳቢና ከተለያዩ መረጃዎች አንጻር በአደባባይ የሚታይ ያፈጠጠ ችግር ይመስላል። ይሁንና ኢሰመጉ በመረጃዎች ላይ ብቻ ተመስርቶ አቋም ስለማይዝና መግለጫም ስለማያወጣ ፐ/ር መስፍን በቅርብ የሚከታተሉት የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራ በምርመራ ክፍሉ ሠራተኞች በኩል ተጀመረ። የተወሰነ መንገድ ከተጓዘ በኋላ ግን የመንግሥት መዋቅሮችና የባለሥልጣናት አሿሿም ግልጽነት የሌለውና ማስረጃዎቹም በሚፈለገው መጠን ለሕዝብ ክፍት ባለመሆናቸው የተነሳ ምርመራው ሊቀጥል አልቻለም። በቂ የሆነ ማስረጃ ማግኘት ስላልተቻለም በመረጃዎች ላይ ብቻ ተመርኩዞ አቋምን ማንጸባረቅ ለስህተት ሊዳርግም ስለሚችል ኢሰመጉ በጉዳዩ ላይ ምንም ሳይል ቀርቷል። ልክ እንደዚህ እጅግ በርካታ ጉዳዮችና የመብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጡ መረጃዎች ቢኖሩም ማስረጃ ማግኘት ስላልተቻለ ብቻ በይደር ፋይል ወደ አደባባይ ሳይወጡ ቀርተዋል። ይህ ማስረጃ ላይ የተመረኮዘ የምርመራ ሥራ የኢሰመጉን እድሜ ለማራዘምና ድርጅቱም አለም አቀፍ ተቀባይነትን እንዲያተርፍ አድርጓል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁሌም የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን በተመለከተ ምርምርና ክትትል ሳደርግ ወደ አእምሮዬ የሚመጣው አንዱ ነገር የኢሰመጉ የምርመራ ሠራተኛ ሆኜ ሥራ የጀመርኩ ቀን ለእኔና ለሌሎች የምርመራ ክፍሉ ባልደረቦች ፐ/ር መስፍን ቢሯችን ድረስ መጥተው ያሳሰቡንና የመከሩን ነገር ነው። እንዲህ ነበር ያሉት:-



*"...የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን የማጣራት ሥራ እጅግ ከባድ ነው። አንድም በየቀኑ የተጎዱና የተከፉ ሰዎችን በደልና እሮሮ መስማት እያደር አይምሮን ይጎዳል፣ ልብን ያሳሳል፣ ያስጨንቃል፣ መንፈሳችሁንም እረፍት ያሳጣል። በተለይ ይህ አይነቱ ሥራ እንደ*

ወደ ገጽ 26 ዞሯል

# "ጠፍአት አገርነ"
## ትናንት ሚታ ጨረቃዋንም አዋልደናል

ከገጽ 10 የዞረ

ጽጋቡ ገብረመድህን አርአያ

የአንድ ቀን ጦርነት! አጤ ዮሐንስና የጦር አበጋዛቸው ጉራዕ ላይ በአንድ ቀን ጦርነት፤ እንዲሁም ጉንደትና ጉዳጉዲ ላይ ግብጽን በአንድ ቀን ጦርነት፤ ምኒልክና ጣይቱ በጦር አዛዦቻቸው አማካይነት አድዋ ላይ በአንድ ቀን ጦርነት የኢጣልያንን ሠራዊት ድባቅ መቱ። በማይጨው፣ በሽሬና በመረብ ከፋሽስት ኢጣልያ ጋር በተደረገው ጦርነት ሁሉ ግን የኢጣልያ የጦር ስልትና አቅም የመርዝ ጋዝ በመሆኑ ለጊዜውም ቢሆን በሌሎች ስልቶች መዋጋቱን ተያያዝነው። የሽምቅ ውጊያን ለዓለም አስተዋወቅን። ይሁንና ከ1928 እስከ 1929 (የካቲት) ድረስ የነበረው የሽምቅ ውጊያ ዝግጅታችንና የአርበኝነት ጦርነት መሰናዶው ጊዜ የፈጀ መስሎ ነበር። ኢጣልያኖች በዚህ አንጻራዊ ሰላም ሳይታለሉ አልቀሩም። ይሁንና የተጠራቀመውን የፋሽስቶች ግፍ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. አብርሃ ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም፣ ስምኦን አደፍርስ ፣ አያና ብሩ፣ ዳባ ብሩ፣ በሻህ ውረድ፣ ለጥይበሉ ገብሬ . . . በምስጢር ሲያካሂዱ የቆዩት እንቅስቃሴ የተገፈፈበት ነበር። ማርሻል ግራዚያኒን ለመግደል የተደረገው ሙከራ ለጊዜው ባይሳካም ከዚያ በኋላ በተከተለው የሰላሳ ሺዎች የግፍ ጭፍጨፋ ምክንያት የአርበኝነቱ ጦርነት ተቀጣጠለ። ተዳክመው የነበሩ የአርበኞች መሪዎች የበለጠ ተጠናከሩ፤ ባልታሰበ ፍጥነትና አዲስ ወኔ ሺህ በሺህ ወገኖቻችን ከትግሉ ግንባር መሰለፍን ብሔራዊ ግዴታቸው አደረጉት። ይኸና የመሳሰለው ሁሉ ወኔ የሚዘራ ቅባት ፣ መንፈስን ለትግል የሚቀሰቅስ ኃይል ሆነ።

በወያኔያዊት ኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግልና ሰላማዊ ትግል ብቻ እንደማያዋጣ፣ በዚህም አማካይነት አንድና ሁለት ሰዎች እንደምንም ከዘረኞች ምክር ቤት በማስገባት ቀስ በቀስ የዴሞክራሲን አመራር ለማስፈን ይቻላል የሚል የለበጣ ፖለቲካ ሲሰነዘር ቆይቷል። ለወያኔ የበጀትና የደህንነት፣ የጦር መሰናዶና የመሳሰለውን አመራርና ድርጎ የመደቡላት የአውሮፓና የአሜሪካ መንግስታት እያለቅንና እየተሰዋን ዲሞክራሲን ለማስገኘት መሞከር እንዳለብን ያስተምሩናል። ሥጋችንና ነፍሳችን ለመስዋዕትነቱ ያልበቃው የዚህ መንግስት ፍላጎት ከዚህም ሁሉ በላይ መሄዱን ፍርድ ቤት ቢኖር በምስክርነት ልናቀርባቸው የሚገባን አሜሪካና የአውሮፓ ህብረት በሆኑ ነበር። በየጊዜው የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ለኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፍትህ የሚያወጣቸው መረጃዎችና እነ ሒዩማን ራይትስ ዋችን የመሳሰሉት ድርጅቶች መግለጫዎች ብዙ ብዙ ይናገራሉ። እስከናካቴውም ወጣ ብለው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን "ይህን ያህል ፍዳና አበሳ ደርሶብናል ማለት ነው?" እያሉ ያፌዛሉ።

ቀደም ሲል የፋሽስት ኢጣልያን ወረራና ግፍ አንስተን አልቋጨነውም። ንዴትና ቁጣ እንጂ ፍርሃትና የወኔ ድክመት የሌለባቸው ታላላቅ ጀግኖቻችን አዲስ አበባን ከደቡብ፣ ከሰሜን፣ከምዕራብና ከምስራቅ ጥሶ በመግባት ጣልያንን መድረሻ ለማሳጣት ሁሉም ነገር ዝግጁ ነበር። የወሎው ጳጳስ ታላቁ አቡነ ጴጥሮስ፣ የራስ ካሳ ሦስት ልጆች፣ ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ተጫን . . . ወዘተ መስዋዕት የሆኑባቸውን ወቅቶች ያስቧል።

በአንድ ወቅት መራራና ሁሉን አቀፍ የሆነውን ትግል የመረጡትንና በአገር ውስጥ በሰላም እንታገላለን በማለት ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉትን ሠራዊተ ታጋዮች ለማጋጨት የተደረገው ሙከራ ትዝ የሚል ነው። ለስለስ ባለ ሁኔታ እንግለጠውና ሰላማዊ የተባለው ትግል ብዙ ርቀት ሳይወስድ እንደገና የኢትዮጵያ ልጆች በግፍ ወደሚጨፈጨፉበት ደረጃ ተረማምደናል። ብዙ ብዙ የተባለለትና ቢበዛም አንድና ሁለት ሰዎችን በመናጆ መልክ የሚቀበሉበት የፌዝ ምርጫ ቁም ነገር ሆኖ "አጣማጅ" ሳይቀር እየጠራረገ የማሳደድና የማሰር፣ የመደብደብና የማንገላታቱ ተግባር በአዲስ ስልትነት ቀጥሏል። በአጠቃላይም አገራችን ከነጻነት ወደ ፍጹም ገሐነምነት እየተለወጠች ናት።

የኢትዮጵያም ሆነ እንዲህ ያለው መዓት የተከፈተበት ሕዝብ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚነሳሳ ይታወቃል። ከአገሪቱ ሲሣይ ሁሉ የተገለለ ሕዝብ፣ በጭፍንና በፍርደ ገምድልነት ሞት የተፈረደበት ሕዝብ፣ የፖለቲካውን ዕድል የተነፈገ ሕዝብ፣ የተገፋና የተጨቆነ ሕዝብ ምን እንደሚያደርግ ምክርም ቅስቀሳም አያሻውም። ይርጋ ዱባለ "ወተት ይሸፍታል እንኳን . . . " በማለት ጨርሶታል። ለዚህ ደግሞ መዝሙሩ ተደርሷል። የጋራ መፈክራችን በስምምነት ተነድፏል።

ሁላችሁም በዚህ የፈተና ወቅት በልባችሁ ያለው ምን እንደሆነ ይታወቃል። በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ያለው ዜጋ ሁሉ ትዕግስቱ ከድንበር ላይ መድረሱ ይታወቃል። እንዲያም ሆኖ "ምን ይሻላል? ምን እናድርግ? ምን ይጠበቅብናል? . . . " የሚሉ ጥያቄዎች ቁርስ ምሳ ራታችን ሆነዋል። ዕድሜዬንና አንዳንድ ግምትም በማከል ብዙ ሰዎች "ምን ይመስልሃል?" ይሉኛል።

በእኔ በኩል አንድ ትዝታ አለኝ። ጨረቃዋን በገባያን፣ ፀሐይዋንም ባለችበት ከመውጣት በአንድ ስፍራ ያቆመ ኢያሱ ብቻ ነው። እኔ ደግሞ ትናንት ምሽት ላይ ጨረቃዋ ስትወጣ አይቻለሁ። ከጥቂት ጓደኞቼ ጋርም እንዳዋለድኳት ይሰማኛል። እየመጣ ያለውን የሕዝብ ጎርፍ የሚያቆም ኃይል የለም ባይ ነኝ። ስንነጋገርበትና ስንጠብቀው የቆየነው የሕዝባዊ አርበኝነቱ ተጋድሎ ደወል ሳይጠበቅ፣ ማን ይምራኝ ሳይል ሲጀመር እየተሰማኝ ነው። አገሪቱ በአንድ ተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ ወደ ጦርነት አውድማ ስትለወጥ እየታየኝ ነው። ሕዝቡ ወደ ሠራዊተ - አርበኝነት ሲዛወር ማየቱ፤ ወጣቱ በሙሉ፣ ሴቱ በነቂስ፣ ተማሪው፣ መምሕሩ፣ የሀይማኖት አባቶች . . . ከሰልፉ ተራ ገብተው . . . ሲንቀሳቀሱ ማየት የሩቅ ጊዜ ህልም አይደሉም። ሁሉም ሰው በባከነው ጊዜ የባከነው የአገርና የሕዝብ ሕይወት እየከነከነው ነው።

በዚህ ዓይነቱ ጊዜና ሁኔታ ዘመናትን አጣጥፎ ጀግኖች አባቶችን ማስታወስ ግዴታ ይሆናል። አቡነ ጴጥሮስ የክብርን ሞት ሲቀበሉ የተናገሩትን ታስታውሳላችሁ። "እናንተም ልጆቼ ኢትዮጵያውያን ለፋሽስቶች እንዳትገዙ አወግዣችኋለሁ! የኢትዮጵያንም ምድር እንዲሁ ለፋሽስቶች እንዳትገዛ አውግዣለሁ!" ወገኖቼ የኢትዮጵያ ልጆችን ለማስታወስ የምወደው ይህ ግዝት እንዳለብን ነው። አለዚያ ዛሬ የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም በእጃችን አለ። ትግሉ የተባረከ፣ በእግዚአብሔር የተባረከ፣ በሕዝብ የሚከናወንና ምድሪቱና እንስሳቱ የሚካፈሉበት ነው።

ሁላችንም ዛሬ ያለብን ኃላፊነት በዘረኞች ላይ የሚካሄደውን የአርበኝነት ትግል ወያኔዎች ወደ ትግራይ ሕዝብ የሕልውና ተጋድሎ እንዳይለውጡት ነው። የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያ ኅብረተሰብነትና አካልነት ያስወጣ ማነው? አጥንታችን አጥንቱ፣ ሥጋችን ሥጋው አይደለምን? ለወያኔ መግለጫ ተስማሚ መስሎ ስለታየን "የአናሳ ብሔረሰብ ተወካይ" እያልን ስንጠራው ቆይተናል። በመሰረቱ ግን ትግሪኛ ተናጋሪውን ኢትዮጵያዊ "አናሳ" ወይም ንዑስ - አለዚያም በጥሬ ቃልም ሆነ በፖለቲካ ፋይዳው ዝቅተኛ ለማድረግ ፍላጎት እንደሌለን መታወቅ አለበት። ትግራይ በኢትዮጵያ ሥነ መንግስት፣ በባሕል፣ በሐውልቶችና በታሪክ ቅሬታዎችዋ ዐቢይ ሚና ያላት ናት። አናሳ የሚባለውም ቃል ሊጠቀስ የሚገባው ወያኔዎች የሚከተሉትን ፖለቲካ ነው። አናሳ አሳብና ፖለቲካ፣ አናሳ ፍልስፍናና የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ አናሳ ማሕበራዊ አመለካከትና አግጣጫ የሚከተለውን "አናሳ የፖለቲካ ድርጅት" ግን ከሥልጣን በማውረድ ረገድ ዋናው ተፋላሚ የትግራይ ሕዝብ ነው። በተግባር በትግሉ አደባባይ ያገናኘን! አሜን ወአሜን!

◇ ◇ ◇



# በካድሬዎች የተወረረ ዩኒቨርሲቲ ሆኗል ነው የምልህ አለቀ!

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ

**አሻራ፡-** በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ የመማር ማስተማሩ ሂደትና ባጠቃላይም የትምህርት ጥራቱን ዝቅተኝነት ብዙዎች ይስማሙበታል። ለጥራት ጉድለቱ በዋናነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የትምህርት ፖሊሲው ሆኖ በተጓዳኝም የአካዳሚ ነጻነት ያለመኖሩ እንደ ምክንያት ገዝፎ ይጠቀሳል ፤ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** ስለ አካዳሚ ነጻነት የተጻፈው በ1918 አሜሪካን ሃገር ነው። አራት መሰረታዊ የነጻነት መርሆችን ይዟል።አንደኛው በነጻነት ምርምር የማድረግ ነጻነት ሲሆን ሁለተኛው በምርምር ያገኘህውን በነጻነት የማቅረብ መብት ነው። ሶስተኛው፤ (ኤክስታራ ሚረር) ይሉታል በመማር ማስተማሩ ዘርፍ ያለው ምሁር በሃገሩ ውስጥ እየሆነ ስለላው ነገር በነጻነት የመተቸት መብት እንዳለው የሚደነግግ ነው፡፤ አራተኛው ደግሞ በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በተቋሙ ውስጥ በሚከናወኑ ጉዳዮች ላይ እንዲተቹና እንዲሳተፉ ነጻነት የሚሰጥ ነው።

እኔ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበርኩ። በዛ ጊዜ የነበረው የአካዳሚ ነጻነት ዛሬ 10% እንኳ የለም። ሁሉም አንገቱን ደፍቶ ‹ተሰማሁ..? አልተሰማሁ...?› እያለ በስጋት የሚኖርበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው። ሌላው ትልቁ ችግር መንግስት በመማር ማስተማሩ ላይ ፍጥጥ ብሎ ጣልቃ መግባቱ ነው።

ካድሬው ይመጣና ፕሮፌሰሩን 5 ለ 1 ላደራጅህና ስልጠና ልስጥህ ይለዋል።(ሳቅ) እግዚአብሄር ያሳይህ ! የዩንቨርሲቲው ፕሮፌሰር 5 ለ 1 ተደራጅቶ በካድሬው ስለ መማር ማስተማሩ ሂደት የፖሊሲ ስልጠና ሲሰጠው(ሳቅ) ። 24 አመት በካድሬነት የሰራ ሰው ይመጣና አስተማሪ ይሆናል። ማነው እሱ? ስትል ዶክትሬት አለው ይሉሃል። ከየት አመጣው? ስትል በተልኮ አገኘው ትባላለህ።ቀልድ ነው የተያዘው ።

እኔ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 7 ዓመት አስተምርያለሁ። በጋዜጣ ያነበብኩትን ወይም በወሬ የሰማሁትን አይደለም እንዲህ ሆነ እንዲህ ሆነ የምልህ፤ ከውስጥ ሆኜ የማውቀውን ነው የምነግርህ።

ምን አለፋህ! የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት በካድሬዎች የሚታዘዝበት፤ አድርግ የተባለውን ሁሉ የሚያደርግበት ፤ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ምንም ሚና መጫወት የማይችሉበት፤ በካድሬዎች የተወረረ ዩኒቨርሲቲ ሆኗል ነው የምልህ። ዩኒቨርሲቲው ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያ እንደተለወጠ ነው የምነግርህ። አለቀ. . .(ሳቅ)

**አሻራ፡-** ሌላው ለጥራቱ ጉድለት የሚጠቀሰው ምክንያት የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ከ(BPR) ጋር በተያያዘ ከ2008 (እ.አ.አ) ጀምሮ ከ( Collegial Governance) ወደ ( managerial model) መቀየሩ ነው ይባላል ። ይህን እንደምክንያት የሚያነሱ ወገኖች የአስተዳደር ዘይቤው ለውጥ መምህራኑ (academic staff) የራሱን ካሪኩለም የመቅረጽም ሆነ ሪቪው የማድረግ ሃላፊነቱን (ስልጣን) ስላሳጣው የመማር ማስተማሩን ሂደት ሙያዊ አያያዝ እንዳይኖረው አድርጎታል ይላሉ ...እርስዎ በዚህ ይስማማሉ።

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** አሁን ባነሳኸው የካሪኩለምና የዩኒ አስተዳደር ላይ ጥናት ያደረጉ ጠንካራ ጠንካራ ሰዎች አሉ። እነሱ በዝርዝር ሊያስረዱ ይችላሉ። ላገናኝህም እችላለሁ። እኔ ልገልጽልህ የምችለው ጠቅለል ያለውንና ጎልቶ የሚታየውን ችግር ነው። ነገሩ የተበላሸው እኮ! አንድ ካድሬ መምህራኑን ሰብስቦ ተማሪውን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ሲያሰለጥናቸው ነው። ተማሪዎች አንድን ኮርስ ሁለት ሶስት ወር ከተማሩ ይበቃቸዋል ይሉሃል። ሁለት ሶስት ወር በለብ ለብ ተምሮ ሲወድቅ ደግሞ እንደገና ለብ ለብ አድርገህ አሳልፈው ይሉሃል። ስለዚህ መጀመሪያውኑ ለወደቀው ተማሪ ሲና ቢ ሰጥተህ ማሳለፍን ትመርጣለህ። ምክንያቱም የሚፈለገው ይህን ያህል ሰው ተመረቀ የሚለው እንጂ ምን ያህል አወቀ? የሚለው ስላልሆነ የመምህራኑ ሃላፊነት ማሳለፍ ብቻ ነው።

80 ተማሪዎችን አስተምረህ አስሩ ሲወድቁ፤ አስሩን እንደምንም አሳልፋቸው የምትባል ከሆነ መጀመሪያውኑ ማሳለፍን ትመርጣለህ። ምን አለፋህ ሁሉም ነገር ለበጣ ነው። ትምህርት ማዳረስ በሚለውና በትምህርት ጥራት መካከል ያለው ልዩነት አልገባቸውም። ወይም ልዩነቱን ሊያዩ አልፈለጉም።

አሁንም ገና ስንት... ዩኒቨርሲቲ እንገነባለን እያሉ ነው። ምንም ሪሶርስ የሌለበት በርሃ ውስጥ ዩኒቨርሲቲ ከፍተው ምን ሊያደርጉት እንደሆነ አይገባህም። ብቻ ይህን ያህል ዩኒቨርሲቲ ከፈትን ይህን ያህል ተማሪ አስመረቅን ይሉሃል...ቁጥር ብቻ!

**አሻራ፡-** የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ(Higher Education Relevance and Quality Agency (HERQA)) የሚባል ተቋም እንዳለ ይታወቃልና፤ ይህን መሰሉን የጥራት ጉድለት ችግር ለመቅረፍ ምን ሚና ይጫወታል?

**ዶ/ር ዳኛቸው፡-** እሱ የማይሆን ነገር ነው። ኳሊቲ ኮንትሮል ይደረግ ቢባል 90% ተማሪ አያልፍም ነው እኮ የምልህ። የትምህርትና ስልጠና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ ስራ ምን እንደሆነ ለኔም አይገባኝም፡፤

አንድ ነገር ልንገርህ ፡ በዲፕሎማ ሁለተኛ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ወደ ዲግሪ ከፍ ማለት አለባቸው ተባለና የሰመር ኮርስ እንዲወስዱ ተደረገ። እንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲያሻሽሉ ስልጠና ይሰጣቸው ተባለ፡፡ መምህራኖቹ 45 ዓመትና ከዚያ በላይ ናቸው። ሲጀመር እንዴት ነው በዚህ እድሜ ቋንቋ ሊያሻሽሉ የሚችሉት? አብዛኞቹ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መምህር ሆነው እንግሊዘኛ መጻፍ እንኳ አይችሉም። እንግሊዘኛ ቋንቋን የእውቀት መለኪያ አድርጌ መውሰዴ አይደለም። ነገርግን በመማር ማስተማሩ ሂደት ከአንድ መምህር የሚጠበቅ የቋንቋ ችሎታ አለ፡፡ ያ የለም ነው የምልህ፡፡ የትምህርት ጥራቱን ዝቅጠት ላሳይህ ፈልጌ ነው።

እኔ የምልህ 30 እና 40 ልጆች አስተምረህ 3 እና 4 የሚሆኑ በራሳቸው ጥረት ጠንክረው የሚወጡ ልጆች ልታገኝ ትችላለህ። ከነሱ ጋር መስራት ይቻላል። ሌላውን ግን ተወው።

መጀመሪያ እነሱ (ካድሬዎቹ) ለትምህርት ክብር የሚሰጡ አይደሉም። ዶክትሬትና ማስትሬት በቀላሉ እንደሚገኝ ነው የሚያውቁት። ምን ያድርጉ? አንዱን ካድሬ ይጠራና ከዛሬ ጀምሮ የትምህርት ሚኒስቴር ነህ ይለዋል። ጣጣ ነው እኮ የገባነው።

በቅርቡ አንድ አርቲክል ጽፌያለሁ። ይሄ ልማት፤ ልማታዊ የሚሉት ነገር እንዴት እንደበጠበጠን የሚያስረዳ አርቲክል። መማር ሳይሆን ያለብህ ከሚወደደው ብሄር መምጣት ብቻ ነው የሚያስፈልግህ። ጸባይ ማረሚያ ከገባው ብሄር ከመጣህ አንተ አልቆልሃል! ይሄው ነው።

አሪት ተሸሮ ወንጌል የሚሰበክበት ዘመን እንደሚባለው ሁሉ፤ ትምህርት ተሸሮ ስልጠና የሚሰበክበት ዘመን ላይ እንደምንገኝ እነገርሃለሁ።(ሳቅ) በትምህርት እንጂ በስልጠና ደግሞ የትም አይደረስም።

ወደ ገጽ 40 ዞሯል

# የማውቀውን ያህል ....

ከገጽ 23 የዞረ

*ኢትዮጵያ ባለ አገር ላይ ሲሆን ደግሞ ጉዳቱ የከፋ ነው። ሰዎች ተበደልን ብለው ሲመጡና ሃዘናቸውን ሲገልጹ አብሮ ማዘን እና ህመማቸውን መጋራት ሰዋዊ ግዴታችሁ ቢሆንም ይህን በማድረጋችሁ ደግሞ ተበዳዮቹ የበለጠ እንዲቀርቧችሁ፣ እንዲያምኑዋችሁና ሌላ ቦታ ለመናገር የፈሩትን ሁሉ እንዲነግሩዋችሁም በሩን ይከፍታል። ስለዚህ ሲያዝኑ አብራችሁ ማዘናችሁን ግለጹ። ስሜታቸውንም ተከታተሉ። ይሁንና መርማሪዎች መሆናችሁን ደግሞ አትርሱ። በሰዎቹ ሃዘን ብቻ ከተመሰጣችሁና እናንተም ብሶተኞች ከሆናችሁ ስሜታዊነት ይነግሳል፤ ምርመራውም ይረሳና በቂ ማስረጃ እጃችሁ ሳታስገቡ ወደ ድምዳሜ ትደርሳላችሁ። ይህ ደግሞ የጉዳዩን ፍሬ ነገር በቅጡ እንዳትረዱና ከግራ ከቀኙ ያሉ እውነታዎችን እንዳታዩ ይጋርዳችኋል። ስለዚህ በጉዳዩ ከልብ ማዘናችሁን ለአቤቱታ አቅራቢዎቹ አሳዩ፣ ግን በያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በአዕምሯችሁ ውስጥ ትላልቅ ጥያቄዎችን ያዙ። አቤቱታ አቅራቢዎቹን ከሸኛችሁ በኋላ ለእነዛ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ምርምራችሁንና ማስረጃ ማሰባሰባችሁን ቀጥሉ።. . .”*

የሚል ነበር። ይህን ምክራቸውን በትክክል ሥራ ላይ ያዋለነው መሆኑንም አፌን ሞልቼ ለመናገር እችላለሁ። ካዘኑት ጋር አብረን እናዝን ነበር። ህመማቸውንም እንታመም ነበር። ከዛም አልፎ ያለንን እናካፍል ነበር። ምርመራችንንም ከስሜት በጸዳ ግን በተቆርቋሪነት ስሜት እናካሂድ ነበር። በስምንት አመታት ውስጥ በሺዎች የሚቆጥሩ አቤቱታዎችን አጣርተናል። በርካታ መግለጫዎችም በኢሰመጉ ወጥተዋል። አንዳቸውንም ግን በሃሰት ማስረጃ ላይ የተደገፉ ናቸው ብሎ የተቃወመ የለም። ወያኔን ጨምሮ። ከዚያ ይልቅ በመንግሥት የተላኩ የደኅንነት አባላት በተደጋጋሚ ጊዜ ተበዳዮች መስለው ተደበደብን፣ ታሰርን፣ ስቃይ ተፈጸመብን እያሉ በተደጋጋሚ ጊዜ የምርመራ ክፍላችንን ይጎበኙ ነበር። እነሱንም እያዘንን አስተናግደን በምርመራ ሂደታችን ውስጥ ግን ማንነታቸውን በቀላሉ ለመረዳት እንችል ስለነበር ኢሰመጉን ስህተት ላይ የመጣል ተልኳቸውን በተደጋጋሚ ጊዜ አክሽፈናል። ለዚህ ሁሉ ግን ክብርና ምስጋና ለፕ/ር መስፍን ይሁን፤ ትምህርታቸውና ምክራቸው በቀላሉ የማንታለል አድርጎናል።


እግዚያብሄር እድሜን ከሙሉ ጤንነት ጋር ለትግል አቅጣጫ መሪዬ፣ ለመንፈሳዊ አባቴ፣ ለሥራ አጋሬና አለቃዬ፣ ለምወዳቸውና ለማከብራቸው ፕ/ር መስፍን እንዲሰጥልኝ እየተመኘሁ ጽሑፌን ልቋጭ።

የፕ/ር መስፍንን መልካም ሥራዎች ለመዘከርና ለትውልድ ለማቆየት አልማችሁ ይህን በእሳቸው ሥራዎች ዙሪያ የሚያተኩረውን መጽሄት ለማዘጋጀት ለተነሳችሁትና እኔም ስለሳቸው ከማውቀው እጅግ ጥቂቱን እንዳካፍል እድሉን ለሰጣችሁኝ አዘጋጆች አክብሮቴ የላቀ ነው። ፕ/ር መስፍንን እንዳከበራችሁ ሁሉ እናንተም የተከበራችሁ ሁኑ።

ከአክብሮት ጋር

ያሬድ ኃይለማርያም

ከስደት አገር - ቤልጂየም



# የምንሳሳላቸው የሀገር ዋርካ ...!

(አያሌው ሁንዴሳ-ሲድኒ)


አገራቸውን በተለያየ ደረጃ በቅንነት ያገለገሉ በርካታ ኢትዮጵያውያንን አውቃለሁ። በየምዕራፉ ብቅ እያሉ በደልን በማውገዝ ድምጻቸውን የሚያሰሙ ወገኖችም አላጣንም። ለሁሉም ከፍተኛ አክብሮት አለኝ። የደሀውን ህይወት በተግባር እየኖሩ፣ ያላንዳች ፍርሀት ስለሙብቱ በአደባባይ እየጮሁና ከአንባገነኖች ጋር እየተላተሙ ህይወታቸውን ሙሉ በጽናት ሲያገለግሉ የኖሩትን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምን ግን በተለየ ዓይን ነው የማያቸው። በስስት።

እኚህን የኢትዮጵያ ውድ ልጅ ለመጀመርያ ጊዜ በአካል ያገኘኋቸው በ1986 (1992 እ.ኤ.አ.)ዓ.ም. እንደነበር አስታውሳለሁ። በወቅቱ የሰራተኛውን መብት ለማስጠበቅ ጠንክረው በሚንቀሳቀሱ የሰራተኞች ማህበራት መሪዎች ላይ የወያኔ አገዛዝ የኃይል እርምጃዎችን መውሰድ ጀምሮ ነበር። በዚሁ ጦስ እኛ ከተወከልንበት የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለስልጣን ብቻ በርካታ ሰዎች በፖለቲካ ውሳኔ ከስራ ተባረርን። ይህንኑ የመብት ረገጣ ለኢሰመጉ ሪፖርት ለማድረግ ደግሞ ከሁለት ባልደረቦቼ ጋር ተወክልንና ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ ይዘውን ሄዱ። ጉዳዩን ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር በዝርዝር እንድንወያይበት ስላስቡም ወደ ቢሯቸው ወሰዱን።

ከረጅም ቆይታ በኋላ ከፕሮፌሰር መስፍን ቢሮ ስንወጣ ስለሳቸው የነበረን አድናቆትና መመካት ይበልጥ እንዳደገ እርስ በርሳችን ያወራን ይመስለኛል። ያቺ አጋጣሚ በርቀት በስራዎቻቸውና በቁርጠኝነታቸው የማከብራቸውን ሰው ከሌላ አኳያም ማየት የቻልኩባት አጋጣሚ ሆናልኛለች። ፕ/ር ገና ከጅማሬው ነጻ የሆነ ስሜት እንዲያድርብን ማድረግ ችለው ነበር። ዘና ብለን እንደ ጓደኛ እንድናወራቸው የሚያደፋፍር በወቅቱ ይህ ነው ለማለት ያዳገተኝ መላ ሳይኖራቸው አልቀረም። ብቻ እየተቀባበልን እያንዳንዷን ዝርዝር ጉዳይና ያለፍነውን ፈተና ገለጽንላቸው። እሳቸውም በሚገርም ትዕግስትና ጽሞና አደመጡን።

“እናንተን መሰል ለመገዛት ፍቃደኛ ያልሆኑ ‹መብቴን› ባይ ወጣቶች ማየት ተስፋ የሚያለመልም ነው።” አንዳሉን አስታውሳለሁ። መጪ ፈተናን አውቆ የመንፈስ ዝግጅት የማድረግን አስፈላጊነት በተመለከተም “የወክለንን ሰራተኛ መብት እናስከብራለን እስካላችሁ ድረስ መክፈል ያለባችሁ ዋጋ እንዳለ እንዳትረሱ!” የሚል ምክር የሰጡን ይመስለኛል።

. . .እንሆ ባለፈው ኦክቶበር (2014ዓ.ም.) ደግሞ በአውስትራሊያ የተለያዩ ከተሞች የምንኖር ኢትዮጵያውያን የእኚህን የኢትዮጵያ ውድ ልጅ የዕድሜ ልክ አገልግሎት የምንዘክርበትና ምስጋና የምናቀርብበት ዕድል ለማግኘት በቃን። መምጫቸው እየተቃረበ ሲመጣም በየስቴቱ የተመደብን የፕሮግራሙ አዘጋጆች ሽር ጉድ ጀመርን። በዚያን ሰሞን የወሬያችን መጀመርያ፤ የወጋችን ማሳረጊያ ፕ/ር ብቻ የሆኑ እስኪመስል ድረስ በስፋት እናነሳቸው ነበር። መጽሀፎቻቸውና በርካታ መጣጥፎቻቸው እንደ አዲስ አወያዩን። በተለያዩ ጊዜያት ያደረጓቸውን ንግግሮች ሳይቀር ስንጠቃቅስ ሰነበትን። እያንዳንዳችን እንደዕይታችን ይበልጥ ስለምንወድላቸው ነገሮች አወሳን። ትጋታቸው፣ ድፍረታቸው፣ ብስለታቸው፣ ጽናታቸው፣ የዕውቀታቸው ጥልቀት . . . ሌላም ሌላም። አንድ ቀን ግን አንድ በቅርበት የሚያውቃቸው ሰው “ከሁሉም በላይ አይለወጤነታቸው ይገርመኛል” ሲል ለየት ያለ ዕይታውን ገለጸ። “ብዙ ሰዎች በተለያዩ ዘመናት በጽሁፍም ሆነ በንግግር የሚገልጿቸውን ሀሳቦች እርስ በርስ ብታናጽሯቸው የተለያዩ ሆነው ታገኟቸዋላችሁ። መሰረታዊ ያሉትን አቋም ይቅርና ታሪክ ቀመስ ትንታኔዎች ላይ እንኳ ከዓመት ዓመት የሚለያዩ፣ አንዳንዴም ጭራሽ የሚቃረኑ ይሆኑባቸኋል። አድማጭ እያዩ፣ ወይም በውስጣቸው ያልተብላሉ ሀሳቦችን ወደ አደባባይ እያመጡ . . . ሊሆን ይችላል። ፕሮፌስር መስፍን ግን ከ30 ዓመት በፊት የገለጿቸው መሰረታዊ ኃሳቦች ዛሬ ከሚጽፏቸው ጋር ሲጣረሱ



# ጥቂት ስለ ጋሽ መስፍን

(መስፍን ገብረስላሴ - ሲድኒ)

እሁድ ኦክቶበር 26 ቀን 2014 ዓ.ም. ፦

ሲድኒ አውስትራሊያ በሚገኝ አንድ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ጥቅጥቅ ብለን ሞልተናል። ትልቅ እንግዳ እንጠብቃለን። የኢትዮጵያ አምላክ ስለዚህች አገር የዋሉትን ውለታ ይክፈልዎ ልንል። ልናመሰግን።

ሰዓቱ ደረሰ። ቸብ፤ ቸብ፤ ቸብ! . . . እልልልል . . .ቸብ፤ ቸብ፤ ቸብ! . . . እንግዳችን ከዘራቸውን ያዝ እንዳደረጉና የቀድሞ አርበኞቻችንን በሚያስታውስ ዓይነት ጸጉራቸውን እንዳጎፈሩ ወደ አዳራሹ ገቡ። ልብ ብዬ አየኋቸው። ያ ትህትና፣ ቀልደኛነትና አይበገሬነት የሚታይበት የፊት ገጽታቸው አሁንም እንዳለ ነው። ተጨማሪ ዘመን ማስቆጠሩን ከማሳበቁ በቀር።

የኢትዮጵያውያኑ አቀባበል ልባቸውን እንደነካው ፊታቸው ላይ ይነበባል። በተዘጋጀላቸው ቦታ ሲቀመጡ ሁሉ የተሰበሰበው ህዝብ በቆመበት ሆኖ በጭብጨባና በእልልታ ፍቅሩን እየገለጸ ነበር። ከአፍታ በኋላ ፕሮግራሙ ተጀመረ። የመድረክ መሪው ፕሮግራሙ የምስጋና ቢሆንም እንግዳችን የሚሉት ካለ እስቲ ዕድሉን ልስጥዎ? ሲሉ ጋበዟቸው። “ ካላችሁኝማ ትንሽ ልበላ። የፈለከውን ተብዬ የለ? . . .” ብለው ጀመሩ። እናም ቀጠሉ። “. . .የሰብአዊ መብቶች . . .” ይሄኔ ነበር እኔም በሃሳብ ፈረስ አስራ አራት ዓመታትን የኋሊት ሽምጥጨፍ ወደ ሽገር የገሰገስኩት። . . .

*እሁድ ሚያዚያ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ፦ ፒያሳ የሚገኘው የብሄራዊ ሎቶሪ አዳራሽ ከአፍ እስከ ገደፉ በተማሪ ተሞልቷል። ቸብ፤ ቸብ፤ ቸብ!. . . አዳራሹ አንዳች ደስ የሚል ልዩ መንፈሳዊ ኃይል የሰፈነበት መሰሏል። ጠንካራ ስሜትና ጉጉት በሁሉም ላይ ይነበባል። የጋለ፣ የደመቀ ነበር ‹ቸብ ቸቡ!›። በፍቅር የተጠበቁት እንግዳ፤ በአክብሮት የሚታዩት አዛውንት የነፍሳቸው ጩኸት፣ የህይወታቸው መገለጫ የሆነውን የእምነታቸውን አስተምህሮት ሊሰጡን፣ ሊወያዩን እየገቡ ነበር።*

. . . ልክ ትላንት የተፈጸመ ያህል የሆነው ሁሉ በምናቤ ቁልጭ ብሎ ይታየኝ ጀመር። ከአንደበታቸው የወጡ ቃላት፣ ሐረጎች፣ ዓርፍተ ነገሮች ሳይቀር ከአእምሮዬ ጓዳ እየተግተለተሉ ወጡ። *“. . . ሰብዓዊ መብት የተፈጥሮና የፖለቲካ መብቶችን የጠቀለለ ነው።” “. . . ሰው ሆኖ በመፈጠር የተገኙ መብቶች አሉ። የማንንም ፈቃድ የማይሹ። . . ጉልበተኞች ሲፈልጉ የሚሰጡን ሲፈልጉ የሚነፍጉን ሊሆኑ የማይገባቸው።” “. . . አሁን ስልጣን ላይ ሆነው አገር እየጎዱ ያሉት ትምህርት አቋራጮች ናቸው። አደራ እናንተ ይህን ስህተት እንዳትደግሙት።” . . . “ የመንፈስ ልዕልና” . . . “ምት ዓይነቱ የተለያየ ነው።” . . . “ ቂመኛና በቀለኛ አትሁኑ፤ እናንተንም አገርንም ይጎዳል።” . . . “ዓለም ላይ ሁላችንም እኩል የምንሆነው ሰው በመሆናችን ነው።” . . . “ተፋቀሩ፤ ተዋደዱ፤ አንድ ሁኑ፤ ተባበሩ፤ መብታችሁን ለማስከበር ጉልበት ይሆናችኋል።”* . . . ሌላም ሌላም አባባሎቻቸውና አስተምህሮቶቻቸው መጡብኝ።

እንሆ የአሻራ መጽሄት አዘጋጆች በአሁኑ እትማችን የምንዘክረው ፕ/ር መስፍን ወልደ ማርያምን ነውና ከትውስትህ እንድታካፍለን ዕድል እንስጥህ አሉኝ። ፕሮፌሰርን በአካል ያገኘኋቸው አጋጣሚዎች ብዙ ባይሆኑም ስራዎቻቸውን የሚከታተል፣ “የኔ ጀግና” ብሎ የሚመካባቸው ሰው ነኝና ጥቂት ለማለት ወደድኩ። ለዛሬ የጓደኞቻቸውን አጠራር ተውሼ ‹ጋሽ መስፍን› እያልኩ ነው የማነሳቸው።

## <u>አንድ ሰው ብዙ ነው!</u>

ጋሽ መስፍንን በአካል አግኝቶ ለመወያየት ለመጀመርያ ጊዜ ዕድል የገጠመኝ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የተማሪ አገልጋይ (ተወካይ) በነበርኩበት ወቅት ነበር። በወቅቱ (በ1990ዎቹ መጀመርያ ዓመታት ማለት ነው) ት/ቤቶቹ ባልተለመደ መልኩ በብሄር የማሰብ ፋሽን

አታገኟቸውም። . . .”አለን። በርግጥም የሚያስደምም ዕይታ ነበር። ፕ/ር በግል ውይይትም ሆነ በአደባባይ ሁሌም አንድ ናቸው።

. . . ከዛሬ 7 ወር በፊት (ኦክቶበር 24 ቀን) የሲድኒ ተራ ሆነና ከአየር ማረፊያ ተቀበልናቸው። እኔም ከ20 ዓመታት በኋላ ዳግም በአካል ላገኛቸው በቃሁ። ልዩ ስሜት ነበር የተሰማኝ። ከዕድሜ ጋር ከሚመጣ አካላዊ ድካም በቀር አሁንም ከነግርማ ሞገሳቸው ናቸው። . .እኚህ የምናከብራቸው፣ የምንሳሳላቸው የአገር ዋርካ ለአንድ ሳምንት ያህል አብረውን ቆዩ። በተለይ እኔ ከአዘጋጆቹ መሀል ቆይታቸው ምቹ እንዲሆን የመከታተሉ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ሁለት ዕድለኞች አንዱ ነበርኩና ውሎና አመሻሼ አብሯቸው ሊሆን በቃ።

ከፕሮፌሰር ጋር ማውራት ቀላል ነው። እንደቁምነገራምነታቸው ሁሉ ሳቂታ፣ ቀልድ አዋቂና ተጫዋችም ናቸው። ዘና ብለው ዘና ያደርጋሉ። አዋዝተው ያወጋሉ። የማስታወስ ችሎታቸው ዕድሜያቸውን ያስረሳል። 40 እና 50 ዓመታት ያለፈውን ገጠመኝ በ20 ዓመት ወጣት የማስታወስ አቅም ቁልጭ አድርገው ይተርኩታል። ያቺ ሌሎች ሰዎችም ዘና ብለው እንዲናገሩ የሚያስችሉባት ልዩ መላ ዛሬም አለች። ምናልባት ከንቀት የጸዱ መሆናቸውን የሚያሳብቀው ጠያቂነታቸውና ቀና ፍላጎታቸውን የሚያንጸባርቁት ዓይኖቻቸው ይሆኑ ይሆናል። ብቻ ሰዎች ከአፍታ በኋላ የጓደኛ ያህል በነጻነት ያወሯቸዋል። መረጃ የሌለው አፍ-ነጠቅ ወሬ ካልሆነ በቀር በጽሞና ነው የሚሰሙት። መስመር ያልያዘ ከሆነ ግን ጠያቂ ናቸውና በጥያቄ ያጣድፋሉ።

ፕ/ር ከሲድኒ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ጋር በዋናው የምስጋና ዝግጅት ላይ የተገናኙት ኦክቶበር 26 ቀን ነበር። አዳራሹ በመሙላቱ በርካታ ሰዎች በረንዳዎቹ ላይ ተቀምጠውና ቆመው ለመከታተል ተገደው ነበር። ዕንግዳችን ገና ወደ አዳራሹ ሲገቡ በጉጉት የተጠባበቃቸው ታዳሚ በጋለ ጭብጨባና ዕልልታ ነበር የተቀበላቸው። ፕ/ር ማይክሮፎኑን ከያዙ በኋላ ግን ሁለንተናችን ጆሮ ብቻ ሆነ። በተለመደው ብቃት አዳራሽን ተቆጣጠሩት። ታሪክ ራሱ ስጋ ለብሶ የመጣ ያህል የሁሉም ሰው ቀልብ ዕንግዳችን ላይ ሆኖ አመሸ።

. . . በሲድኒ ቆይታቸው እንዳመቺነቱ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ፕሮግራም እየተያዘላቸው ያገኟቸው ነበር። ሁሉንም የጓደኛ ያህል አቅርበው ሲያዋዩዋቸው አስተውያለሁ። ግላዊ ገጠመኞች በተነሱ ቁጥርም ከማህበራዊና አገራዊ ተጸዕኖው ጋር እያዛመዱ የሚሰጧቸው ትንታኔዎች ነበሯቸው። ለምሳሌ አንድ ቀን ስለቤተሰብ ከመጨነቅ ጋር የተገናኘ ታሪክ ሰሙና እንዲህ አሉ፦ “ስለራሱ ብቻ የሚያስብ ገና ሰው መሆን ደረጃ ላይ ያልደረሰ ነው። ስለቤተሰብ ማሰብ ሰው ከመሆን ጋር የሚመጣ ነው። ያ ስሜት ሲዳብር ለማህበረሰብ፣ ለአገር ወደማሰብ ከፍ ይላል። ይሄኔ ነው ወደ ምልዑ ሰብዕና የሚደረሰው።”

ስለተበዳይ ብዙሀን እየተሚገቱ የተጓዙት ጉዞ ረጅምና አታካች ነው። መታከት ግን ታይቶባቸው አያውቅም። የመብት ተሟጋችነታቸው በርካታ ጨካኝ ወንጀለኞችን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል። የኢሰመጉ የምርመራ ቢሮ ያረጋገጣቸውና ይፋ የወጡ ሪፖርቶች ‹የሲኦል መልዕክተኛ› የሚመስሉ ጨካኞች የፈጸሟቸውን በርካታ ግፎች ማጋለጣቸውን ልንረሳው አንችልም። እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ግን ፕ/ርን ሲያዝኑ እንጂ ሰዎችን ሲጠሉ አናያቸውም። “ጥላቻ ማለት እሳት በብብት ውስጥ ይዞ መዞር ማለት ነው። ሰው በጥላቻ ከተነዳ አስተውሎቱ የተጋረደ የስሜቱ እስረኛ ነው የሚሆነው።” የሚል ዕምነት አላቸው። ከዚህ ደግሞ ጥፋት እንጂ ውጤት ማግኘት እንደማይቻል ጠንቅቀው የተረዱ ሰው ናቸው።

ፕ/ር የዕድሜ ልክ አገልግሎት ቢሰጡም የራሴ የሚሉት መኖርያ እንኳ የሌላቸውና ጥሪት ያልቋጠሩ ሰው ናቸው። ይህ ብዙዎቻችንን ያሳስበን እንጂ እሳቸውን የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ አይመስልም። “ሰው ንዋይ ወዳድ በሆነ ቁጥር ሰውነቱን እያጣ ይሄዳል። ምቾት ሲለመድ (ያንን ለሚሟላት) ሰብዕናን ወደመሸርሸር ሊወስድ ይችላል።” የሚል ዕምነት አላቸው። ምቾትን መለመድ ድህነትን የማስረሳት አቅም



ወደ ገጽ 36 ዞሯል

ተጠናውቷቸው፤ አንድ የሚያደርጉን ድልድዮች ሁሉ እየፈራረሱ ሲሄዱ ማየት ጀምረን ነበር። ኢትዮጵያዊነትና ተማሪነት አንድ ሊያደርጉን ያልቻሉበት ክፉ ወቅት። ዩንቨርሲቲው በዚህ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ መውደቁ ይመስለኛል ወደ ጋሽ መስፍን ጋ እንድንሄድ ያነሳሳን። መጀመርያ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ጽ/ቤት ሄደን ፕሮግራም ተያዘልንና በቀጠሮው ቀን አገኘናቸው። ካዛንቺስ (ቤልየር) በሚገኘው ቢሯቸው ውስጥ ጊዜ ሰጥተው አነጋገሩን። በዩንቨርሲቲ ውስጥ የሚታየውን አሳሳቢ ስሜትና አደጋ ዘረዘርንላቸው። ጋሽ መስፍን ለመወያየት የማይከብዱና ሰው እንዲናገር የሚያደፋፍሩ በመሆናቸው በስፋት ነበር ያወያየናቸው። በዕለቱ ከመሰጡኝ ጉዳዮች አንዱ ስለአንድ ሰው ብዙነት የገለጡት ሀሳብ ነበር።

እኛ በግቢያችን (ዩኒቨርሲቲ) ስለነበረው ችግር ስንዘረዝር በተለይም ከትግራይ የመጡ ወንድም እህቶችችንን በተመለከተ አንድ ትዝብት አነሳን። የተወሰኑት ስርዓቱን በዓላማ በመደገፍ፣ አንዳንዶቹም በፍራቻ ከሌላው ተማሪ ጋር እንደማይቀራረቡና ይባስ ብለው የሚያስፈራሩና የሚያሳስሩ ሁሉ እንዳሉ ነገርናቸው። ጠቅለል አድርገን ማቅረባችን ለጋሽ መስፍን አልተዋጠላቸውም። “ከመሀላቸው አንድም ከዚያ የተለየ፣ እንደ ተማሪ የሚያስብ የለም ነው የምትሉኝ? እንደዚያ ማለታችሁ ከሆነ ያላችሁትን ለማመን እችገራለሁ” አሉን። እንደማህበራዊ ሳይንስ ተማሪነታችን ስለአብዛኛው መናገር የተለመደ በመሆኑ በጣም ጥቂት ስለሆኑት የተለዩ (exceptional) ሰዎች ማንሳቱ አላሳሰበንም ነበር። ጥያቄያቸውን ተከትሎ ግን ጠቅለል ማድረጉን ተውነው። “እኔ የማውቀው አንድ ሙሴ የሚባል ተማሪ አለ። ሌሎችም ጥቂት እሱን መሰሎች አይጠፉም ብዬ አስባለሁ” አልኳቸው። “ይሄን ነዋ የምፈልገው። አንድ በጣም ብዙ ነው። ይሄ ባይሆን ነበር ለማመን የምቸገረው” አሉኝ። በርግጥም አባባላቸው ትልቅ ትርጉም የሚሰጥ ነው። ሰዎች የፋብሪካ ውጤት አይደሉም። መገምገም ያለባቸውም እንደግለሰብ ባላቸው ሚና እንጂ በጅምላ ሊሆን አይገባም። የተለዩ ጥቂቶችን በብዙሀኑ ስም መጠቅለል ለስህተት ይዳርጋል። አንድም ብዙ ነውና።

ያን ዕለት ኢሰመጉ በችግሩ ዙርያ ምን ለማድረግ እንደሚችል ስራ አስፈጻሚው እንደሚመክርበት ገልጸው በቀጠሮ ሸኙን። ውሎ አድሮ ኢሰመጉና የተማሪው አገልጋዮች ተወያይተን በዩንቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ለማድረግ ላቀድነው ውይይት አጀንዳ ቀረጽን። ግቢ ውስጥ የመወያየቱ ዕቅድ ግን ፍቃድ በመከልከላችን አልተሳካም። በምትኩ ኢሰመጉ ወጪውን ሸፍኖ በብሄራዊ ሎቶሪ አዳራሽ ለመወያየት ተቻለ።

በጉጉትና በጋለ ስሜት ሲጠባበቅ የቆየው ተማሪ ወደ ውስጡ ጠልቆ የተመለከተበት፤ ህሊናውን የፈተሸበት ልዩ ታሪካዊ ቀን ነበር። ጋሽ መስፍን ነፍሳችንን የሚዳብሱ፣ ከአይምሯችን የሚዋሀዱ መሰረታዊ ትምህርቶች ሰጡን። ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ህጎችና ድንጋጌዎችን እያጣቀሱ አወያዩን። (በዚያ መድረክ ፕ/ር አንዳርጋቸው፣ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና ዶ/ር መኮንን ቢሻውም ነበሩ። የማስታወሻዬ ትኩረት ጋሽ መስፍን በመሆናቸው ግን በዚያው መገደቡን መርጫለሁ) “የሰው ልጅ ስለመብቱ የተረገመ ነው” ያለውን ፈላስፋ እያጣቀሱ ለመብታችን ቀናዒ እንድንሆን አነቁን። እንድንፋቀር፣ እንድንተባበር በጽኑ አሳሰቡን። . . . ያ ሙሉ ቀን የዘለቀ መድረክ እጅግ ፍሬያማ ነበር። ይህን ዕምነቴን ጋሽ መስፍንም እንደሚጋሩት ተስፋ አደርጋለሁ።

ከውይይቱ በኋላ የተማሪው መንፈስ ተቀየረ። የተነቃቃና መብቴን አትንኩ ባይ ሆነ። መንግስትንና ዩንቨርሲቲውን “መብቶቻችንን መልሱ” ስንል ሞገትን። “የነቃና ሁለገብ ሰብዕና ያለው ተማሪ መብቱን ይጠይቃል በሚል አፈና አሰፈናችሁ፣ ከፍፍል ፈጠራችሁብን። በዚህ ሁኔታ ልትቀጥሉ ግን አትችሉም!” አልናቸው። ከዚህ ሁሉ በኋላ የሆነው ሁሉ ሆነ። ከርዕሴ ላለመውጣት ስል አልገባበትም። ጋሽ መስፍን ‹አንድ ብዙ ነው› ያሉት ነገር ግን ዕውን ሆነና ከመብት ጥያቄው በኋላ መንግስት የወሰደው የሃይል እርምጃ እነ ሙሴንም ሳይምር ቀረ። ገዢዎቹም ለካ የአንድን ብዙነት ያውቁ

ወደ ገጽ 35 ዞሯል

# የዓረቡ ዓለም መቆራቆስ ቀይ ባሕርን ይሸጋገር ይሆን?

የሱፍ ያሲን

*ከገጽ 17 የዞረ*

ልውጥ" ሃገር ናት። እስራኤል ዓረብ ያለመሆኗ ጉዳይ እምብዛም አያከራክረንም። ኢራንና ቱርክ ግን ሙስሊም ሃገራት እንጂ ዓረብ ሃገራት አለመሆናቸው ብዥታ የምፈጥርብን ወገኖች አለን። በታሪክ ኢራንና ቱርክ ከዓረቦች ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ሲሯኮቱ የኖሩ ሁለት ሙስሊም ሃገራት ናቸው። ኢትዮጵያ ሃገራችንም በእነሱ አጠራር ሓበሻ በዚሁ ፍረጃ መሠረት ሌለኛዋ ""ዓጀም" ሃገር ናት። ይህ የመካከለኛው ምሥራቅን አሰላለፎችና አወጋገኖች በቅጡ ለመረዳት ቀዳሚው ትምህርት ነው። ሃገራችን ኢትዮጵያም ብትሆን የዚህ የመካከለኛው ምሥራቅ ቀጠና አካልና ተካታችነቷ የሚይዋጥልን ወገኖች በጣም ብዙ ነን። ባለፈው አርቲክል እነዚህ ዓረብ ያልሆኑ የመካከለኛው ምሥራቅ ሃገራት ከዓረብ ሃገራትና ከአሜሪካ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለመቃኘት ተሞክሯል። በተለይም ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት ማብቂያ ወዲህ። ሁለተኛው አስፈላጊ ግንዛቤ ይህ ነው፣ በእኔ እይታ። የዓረቦችና የእስራኤል ጠላትነትና ተፋጣጭነት እምብዛም አያነጋግረንም፣ አያመራምርንም። ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ ጠላትነት እንጂ መልካም ጉርብትና ከአጎራብች ዓረብ ሃገራት ጋር ኑሯት አያውቅምና። ያም ሆነ ይህ አይሁዶች ግን ከዓረቦች ጋር በዚሁ አካባቢ ኖረዋል፣ ለብዙ ሺ ዓመታት። እስራኤል እንደ አንደ የአይሁድ ሃገር የዛሬ 66 ዓመታት ከመመሥረቷ በፊት። ኢራንና ቱርክም እንደ ሙስሊም ሃገራት ከዓረቦች ጋር ሲነታረኩ ኖረዋል። እነዚህ ሃገራት ከአጎራባች ዓረብ ሃገራት ጋር ትስስርና ግንኙነት ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው በመራኮትም፣ በዘልማድ በፋሪሶችና በዑስማን ቱርኮች መካካል የነበረ ዘመን ያስቆጠረ የውዝግብ ታሪክ አላቸው። ከ1979ኙ የኢራን የአያቱላሂዎች አብዮት በኋላ እንደገና የተቀሰቀሰ ወይም ያገረሸበት መራኮት ነው ማለት ይቻል ይሆናል። የሱኒ-ሺዓ ውዝግብ መልክ እየወሰደ የመጣውም ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው። በዚህ አዲሱ ገመድ ጉተታ ወይም መቆራቆስ የተለያዩ አካባቢ ሃይሎች ይጠቀማሉ። ኢራን በአካባቢው የሺዓ የበላይ ጠባቂ ብቻ ሳትሆን ኢራቅን በቁጥጥሯ አውላለች ነው ክሱ። ሶሪያም በሕዝቡ-ኦላህ ጦርኞች አማፃኝነት ተፅእኖዋ ሥር አድረጋለች መባሉ ሌለኛው ክስ ነው። ሊባኖስንም እንዲሁ። አሁንም ይህ በሻዓ አማኞች በኩል የምታሳድረው ተፅእኖ በየመን ላይ በአንሳሩ-አላህ (ሑቲ አምፅያን) አማፃኝነት ለማደላድል እየተዘጋጀች ነው ነው ሰሞነኛው ክስ። አሁንስ አበዛችው ተብሎ "የግመሉን ወገብ የበጠሰው ገለባ" ሆኖ የተገኘው ግን ይኸው የየመን ሺዓዎችን መርዳቷ ነው። ራቅ ያሉትን እነ ፓኪስታንን የመሰሉ ዓረብ ያልሆኑ ሱኒ ሃገራትንም ጭምር ያስቆጣው ይኸው ድርጊቷ ነው ተብሏል። ከመካከለኛ ምሥራቅ ውጭ ወይም ራቅ ያሉ ሌሎች ዓረብ ያልሆኑ ሙስሊም ሃገርት በርካታ ናቸው። ከፍተኛ የሙስሊሙ አማኝ ቁጥር የሚገኙባቸውን እነ እንዶኔዢያንና የኑኬለር ባለቤት የሆነችውን ፓኪስታኒን ያካትታል። ባንጋላዳሽ፣ አፍጋኒስታንና ማሊዢያን የመሳሰሉ ሃገራትም በዚህ ፈርጅ ውስጥ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ከሞላ-ጎደል ሱኒ ናቸው - በእምነታቸው። በጥቅሉ ሲታይ ኢራን የምትመራቸው የሺዓ አማኞች ከሱኒዎች ጋር ሲነፃፀር በቁጥር በጣም ውህዳን ናቸው። በበርካታ እስታቲስቲኮች መሥረት 2.2 ቢሊዮን ከሚገመተው ሕዝበ ሙስሊም ከ15 በመቶ አይበልጡም ነው። በሙስሊሙ ትብብር ድርጅት ሥር የተጠለሉት 57 ሃገራት ናቸው።ከዚህ ውስጥ 22 ሃገሮች የዓረብ ሊግ ወይም የራቢጣ አባል ናቸው። እነዚህ ሃገራት እስከ 400 ሚሊዮን ነዋሪ አላቸው ተብሎ ይገመታል። ዓረቦቹ ከሙስሊሙ ዓለም አንድ -አምስተኛ ቢሆኑ ነው፣ በዚህ ስሌት።

ወደ የመን በምንመጣበት ጊዜ በየመን ሺዓ የሆኑት የሑቲ አማፅያንን ወይም አንሳር-ኦላህ የሚቃወሙ በርካታ ፖለቲካዊ ኃይሎች አሉ። ሕጋዊነት ተጣሰ ብለው ከሚፋለሚቸው የፕሬዝዳንት አቡዱ ራቡ ማንሱር ሃዲ ደጋፊዎች በተጨማሪ ከሙስሊም ወንድማማቾች ጋር የሚደመር አል-ኢስላሕ ፓርቲ፣ የደቡብ ዓራቢያን ባሕር ሰላጤ አል-ቃዒዳ እና የደቡቡ ንቅናቄ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። የጎሳ መሪዎችና ሚሊሺዎቻቸውም ራሳቸውን የቻሉ ፀረ ሑቲ ኃይሎች ናቸው። በደፈናው አብላጫ የሆነው የየመን ሱኒ መዝሃብ (ክፍለ እምነቱ) ተከታዮች የሑቲ አማፅያንን ሥልጣን መቆጣጠርን አይደግፉም ቢባል ከእውነት አይርቅም። በተቃራኒው ከሑቲ አማፅያን ጎን ከቀድሞ ፕሬዝዳንት ከዓሊ ዓብዳላ ሣሊሕ ትእዛዝ የሚቀበሉ ቁጥራቸው የማይናቅ የብሔራዊ መከለኪያ ሠራዊቱ አባላት አሉ።

ከላይ የተመለከትናቸው በመካከለኛ ምሥራቅ ቀጠና የሚካተቱ ዓረብ ያልሆኑ"ዓጀም" ሃገራት የራሳቸው ውጥኖች አሏቸው። ቱሩክ የራሷ እቅዶች አሏት። እሷም የራሷ አካባቢያዊ ሚናና ቦታ ፈላጊ ናት። ዓረቦች እንደሚሉት የተገረሰሰው ገናናው ዑስማናዊው አጼ-ግዛቷን ትናፍቃለች። አመቺ መግቢያ ቀዳዳ አገኘሁ ብላ የምትገመተው በሱኒ ካርድ በመጫወት ነው። ኢራኖቹም እንዲሁ የራሳቸው ትልም ነዳፊዎች ናቸው። ጊዜ ያለፈበትን የቀድሞ ገናና ታሪካቸውን ያስታውሳሉ። ሁለቱ ሃገራት የጋራ ድንበር አላቸው። ኢራን በሶሪያም በኢራቅም ተደላድላላች። በእርግጥ ቱርክ የኢራን ከልክ ያለፈ የመስፋፋት ምኞት ሊያሳስባት እንደሚችል እሙን ነው። ዓረቦች እንደሚሉት ኢራን "አብዮቷን ወደ ጎረቤት ማዘመት ከጀመረች" ወዲህ ነው መባሉን ልብ ይሏል። እስራኤልም የዓረቦችን መሬት ከመቆጣጠሯ በተጨማሪ የአዲሱ መካከለኛ ምሥራቅ ፕሮጀክት አካል መሆን ትመኛለች። የተለያዩ የሙስሊም አክራሪ እንቅስቃሴዎች የሚገፉበት ዓረቡ ዓለም ለአንድነቱና ለኢኮኖሚ እድገቱ ያቀዳቸው ውጥኖች የውሃ ሽታ ሆነው ተነኑ። ይህንን ሕልምና ማንነት ገላጭ ተደርጎ የሚወሰደው የዓረቡ ራቢጣም በ 70 ዓመቱ የፈይደው ነገር የለም። ይህን የመካከለኛ ምሥራቅ አካባቢ ሃገራትና መንግሥታት አወጋገኖች፣ አሰላለፎችና የሃይል ስሌቶች ከሥር መሠረቱ አናግቶ ካርታዎችን ጭምር የሚያስለውጥ እድገቶች በመመልከት ላይ ነን።የቱርክ መሪ ጠይብ ረጀብ ኦርዱኻን ዛሬ ወደ ኢራን ዋና ከተማ ቴህራን የተጓዙ ናቸው። ሊያስታርቁ ወይስ ሊያስጠነቅቁ? የታወቀ ነገር የለም። የመካካለኛ ምሥራቅ ምስቅልቅል የእነዚህ ሁሉ ውጥኖችና ተለዋዋጭ አሰላለፎች ተቃርኖ ነው ቢባል እምብዛም ማጋነን የለበትም። ውስብስብ ያለውን ሁኔታ አለቅጥ አቃለልክ እንዳትሉኝ እንጂ።

ሃገራችን ኢትዮጵያ በመካከለኛ ምሥራቅ ተካታች አራተኛዋ ዓረብ ያልሆነች ሃገር ናት ብለናል። "ሙስሊምም" ያልሆነች ብቻ ሳትሆን በረዥም ታሪኳ "ክርስትያን" የሚለው ታፔላ የነበራት ሃገር ናት። እነዚያ ሦስቱ ከላይ የተጠቀሱት እስራኤል፣ ቱርክና ኢራን ከነበራቸውም ሆነ ካላቸው ማዕከላዊ ሚናም ሆነ አተረማማሽ ፕሮዥክቶች ባለቤት ያልሆነች ሕዳግ ሃገር ናት የሚለውን መጨመሩም አይከፋም። በጆግራፊያዊ አቀማመጥም ቢሆን በቀጠናው ጠረዝ ላይ ጉብ ያለች "ባይተዋር" ሃገር ናት ቢባል ማጋነን የለበትም። የሶሪያን ምስቅልቅል ብንወስድ እነዚህ ሦስት ሃገራት ያላቸው አሉታዊም ሆነ

አዎንታዊ ሚናም ሆነ አበርክቶ ኢትዮጵያ ሊኖራት መቼም አይችልም። "አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው" ያለው የትኛው አንጎራጓሪ ነበር?። ያም ሆነ ይህ እሷ እቅድ ባይኖራትም ሌሎች ስለ እሷ እቅድ ከነደፉ አልሸሹም ዞር አሉ ነውና መሻሻ የለም። አለችበት።አለንበት! በአዲሱ The Islamic State of Iraq & Syria -ISIS or Da'ish ኢትዮጵያ አርዳል አል-ሐበሻ ተብላ ከሌሎቹ በርካታ ሃገራት ባንድ ላይ ተከልላ የአይሲል የካሊፌት መንግሥት አካል (ወላያ?) ሆናለች። አትደንግጡ! በካርታ ላይ ነው። ውጥኑ ወያኔ/ኢሕአዴግ እንደሚያስፈራራው አንገብጋቢ የስጋት ምንጭ መቼም ሊሆን አይችልም። ግን አይመለከተንም ብሎ መዘባነንም ተገቢ አይሆንም። የምዕራብ አፍሪካው "ቦኮ ሐራም " በአይሲስ ሥር መደራጀቱን ይፋ አድርጓል። የሶማሊያው አል-ሸባብም ከአልቃዒዳ ጋር ያለውን ቁርኝት ይፋ ካደረገ ቆይቷል። እነዚህ አክራሪ ሙስሊማዊ ድርጅቶች ወደ አፍሪካ እየዘለቁ ናቸው። እነዚህ አክራሪዎች በአፍሪካ -በቀል ተቀፅላዎቻቸው አማኻኝነት ከዓረቡና ከመካከለኛ ዓለም ዘልቀው ሃገራትን የማሸበር ብቃት አላቸው ማለት ነው። ኢትዮጵያንም በራሷ ሃገር-በቀል፣ ሁሉንም ካሂድ የሚያሰኝ (ተከፊሪ) ድርጀት ሊያተረማምሷት ማቀዳቸው የማይታሰብ ከቶ ሊሆን አይችልም። በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ለውጥ መታፈኑ ለዚህ ተጨማሪ አመቺ ሁኔታና መግቢያ ቀዳዳ እንደሚፈጥርላቸው እሙን ነው።

በአሰባሳቢ ማንነት መጽሓፌ ውስጥም የሱኒ-ሺዓ መስመር በ1979ኙ የኢራኑ ሻህን ከሥልጣን ያሽቀነጠረው የአያቱላሆች አብዮት ፍንዳታ ወቅት ላይ የሁላችን ቀዳሚ ጥያቄ "የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሺዓ ናቸው ወይስ ሱኒ " የሚለው ነበር ማለቴ ትዝ ይለኛል። ያን ጊዜ ጥያቄው የሁላችን ነበር። ምክንያቱም ሱኒ -ሺዓ ተብሎ መወዛገቡ ለሁላችን እንግዳ ደራሽ ክስተት ነበረና። ዛሬ ሙስሊሙን ዓለም በሁለት ጎራ ክፍሎ እያናቆረ፣ እያቀራቆሰና እያተረማመሰ ነው የተባለው የሱኑ-ሺዓ ክፍፍል እንኳን ለእኛ ለቀጠናው እንግዳ ነበረና። በሌላ በኩል ይህ ከእስልምና ጅማሮ አንስቶ የነበረ ክፍፍል ወይም ከፋፋይ መስመር ነው። በተለያዩ የታሪክ ምዕራፎች እያገረሸበት የውዝግብ መነሾ ሲሆን ደግመን ደጋግመን በታሪክ ተመልክተናል። በየመን የነበረው ሁኔታ ግን ፈፅሞ የተለየ ነበር ማለት ያስደፍራል። ዙዩድ (ግለሰቡ ዘዲ ይሰኛል) የተባሉት የየመን ሺዓዎች ወይም የዛሬው "የሑቲ አማፅያን" (ራሳቸውን አንሳር-ኡላህ ብለው ይጠራሉ) ከማኛውም ሺዓ አማኝ ለሱኒው አማኝ ቅርበት ያሏቸው ናቸው። በረዥሙ የየመን ታሪክ ይህንን ልዩነት እንደ አንድ የመዝሓብ (ክፍለ እምነት) አግላይ መስመር የተመለከተ ሰው አልነበረም ቢባል ምንም ማጋነን የለበትም። የመንን ለ 32 ዓመታት አንቀጥቅጦ የገዛው ዓሊ አብዳላ ሣሊሕ በእምነቱ ዘዲ ወይም ሺዓ እንጂ ሱኒ እንዳልነበረ የሚያውቅ ስንቱ የየመን ዜጋ ነው?። ዛሬ ከሰሜን የመን ጫፍ ከሣዕዳ ከገሰገሱት ሑቲ አማፅያን ጋር ሆኖ የቀድሞ ሠራዊቱን ከጎናቸው ማሰለፉ ግራ-አጋቢ ነው። ወያኔ አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ወቅት ላይ " እገሌ እኮ ትግሬ ሆኖ ተገኘ" መባል እንደተጀመረው አይነት አስተዛዛቢ ድንገት ደራሽ ክስተት ነበር። እንደ አሁኑ አለያይ ችካል ሆኖ ጎራ አስልይቶ ያገዳደለበት አብነት የለም ቢባልም ማጋነን አይሆንም። ዓሊ ዓብዳላ ሣሊሕ ዋና የሥልጣን ማቆያ ካርዱና ኮርቻው የጎሳ ካርድ እንጂ የመዝሓብ (የእምነት ክፍሉ) ካርድ ስላልነበረ ነው። ብዙ ዝርዝር ውስጥ ገብተን እንዳንቀር ፈርቼ ነው እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የጎሳ አባልነት እንጂ የክፍለ-እምነቱ አባልነት ተፅእኖ ፈጣሪም ታሳቢም አልነበረም፣ በሃገሪቷ ፖለቲካ። የዓሊ ዓብዳላ ሣሊሕ የሥልጣን መደላድል መሠረቱ ከእነ ሼኽ አል-አሕመር ቤተሰብ ጋር በሓሺድ ጎሳ በኩል የነበረው የጠበቀ ትስስርና አለኝታነት እንጂ በመዝሓብ አልነበረም። እስከዚያ ድረስ ሣዑዲ ዓረቢያ በየመን የምታሳድረው ጫና የሚተላለፈው በእነዚህ ጎሳ መሪዎችና በእነሱ አመኻኝነት በሚፈሰው ገንዘብ ነበር እንጂ እምነት-ተኮር ታጣቂ ማሊሺያ ኃይል ላይ በመተማመን ከቶ አልነበረም።

በዚህ አካባቢ ውዝግቦች መልካቸውን እየለወጡ፣ አሰላለፎችና አወጋገኖችን ከሥር መሠርቱ ያናጉ ናቸው ብለናል። አዳዲስ አሰላለፎችን እየተመለከትን ነን። የዛሬ 8 ወር አካባቢ የመካከለኛ ምሥራቅ ሃገሮችንና የቀጣናው ነባር አሰላለፎችና አወጋገኖችን ከየት መጣ ሳይባል ባንዴት ጀንበር ከሥር መሠርቱ አናግቶ ሁሉም ኃይሎች ስሌቱን እንዲከልሱ ያስገደደው አይሲስ (ISIS or Da'ish) የሃገሮች ነባረ ድንበሮችን አፋልሶ አካባቢውን አንድ ዓውደ ውጊያ አድርጎት አረፈው። በእነ ጃማል ዓብዱል ናስር ዘመን የነበረው ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ብሔረተኛ ጎራን በሱኒ-ሺዓ እምነት ተኮር ክፍፍልና አወጋገን ተካውና አመሰቃቀለው። የሰሞኑ የየመን ጦርነት ደግሞ እነዚህን ሁለት ጎራዎችን ነው ያፋጠጠው። የዓረብ ሃገሮችን አንድ የማድረግ ውጥን ሆኖ የተነሳሳው የጃማል ዓብዱል ናስር ዓረብ ብሔረተኛ እንቅስቃሴ አቅጣጫ ፀረ ኢምፔሪሊዝምና ፀረ ዘውድ አገዛዞች በመሆኑ፣ የመን ላይ ከ1962 እስከ 1967ዓ.ም. የተፋለመው ከሣዑዲ ንጉሥና አድሓሪ ልዑላን ጋር ነበረ። ዛሬ ግብፅ የሣዑዲ አሚሮች ተላላኪ ናት። ውዝግቡ መልኩን ቀየረ፣ የውጊያው መስመሩም ተለወጠ።

ባንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ ዓረቦች ለ400 ዓመታት በእስልምና ስም አንቀጥቅጠው ከገዟቸው ቱርኮች ነፃነት ለመቀዳጀት ነፃ እናወጣችኋን ካሏቸው ከፈረንጅ ቅኝ ገዢ ኃይሎች ጋር ተባባረው አሽቀነጠሯቸው። ነፃ መንግሥታት ቢመሠረቱም አንድነታቸውን አላረጋገጡም፣ እስከ ዛሬ። ቅኝ ገዢዎቹ የገቡላቸውን ቃል ባለመፈፀም ከዷቸው። በተፃራሪው ቱርኮቹ እስከ ዛሬ ዓረቦችን ክህደታቸውን ይቅር አላሏቸውም። ይህ ቁጥርጥሮችን ሁሉ ቁጥርጥር ያደረገ ቁጥርጥር ነው ማለት ያስኬዳል። የተቀጣጠለው የዓረብ ዓለሙ መነሳሳት እስራኤልን እንዳትቋቋም ማድረግና ታናናሽ መንግሥታት ባንድ ላይ አዋህዶ የዓረብ ብሔርን (ሃገራትን) አንድ የማድረግ መዳረሻ ግብ ነበረው። ይህ ውጥን አልተሳካም ብቻ ሳይሆን በእንጭጩ ተቀጨ። ወደ ታሪክ ዳራ ብንመለስ ከዚህ በፊት እንዳልነው ቱርክና ኢራን በዚህ ቀጠና ያሉ ሁለት ዓረብ ሳይሆኑ ሙስሊም የሆኑ ወሳኝነት ያላቸው ሃገራት ናቸው። ዓረቦች በእስልምና ሽፋን ሊያሳድሩባቸው ለአቀዱት ባሕላዊ ተፅእኖ አልተንበረከኩላቸውም። ይህም ሌለኛው ቁጥርጥር ነው። ከዓረቦች ብቻ ሳይሆን ቱርኪና ፋሪስ (ኢራን) እርስ በርሳቸው የተፋለሙበት ረዥም የታሪክ ምዕራፎች በመኖራቸው ጉርብትና እንጂ ፍቅር በመሃላቸው የኖረበት ዘመን ኢምንት ነው። ዓረቦቹም የሁለቱ ዓረብ ያልሆኑት የኢራንና ቱርክ መሪነት አልተዋጠላቸውም። ከ1980 እስከ 1988 ዓ.ም. ድረስ የዘለቀው ደም-አፋሳሽ የኢራቅና የኢራን ጦርነት ለዚህ ዓይነተኛ አብነት ነው። በኋላ ላይ ከአሜሪካኖች ጋር ወግነው የዘመቱበት የገልፍ ዓረብ አሚሮች ያን ጊዜ ሣዳም ሁሴንን የደገፉት ታሪካዊ ጠላት አድርገው የሚመለከቷቸውን ፋሪሶችን እንዲከላከልላቸው ነበር። ያን ጊዜ እንደ አሁኑ የሱኒ-ሺዓ መራኮት እቅድ ሆኖ አልታየም እንጂ።

ምንም እንኳን የሺዓ-ሱኒ ልዩነትና ክፍፍል ከ1973ዓ.ም. በፊት የነበረ መሿኮት ቢሆንም ሣዑዲ ዓረቢያና የእሷ ተቀጽላ ገልፍ ሃገሮች የዓረቡ ዓለም አመራር

ወደ ገጽ 37 ዞሯል

# አደጋን ንቀው ፣ ሞትን ለሚተናነቁ ዜጎቻችን መሰደድ የአገዛዙ ሚና

ከዳንኤል ድርሻ (ናይሮቢ)

አብዱርህማን ከማል ጥርሱን የነቀለው፣ አፈር ፈጭቶ ጭቃ አብኩቶ የልጅነት ዕድሜውን ያሳለፈው፣ የኮሌጅ ትምህርቱን አጠናቅቆ ሥራ የጀመረው . . . ጨርቆስ ‹ድድ ማስጫ› አካባቢ በሚገኘው የወላጆቹ አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ነው። ከጨርቆስ በቅርብ ርቀት፣ ከገነት ሆቴል ወረድ ብሎ በሚገኘው ፖፖላሬ የግል ጋራዥ ውስጥ በሌሊት የጥበቃ ስራ የተሰማሩት አዛውንት ወላጅ አባቱ ጋሽ ከማል ከ700 ብር በማይዘል የወር ደሞዛቸው (በጡረታ የሚያገኟትን ስም አይጠሬ ብር ጨምረውባት) ስድስት ቤተሰብ ያስተዳደሩበት ‹ተዓምር› ሁሌም እንደገረመው ኖሯል። ከንግድ ስራ ኮሌጅ (ኮሜርስ) ከተመረቀ በኋላ በጓደኞቹ አማካኝነት በጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅት ውስጥ በተቀጠረ የመጀመሪያው ሳምንት ሀሳቡ፣ ህልሙ፣ ዕቅዱ . . . ብዙ እንደነበር አይዘነጋውም።

ቤተሰቡን በወር ወጪ መደገፍ ፣ ብርድና ቁር የሚፈራረቅባቸው አዛውንት አባቱን ማሳረፍ፣ ከደምወዙ ሸርፎ ሥራ ላልጀመሩ ጓደኞቹ የኪስ ገንዘብ መቁረጥ፣ ሁለት ልጆቻቸው በሞት ተለይተዋቸው የሰቀቀን ኑሮ የሚኖሩት ጎረቤታቸውን እማማ አልታዬን መደጎም . . . ብዙ . . . ብዙ ኃሳቦችና ዕቅዶች ነበሩት። ደሞዝ ደርሶ የቱን ከየቱ እንደሚያደርገው ግራ እስኪገባው ድረስ።

አዛውንት አባቱን ከስራ ሳያሳርፍ፣ በምረቃው ዕለት አይገቡ ገብተው ‹ሰርፕራይዝ› ድግስ አዘጋጅተው ያስደነቁትን ጓደኞቹን የኪስ ወጪ ሳይሸፍን፣ ለእማማ ልታዬም ከሁለቴ በላይ ‹የቡና ማፍያ› ሳይደጉም . . . በድንገት ከስራው መባረሩ ተስፋውን ይበልጥ አጨለመበት። ከወራት የስራ ፈትነት የመንከራተት ህይወት በኋላ በገዢው ፓርቲ ይዞታ ስር በሚገኘው ‹የዜና አገልግሎት ተቋም› በትርጉም ክፍል ተቀጥሮ ‹ደህና› የሚባል ደሞዝ ማግኘት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም የመስሪያ ቤቱን ቢሮክራሲ ተቋቁሞ ለማለፍ ግን በእጅጉ ተቸገረ። ‹በቡህ ላይ ቆረቆር› እንዲሉ ፈጽሞ በማያምንበት የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ገብቶ እንዲንቀሳቀስ የሚደረግበት ጫና ህሊናውን አስጨነቃት። በዚህም የፓርቲ አባልነት እንዲሞላ የቀረበለትን ‹ፈተና› ማለፍ ሳይችል ቀረ። አገዛዙን ካዋቀሩት አንዱ የሆነውና አብዱራህማን የጉራጌ ተወላጅ መሆኑን ያረጋገጠው የመስርያ ቤቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን) ከንፍ ፎርም ሞልቶ መታወቂያ እንዲወስድ ያቀረበለት ጥያቄና ቀነ ገደብ ከተጠናቀቀ ከቀናት በኋላ በየሰበቡ ማስጠንቀቂያ ይሰጠው ጀመር። በስራው ላይ አንዳች እንከን ሳይገኝበት ‹የፓርቲ አባልነትን አልቀበል› በማለቱ ብቻ መጉላላቱ የበረታበት አብዱ ከስራ ቦታው መቅረት ጀመረ። በወጣቱ ‹ግትር አቋም› የተበሳጩት የአገዛዙ ሹማምንት አለቃዎቹም በአብዲ ላይ የበቀል በትር የሚያሳርፉበት ‹ጥሩ ምክንያት› በማግኘታቸው ‹ላልተወሰነ ጊዜ ያለደሞዝ ዕረፍት እንዲያደርግ› ውሳኔ አሳለፉ። ከስራ መባረሩ የገባው አብድራህማን በተደጋጋሚ መልቀቂያ እንዲሰጡት ቢጠይቅም "ያንተ ሁኔታ እየተጠና ነው ፤ ከስራ ስላልተባረርክ መልቀቂያ ልንሰጥህ አንችልም" በሚል ‹ከስቃዩ ተምሮ ወደነሡ እንዲመለስ› ‹አየር ላይ› አስቀሩት። ይሄኔ ነበር በአገሩ ባይተዋር፣ ሁለተኛ ዜጋ እንዲሆን የተፈረደበት ወጣት ልቡ የሸፈተውና የስደትን ጎዳና ማማተር የጀመረው።

ገንዘብ ባለ ወቅት ተካፍሎ መብላትን ፣ መተጋገዝን፣ በችግርና በደስታ መረዳዳትን፣ በእንግልትና በመከራ ተደጋግፎ መኖርን በሚያውቀው ማህበረሰብ ውስጥ እንደመኖሩ ችግርን ተቋቁሞ መኖሩ አልገደደውም። ሆኖም ግን የወደፊት ተስፋው በገዢው ፓርቲ ካድሬዎች መነጠቁ ከሀገሩ ተነቅሎ የመውጣት ውሳኔ ላይ እንዲደርስ አደረገው።

❋ ❋ ❋

አብድራህማን የጨርቆስ ልጆች ህይወት አንድ ህያው ምስክር ነው። ይህ ሰው የጨርቆስ ብቻ ሳይሆን የአዲስ አበባ፣ ብሎም የኢትዮጵያ ወጣቶች የጨለመ ተስፋ አንድ ማሳያ ነው። አብድራህማን በስራ አጥነት ብቻ ሳይሆን በስራ መነፈግ ለእንክርት የተዳረጉ የኢትዮጵያ ወጣቶች አንድ መልክ ነው። ዜጎች የሚወዷት አገራቸውን ለቅቀው፣ ከአውሬና ከጀልባ አደጋ ጋር እየተጋፈጡ የሡሃራ በረሀንና የሜዲትራንያን ባህርን የጉዞ ሰቆቃ ለመጋፈጥ ለምን እንደሚገደዱ ከሚያሳዩ ምክንያቶች መሀል የዚህ ወጣት ውሳኔ በናሙናነት መጠቀስ የሚችል ነው። አውሮፓን አልመው የሡሀራ በረሃ የበላቸው፣ የሜዲትራኒያን ጨዋማ ባህር የዋጣቸው ኢትዮጵያውያን ማንነት አንዱ አስረጅ ነው። ሊቢያ ውስጥ ኢትዮጵያውያን የመሰየፋቸውን መሪር ዜና እየሰሙ ሳይቀር ወደዚያው መጓዙን ብቸኛ አማራጫቸው ያደረጉ ወገኖቻችን የአብድራህማንን ታሪክ ባንዱም ሆነ በሌላ መልኩ የሚጋሩ ናቸው።

ሀገሪቷን በጠመንጃ ኃይል የሚገዛው መንግስት ዜጎች በሚያስደነግጥ ቁጥር ለስደት የሚዳረጉት ስርዓቱ በፈጠረባቸው አስጨናቂ ተጽዕኖ ሳቢያ መሆኑን አለባብሶ "የችግሩ ፈጣሪዎች ደላላዎች ናቸው" በሚል ፕሮፖጋንዳ ላይ የተጠመደው ዕውነቱ ጠፍቶት እንዳልሆነ መረዳት አይገድም። የዜጎች ፍትህና መሰረታዊ ነጻነቶችን ማጣትና ሰርቶ መብላት እንኳ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ መማቀቅ የስደቱ ዓይነታ ምክንያት መሆኑን መቀበል አይፈልግም። ለዚህ ብሄራዊ ውርደት ኃላፊነቱን ለመውሰድ ያልደፈረውም አገዛዙ ከስልጣን መንበሩ ባሻገር ለዜጎች ሰቆቃ ደንታ ቢስ በመሆኑ ብቻ ነው። ብዙ አገራት ዜጎቻቸው ቢሰደዱባቸውም የኢትዮጵያውያኑ ግን ፍጹም የተለየ ሆኗል። በኢኮኖሚ አቅማቸው ከኛ ወዳልተሻሉ አገራት ሳይቀር የመሰደዳችን ምስጢሩ መንግስት አሳዳጅ ሆኖ በመገኘቱ ጭምር ነው። የስራ አጥነቱ ችግር ወጣቱን በገፍ የሚያሰድደው ዜጎች ባላቸው አቅም መስራት የሚችሉባት አገር ስላልተፈጠረችልን ነው። የካድሬዎቹን፣ የፖሊስና የደህንነቱን አፈና ተቋቁመን ለመስራት ብንታገልም . . . ጥረታችን ከንቱ ሆኖ አገራችንን ለመልቀቅ የተገደድነው በአመለካከታችሁ የተለያችሁ በመሆናችሁ መኖርያችሁ እስር ቤት ነው ብሎ በወሰነብን የኢህአዴግ አገዛዝ ጭፍን እርምጃ ነው። "ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ልዩነትን ማስተናገድ አትችልም፣ የሚያደመጠውም የአንድ ፓርቲ ድምጽ ብቻ ነው" በሚል ‹መርህ› የሚተዳደረው መንግስት ጡጫው በመክፋቱ ነው ሀገራችንን ለቀን ለመሰደድ የተገደድነው።

በጦርነት በታመሰችው የመን፣ በመንግስት አልባዋ ሱማሊያ፣ በአፍሪካውያን ጥላቻ በተሞሉ ዜጎቿ በምትናጠው ደቡብ አፍሪካ፣ ማዕከላዊ መንግስቷ ሊቆጣጠረው ባልቻለው ግዛቷ አሸባሪዎች በሚፈነጩባት ሊቢያ . . . ወዘተ የሚሰማው ሥቃይ የሚያቃጥል የሚያንገበግበኝ እንደ አብድራህማን እና ጓደኞቹ የጨርቆስ ልጅ

ስለሆንኩ ብቻ አይደለም። እነ ኢያሱ ይኩኑ አምላክ እና ባልቻ በለጠ ወዘተ እኔ የኖርኩበት ሠፈር ልጅ በመሆናቸው በውስጤ በፈጠርኩት የቀረቤታ ስሜትም አይደለም። በአገዛዙ ተገፍቼ ከአገሬ የወጣሁ ‹ትኩስ› ስደተኛ በመሆኔ ብቻም ከቶ አይደለም። ወንድሞቼንና እህቶቼን ለስደት የሚዳርገው ገፊ ምክንያት እየተባባሰና እየከፋ እንጂ እየተለወጠ ሲሄድ ባለማየቴ እንደሚከፋ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባደረብኝ የሀዘንና የመከፋት ስሜት እንጂ። ይህም ብቻ አይደለም። ‹ስልጣን ወይም ሞት› ብሎ ሀያ አራት ዓመታት ያህል በምኒሊክ ቤተ መንግስት የመሸገው ቡድን ለተጎዱ ዜጎቻችን ጋሻና መከታ መሆኑ ቢቀርብን እንኳ ለአፍ ያህልም ቢሆን ‹አለሁላችሁ› ለማለት ያለመፍቀዱም ያንገበግባል።

❋ ❋ ❋

እንደማላዊና ዚምባብዌ ያሉ መንግስታት ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ዜጎቻቸው ለደረሰባቸው ጥቃት በአፋጣኝ ቁጣቸውን ሲገልጹ፣ የአዲስ አበባው መንግስት በሊቢያ የተሰዉ ዜጎቻችን ‹ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን እናጣራለን› የሚል ‹ብሽሽቅ› ውስጥ መግባቱ እንደ አንድ ዜጋ ቆሽት የሚያደብን ነው። ህዝቡ በማህበራዊ ሚዲያዎችና በሌሎቹ መድረኮች ተቃውሞውን አጠናክሮ ባያሰማ ኖሮ ‹የእነ ቴዎድሮስ አድሀኖም መንግስት የሚች ዜጎቻችንን የሀዘን መግለጫ ያሰማ ነበር ወይ?› የሚለው በእጅጉ የሚያጠራጥር ነው። ዜጎችን መታደግ ሳይሆን ከሀገር ማሰደዱን ሥራዬ ብሎ የተያያዘው መንግስት ችግሩን ከራሱ ለማራቅ "ደላሎች" ላይ ጫጫታ እንዲበረክት ማድረጉም፣ ጉዳዩን ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ እንጂ መቼም ቢሆን ለመቅረፍ ተነሳሽነት እንደሌለው የሚያረጋግጥ ነው። ለዓመታት በደቡብ አፍሪካዊያን ‹ዜኖፎቢያ› ጥቃት ሲጣልባቸው የኖሩ ዜጎቻችን እንባ ቅንጣት የሀዘን ስሜት ያልፈጠረባቸው ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ይህንን ለቁጣ የሚያስነሳ ድርጊት "ችግሩ ጊዜያዊ ነው" ብለው በአደባባይ መደስኮራቸው፣ የመንግስት ቃል አቀባዩ ሬድዋን ሁሴን በሊቢያ የደረሰውን ግድያ አስከትሎ "ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን እናጣራለን" ማለታቸው፣ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም በዚህ ዙርያ የተጋጋለው የህዝብ ቁጣ ላይ ዉሃ ለመቸለስ "መንግስታችን በስደተኛ ኢትዮጵያውያን ላይ ለተወሰደው ጥቃት ተመጣጣኝ እርምጃ ይወስዳል" ያሉትን ቃል አጥፈው "ዋንኛ ተጠያቂዎች ደላላዎች ናቸው" የሚል ዜማ መቀየራቸው . . . ኢትዮጵያውያን ሀገር እንጂ ተቆርቋሪ መንግስት የሌላቸው መሆኑን ማሳያ አብነቶች ናቸው።

❋ ❋ ❋

ደላላዎች የስደት አቀጣጣይ አካላት እንጂ የስደት ዋና ምክንያቶች አለመሆናቸው ግልጽ ነው። ለዜጎቻችን ስደት የተለያዩ ሠበቦች ቢደረደሩም አገር ጥሎ ለመውጣት ዋና ምክንያታቸው ግን የዕለት ተዕለት ኑሮን መግፋት በመቸገራቸውና  የተስፋ ማጣት ጭለማ ስለዋጣቸው ነው። ለዚህ ተስፋ ቢስነትና ስጋት የዳረጋቸውና ምትክ የሌላት አገራቸውን ወደኋላ ሳይመለከቱ እንዲሰደዱ በማድረጉ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ደግሞ ከስርዓቱ ውጪ ማንም ሊሆን አይችልም። ለውስጣዊ ችግሮች ውጫዊ ጠላት በመፈለግ የሚታወቀው ኢህአዲግ ዋና ተጠያቂነትን ከራሱ ወደ ደላሎች ለማዞር የሚውተረተረውም ህዝቡን አደንዝዞ ለመግዛት ካለው መርህ መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

ለስደት ዓይነተኛ መንስዔዎች ተደርገው የሚጠቀሱ ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች አሉ። ገፊ (Pushing Factors) እና ሳቢ (Pulling Factors) ምክንያቶች በመባል ይታወቃሉ። ‹ገፊ ምክንያቶች› የምንለው ዜጎች በአገራቸው ሠርተው መኖር፣ በነጻነት መንቀሳቀስ፣ ከግፍና ሰቆቃ መላቀቅ . . . ያለመቻላቸውን አምነው አማራጭ በማጣት ህይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ ከቀያቸው እንዲሰደዱ የሚገደዱበትን ከቁጥጥራቸው ወጪ የሆነውን ሁኔታ ነው። ‹ሳቢ ምክንያቶች› የሚባሉት ደግሞ በሌላ ሀገር ሊገኝ ይችላል ተብሎ በሚታሰብ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ገቢና ምቹ ህይወት . . . ተማርከው ወደ ሁለተኛ አገር ፈቅደው መጓዝ የሚመርጡበት ነው። በኢትዮጵያ ያለውን ዕውነታ ስንመለከት ዜጎች ባብዛኛው ለስደት የሚጋለጡት በገፊ ምክንያቶች ሳቢያ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው። ለዚህ ደግሞ የገዢው ፓርቲ ሹማምንቶችና የፕሮፖጋንዳ ወፍጮ ማሽኖቻቸው ያለማቋረጥ እንደሚለፍፉት የስደቱ ዋና ተዋንያን፣ መሪና አስተባባሪዎች ‹ደላላዎች› አይደሉም። ባስገዳጅ ሁኔታዎች ራስን ለማዳን ወይም መኖር ለመቻል ሲባል የሚደረጉት የስደት ጉዞዎች በደላላም ሆነ ያለደላላ የሚተገበሩ መሆናቸው በአገዛዙ የሚሰጡ ሰበቦች ውሀ የማይቋጥሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

የገጠር ነዋሪዎች ከብቶቻቸውን እየሸጡ፣ ከተሜዎችም ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩባትን ማናቸውንም ዓይነት ጥሪት እያራገፉ ለስደት የሚዳረጉት በካድሬዎች እንደሚለፈፈው በሀገሪቱ ውስጥ ሰርቶ መለወጥ የሚቻልበት የስራ ምቹ ሁኔታ ስለተስፋፋ አይደለም። የተሻለ የኢኮኖሚ አቅም የነበራቸው ዜጎችም ቢሆኑ በገፍ ለስደት የሚዳረጉት ባብዛኛው ‹ገፊ› በተሰኙት ፋክተሮች ነው። የመኖር ዋስትና ፍለጋ።

ሌላው በተለይም በከፍተኛ ሙያተኞች አካባቢ የሚታየው የስደት መንሴዔ ደግሞ አገሪቷ ተመጣጣኝ የኑሮ ዋስትና መስጠት ያለመቻሏ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በርካታ የሀገራችን ዶክተሮችና ሌሎች የህክምና ባለሙያዎች ወደ አሜሪካና አውሮፓ ብቻ ሳይሆን ወደ ኬንያና ኡጋንዳ ሳይቀር የሚሰደዱት ስራቸውን የሚመጥን ገቢ ባለማግኘታቸው ጭምር መሆኑም ይነገራል። በምዕራብ አፍሪካ የኢቦላ ቫይረስ ትልቅ ስጋት በፈጠረ ሰሞን ወደ ሴራሊዮንና ላይቤሪያ ከዘመቱ ዶክተሮች ውስጥ "በአገሬ የማገኘው ደሞዝ ጫማ እንኳን ሊያስቀይረኝ ባለመቻሉ ከኢቦላ ቫይረስ ጋር ተጋፍጬ በማገኘው አበል ለቤተሰቤ ህይወት ዋስትና የሚያስገኝ ንግድ ቢጤ እጀምራለሁ፤ ካልተሳካም ኢቦላ ይወስደኛል።" ያሉ መኖራቸውን ማስታወሱ የሚገልጸው ቁምነገር ይኖረዋል። የኢቦላ ዘማች ዶክተሮች በጤና ጥበቃ የተመረጡት ለገዢው ፓርቲ ባላቸው ታማኝነት መሆኑ ሳይዘነጋ።

❋ ❋ ❋

ኢትዮጵያ የስደተኞች አምራች ትልቅ ፋብሪካ እየመሰለች መጥታለች። ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ሳቢያ የሚደርስባቸውን ተጽዕኖ መቋቋም እየተሳናቸው ይሰደዳሉ። በግፍ ከመኖሪያቸው እየተፈናቀሉ፣ ከስራቸው እየተባረሩና መድረሻ እያጡ ድንበር የሚያቋርጡ ብዙ ናቸው። ምናምኒት የሌለውም ሆነ የኢኮኖሚ አቅሙ በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኘው ሳይቀር መሰረታዊ መብቶቹ ባለመከበራቸውና የመኖር ዋስትና በማጣቱ ስደትን እንደብቸኛ አማራጩ ለማየት ሲገደድ ይታያል። ባኳያው ደግሞ ለዚህ ፍልሰት ዋንኝ ተጠያቂ የሆነው የስርዓቱ አጋፋሪዎች ሳይቀሩ ስደትን የመጨረሻው ተስፋቸው ያደረጉ ይመስላሉ። ገዢው ፓርቲ ተራ ዜጎችን ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ሹማምንቱን ሳይቀር በገፍ ለስደት ያበቃ መሆኑ ይታወቃል። ከከፍተኛ ባለስልጣናቱ መሀል የአሜሪካና አውሮፓ ሀገራትን ዜግነት ይዘው

ወደ ገጽ 41 ዞሯል

# አይ ኤስ ማነው? ኢራኖች እንደሚሉት አይ ኤስ እውን የአሜሪካ ስሪት "ሜድ ኢን አሜሪካ" ነውን?

እዮብ ሳህሌ

ባለፈው ኤፕሪል ወር 28 ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሊቢያ ውስጥ በዘግናኝ ሁኔታ መገደላቸው የሁላችንንም ቅስም የሰበረ መሪር ሀዘን ነው። ይህ የኃይማኖት ካባ ለብሶ የሰይጣን ስራ የሚሰራው የሽብር ቡድን ‹እስላማዊ መንግስት› በሚል ለራሱ በሰጠው ስም ነው የሚታወቀው። ዋና መሰረቱ ኢራቅ ሆኖ በተለይም በሶርያ የተስፋፋውና የዓለማችን ሀብታም የሽብር ቡድን ለመባል የበቃው አይ ኤስ ‹በርግጥ ማነው? ዓላማውስ ምንድን ነው?› ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ መላምቶች ሲሰጡ ነው የቆዩት።

የኢራኑ ሀይማኖታዊ መሪ አያቶላህ ኮሚኒና መንግስታቸው አይ ኤስ የሲ አይ ኤ ‹ልጅ› ስለመሆኑ አጠንክረው ይገልጻሉ። በኢራንና ሊባኖስ ያሉ ሚዲያዎችም የተቀነባበረ መሆኑ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ‹መረጃ› አቅርበው አሜሪካ፣ እንግሊዝና እስራኤል ላይ ጣታቸውን ሲቀስሩ ቆይተዋል። ባኳያው ደግሞ በዓለም ዙርያ ያሉ የተለያዩ ጋዜጠኞች፣ የመረጃ ሰዎችና ምሁራን ሰፋፊ ጥናቶችን እያደረጉ የየበኩላቸውን ትንተና ቢያቀርቡም ሁሉንም የሚያስማማና የተሟላ ምላሽ ግን እስካሁን ማቅረብ አልቻሉም። በርግጥም አይ ኤስም ሆነ መሪው አቡበከር አል ባግዳዲ በሸፍንፍንና ሆን ተብሎ በሚሰራጭ ማደናገርያ ስር የተከለሉ በመሆናቸው ምንነታቸውንና ማንነታቸውን ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት አዳጋች አድርጎታል።

ያም ሆኖ ግን የተለያዩ አጥኚዎች ከደረሱባቸው መረጃዎችና አሳማኝነታቸው ጎላ ከሚል ትንታኔዎች በመነሳት ይህ ጽሁፍ ስለወንድሞቻችን ገዳይ "አረመኔው አይ ኤስ" ጥቂት ለማለት ይሞክራል።

**የሊቢያ ትርምስና አይ ኤስ** :- እራሱን ‹እስላማዊ መንግስት በሊቢያ› እያለ የሚጠራው ቡድን እንቅስቃሴ ከጀመረ ገና አንድ አመቱ ነው። ሶርያ ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የተወሰኑ የሊቢያ ተዋጊዎች በ2014ዓ.ም. አጋማሽ አካባቢ ወደ ሊቢያ ተመልሰው ደርና በተባለችው ምስራቃዊ ከተማ መደራጀት መጀመራቸውን ነው መረጃዎች የሚያሳዩት። ያ ወቅት ደግሞ በምዕራቡ ዓለም እየታገዙ ኮለኔል ጋዳፊን ከስልጣን ያባረሩት የተለያዩ ኃይሎች እርስ በርስ ተናቁረው ሁለት መንግስት እስከማቆም የደረሱበት ወቅት ስለነበር ‹እስላማዊ መንግስት በሊቢያ› ብሎ መንቀሳቀስ ለጀመረው ቡድን ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል።

በሊቢያ በአንድ በኩል በ2012ዓ.ም. የአሜሪካውን አምባሳደር ክሪስ ስቲቨንስን በመግደልና የብሪቲሹ አምባሳደር ሰር ዶሚኒክ አስኪዝ ላይ ሙከራ በማድረግ የሚጠረጠረው አንሳር አል-ሸሪያን ጨምሮ የተለያዩ እስላማዊ ቡድኖች በጋራ ቆመዋል። መዲናዋን ትሪፖሊን የተቆጣጠሩትም እነዚሁ በኳታርና ቱርክ የሚደገፉ የሚሱራታ ሚሊሺያዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ያለው በህዝብ የተመረጠው ፓርላማ ደግሞ ከትሪፖሊ ተሰዶ በምስራቃዊዋ ቶብሩክ ከተማ ላይ ነው የተሰየመው። በርግጥ በሚሊሻዎቹ ስር ያለው የትሪፖሊ ከፍተኛ ፍ/ቤት ህጋዊውን ፓርላማ ውድቅ በማድረጉ ሌላ ፓርላማ መዲናዋ ላይ ተሰይሟል። 40ሺ ተዋጊዎች እንዳሉት የሚነገርለትን የሚሱራታ ብርጌድ የሚቀናቀኑት እስላማዊ ያልሆኑ ኃይሎች በፊናቸው የሊቢያ ጦር አዛዥ በሆኑት በጄ/ል ካሊፍ አል ሀፍታር ስር ተሰልፈዋል። ዋና መቀመጫቸውን ቤንጋዚ ላይ ያደረጉት ጄ/ል ሀፍታር እስላማዊ ሚሊሽያዎቹ ላይ ጦርነት ካወጁበት ከ2014ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ በየአቅጣጫው እየተዋጓቸው ነው ያሉት። ይህኛውን ወገን የሚረዱት ዩናይትድ አረብ ኢምሬትና ግብጽ ናቸው። ሁለቱም ባላንጣዎች የየራሳቸውን ፓርላማና አስተዳደር በማቋቋማቸው ዛሬ ሊቢያ በሁለት መንግስታት ስር እየተመራች ነው ማለት ይቻላል።

በሊቢያ በሚታየው ይህን በመሰለው ትርምስና ህግ አልባነት በመታገዝ ከሶርያ የተመለሱት የ‹እስላማዊ መንግስት በሊቢያ› መስራቾች ባጭር ጊዜ ውስጥ የአዳዲስ አባላት ምልመላቸውን ሲያጧጡፉ፤ ከውጪ ደግሞ በተለይም ከቱኒዚያ፣ አልጄሪያ፣ ከሳውዲ አረቢያና ከሌሎችም አገራት ተዋጊዎች ድንበር አቋርጠው እየገቡላቸው ነው። ሊቢያ ላይ ትኩረት ያደረገው እስላማዊ መንግስት በ2014ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ከሶርያ ወደ ሊቢያ ልዑካን በመላክ የአዲሱ ቡድን መሪዎች ለካሊፌቱ መሪ ለአቡበከር አል ባግዳዲ ታማኝነታቸውን ምለው እንዲያረጋግጡ አደረጋቸው። የሊቢያው ግሩፕም በትሪፖሊ፣ በምስራቅና በደቡብ ያሉ ክልሎችን የካሊፌቱ ግዛቶች ናቸው ሲል በማወጁ 3 የአይ ኤስ አገረ ገዢዎች ተሰይመዋል።

‹እስላማዊ መንግስት በሊቢያ› ባሁኑ ወቅት 3ሺ ያህል ተዋጊዎች እንዳሉት ይገመታል። ብዙ አካባቢዎችን መቆጣጠር ባይችልም የጠረፍ ከተማዋን ስርቴን ጨምሮ የተወሰኑ ቦታዎችን ይዟል። የአገሪቷ 3ኛ ትልቅ ከተማ የሆነችውና 500ሺ ነዋሪዎች ያሏት ሚሱራታ ለእስላማዊ ሚሊሻዎቹ መነሻቸው ነች። የሚሱራታ ብርጌድ 40ሺ ተዋጊዎች በየአቅጣጫው ከጄ/ል ካሊፍ አል-ሀፍታር ጋር እየተዋጉ በመሆናቸው አናሳ ቁጥር ያለውን የአይ ኤስ ሊቢያ ክንፍ ፈጥነው መዋጋት አልቻሉም። የተባበሩት መንግስታት ከጄ/ሉ ጋር ሊያስማማቸው ለወራት ቢደክምም እስካሁን የተሳካ ነገር የለም። ሚሊሻዎቹ በጄ/ሉ ከሚመራው ኃይል ጋር መስማማትና ፊታቸውን ወደ አዲሱ ጠላት ማዞር ካልቻሉ አይ ኤስ እያበጠ የመሄድ ዕድል ማግኘቱ እንደማይቀር ብዙዎች ስጋት አላቸው። በተለይም ‹እስላማዊ መንግስት ወደ ግብጽና ቱኒዚያ እንዲስፋፋ ሊቢያ ጥሩ ቤዝ ልትሆነው ትችላለች› የሚለው ስጋት ከየአቅጣጫው እየተሰማ ነው።

‹እስላማዊ መንግስት በሊቢያ› እስካሁን በተቆጣጠራቸው ጥቂት ቦታዎች ላይ አክራሪ እስላማዊ ህጎች እያወጣ በማስፈጸም ላይ ነው። ሲዲና ሲጋራዎች ሳይቀር እስላማዊ አይደሉም በሚል ይቀማል። ከተለያዩ አገራት ተዋጊዎች እንዲጎርፉለት ቀልብ ለመሳብ ሲልም ስሙን የሚያስጠሩ ማናቸውንም ዓይነት የጭካኔ ተግባራት መፈጸሙ እንደማይቀር ተገምቷል። ምናልባትም ባለፈው ኤፕሪል በንጹሀን ወንድሞቻችን ላይ የፈጸመውን ዘግናኝ ግድያና ከዚያ ቀደም ሲልም በወርሀ ፌብሯሪ በግብጻውያን የኮፕቲክ ቤ/ክርስቲያን ተከታዮች ላይ የፈጸመውን ተመሳሳይ ግፍ በቪዲዮ መልቀቁ ለዚሁ ዓላማው መሳካት ሲል እንዳደረገው ይገመታል።

እንደታሰበው ሚሊሺያዎቹና የጄ/ሉ ቡድን ከተስማሙ እስላማዊ መንግስት ሊቢያ ውስጥ ለመስፋፋት የኢራቅና ሶርያን ዓይነት አመቺ ሁኔታ እንደሌለው ተንታኞች ያስረዳሉ። ሊቢያ ከ6.2 ሚሊዮን ህዝቧ አብዛኛው ሱኒ በመሆኑ እንደለመደው የዕምነት ክፍፍልን በኃይል ማሰባሰቢያነት ሊጠቀምበት አይቻለውም ይላሉ። አሁንም ቢሆን የአገሪቱ የነዳጅ ሀብት በሁለቱ ‹መንግስታት› እጅ በመሆኑ አይ ኤስ በሊቢያ የዳበረ የገንዘብ ምንጭ ሊያፈራ አልቻለም። ሚሊሻዎቹና ጄ/ሉ ተኩስ አቁም ተፈራርመው ዋና ትኩረታቸውን ወደ ‹እስላማዊ መንግስት በሊቢያ› እንዲያዞሩ ርዳታ የሚሰጧቸውን አገራት ጨምሮ ዓለም አቀፋዊ ግፊት ሊደረግባቸው ይችል ይሆናል። ይህም ንጹሀን ወንድሞቻችንን የሰየፉት አረመኔዎችን ግብአተ መሬት የሚያፋጥን ምልክት እንደሚሆን ተስፋ አለን።

**አል-ባግዳዲና ድርጅቱ**:- አቡበከር አል-ባግዳዲ የእስላማዊ መንግስት (IS) መሪ ነው። ከጁን 2014ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ ራሱን ‹ካሊፍ› አድርጎ ሾሟል። በሽብርተኞች መዝገብ ላይ ‹ኦሳማ ቢን ላደንን የተካ› እስከመባል ስሙ ገኗል። ትክክለኛ ማንነቱን ግን ማንም በተሟላ መልኩ ሊገልጸው አልቻለም። ከሁለት የቆዩና ጥራት የጎደላቸው ፎቶግራፎቹ በቀር ዛሬ ምን እንደሚመስል በእርግጠኝነት የሚናገር የለም። ኦሳማን ጨምሮ ሌሎች የሽብርተኛ ቡድን መሪዎች በካሜራ እየተቀረጹ የፕሮፖጋንዳ ቪዲዮዎችን የመበተን ልምድ ቢኖራቸውም አል-ባግዳዲ ግን ይህን አያደርግም። የቀድሞ አለቃውን አቡ ሙሳብ አል-ዛርቃዊን ጨምሮ በርካታ የሽብር አለቆች በአሜሪካ ሰው አልባ አውሮፕላኖች (ድሮንስ) እየታደኑ መጋየታቸው ምስሉን አደባባይ ከማውጣት እንዲቆጠብ ያደረገው ይመስላል። አድራሻውንም ሆነ ምስሉን ለመደበቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ነው የሚነገርለት። ከድርጅቱ ያፈነገጡና አግኝተነው ነበር የሚሉ የቀድሞ ሽብርተኞች ሳይቀር መልኩን መግለጽ አዳግቷቸዋል። "ሰዎች የሚያናግረው ማስክ አድርጎ ነው" ያሉ አሉ። ከስንት አንዴ ህዝብ ወዳለበት ቦታ ሲገኝ እንኳ የሚደረግለት ጥበቃ ጠንከር ያለ እንደሆነም ይነገራል። ለምሳሌ ኒውስ ዊክ ያናገረው አንድ የ29 ዓመት የራቃ (ሶርያ) ነዋሪ አል-ባግዳዲ እሱ በነበረበት መስጊድ ድንገት የተገኘበትን ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር የገለጸው። "በአንድ አፍታ የሞባይል ኔትወርክ ሽፋን ጠፋ። የታጠቁ ጠባቂዎችም አካባቢውን ዘጉት። ማንም ሰው ፎቶም ሆነ ቪዲዮ ማንሳት እንደማይችል ተነገረን። በጣም ስሜት የሚረብሽ ነበር። መጨረሻ ላይ ባግዳዲ ከአናት እስከ እግሩ ጥቁር ለብሶ ብቅ ሲል ‹ጠባቂዎቹ አላህ ዋክበር!› እያሉ መጮህ ጀመሩ። ለሱ

⇒

ያለንን ታማኝነት በመሀላ እንድናረጋግጥም አስገደዱን። ከሄደ በኋላም ቢሆን ለ30 ደቂቃ ያህል ማናችንም ከመስጊዱ ለመውጣት አልተፈቀደልንም ነበር።" ብሏል።

ዕውነተኛ ስሙ ኢብራሂም አዋድ ኢብራሂም አሊ አልባድሪ እንደሚባል የተለያዩ አጥኚዎች ገልጸዋል። አንዳንዴ አቡ አዋድ፣ አንዳንዴም አቡ ዱአ እየተባለ ይጠራ ነበርም ተብሏል። ከባግዳድ በስተሰሜን በምትገኘው ሳማራ ውስጥ መወለዱን ሁሉም የተስማሙበት ቢሆንም ዕድሜው ላይ ግን የተለያየ አሀዝ ይሰጣሉ። አንዳንድ ሪፖርቶች በ1971ዓ.ም. መወለዱን ሲገልጹ፣ ሌሎች ደግሞ ከዚያ ያተልቁታል።‹እስላማዊ መንግስት› በሚያሰራጫቸው የፕሮፖጋንዳ ጽሁፎች ላይ ከፍተኛ የሀይማኖት ምሁር ተደርጎ ቢጠቀስም አጥኚዎችም ሆኑ እናውቀው ነበር የሚሉ የሳማራ ነዋሪዎች ግን አልተቀበሉትም።

አል-ባግዳዲ ወደ ሽብር እንቅስቃሴ የገባው አሜሪካ ኢራቅን ከወረረች በኋላ መሆኑ ታምኖበታል። ኤፕሪል9 ቀን 2003ዓ.ም. የአሜሪካ ኃይል ባግዳድ ሲገባ የሳዳም ቁልፍ አጋሮች በተለይም ወደ ሱኒ ‹ትሪያንግል› ተበትነው ተደብቀው ነበር። ቀስ በቀስ ከአሜሪካኖቹ ጋር በሚዋጉ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ እየገቡ ያጠናከሯቸው እንደነበር ተመስክሯል። ‹እስላማዊ መንግስትን›ም በዋናነት ያጠናከሩና ለባግዳዲ ቀኝ እጅ የሆኑት እነዚሁ የቀድሞ የሳዳም ሁሴን ከፍተኛ የጦርና የመረጃ መኮንኖች መሆናቸው በበርካታ ሪፖርቶች ላይ ቀርቧል።

አል-ባግዳዲ መጀመርያ የተቀላቀለው ጀማት ጃይሽ አህል አል-ሱና ዋል ጀማ የተባለውን ድርጅት ነበር። በ2005ዓ.ም ፋሉጃ ውስጥ በአሜሪካ ወታደሮች መያዙ ደግሞ እጅግ ጥሩ አጋጣሚ ሳይሆንለት አልቀረም። በወቅቱ የኢራቅ አልቃይዳ መሪ ከነበረው ዮርዳኖሳዊው አሸባሪ ከአቡ ሙሳብ አል ዛርቃዊ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ፍለጋ በተደረገ አሰሳ ነበር ባግዳዲም አብሮ የታፈሰው። ከሽብርተኛ ድርጅት ጋር ግንኙነት አልህ በሚል ጥርጣሬ እንጂ በሽብር ተግባር ላይ ሲሳተፍ ባለመያዙ የእስረኛ መዝገቡ ላይ የተጻፈው ‹ሲቪል እስረኛ› ተብሎ ነበር። በእስር የቆየበት በደቡብ ኢራቅ የሚገኘው ‹ካምፕ ቡካ› የተለያዩ ልምድ ያላቸውና የተካኑ ሽብርተኞችም የሚገኙበት እስር ቤት ነው። ይህም ከበርካታ ሽብርተኞች ጋር በቅርበት ለመተዋወቅና ልምድ ለመቅሰም ሳይረዳው የቀረ አይመስልም። ለምሳሌ ካምፕ ቡካ ውስጥ ከተዋወቃቸው ሰዎች መሀል ዛሬ የአይሲስ ቃል አቀባይ የሆነውና አቡ መሀመድ አል አድናን በሚል ስም የሚታወቀው ጠሀ ሶቢ ፋላህ አንዱ መሆኑ ታውቋል።

አል-ባግዳዲ ከተፈታ በኋላ በሽብር እንቅስቃሴው ቀጥሏል። ኦክቶበር 15፣ 2006ዓ.ም. ‹አልቃይዳ በኢራቅ›ን ጨምሮ የተለያዩ ቡድኖች ተጣምረው ‹እስላማዊ መንግስት በኢራቅ› የተባለውን ድርጅት ሲመሰርቱ አል-ባግዳዲም አንዱ ሆነ። ለመሪነት የበቃው ግን አብዛኞቹ መሪዎች ከተገደሉ በኋላ በሜይ 2010ዓ.ም. ነበር።

በ2011ዓ.ም. በሶርያ የርስ በርስ ግጭት መቀጣጠሉ ለባግዳዲ መልካም አጋጣሚ ፈጠረለት። የኢራቅ ሱኒዎች በአሜሪካ ድጋፍ ሊወጉት በመነሳታቸው እየተዳከመ የመጣው ድርጅቱን ሶርያ ውስጥ ገብቶ በማጠናከር በ2013ዓ.ም. በተደራጀ ኃይል ኢራቅ ውስጥም ዳግም እንዲስፋፋ አስችሎታል። ይሁንና በ2013ዓ.ም. ‹እስላሚክ ስቴት ኦፍ ኢራቅ ኤንድ ሌቫንት› (ISIL ) የተባለ ድርጅት መመስረቱ ከአልቃይዳ ጋር አጋጭቶታል። የአልቃይዳው አለም አቀፍ መሪ አይማን አልዛዋሪ፣ አል-ባግዳዲ ኢራቅ ብቻ እንዲቀርና ሶርያ ውስጥ የአልቃይዳ ክንፍ የሆነው ጃባት አል ኑስራ እንዲንቀሳቀስ ቢያስጠነቅቅም አል-ባግዳዲ ሊሰማው ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። ፈጣን እርምጃ እየወሰደ መጓዙ የወጣት አክራሪዎችን ቀልብ እንደሳበለትና በዚህም ሳቢያ ከአልቃይዳ በላይ እየገዘፍ ሲሄድ የተሰማው ይመስላል።

ለዚህም ይመስላል ባለፈው ዓመት ጃንዋሪ 2014ዓ.ም. ደግሞ እራሱን ካሊፍ ‹CALIPH › አድርጎ ሰይሟል። ይህ ማበጡ አልቃይዳን ጨምሮ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ሊያናቁረው ቢችልም በሀብትና በሰው ኃይል በመበልጸጉ ግድ የሰጠው አይመስልም። ባሁኑ ወቅትም ሶርያ ውስጥ የአልቃይዳ ወኪል የሆነውን አል-ኑስራን ጨምሮ ከተለያዩ ቡድኖች ጋር እየተዋጋ ነው ያለው።

ዛሬ ‹እስላማዊ መንግስት› በተለያዩ ዓለማት ያሉ ወጣት ጽንፈኛ ተዋጊዎችን እየሳበ ነው። የአሜሪካ ጸረ ሽብር ማዕከል ዳይሬክተር የሆኑት ኒኮላስ ራስሙሰን በፌብሯሪ 2015ዓ.ም. ለኮንግረስ እንዳስረዱት ከሆነ ከ150 በላይ አሜሪካውያንን ጨምሮ 3400 የሚሆኑ ሰዎች አንዱን ወይ ሌላውን ድርጅት ለመቀላቀል ከምዕራቡ ዓለም ወደ ሶርያ ተጉዘዋል። በአጠቃላይ ከ90 አገራት የተጓዙት ሰዎች ድምር 20ሺ እንደሚደርስም ገምተዋል። ሌሎች ጥናቶች ደግሞ ወደ ሶርያ ከሚጓዙት ተዋጊዎች መሀል 80 በመቶው የሚቀላቀሉት አይሲስን እንደሆነ ጠቁመዋል። ቀደም ብሎ በ2014ዓ.ም. ይፋ የወጣ የሲ አይ ኤ ሪፖርት የአይሲስ ተዋጊዎች 30ሺ እንደሚደርሱ ቢጠቁምም በየጊዜው ቁጥሩ እያደገ በመሄድ ላይ እንደሆነ ነበር ያመላከተው።

አይሲስ በተለይም የኢራቋን ሁለተኛ ትልቅ ከተማ ሞሱልን በጁን 2014ዓ.ም. ሲቆጣጠር ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ነበር የከተተው። በወቅቱ ከሞሱል ማዕከላዊ ባንክ ብቻ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ማግኘቱም ተዘግቧል። የለንደን ኪንግስ ኮሌጅ ተመራማሪው ፕ/ር ፒተር ኒዩማን ከሞሱል በፊት የአይሲስ ሀብት ከ900 ሚሊየን ዶላር የማይበልጥ እንደነበር ገልጸው፣ አሁን ግን ከ2 ቢሊየን ዶላር በላይ እንዳለው ይገምታሉ። ብዙም የገንዘብ አቅም ያልነበረውና በሽር አል አሳድን ይዋጋል በሚል በተለይም በኩዌትና በሳውዲት አረቢያ ባሉ ባለጸጎች ይደጎም የነበረው አይሲስ ዛሬ በአለማችን አቻ የሌለው ሀብታም የሽብር ድርጅት ለመባል በቅቷል።

## አይ ኤስ የአሜሪካ ስራት ነውን?፡-

በርካታ ኢራናውያን አይሲስ የተፈጠረው በሲ አይ ኤ ነው ብለው ያምናሉ። አያቶላህ ኮሚኒ በተደጋጋሚ "አሜሪካ አይሲስን የፈጠረችው ኢራቅ ላይ ዳግም እግሯን ለማስገባትና የኢራን ወዳጅ የሆነውን አል አሳድን ሶርያ ውስጥ ለመውጋት ነው" ሲሉ ተናግረዋል። ሌሎች የኢራን ባለስልጣኖችም አይሲስን የአሜሪካ ስራት "ሜድ ኢን አሜሪካ" እያሉ ነው የሚገልጹት። "እያደገ የመጣውን የኢራን ተጽዕኖ ለመመከትና መካከለኛው ምስራቅን ለመከፋፈል ተብሎ የተፈጠረ ሴራ ነው" ሲሉም ያማርራሉ። የኢራን ሚዲያዎችም ተመሳሳይ ሰበካ ላይ ቆይተዋል። ለምሳሌ ጃቫን የተባለው የኢራን አብዮታዊ ጋርድን አመለካከት እንደሚያንጸባርቅ የሚነገርለት ጋዜጣ ማኔጂንግ ዳይሬክተር የሆነው አብደላ ጋንጂ "አሜሪካ አይሲስን የምትደግፈው የእስላሙን ዓለም በማናጋት የእስራኤልን ደህንነት ለማስጠበቅና ጥቅሟን ለማስከበር ስትል ነው።" ባይ ነው።

ይህን መሰል ጥርጣሬዎች መነሻሸው ከተመሳሳይ አቅጣጫ (ከኢራን መንግስት) ቢሆንም እያደር ግን በአረቡ ዓለም እየተዛመቱ ይገኛሉ። ይህም የሆነው ሚስጥራዊ መረጃ እንደተገኘ ተደርጎ ዜና በመሰራቱ ነበር። ጁላይ 6 ቀን፣ 2014ዓ.ም. ጀርመን አገር ነዋሪ በሆነው ካሪም አል ባይዳኒ በተባለው ሰው አማካኝነት የአሜሪካ ብሄራዊ ደህንነት ኤጀንሲ (NSA) ምስጢሮችን በማጋለጥ የሚታወቀው ኤድዋርድ ስኖውደን የአይሲስና የአሜሪካን ምስጢራዊ ግንኙነት ይፋ እንዳደረገ ተገለጠ። ኤጀንሲው ከእንግሊዙ ኤም አይ 6 እና ከሞሳድ ጋር በመተባበር በዓለም ዙርያ ያሉ ሽብርተኞችን ወደ መካከለኛው ምስራቅ በመሳብ አካባቢውን ለማመስና የእስራኤል ጠላቶች እንዲተላለቁ ለማድረግ ማሴሩ ከሚስጥራዊ ፋይሎቹ ውስጥ ተገኘ ነው የተባለው። ጭራሽም አል-ባግዳዲ አንድ ዓመት የፈጀ ስልጠና በሞሳድ እንደተሰጠው ሳይቀር ተጠቅሷል። ወዲያውኑም የተለያዩ የኢራንና የሊባኖስ ሚዲያዎች ወሬውን እየተቀባበሉ አስተጋቡት። የስኖውደንን የቆየ ምስል እያሳዩም በጉዳዩ ላይ ቃለ ምልልስ የሰጠ አስመስለው አቀረቡት። ይሁንና ሁሉም ዘገባዎች አንዳቸው ሌላቸውን እንደምንጭ ከመጥቀስ ውጪ ወደ መረጃው ይወስዳል እያሉ የሚያያይዟቸው ሊንኮች በሙሉ የትም የማይወስዱ ነበሩ።

የዜና ‹ምንጭ› የሆነው የጀርመን ነዋሪ የካሪም አል ባይዳኒ ማንነት ሲጣራ የተገኘው ዕውነት ደግሞ የተለየ ሰዕል የሚሰጥ ሆነ። ባይዳኒ ሻይት ኢራቃዊ ሲሆን አል አለም በተባለው የኢራን ቲቪ ላይ ‹አል ኢራቅ አልዮም› (ኢራቅ ዛሬ) የተባለው ፕሮግራም ላይ የሚሰራ ሰው ሆኖ ተገኘ። ወሬውን አጩሆ በዜና መልክ ያስተጋባለት የኢራኑ ፋርስ ኒውስ ኤጀንሲም በተመሳሳይ መልኩ መሰረት የሌላቸው ወሬዎችን ‹ዜና› እያለ ለፕሮፓጋንዳ በማዋል ልዩ ሪኮርድ ያለው መሆኑም ተወሳ። ለምሳሌ በጃንዋሪ 2014ዓ.ም. ባስተላለፈው ‹ዜና› የስኖውደንን ፋይል ‹ጠቅሶ› "የአሜሪካ መንግስት የሚመራው ስፔስ ላይ ባሉ ሌላ ፍጡራን ነው።" ብሎ ነበር። ከዓመት በፊት ደግሞ ‹ዘ ኦኒየንስ› በተባለ አንድ የሽሙጥ ድረ ገጽ ላይ "ገጠር የሚኖሩ ነጭ አሜሪካኖች ከኦባማ ይልቅ አህመዲነጃድን እንደሚደግፉ ከተሰበሰበ የህዝብ አስተያየት ታወቀ!" በሚል የቀረበውን ቀልድ ፋርስ ኒውስ ኤጀንሲ እንደ እውነተኛ ዜና ሊያሰራጨው በቅቶ ነበር። ይህም የወሬውን ከንቱነት ለማሳየት ተጨማሪ ማሳያ ሆነ።

አይሲስን እና አይጨበጤ መሪውን አል-ባግዳዲን በተመለከተ ከየፈርጁ የሚቀርቡት መረጃዎች በርካታ ናቸው። ድርጅቱ ራሱን ‹እስላማዊ መንግስት› ማለቱን ከተግባሩ ጋር እያዛመዱ በዓለም ዙርያ ያሉ በርካታ የሀይማኖቱ ምሁራን በይፋ አውግዘውታል። ‹ተግባሮቹ እስልምናን የማይወክሉ ይልቅስ የሚጻረሩ ናቸው› በሚል ከመቶ በላይ ታዋቂ የእስልምና ምሁራን በሴፕቴምበር 2014ዓ.ም. የጋራ መግለጫ ማውጣታቸውም አይዘነጋም። አይሲስ የሚሰራቸውና በእስልምና የተወገዙ 24 መሰረታዊ ነጥቦችን የሚዘረዝረው ይህ ግልጽ ደብዳቤ በአረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ነበር የተበተነው። የተምታታባቸው አክራሪ ወጣቶች ግን አሁንም እየጎረፉለት ነው።

# ጥቂት ስለ ጋሽ መስፍን

(ከገጽ 28 የዞረ)

ኖሮ ወንድሜ ሙሴን ቀጠቀጡት። እጇም ተሰበረ። ለመቀጣጫነት ያደረጉት ይመስለኛል። ሌሎች ጥቂት መሰሎቼንም ከእኛ ጋር ከት/ቤት አባረሯቸው። ይህም በኢህአዲግ ቤት እንደ ሰውም እንደ ተማሪም ማሰብ እንደማይፈቀድ ያሳየ ሆነ። ‹በእርግጥም አንድ ሰው ብዙ ነው› አልኩ እኔም።

## የመንፈስ ልዕልና

ካልተሳሳትኩ በጣም ከሚወዷቸው ቃላት አንዱና በምግባርም የተቀዳጁት ኃይል ይመስለኛል። ጋሽ መስፍን ቂመኛ አይደሉም። ላመኑት ነገር በጽናት ይቆማሉ። ዕምነታቸውን ይኖሩታል። የሙብት ነገር የነፍሳቸው ጩኸት ነው። ስለ ኢትዮጵያውያን ሙብት የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል። አሁንም እያደረጉ ነው። የአገር ፍቅር የዋኞቸው ጥሩ ኢትዮጵያዊ ናቸው። በወረቀት ላይ እንኳን ኢትዮጵያዊነታቸውን ለድርድር የማያቀርቡ። እዚህ ጋ ኢትዮጵያውያንን በየመታወቂያውና የጉዞ ሰነዱ ላይ ሳይቀር በብሄራቸው ለመስፈር የሚሞክረው አገዛዝ ጋሽ መስፍን ጋ እንዳልተሳካለት ማስታወስ ይቻላል። እኚህ ውድ ሰው የግል መኖርያ እንኳ የላቸውም። ለመሽ እድሜ ብለው ጥሪት አልቋጠሩም። ምኞት ግዴ ናቸው። የደሀውን ህመም፣ ረሀብና እንግልት፣ እርዛትና ሰቆቃ በሪፖርት ሳይሆን አብሮ በመኖር ነው የሚያውቁት። ዕድሜያቸውን ሙሉ ችግሩን እየተቋደሱ አብረውት እየኖሩ ነው የዘለቁት። ይህን አኗኗራቸውን አስመልክቶ በቅርቡ ያወጋንበትን አጋጣሚ አስታውሳለሁ። አውስትራሊያ ብቅ ባሉበት አጋጣሚ አብረናቸው ሻይ ቡና እያልን ነበር። በተለይ እዚሁ(ሲድኒ) የሚኖርና ስለሳቸው ከልብ እንደሚጨነቅ የማውቀው ወዳጄ ይጠይቃቸዋል። "መኖርያ ቤት አሎት?" "የለኝም።" "የቁጠሯት ጥሪትስ?" ፈገግ ብለው "የለኝም።" "ታዲያ እንዴት ነው የሚኖሩት?". . . መልስ ሰጡን። ወዳጄ ጥያቄውን መቀጠል አልቻለም። በመልሳቸው ጥልቅ ሐዘን እንደተሰማው ግን ማስተዋል ችያለሁ። (በዚህ አጋጣሚ ለአገር ውለታ እየዋላችሁ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይህን ጽሁፍ እያነበባችሁ ከሆነ "እግዚአብሄር ውለታችሁን ይክፈል" እላለሁ። በአውስትራሊያ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንም ጋሽ መስፍንን አክብራችሁ በመጋበዝ ለዚህች አገር የዋሉትን የዕድሜ ልክ ውለታ ዕውቅና ሰጥታችሁ ምስጋና ማቅረባችሁ የሚያኮራ ነው።)

ጋሽ መስፍን ቢችሉም እንኳ የተቀማጠለ ህይወት መኖር ምርጫቸው አይደለም። በአንዱ አጋጣሚ "ለምን ይሆን?" ብለን ጠይቀናቸው ነበር። " አልያማ የወገኔን ኑሮ እንዴት በወጉ ላውቀው እችላለሁ? ድህነትን ከረሳሁ የወገኔን ኑሮም ረሳሁ ማለት አይደል?" አሉን። እውነት አላቸው።

## ሱባዔና ጸጉር

ስለጋሽ መስፍን አንድ የሰማሁት ነገር ነበርና በቅርቡ እንዲህ ስል ጠየኳቸው። "በአመት አንድ ጊዜ ለወር ወይ ለሳምንታት ሱባዔ ገብተው ብቻዎን ያሳልፋሉ ይባላል። እውነት ነውን?" አልኳቸው። "እውነት ነው። እንዲህ ጊዜ ሰጥተህ በፍጹም እርጋታ እራስህን መፈተሽ፣ ስራህን መገምገም፣ የሚመጡልህን ሀሳቦች ማስፈር የሚጠቅም ይመስለኛል" አሉኝ። የጸጉር አቆራረጣቸው ሳውቃቸው ጀምሮ ወጥ የመሆኑን ጉዳይም አንስቼባቸው ነበር። ከአንድ ገጠመኝ በኋላ ድንገት ራሴን ባስተካክልስ ብለው እንደሞከሩትና ዛሬም ድረስ በዚያው መልኩ እንደቀጠሉበት ነገሩኝ። የራሳቸው ከርካሚ እራሳቸው በመሆናቸው እንጂ የተለየ ምክንያት እንደሌለው ገባኝ።

## የሞት ዓይነቱ


ጋሽ መስፍን ‹ሞት ሁሉ አንድ አይደለም› በሚል የሚሰጡት ትንታኔ አላቸው። እስቲ በብሄራዊ ሎቶሪ አዳራሹ ውይይታችን ወቅት ይህን በተመለከተ ያነሱትን ቁም ነገር እንደገባኝ አድርጌ ልጥቀሰው። . . . የተፈጥሮ ሞት አለ። ተገድሎ መሞትም አለ። በቁም መሞት ደግሞ ሌላው የሞት አይነት ነው። ጉልበተኞች ብዙ ጊዜ የመጨረሻዎቹን አይነት ሁለት ሞቶች ነው ሊገድሉን የሚፈልጉት። በፍራቻ ተሸብበን የሚገባንን ሳንጠይቅና ሳናስከብር እንድንኖር፣ ለራሳችንም ለአገርም ሳንሆን የመንፈስ ልዕልናችንን ተገፍፈን እንድንኖር። ይህ ደግሞ ህይወት አይደለም። የቁም ሞት እንጂ። ጋሽ መስፍን የቁም ሞትን ሲስረዱ የጠቀሷት ምሳሌም ትዝ ትለኛለች። "አንድ ጉልበተኛ (የመንግስት ታጣቂ) መጥቶ ባላወቅነው ጥፋት ወይም መብታችንን በመጠየቃችን ብቻ መሳርያ ደቅኖ ተንበርከኩ ቢለንና እኛም ግኡዙን ነገር ፈርተን ከተንበረከክንለት ያኔ የቁም ሞት ሞተናል። የለም ያልን እንደሆን ግን የመንፈስ ልዕልናችን ያይላል።" አሉ። ሰሞኑን ደግሞ በሞትም ድል ማድረግ ስለመቻሉ ጋሽ መስፍን የጻፉትን መጣጥፍ አንብቤ ነበር። እንደገባኝ ከሆነ ‹ባለ ጊዜ ጉልበተኞች› ሊያስፈራሯቸው ስለሞከሩ ነበር የጻፉት። ጉልበተኞቹ መረዳት የተሳናቸው የጋሽ መስፍንን የመንፈስ ልዕልና ብቻ አይመስለኝም። ውዱ ሰው በብዙዎቻችን ልብ ውስጥ ያላቸውን ልዩ ስፍራ ጭምር እንጂ። ህመማቸው ህመማችን፤ ስቃያቸው ስቃያችን፤ ራዕያቸው ራዕያችን የሆንን እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውያን አለን።

ጋሽ መስፍን ቀጥተኛ ሰው ናቸው። ከቂምና በቀል የጸዱ፣ የአንድን ሰው ብዙነት የተረዱና ሰዎች ይለወጣሉ የሚል ጠንካራ ዕምነት ያላቸው ሰው መሆናቸውንም እረዳለሁ። የተረዱትን ዕውነት ራቁቷን መግለጽ እንጂ ማንንም ለማስደሰት ብለው መጠጋገን አያውቁበትም። በየአገዛዙ ጥርስ ውስጥ ቢገቡም እንኳ ከልባቸው ዕውነት ጋር እንደቆሙ ነው የዘለቁት። የቅርብ ጊዜ መጽሀፎቻቸውን ካየን ጀግናውን ጀግና፣ ባንዳውን ባንዳ(ለወራሪ ያደረ) ለማለት ችግር እንደሌለባቸው እንረዳለን። ‹የሚያሻሽለን ዕውነትን መፈለጉ ነው፣ ሁሉም የስራውን ያገኝ፣ ዕውነቱ ይታወቅ› ብለውናል። ከስሜታዊነት ርቀው በአስተውሎት ይጓዛሉ። ለዚህ ደግሞ አገር ምድሩን ስሜታዊ ባደረገው የባድሜ ጦርነት ወቅት ‹የዓይን ቀለሙ ያስጠላኝን ሁሉ . . .› ሲባል፣ "ፍትሀዊ እንሁን" በሚል የያዙትን አቋም ማስታወስ ይቻላል። በአንድ መጽሀፋቸው ላይ ስለ አጼ ቴዎድሮስ የገለጹትንም እንደአብነት መጥቀስ ይቻላል። አጼ ቴዎድሮስ ባለራዕይ በመሆናቸው ብቻ ሁሉንም ድርጊታቸውን "እሰይ ለመልካም ነው" ለምንል ሰዎች ጋሽ መስፍን መነጽራችንን ነበር ያስተካከሉልን። መልካሙን ማጎልበት፣ ከስህተትም መማር የሚቻለው ከስሜት የጸዳ ምልከታ ሲኖር ብቻ ነውና።

ጋሽ መስፍን በአዲሱ ትውልድ የሚያምኑ ሰው ናቸው። ወጣቶችን የትግሉ ባለቤት ካላደረግን የሚፈለገው ለውጥ ሩቅ እንደሚሆን አስተውለዋል። ወጣቶቹም ይወዷቸዋል። በፍቅር ‹ፕሮፍ› እያሉ ነው የሚጠሯቸው።

ስለጋሽ መስፍን ባሰብኩ ቁጥር በአዕምሮዬ ድቅን የሚለው አብርሀም ማስሎው (Abraham Maslow) ነው። ይህ አሜሪካዊ የ Behavioural Science ምሁር አንድ ነገር ለማድረግ ስለሚያነሳሱን (Motivate) ጉዳዮች ለማወቅ ባደረገው ምርምር ሂደቱን በአምስት መሰረታዊ ምክንያቶች ይከፋፍለዋል። እያንዳንዱን እርካብ ከታች ጀምረን ወደላይ እየረገጥን ማለፍ እንደሚጠበቅብን ቢዘረዝርም እጅግ ጥቂት የተለዩ ሰዎች ግን ደረጃውን ሳይጠብቁ እላይኛው እርካብ ላይ መድረስ እንደሚችሉ ይነግረናል። በሱ ድምዳሜ ጅማሬው Physiological ( ማለትም ሰው መጀመርያ መጠለያ፣ ምግብ . . .ወዘተ ሊኖረው ይገባል ወይም እነዚህን መሰረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ነው የሚያነሳሳው) ይላል። የመጨረሻውን እርካብ ደግሞ Self - actualization ይለዋል። ሰው እጅግ ስኬታማ ሆኖ ስለተፈጠረለት ነገር መኖር ሲችል እንደማለት ነው። ታዲያ ማስሎው አንዱ ሳይሟላ ሌላውን ማድረግ ስለማይቻል (ለራስ የተደላደለ ኑሮ ሳይኖሩ ስለሌላው ማሰብ ስለሚያዳግት) ደረጃውን ጠብቀን መውጣት አለብን ባይ ነው። ወደ ጋሽ መስፍን ስመለስ ታዲያ ማስሎው ‹እጅግ ጥቂት› ካላቸው የተለዩ ሰዎች› መደብ ነው የማገኛቸው። ሳይኖራቸው፣ ሳይደላቸው ህይወታቸውን ሙሉ ስለ ሌሎች መኖር የመረጡ ውድ የኢትዮጵያ ልጅ። ስለሌሎች መኖር፤ ስለሀገር መኖር፣ ከህዝብ ጋር መራብ፤ ከወገን ጋር መታሰር፣ ከአገሬው ጋር መደብደብ. . . ምንኛ መታደል ነው?

ለጋሽ መስፍን ያለኝ መልዕክት አንድ ነው። ፈጣሪ አብዝቶ ይባርክዎ። የወጡበት መህጸን የተባረከ የተቀደሰ ነው። ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን ጨምሮ ለዚህች አገር የሚያልሙት መልካም ህልም ሁሉ ዕውን ሆኖ ለማየት ፈጣሪ አምላክ ያብቃዎ። ቸር እንሰንብት!



# የምንሳሳላቸው የሀገር ዋርካ ...!

(አያሌው ሁንዴሳ-ሲድኒ)

ከገጽ 28 የዞረ

እንዳለው ደግሞ በሚያውቋቸው ሰዎች ላይ ሳይቀር አይተው የታዘቡ ሰው ናቸው። “ድህነትን መርሳት ወገንን መርሳት ማለት ነው።” ያ ደግሞ ለፕ/ር የሚታሰብ አይደለም። ይልቅስ ከደሀው ወገናቸው መሀል ሆነው ችግሩን እያዩና እየተካፈሉ ባንዲት የኪራይ አፓርታማ ውስጥ በጡረታ ገቢ እየተዳደሩ መኖሩን መርጠዋል።

በርግጥም ፕ/ር ደሀ አገራቸውን ሙጥኝ ብለው ስለደሀው ህዝባቸው እንደተሟገቱ የዘለቁ ብርቱ ሰው ናቸው። ህይወታቸው በተለያየ መልኩ ከድህነት ጋር ስለመቆራኘቱ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። ጥረት ድካማቸውን ያየ፣ ሙግት ትግላቸውን ያስታወሰ፣ የአገልግሎታቸውን ፈርጆች ያሰላ ሰው ጥላቻን አምርረው የሚጠሉት ፕ/ር መስፍን - አንድ ዓይነታ ‹ጠላት› እንዳላቸው ግን ልብ ይላል። ይህ ‹ጠላት› ድህነት ይባላል። የህዝቡ የኑሮ ድህነት፣ የፍትህ ድህነት፣ የዲሞክራሲ ድህነት፣ የመልካም አስተዳደር ድህነት፣ የሰብዓዊ መብቶች ድህነት . . . የኢትዮጵያ ድህነት! ይህን ክፉ ‹ጠላት› ደግሞ በየፈርጁ ሲታገሉት ኖረዋል። በሙያቸው ታገሉት። በፖለቲካው ታገሉት። በመብት ተሟጋችነታቸው ታገሉት። በብዕራቸው፣ በልሳናቸው፣ . . . ታገሉት። አሁንም እየታገሉት ነው። ከህዝቡ ጋር ካልሆነ በቀር ግን ለብቻቸው ላይገላገሉት ለራሳቸው ቃል የገቡ ይመስላል። ይህ አይደል ከፍታ ማለት? ይህ አይደል የሞራል ልዕልና? . . .

ከፕ/ር ጋር ድንቅ ሳምንት ማሳለፌ ለኔ የተለየ ትዝታ ነበረው። እያንዳንዷን አፍታ በስስትና በደስታ አስታውሳታለሁ። ኔልሰን ማንዴላ ከአጼ ኃ/ስላሴ ጋር የተገናኙበትን አፍታ በመጽሀፋቸው ላይ ሲያስታውሱ “. . . የታሪክን እጆች የመጨበጥ ያህል ነው።” ነበር ያሉት። እኔ ደግሞ በአቅሜ “የግል ህይወቱን ቸል ብሎ ለብዙሀኑ ከኖረ፣ ፍርሀትን ድል ነስቶ ለሚያምንበት የልቡ ዕውነት ከቆመ፣ ህይወቱን ሙሉ ምቾት ንቆ ለአገሩ ሲል ከዳከረ፣ የሞራል ልዕልናው ልቆ ‹የአገር አድባር› ከተባለ . . . የኢትዮጵያ ውድ ልጅ ጋር ሰነበትኩ” ለማለት እወዳለሁ።

. . . የፕሮግራም ጉዳይ ሆነና ግን እንሆ መለያየችን ደረሰ። ፕ/ርን ገና በ3 የተለያዩ የአውስትራሊያ ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በጉጉት እየተጠባበቋቸው ስለነበር ሲድኒዎች ባር ባር እያለን መሸኘት ግድ ሆኖብናል። ከጉዟቸው አንድ ቀን አስቀድሞ ግን ወደ ኒውዚላንድ ቆንሲላ ቢሮ መሄድ ነበረብን። የኦክላንድ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ፕ/ር መሀላቸው እንዲገኙላቸው ስለወተወቱና እሳቸውም ፍቃደኛ ስለሆኑ የቪዛ መጠየቂያ ፎርም ለመሙላት ነበር የሄድነው። ያን ዕለት ማድረግ ያለብንን አድርገን እንግዳችንን ሸኘናቸው።

ፕ/ር ወደ ሜልቦርን ከተመለሱ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ግን ከኒውዝላንድ ኢሚግሬሽን መ/ቤት የተላከ አንድ አስገራሚ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል። “የቪዛ ጥያቄዎን እንድናጤን ብሄርዎን ፎርሙ ላይ ይግለጹ” የሚል። ይህ ጥያቄ በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ ድርድር ለማያውቁትና ከኢትዮጵያ በቀር ሌላ መገለጫ ለሌላቸው ሰው ትልቅ ድፍረት ሆኖ ነው የታያቸው። መብቱን የሚስከብረው ባለቤቱ ብቻ ነው። ሁኔታው ከኢትዮጵያዊነት ጋር የተጣላውና የስልጣን መሰረቱን ዜጎችን በመከፋፈል ላይ ያዋቀረው ወያኔ ‹የዜጎቹ ዓይነተኛ መገለጫ ብሄራቸው ነው› በሚል መንፈስ የሚያራምደውን የጥፋት ፖሊሲ የኒውዚላንድ መንግስትም ተቀብሎ እያራገበለት ያለ ነው የሚያስመስለው። ለዚህ ደግሞ ‹መብቴን አትንኩ› ባዩ ፕ/ር ለኒውዚላንድ መንግስት የሚገባውን ምላሽ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አገኙት። “. . .መላው አውሮፓንና አሜሪካን ጨምሮ ወደተለያዩ አገራት ተጉዣያለሁ። አንድም ጊዜ ግን ‹ብሄሬን›ም ሆነ ቋንቋዬን እንድገልጽ ተጠይቄ አላውቅም። ጥያቄህ ከዘረኝነትም የከፋ ስለመሆኑ እንደምትስማማ ጥርጥር የለኝም። ቪዛችሁን ለማግኘት የምከፍለው ዋጋ እንዲሆን ፈልገህ ከሆነ ግን ውብ ደሴቶቻችሁ(ኒውዚላንድ) ላይ መቼም ቢሆን እግሬን ማሳረፍ እንደማልፈልግ በክብር እነግርሀለሁ . . .” የሚል ጠንካራ መልዕክት ያለው ደብዳቤ ልከውላቸዋል። (ደብዳቤያቸው በ1995 ዓ.ም. የኔዘርላንድ ኤምባሲ የኢሰመጉን እጅ በገንዘቡ ለመጠምዘዝ በሞከረ ወቅት የጻፉለትን ጠንካራ ምላሽ ያስታውሳል።) እኔም ይህንኑ ለኒውዚላንድ ኤምባሲ የላኩትን አንጀት አርስ ደብዳቤ አያይዤ ይህቺን አጭር መልዕክቴን ልቋጭ።

Date: Tue, 4 Nov 2014 05:06:42


Dear Mr. Mungoni,

Thank you very much for the trouble you took to respond to my application for a visa to New Zealand. I am perfectly aware that you were following the directive given to you, But your new request which requires me to tell you more than my nationality is something entirely new to me. I have traveled in every country in Europe, Canada, the US, Russia and Mongolia, India, Sri Lanka, Thailand, and in every country of my continent, Africa; and now to Australia. Nowhere have I been requested for information on my "ethnicity" and language, and the script of my language. I am sure you agree that your demand is worse than racism. If you want me to submit to this demand as a price for your visa, then I tell you, Sir, I shall not want to set foot on your beautiful islands. I shall bother you no more!

Sincerely yours
Mesfin wolde Mariam

በመጨረሻም **:-ውድ ፕ/ር መስፍን:-** *ለሚወዷት - ለምንወዳት አገራችን ዘመንዎን ሁሉ ደክመዋል። አሁንም ታክተኝ አላሉም። ትጋትዎን፣ ተቆርቋሪነትዎን እና ጽናትዎን የሚያይ አምላክ ጤናና ዕድሜውን ይስጥዎ! ምኞትዎንና ጥረትዎን ተገንዝበ ተግባራዊ የሚያደርግ ትውልድ ኢያሳጣዎት!*

*አክባሪዎ! አያሌው ሁንዴሳ*



# የዓረቡ ዓለም መቆራቆስ ቀይ ባሕርን ይሻጋገር ይሆን?

የሱፍ ያሲን

*ከገጽ 30 ዞረ*

መድረክ ላይ ብቅ ማለት የጀመሩት በዚያን ዓመት ነው። በወቅቱ ከግብፅና ሶሪያ ጋር ወግነው ምዕራባውያኑ ላይ የነዳጅ ሽያጭ እገዳ ጣሉና ክንዳቸው ፈረጠመ።

የገልፍ አሚሮቹ በነዳጁ ቢልዮኖች ዘመናዊ መሣሪያ በገፍ ሸመቱና የዓረቡን ዓለም የመሪነት መዘውር ይገባናል ጥያቄ መቀናቀን አማራቸው። በአመዛኙ በብሔረተኛ ኃይል ከኢምፔሪያሊዝምና ከራሳቸው ከዓረቡ የዷሊት ኀታች ኃይሎች ጋር ፍልሚያ ነበራቸው ብለናል። እነዚህ ኃይሎች በተራቸው በዚያን ጊዜ ከምዕራባውያኑ ኃይሎች ጋር የተመሰረቱት የጦር ቃል ኪዳኖችና አወጋገን ለይታዎችም ሆኑ አሰላለፍ ይህንኑ የጊዜው እውነታ ያንፀባርቁ ነበር። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ተርኪን ፣ኢራንን ፣ ኢራቅንና ፓኪስታንን ያካተተው የማዕከላዊ መከላከያ ቃል ኪዳን ወይም በፈረንጅኛ ምሕፀረ-ቃሉ (CENTO Center-al Treaty Organization ሰንቶ) ዋና መቀመጫው መጀመሪያ ባግዳድ ስለ ነበር ነው የባግዳድ ውል ተብሎ የሚታወቀው። በ1958 የኢራቁ ንጉሥ በወታደራዊ መፈንቀለ መንግሥት ሲወገድ ነበር መቀመጫው ወደ ኢራን የተዘዋወረው። በ1979 በኢራን የአያቶላሆች አብዮት ስምምነቱ ፈረሰ፣ የመከላኪያ ቃል ኪዳኑ ትብብርም ተበተነ።

ዓረቦች በአንደኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ ማግሥት አንድ ጠንካራ ብሔራዊ መንግሥት ለመመሥረት ያቀጣጠሉት አብዮትና መነሳሳት ከሸፈት ባንድ ሥር የሚያካልልቸው መንግሥት በመፍጠር ምትክ በ22 ሃገራት የተሸነሸኑ ትናንሽና ተነታራኪ መንግሥታትን ወልዷል። የዓረቡ ራቢጣ በ70ኛ ምሥረታ ዓመቱ ዋና ዋና ተልዕኮዎችን ማጠናቀቅ አልቻለም። የዓረቦቹ ውህደት አልተሳካም። ለታሪካዊ ስህተቱ ዓረቦቹና ቱርኮች የክስ ጣት ይቀሳሰራሉ፣ እንደተመለከትነው። የሳይኬስ ቢኮ (Sykes-Picot) ስምምነት የሃገራት ካርታዎችን እነ አይሲስ አይቀበሉትም። አዳዲስ ካርታዎችን የሚያስነድፉት ያለ ምክንያት አይደለም። በ1923ዓ.ም. ላይ የተገረሰሰውን የሙስሊም ካሊፌትን እንደገና የማቋቋም ሕልም እንግበው ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከሩ ናቸው። በጀማል ዓብዱል ናስር ዘመን (1952 -1970) ያቀጠቀጠው የዓረቡ ብሔረተኛ እንቅስቃሴ ግለቱ እየቀዘቀዘ ከመጣ ውሎ አድሯል። በድፍድፍ ዘይት ሃብታቸው የሚተማመኑት የገልፍ ሃገራት የበላይነት እየሰፈነ ነው። ዛሬ እነዚህ ሃገራት የዓረቡን ዓለም እጣ ፋንታ እየተቆጣጠሩ የመጡ ይመስላል። ግብፅን የመሰለ መሪ ሃይል ከጥቅም ውጭ ሆናለች። በ1978 ዓ.ም. የካምፕ ዴቪድ ስምምነት ከእስራኤል ጋር ከተፈራረመችበት ጊዜ አንስቶ ኮኮቧ እየዘቀዘቀ መጥቷል። የየመንን ጉዳይ እንደ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። በ1962 ላይ በየመኑ ኢማም አሕመድ ላይ ወታደራዊ መፈንቀለ-መንግሥት በተደረገበት ወቅት በዘውድ ሥርዓት መላሾችና በሪፓብልኩ ደጋፊዎች መካከል ለሰባት ዓመታት በተጧጧፈው ውጊያ ሳዑዲ ዓረቢያ የመጀመሪያዎቹን ስትደግፍ የግብፁ ጀማል ዓቡል ናስር የሪፓብሊካኖች ወገን ለመደገፍ ወታደሮች ወደ የመን ልካ ነበር። በ1967ዓ.ም. የእስራኤል ጦር በግብፅ ሠራዊት ላይ ባደረሰው ሽንፈት ናስር ብቻ ሳይሆን የብሔረተኛው ሓይል ነው የተዳከመው። ግብፅ ወታደሮቿን ከየመን ማስወጣት የግድ ነበረባት። ዛሬ ሳዑዲ ዓረቢያና ግብፅ ባንድነት የሑቲ አማፅያንና ከበስተጓላቸው አለች የምትባለውን ሻዓይቱ ኢራንን እየተፋለሙ ናቸው። በሕጋዊነት እንመልሳለን በሚለው ሽፋን። በእነናስር ዘመን ፍልሚያው በብሔረተኛው ኃይልና በኢምፔሪሊያሲቱ የሚደገፉ አድሓርያ ነገሥታትና አሚሮች መሃል ነበረ የሚጧጧፈው። ዛሬ ግን በኢራንና በሳዑዲ ዓረቢያ መካከል የሚደረግ የሱኒ-ሺዓ የእጅ አዙር ጦርነት መልክ ተላብሷል። አንዱ ሲሸነፍ ሌላውን ተተኪ ድርጅት መቀፍቀፍ ተለምዷል። በተለያዩ ስሞች። በተለያዩ አወጋገኖች። ትንንሽ ቡድኖች ከአንዱ ዓውደ ወጊያ ወደ ሌላው ይዘምታሉ። ድንበር ዘለል ናቸው። የሃገራትን ቅኝ ገዢ ሰራሽ ድንበሮች አንቀበልም ባዮች ናቸው። ለእነሱ ሃገራት አንድ አውደ ውጊያ ሜዳዎች ናቸው።

አሜሪካ ብቻ ሳትሆን የገልፍ አረብ ሃገሮችም ጭምር የኢራንን የአካባቢ ሃያልነትዋን መቀበል ሊገደዱ ነው። ልክ በሻሁ ዘመን የነበረችበትን ሁኔታና ሚና መቀዳጀት ባትችልም በሶሪያ፣ በኢራቅና በሊባኖስ ተደላድላለች። በባህሬን ቀላል የማይባል ተጽዕኖ ማሳደር ትችላለች። በየመንም እንደምንመለከተው ጫና አሳዳሪ ሃይል ሆናለች። ለአሁኑ የየመኑ ችግር ሳዑድ አረቢያና ተቀጽላዎቹዋ ተጠያቂ የሚያደርጉዋት ያለምክንያት አይደለም። ነገር ግን ለየመኑ ትርምስምስ በቂ ሌሎች ውስጣዊ ምክንያቶችም አሉ።

ሩሲያ ወደ አካባቢው እየተመለሰች ነው። የየመንን ጉዳይ ለተ.መ. ድ. ፀጥታ ምክር ቤት ለማቅረብ ተነሳሽነቱን ጨብጣለች። ሳዑዲ ዓረቢያ የገልፍ ዓረብ ሃገሮችን አስተባብራና፣ ግብፅ፣ ሱዳን፣ ሞሮኮና ፓኪስታንን በአንድ አሰልፋ በሑቱ አማፅያን ላይ ጦርነት አውጃለች። እዚህ ላይ በዓረቡና በሙስሊሙ ዓለም ሱኒ-ሺዓ ችካሉ ወይም ግርግዳው መስፋፋቱ ብቻ ሳይሆን ከእነአካትዬው ዋና መለያያ መስመር እየሆነ መምጣቱን የየመን ቁሩቁስ በማያጠራጥር መልኩ ያረጋግጣል። ከሁሉ በላይ ለየት ያለ የሱኒ-ሺዓ መስመር ይታይበት የነበረው የየመኑ የዘይዲ ሺዓዎች ወይም ሑቲ አማፅያን ‹ወደ ዳር ተገፋን› ስሞታና ያስከተለው የአካባቢ ኋላቀርነት ጥያቄ ዛሬ የእምነት ክፍፍል ልባስ ለብሶ፣ ሺዓ-ሱኒ መስመር አስለይቶ እያራኮታቸው ነው። ዓረቦቹ ወይም አብላጫ የሆኑት ሱኒዎቹ የኢራንን መስፋፋት ለማቆምም ታጥቀው የተነሱ ይመስላሉ። እሷ ደግሞ ለፍልስጤም ጉዳይ ጥብቅና የመቆሙን ነገር ከማንም ዓረብም ሆነ ሙስሊም መንግሥት በላይ አለሁበት ባይ ካርዷን ከመጠቀም ወደኋላ የምትል አትመስልም።

በመደምደሚያ፣ ኢራን ከአሜሪካና ከሃያላን ሃገሮች ጋር የኑክሌር ስምምነት መፈራረሙ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ማላላትና ብሎም ማስነሳት ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ አካባቢ ሃያል ሃገር ተቆጥራ መወሰድን ስለሚያካትት ወደ እሷ ያዳላል ማለቱ ያስኬዳል። በዚያ ላይ ስምምነቱ የተ.መ.ድ ፀጥታ ምክር ቤት ይሁንታም ይታከልበታል ነው እየተባለ ያለው። በዚህ ጉዳይ ከተስማሙ በሌሎች አካባቢያዊ ዶሴዎችም ስምምነት ላይ መድረስ ይቻል ይሆናል የሚል ተስፋ ነው በብዙዎች የአካባቢው ታዛቢዎች ዘንድ የሰፈነው። ይህ ስምምነት በርካታ ዶሴዎችን ባይፈታም እንኳን ያለዝባል፣ ያለሳልሳል፣ ክፍተቶች እንዳይሰፉና ወደ ኀርጓዳ ሽለቆነት እንዳይለወጡ ያደርጋል። በሌላ በኩል ይኸው የኢራን የአካባቢ ኃይል መሆን ነው የገልፍ ዓረብ ሃገራትና መሪያቸው ሣዑዲ ዓረቢያን የሚያባናናቸው። ሆኖም ይህን ቁሩቁስ የኢራን እና የሳዑዲ አረቢያ የእጅ አዙር ጦርነት ነው ብሎ መደምደምም አይቻልም። የእስራኤሎች የሕልውና ስጋትና ፕሬዝዳንት ኦባማ በታሪክ የሚዘከሩበትን ቅርሰ-ውርስ (ሌጋሲ) የመተው ፍላጎትና ምኞትም ጉዳዩን ያወሳስበዋል።

➡

አሜሪካ በየመን ሑቱ አማጽያንን ወይም አንሳራ-አላህን የምትዋጋው ከአልቃዒዳ ሰዎች ጋር ሆና ነው። በዚህ ጎራ አል-ኢስላሕ የተባለው ከሙስሊም ወንድማማቾች የሚደመር ቡድን ጋር ሆና የቀድሞ ሸሪኳን ዓሊ ዓብደላ ሣሊሕንም ትዋጋለች። በተቃራኒው ግን አይሲስና አልቃዒዳን በሶሪያ ትዋጋቸዋለች። እነዚህን ሓይሎች ባንድ የውጊያ አውድ እንደ አጋር መቁጠር በሌላው አውደ ውጊያ ደግሞ እንደ ደመኛ ጠላት መፈረጁ ምንም የማይሳነው የዓረቡ ዓለም ውጥንቅጥና ቁጥርጥር ያሉ ስሌቶቹ ናቸው። ኢምክንያታዊ ቢመስሉና ለመረዳት ቢያስቸግሩም አይገርምም። "በመካከለኛው ምሥራቅ" የሚመስል ነገር ግን በተግባር የምንመለከተው፣ ‹አይሆንም!› ብለን አፋችን ሞልተን መናገር የሚቻልን ነገር የለም ማለቱ ሳይሻል አይቀርም። በተለይም የተለመደውን የመካከለኛው ምሥራቅ "የሤራ ቲዮሪዎች" በግምት ከወሰደን። ስለዚህም ነገ ምን ሊከሰት እንደሚችል መተንበይ የሚያስቸግረውም ከዚሁ ውስብስብ ሁኔታ በመነሳት ነው። ዛሬ የሚመስሉን አዳዲስ ጎራ ለይታዎች፣ አሰላለፎችና አውጋገኖች ብቅ ሊሉ እንደሚችሉ እሙን ነው። አይሆንም ተብሎ የሚወረወር ታሳቢ አይኖርም።

የዓረቡ ራቢጣ የሃገር ሕልውናና ሕጋዊነት በተናጋ ቁጥርና በተናጋበት ሃገር ዘሎ ጣልቃ መግባት አይቻለውም። ይህ በተግባር የማይሞከር ውጥን ይሆናል። ሣዑዲያና ግብረ አበሮቿ የመንን የመረጡበት በቂ የራሳቸው ምክንያት አላቸው። ጉዳዩ መቼም የየመን ፕሬዝዳንት ሕጋዊ መንግሥት የማስመለሱ ጉዳይ ሊሆን አይችልም ። የኢራንን መስፋፋት የግድ ማስቆም ወዳለባቸው ደረጃ መደረሱን ግንዛቤ በመወሰድ ይመስላል። የዓረቡ ፀደይ ሕዝባዊ መነሳሳት ያልዳሰሳቸው ሃገራት እንደመሆናቸው መጠን መከላከያ መስመሩን ማስመር የግድ ያስፈልገናል ከሚለው እምነት የሚነሱ ይመስለናል። የአሜሪካኖችን ድጋፍ ያረጋገጡበት ሁኔታም አለ - ሣዑዲያ ዓረቢያና ተቀጽላዎቿ። ኢራቅ፣ ሶሪያና ሊቢያን የመሳሰሉት የዓረቡ ዓለም ዓይነ-ግቡ ሃገራት ሁሉ ከመድረኩ ተገፍትረዋል። ገሚሱ ከተጨናገፉ ሃገራት ጎራ ተመድበዋል። አሁን የመን ዱካቸውን እየተከተለች ነው ። ግብፅም የራሷ ውስጣዊ ደህንነት ችግር አሽመድምዷታል። እነ አልጄሪያ በራሳቸው ውስጣዊ ችግር ተጠምደዋል። ዓረብ ያልሆኑትን እነ ቱርክና ፓኪስታንን በፀረ ሱኒ ዘመቻ ማስተባበር የምትችለውም ሣዑዲ ዓረቢያ ናት። በሂደቱ የጋራ ጥምር ጦር መቋቋም እቅድን በመተግበር በዓረቡ ራቢጣ ሕይወት የመዝራቱ ተግባርም እየተከናወነ ነው።

አወጋገኖችና አሰለላፎች ሲቀያየሩ በሰፊው ተመልክተናል። ቃል ኪዳኖች ሲታደሱ፣ የቆዩ ሲፈርሱ እንመለከታለን። አውደ ውጊያዎቹ እየሰፉ መምጣቸውንም ልብ ብለናል። በዚያው መጠን ‹ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ወደ አፍሪካ ቀንድ ይሸጋገራል ወይ?› ብዬ በመግቢያው ላይ የወረወርኩት ጥያቄ መልሱ ‹ማንም አያውቅም› ነው። አንድ ነጥብ ግን ግልፅ ነው። የአየር ድብደባው ስንት ጊዜ እንደሚዘልቅ አልታወቀም። ሣዑዲዎቹ ከደጋፊዎቻቸው ጋር በማበር ያቀጣጠሉት እሳት እየተንቦገቦገና ግለቱ እየጨመረ ነው። መቼና እንዴት እንደሚጠፋ የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። በተለይም የታቀደው የእግረኛ ጦር ማሰማራቱን ዘመቻ ከገፉበት። ጦርነት ከተለኮሰ በኋላ ለኳሹ መጀመሩን ነው እንጂ የሚያውቀው - ማለቂያው ከቁጥጥሩ ውጭ በመሆኑ ጦርነት የማስቆም ውሳኔው በእጁ አይደለም። ጠብ ጫሪው ወገን ትንኮሳውን መለኮሱን ያውቃል እንጂ የተበደሉትና የዘመቻ (የወረራ) ተቀባይ የሆኑት ወገኖችን ግብረ-መልስ በቅድሚያ አያውቀውም። በመካከለኛ ምሥራቅ ትርምሶች የምንመለከተውም ይኸው ነው። ለጊዜው እሳቱ የመንንና ዜጎቿን እየለበለበ ነው። ያም ሆነ ይህ የመን ወደ ነበረችበት ሁኔታ በምንም መልኩ አትመለስም። በዚህ ላይ የሁሉም ስምምነት ያለ ይመስላል። ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ወደ አፍሪካ ቀንድ ከመተላለፉ በፊት ግን ሣዑዲ ዓረቢያና የቀበጡ ልዑላኖቿን ያቃጥላል። ሣዑዲ ዓረቢያም ሆነች ኢራን። የዓረብ ሕዝቦች ለዲሞክራሲና ለነፃነት ያደረባቸውን ተስፋ ትርምሱ ለጊዜው አጨልሞታል። በየመን ትርምስምስና የሃገር መዝለፍለፍ የሚጠራ ወይም ዳቦ የሚቆረስለት አዲስ ስያሜ ምንም ይሁን ምን እነዚያ ተፋላሚ ኃይሎች የሚርመሰመሱባት ጭንጋፍ ሃገር ትሆናለች፤ ልክ ከዚህ በፊት ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ሊቢያ እንደሆኑት ማለት ነው።

ምናልባት የሣዑዲ ዓረቢያ የቀድሞ ንጉሥ ዓብዳላ በዓረቦች ስም ያቀረቡትን የመፍትሔ ሓሳብ እስራኤል እንድትቀበል መገፋፋቱ የልዕለ ሃያሏ ሃገር ፋንታና የቤት ሥራ ይሆናል። ይህ የተስተጓጎለውን የሰላም ውይይት እንደገና ማስጀመር ያስችላል። አሜሪካና አምስቱ ሃገራት ከኢራን የኑክሌር ስምምነት ተፈራርመው ከዚያ በኋላ ባልተዘጉ ዶሴዎች መነጋገር ከተሳካላቸው፤ ይህ መተረማመሱ ጋብ የማለቱን ምልክት ሊያሳይ ይችላል የሚል እምነት አለን። አንዱ የሶሪያ ጉዳይ ነው። ሌላው የየመን ጉዳይ ነው። የመኖች ወደ መነጋገሪያ ክብ ጠረጴዛ ተመለሰው ብዙ የፈጀውን የብሔራዊ መግባባት ኮንፈረንስ መግባቢያ ስምምነቶችና የገለፍ ሃገራት ተነሳሽነት አሁን ለውይይቱ በቂ መጀመሪያ ናቸው። ከዚያም አልፎ ተርፎ የፍልስጤም ጉዳይ ወደ አንድ መፍትሔ ሓሳብ አቅጣጫ የሚያመራበት ሁኔታ እየተመቻቸ ይመጣ ይሆናል የሚል ተስፋ ይፈነጥቃል። በዚህም የሣዑዲ ዓረቢያ ቦታ ከፍ ይላል። ከኢራን ጋር ለተደረገው ስምምነት ለእሷና ለለዘብተኛ የገልፍ ሃገሮች ማካከሻ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በዚያኑ መጠን የሱኒ-ሺዓ ውዝግቡም ጋብ ይላል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አሜሪካና ኢራን ሳይስማሙ ተፋልሰው ቢቀሩና ያካባቢ ምስቅልቅል ቢቀጥል ግን ትርምስምሱ ለሁሉም ይበቃል። ኢራን በተቀዳጀቻ የጠባቡን ቀይ ባሕር ወሽመጥ ብቻ ሳይሆን ቅርብና ሩቁን ያደበላልቃል ተብሎ ይፈራል። ያን ጊዜ የየመን ጉዳይ በእውነትም የአከባቢውንና የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ጭምር ያናጋል። ይህ ጦርነትና ፍጥጫ ወደ ቀይ ባህር ደጃፋችን ድረስ መጥቶ ሰላማችንን ማደፍርስ ይችላል።

በሌላ በኩል አሜሪካና ኃያላኑ ከኢራን ጋር የኑክሌር ስምምነት በቅጡ ከደረሱና ማዕቀቡም ከተነሳላት ብዙ አንገብጋቢ የአካባቢ ችግሮች ዶሴዎችን እልባት ለመስጠት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ ተብሎ ይገመታል። አሜሪካም እንደ ሻሁ ዘመን እንኳን ባይሆን (ኢራንን የአካባቢ ተቆጣጣሪ - የአካባቢ ፖሊስ ኃይል አድርጋ እስከ መመልከት ትዘልቃለች የሚል ግምት ባይኖርም) በአካባቢው እየተንሰራፋ የመጣውን "የሽበርተኞች ስጋት" እንደ አስከፊው ጠላት በመመልከቷ መተባበራቸው የግድ ነው። የሃያሉ ሃገር የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ዳዒሽን በጋራ የማዋጋቱን ተግባር በምር መያያዝ ነው። ሱኒ ዓረቦችን በተለይም በሱዑዲያ ዓረቢያ የሚመሩት የገለፍ ሃገራትን ላለማስኮረፍ የእነሱ ይሁንታ መገኘት ይኖርበታል እስከተባለ ድረስ። አባማ ከሥልጣን ከመሰናበቱ በፊት በይደር ሊተው የማይቻለው የፈልስጤም ጥያቄም አንድ እልባት የሚያስፈልገው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ላለፉት 66 ዓመታት በዚህ አካባቢ ለተነሳው ውዝግብ ሁሉ በምክንያትነት ለሚጠቀሰው፣ የዓረቦቹ ማዕከላዊ ችግር ሆኖ ለዘለቀው የፍልስጤም ጥያቄ የመፍትሔ ጎዳና ይጠርጋል ተብሎ ተስፋ ይጣልበታል። ይህ በተራው እስራኤሎች ከፍልስጤሞች ጋር ድርድር እንዲጀመሩ ብቻ ሳይሆን በአንድ ዘላቂ የመፍትሔ ሓሳብ ዙሪያ እንዲፈጣጠሙ

የሚያስገድዳቸው ስምምነት መደረሱ የልዕለ ኃያሉ መንግሥት ኃላፊነት ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በአካባቢው ሊቀጣጠል የሚችለው ትርምስምስ አሜሪካኖቹ አሸባሪነትን ከሱኒ ሙስሊሞች ጋር ብቻ ያቆራኙት ያስመስላል። የሙስሊም ሽብርተኞችን ወካይ አድርገው የሳሉት የሱኒ መዝሓብ አማኞች የሆኑትን ዳዒሽና አል-ቃዒዳን ነውና። ይህ ደግሞ ከሺዓዎሽ ወካዩዋ ኢራን ጋር ያስተቃቅፋቸዋል።

የገልፍ ዓረብ ሃገራት አሚሮችም ኢራንን በመፍራት የአሜሪካ የሙሣሪያ እንዱስትሪዎች ደንበኛነታቸውን ክብረ-ወሰን ሳያስነኩ ይቀጥሉበታል። ለነዚህ እንዱስትሪ ኮምፒለክስ የተመቻቸው ደግሞ ለአሜሪካ የሥልጣን ኤሊቶች መቼም እንደሚስማማ ሳይታለም የተፈታ ነው።

◇ ◇ ◇

# የሰብአዊ ሙብቶች እረኛ! ፕሮፍ!

*ከገጽ 14 የዞረ*

ከቁርጠኝነት መሆኑን አትጠራጠሩ። አንድ ምሳሌ ልጨምርበት።

የ1993 ዓ.ምህረቱን የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች የሙብት ጥያቄ ተከትሎ የመንግስት ታጣቂዎች በወሰዱት እርምጃ አዲስ አበባ ውጥረት ሰፍኖባታል። እኛም በየሆስፒታሉ እየተዘዋወርን ስለተገደሉና ስለቆሰሉ ዜጎች መረጃ እናሰባስብ ነበር።አንድ ቀን ታዲያ እኔና ባልደረባዬ ያሬድ የካቲት 12 ሆስፒታል ተገኝተን አንድ በጥይት የቆሰለ ወጣትን ካነጋገርንና ፎቶ ካነሳነው በኋላ ልንወጣ ስንል እንያዛለን። ወዲያውም ታፍነን ጃንሜዳ ወደሚገኘው 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰድን። ቆይቶ እንደወጣን መቅረታችን ያሳሰባቸው ባልደረቦቻችን ባደረጉት የማፈላለግ ጥረት የታገትንበት ቦታ ይደረስበታል ። ይሄኔ ፕ/ር መስፍን፣ ፕ/ር አንዳርጋቸውና ዶ/ር መኮንን (ነፍሳቸውን ይማረውና) ከተፍ ይላሉ። ታጣቂዎቹ መግባት አትችሉም ባይ ነበሩ። ፕሮፍ ግን ወይ ፍንክች አሉ። "በህጉ መሰረት መጠየቅ አለብን፣ የታሰሩበትን ምክንያት ማስረዳትም ግዴታችሁ ነው።" በሚል አቋም ጸኑ። ከቦታውም ንቅንቅ አልልም አሉ። ጽናታቸው ያለውጤት አልቀረም፤ ከምሽቱ 2 ሰዓት ላይ እኔና ያሬድ በዋስ ለመለቀቅ በቃን። ስንፈታ ፕሮፍ በሩ ላይ ቆመው እየጠበቁን ነበር። ልዩ መመካት ነበር የተሰመን። . . . ሁሌም የኢሰመጉ ልጆች ፕሮፍን እንደ አባታችን ነበር የምናያቸው። ፕሮፍም እንደልጆቻቸው ነው የሚያዩን። በስራችን ይተማመናሉ፤ ይጋፈጡልናል፤ ይጨነቁልናልም። ይህን መሰል አጋር የት ይገኛል?

**<u>አዛኙ ሰው፡-</u>**

ፕሮፍ ላመኑበት ነገር ከብረት የጠነከረ መንፈስ ቢኖራቸውም የሰው ልጆችን ጉዳትና ሰቆቃ ማየት የሚያንገበግባቸው እጅግ ሩህሩህና ነፍሰ ስስ ናቸው። ከውስጥ እየፈነቀለ የሚወጣ ዕምባ ግርማ ሞገስ የሰፈነበት ፊታቸው ላይ ክንብል ክንብል እያለ ሲወርድ ላየ ነፍስያን ይረብሻል። ይህን መሰሉን ስሜት ካየሁባቸው አጋጣሚዎች መሀል የኢሰመጉ የክፍ ቀን ደራሽ የሆኑትን ባልንጀራቸውን ዜና እረፍት የገለጹበት አጋጣሚ ይታወሰኛል። እኒህ ሰው የስዊዘርላንድ ኤምባሲ ከመንግስት ጋር በመሞዳሞድ ለኢሰመጉ በርዳታ መልክ የሰጠው ገንዘብ ይመለስልኝ ባለ ወቅት ኢትዮጵያዊያን ሲቆጡና ፕሮፍም መኪናዬን ሸጬ እመልሳለሁ ሲሉ ደራሽ ሆነው አጋርነታቸውን ያሳዩ አገር ወዳድ ነበሩ። ፕሮፍ የእኚህን ወዳጃቸውን የመከራ ጊዜ ደራሽነት አስታውሰው በኢሰመጉ ጉባዔ ላይ ያነቡበት ሁኔታ ዛሬም ድረስ አይረሳኝም።

ፕሮፍ ከድሀው ህዝብ የዕለት ተዕለት ህይወት ላለመራቅ ሲሉ ፒያሳ ኤነሪኮ ካፌ ጀርባ የምትገኘው ጠባብ የኪራይ ቤታቸውን ሙጥኝ ብለው የቀሩ ሰው ናቸው። "እኛ ኢትዮጵያውያን ድህነትን ቶሎ እንረሳለን " የሚለው አባባላቸውን በተለይም በዚያች ጠባብ አፓርትመንታቸው ውስጥ ሆነህ ስታስበው የህዝቡን ህይወት በመኖር ጭምር ለመጋራት የቆረጡ ምኞት ለምኔ መሆናቸው ይታይሀል። እንደ ጓደኞቻቸው ቪላ ገንብቶ ወደ ቦሌና መሰል ሰፈሮች መሄድ ለፕሮፍ አይታሰብም። በድሀ ህዝብ መሀል እራሱን በግንብ አጥር አጥሮ ድህነትን የሚሸውድ ስብዕና የላቸውም - ፕሮፍ።

እኚህ ብርቅ ሰው በሰው ቁስል ይሰቃያሉ። በስቃዩ ይቃትታሉ። ዝም ብሎ በማዘን ግን አይገቱም። ለችግሩ የመፍትሄ አካል ለመሆን ያለእንቅልፍ ይዳክራሉ እንጂ። ለዚህ አገላለጼ እንደ ማሳያ እንዲሆን ሰኔ 4 ቀን 1994ዓ.ም. በአዲስ አበባ የተከሰተን አንድ አጋጣሚ ላስታውስ። በወቅቱ የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ሊደረግ ሽር ጉድ ተይዞ ነበር። መዲናዋ ውስጡን ለቄስ ብላ ላይ ላዩን ጸድታ እንድትታይ ሹማምንቱ ከካድሬዎቻቸውና ከጭፍራ ታጣቂዎቻቸው ጋር ውርውር ይላሉ። በአገዛዙ የከተማዋ የላይ ውበት አቆሻሽና የድህነቱ ገመና ገላጭ ተደርገው የተፈረጁት ደግሞ ጎዳና አዳሪ መጠለያ አልባዎች ነበሩ። በዚህ ሳቢያ ‹የአዲስ አበባን መልካም ገጽታ ለመጠበቅ› በሚል ሰኔ 4 ቀን 1994 ዓ.ም. በፌደራል ፖሊስ ተዘመተባቸው። በስቴዲዮም ዙርያ፣ 4ኪሎ፣ እስጢፋኖስ ቤ/ክርስቲያን አካባቢና በሌሎችም ቦታዎች ቁሩን ችለው የተኙ ከ200 በላይ ምስኪን ኢትዮጵያውያን ከለሊቱ 7 ሰዓት ላይ እየተቀሰቀሱ ከአዲስ አበባ 55 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ወደሚገኝ በልዩ ስሙ ጎርፍ ተብሎ ወደሚጠራ ገበሬ ማህበር ተወስደው ጫካ ውስጥ ተጣሉ። በድቅድቅ ሌሊት መከራ ከወረደባቸው ከነዚህ ወገኖቻችን መሀል ዓይነስውራን፣ አካለ ስንኩላን፣ ህጻናት፣ ሴቶችና አረጋውያን ይገኙበታል። የፌደራል ፖሊሶች ሰለባዎቻቸውን ጫካ ውስጥ ‹ካራገፏቸው› በኋላ በመሳሪያ እያስፈራሩ ዳግም ለመመለስ ከሞከሩ እንደሚገድሏቸው ዝተው ለዱር አራዊት ይተውአቸዋል።

የዚህ መጥፎ ዜና ጥቆማ ፕሮፍ ጋ የደረሰው በአንድ ማምለጥ በቻለ የጎዳና ተዳዳሪ አማካኝነት ነበር። እኛ በጠዋት ቢሮ እንደገባን ፕሮፍ ደውለው ጥቆማውን ካደረሱን በኋላ ባስቸኳይ ወደስፍራው እንድናመራ አበከሩን። እኔና የመስርያ ቤታችን ሹፌር ወዲያው ነበር ጉዞ የጀመርነው። ከአካባቢው ስንደርስ ያየነው ነገርም ስሜትን ክፉኛ የሚፈታተን ነበር። ሰለባዎቹ እንደነጋላቸው ወደ አዲስ አበባ የእግር ጉዞ ጀምረው ነበር። ሌላ ምን መሄጃ አላቸው? ቤሳ ቤስቲ የሌላቸው ጎስቋሎች። በክራንች የሚያዘግሙ፣ በእንፉቅቅ የሚሄዱ፣ በሰው እየተመሩ የሚጓዙ ዓይነስውራንና አረጋውያን አግኝተን አነጋገርን። መረጃ ሰበሰብን። ሁሉም የሚሰጡን መረጃ የሚሰቀጥጥ ነበር። በዚያች ክፉ ለሊት አንድ ሰው በጅብ ተበልቶ ነበር። ተራፊዎቹ እንዴት ሰብሰብ ብለው ዙርያ ክብ እየሰሩ ጋዜጣና የለበሱትን ልብስ ሳይቀር እያወለቁ እሳት በማንደድ ከጅብ ጋር ሲታገሉ እንዳደሩ ተረኩልን። የምንሰማው ብቻ ሳይሆን የምናየውም ቢሆን አንጀት የሚያላውስ ነበር። ርሀቡና የሌሊቱ ውርጭ ያጠወለጋቸው፣ ፍርሀትና ተስፋ ማጣት የደቆሳቸው፣ ደራሽ የለሽ ንጹሀን። ምን እናድርግ? ከስራው ባሻገር ሰብአዊነታችን ኪሳችንን ተገዳደረው።

በዚያው አፍታ ከጓደኞቻቸው ጋር መኪና ውስጥ ተቀምጠው ጉዳዩን በአጽንዖት ወደሚከታተሉት ወደ ፕሮፍ አመራሁና ዝርዝር ሁኔታውን ገለጽኩላቸው። እየተናገርኩ የፕሮፍ ገጽታ በሀዘን ሲኮመታተር፣



⇨

በቁጭት ሲብሰከሰክ ይታየኝ ነበር። . . . ወዲያው እጃቸውን ወደ ኪሳቸው ሰደዱ። ፕሮፍ ከ1000 ብር የማትበልጥ ጡረታ እንዳለቻቸው አውቃለሁ። እሷው ነች መተዳደርያቸው። ካላቸው ብር ከፈሉን ገምሰው ሰጡኝና "እባክህ ዳቦና ውሀ ገዝተህ ስጣቸው፣ መጓጓዣም እርዳቸው?" አሉኝ። አጣዳፊው ስራ ህይወት ማትረፍ ነበርና። . . . ያሉትን ፈጽመን ፊትና ኋላ እየተከታተልን አዲስ አበባ ገባን።

ፕ/ር መስፍን (ፕሮፍ) መላው ህይወታቸውን ለህዝብ ጥቅም የሰጡ ብርቅ የአገር ሀብት ናቸው። ኢሰመጉም በዚያን ሰዓት እኚህን የመሰለ መሪ፣ አስተባባሪና ትጉህ ሰራተኛ በማግኘቱ ዕድለኛ ነበር። እኔም በግል ከፕሮፍ ጋር መስራት በመቻሌ እድለኛ ነኝ እላለሁ። ታላቁ ሰው ያስተማሩኝና ያሳዩኝን የብርሀን መንገድ እያሰብኩ በኢሰመጉ የተሰጠን ስልጠና ማብቂያ ስነ - ስርዓት ላይ ያቀረብኳትን "ብርሀን ይሁን!" የምትለውን መጣጥፌን አርቲስት ጠለላ ከበደ በህዝቡ ፊት ለፕሮፍ በማስታወሻነት እንድሰጥ ስትጋብዘኝ እንዴት ፍንክንክ ብዬ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከዚያ በኋላም በኢሰመጉ ሰራተኝነት ያሳለፍኩት ህይወት ምንም እንኳን ስራው ነፍስን ቢያሳሳና ዋጋ ቢያስከፍልም እንኳ የምኮራበትና የምመካበት ነው። ፕሮፍ ለበጎቹ የሚጨነቅ ታላቅ እረኛ ናቸው። በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባራቸውም የሚያንጹ፣ የሚያምኑበትን የሚገልጹ፣ የሚገልጹትንም የሚኖሩ ልዩ አርአያ ናቸው። ዛሬ እኛ ስደት ላይ ነን። ፕሮፍ ግን በዚያቹ በሚወዷት ምድር በብዕራቸው እያስተማሩ፣ እየመከሩና እያነጹ ክቡር የሀገር ሽማግሌና ህያው ቅርስ ሆነው እየደከሙ አሉ። . . .ብዙ የሚባልላቸው ሰው ቢሆኑም እኔ ግን በዚሁ ላብቃ። ረጅም እድሜና ጤና እየተመኘሁ፣ ዕድሜያቸውን ሁሉ የደከሙለትን የኢትዮጵያን ትንሳኤ እውን ሆኖ ያዩ ዘንድ እጸልያለሁ። ብርሀን ይሁን - ፕሮፍ!

ብዙዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልሱ ጥበበኞች እንደከዋክብት ለዘላለሙ ይደምቃሉ!! ፕሮፍ - የኢትዮጵያ ኮኮብ!

◇ ◇ ◇



## በካድሬዎች የተወረረ ዩኒቨርሲቲ ሆኗል ነው የምልህ አለቀ!

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ

ከገጽ 23 የዞረ

ዛሬም ስልጠና ነገም ስልጠና ፤ እዚህም ስልጠና እዚያም ስልጠና . . . ይሉሃል። የሰለጠነው ደግሞ ውጤት ማምጣት ሲያቅተው፤ እውቀት አንሶት ነው አይሉም፤ ስልጠና አንሶት ነው ይባልና ሌላ ስልጠና ይዘጋጃል፡፡ ስልጠናው ገንዘብ መብያ ነው። ምንአለፋህ ዩኒቨሲቲው ማሰልጠኛ ጣቢያ ሆኗል።

አንድ የሚያስቅ ነገር ልንገርህ፦ በአንድ ኢንስቲቲዩት ውስጥ 5 የሚሆኑ ፕሮፌሰሮች (መምህራን) ፔፐር ያቀርባሉ ተብሎ እኔም ታዳሚ ነበርኩ። በሚገርም መልክ አዳራሹ በተማሪዎች ተጨናንቋል። ተማሪው እንደዛ በብዛት ሲሳተፍ አይቼ ስለማላውቅ ገረመኝ፡፡ በኋላ ሁሉም ነገር አልቆ ከአዳራሹ ስንወጣ ተማሪው ውጭ ላይ ሰልፍ ሲይዝ አየሁት። ምንድነው ሰልፉ? ብዬ ስጠይቅ ፤ ‹አይ ዛሬ ፔፐር የሰሙበትን አበል ሊቀበሉ ነው› አሉኝና አሳዘኑኝም አሳቁኝም።

እግዚአብሄር ያሳይህ! የፕሮፌሰሮችን ፔፐር ለመስማት ገንዘብ ይሰጣችኋል ተብሎ አበል የሚሰጥበት የመማር የማስተማር ሂደት፤ ከዚህ በላይ ምን ሙስኝነት አለ? እንዴት ነው አንድ ተማሪ የፕሮፌሰሮቹን ፔፐር ለመስማት ገንዘብ የሚከፈለው? ምን ማለት ነው? ባጠቃላይ ስልጠና የሚሉት ነገር ደጃዝማቾቹ ግብር አብልተው የፈለጉትን የሚናገሩበት መድረክ እንደሆነ ተማሪውም በግልጽ እየተናገረው ነው።

ካድሬዎቹ መጥተው ለመምህራኑ ስልጠና ሲሰጡ ተማሪው ‹ደጃዝማቾቹ መምህራኑን ግብር እያበሉ ነው› እያለ የሚሳለቅበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነው ያለነው። በኛ ግዜ የፕሮፌሰሮቻችንን ሌክቸር ለመስማት በምን አይነት ጉጉት እንደምንጠብቅ ሳስበውና ይህን ሳይ የደርስንበት ዝቅጠት ያስፈራኛል።

__አሻራ፦__ መንግስት አይን ባወጣ መልክ በመማር ማስተማሩ ሂደት ጣልቃ ገብቶ እንዲያውም ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልክ ዩኒቨርሲቲው በካድሬዎች ቁጥጥር ስር ውሏል እያሉን ነው፤ ይህ ደግሞ የትምህርት ጥራቱን በእጅጉ ጎድቶታል፤ ለመሆኑ ከዚህ በመነሳት ወዴት እየተኬደ ነው ይላሉ?

__ዶ/ር ዳኛቸው፦__ እንዲያውም የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ጥሩ አድርጎ የሚያሳይ አንድ ምሳሌ ልንገርህ፤ ራሴ የተሳተፍኩበት ነው። ሊቀመንበር ምረጡ እንባልና እንሰበሰባለን ፤ እሺ ብለን 3 እጩዎች ተጠቁመው ለውድድር ቀረቡ። ድምጽም ሰጠን።አንደኛው 10 ድምጽ አገኘ፤ ሁለተኛው 4 ድምጽ አገኘ፤ 3ኛው 0 አገኘ፡፤ በኋላ ዜሮ ያገኘው ሊቀመንበር ሆነ ተባልን። የሚገርም ነው።

ይሄ ዜሮ ያገኘው ዶክተር ወዳጄ ነበርና ለመሆኑ አንተ በምን ታምር ነው ሊቀመንበር የሆንከው? አንድ ሰው እንኳ መች ድምጽ ሰጠህ ብዬ ጠየቅኩት። እሱም ሲመልስ " ምን አውቃለሁ ማን እንደነገራቸው አላውቅም በግማሽ ወገን ከእገሌ ዘር መሆኔን አውቀው ነው" ብሎኝ እርፍ። ይቅናህ ብዬ ተለየሁት። እንግዲህ እዚህ ደረጃ ደርሷል ነው የምልህ። ወዴት እየሄድን ነው ላልከው፤ ዩኒቨርሲቲው አልቆለታል አልኩህ እኮ።

አንድ ጊዜ አንድ የመከላከያ ሰራዊቱን ከፍተኛ ባለስልጣን BPR እንደ ሌሎች መስሪያቤቶች ሁሉ በመከላከያ ውስጥ እየተሰራበት ነው ወይ? ብለው ጠየቁት፤ እሱም ሲመልስ "አይ ይህ አይነቱ BPR ለኛ አይሰራም ለኛ የሚሰራውን እያስጠናን ነው" ብሎ መለሰ፡፤ ይህን ያነሳሁት ለምንድነው? መከላከያ ሰራዊቱ እንኳ BPR ለኛ አይሰራም ብሎ አልቀበል ሲል፤ ፍጹም ከመንግስት ተጽእኖ ውጭ መሆን የሚገባው ዩኒቨርሲቲ ግን ሁሉን ተቀብሎ አንዴ BPR አንዴ 5 ለ 1 እያለ ቀልድ መያዙን ልነግርህ ፈልጌ ነው።

__አሻራ፦__ ከቋንቋ ከባህልና ከታሪክ ጋር ቁርኝት ያላቸውን ዲፓርትመንቶች ማዳከምና ብሎም መዝጋት የተፈለገበት ምክንያትስ ምን ይሆን?

__ዶ/ር ዳኛቸው፦__ 6 ኪሎ እየሞተ ነው። 6 ኪሎ ሲሞት 5 ኪሎ ይጠወልጋል የሚል አርቲክልም ጽፌያለሁ። እነሱ 6 ኪሎ ውስጥ ያሉ ዲፓርትመንቶችን በቆሎ አያመርቱም ይሏቸዋል። ሰው በበቆሎ ብቻ አይደለም የሚኖረው። የሃገሪቷን የወደፊት አቅጣጫና ህልውና ላይ ግዙፍ ሚና የሚጫወቱ ብዙ የትምህርት ክፍሎችን ያካተተው ሶሻል ሳይንስ አንቱ የተባሉ ምሁራንን ያፈራ ተቋም ነው። የሚጠላውም የተለየ ሃሳብ የሚፈልቅበት ተቋም በመሆኑ ነው። እነሱ የሚፈልጉት ስልጠና እየሰጡ 50 አመት የሚገዙትን በቆሎ አምራች ዜጋ ማፍራት ነው። እኛ የእንጀራ ልጆች ሆነናል ነው የምልህ አለቀ! ደቀቀ!

__አሻራ፦__ ስለ ጊዜዎ በጣም እናመሰግናለን !

__ዶ/ር ዳኛቸው፦__ እኔም በጣም አመሰግናለሁ! በርቱ!

## አደጋን ንቀው ፣ ሞትን ለሚተናነቁ ዜጎቻችን . . .

(ከገጽ 32 የዞረ)

በሁለት ፓስፖርት የሚንቀሳቀሱ፣ የኢህአዲግ ስልጣን ቋፍ ላይ የደረሰ ሲመስላቸውና ኮሽ ባለ ቁጥር የውጪ ፓስፖርታቸውን የሚመዙ፣ የ‹አዕምሮ› ስደተኞች መኖራቸውን ውስጥ አዋቂዎች በየአጋጣሚው የገለጹት ነው። በምርጫ 97 ሰሞን አውሮፓና አሜሪካ ተሸሽገው ገዢው ፓርቲ በታንክና በጠመንጃ አገር ያረጋጋ ሲመስላቸው ወደ አዲስ አበባ የተመለሱትንም አለመዘንጋት ነው። ጎምቱ ባለስልጣናት ሳይቀሩ የአሜሪካ ዳይቨርሲቲ ቪዛ ለመሙላት የሚሽቀዳደሙት ‹ብድቡሽት ላይ የተመሰረተው› መንግስታቸው አንድ ቀን ጠንከር ያለ ንፋስ ሲገፋው እንደሚደረመስ በመገንዘባቸው መሆኑን አልጠራጠርም። በምርጫ 97 በርካታ ዜጎቻችን በግፍ መገደላቸውን አስመልክቶ በነበራቸው ሚና ጣት ከሚቀሰርባቸው አንዱ ( የአዲስ አበባ ፖሊስ አዛዥ የነበሩት) የህወሀቱ ተስፋዬ መሪሣ የዲቪ ጣጣቸውን ጨርሰው ለአለቆቻቸው ሳያሳውቁ ወደ አሜሪካ ለመሻገር ሲሞክሩ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ በደህንነቶች ተይዘው እንደነበር በወቅቱ በነጻው ፕሬስ ህትመቶች ላይ ተዘግቦ ጸሀይ የሞቀው ዕውነት ነው። ይህ ከሆነ ከወራት በኋላ ‹አረጋግተው› ቤተሰባቸውን ይዘው አሜሪካ ቀልጠው መቅረታቸው በአጣብቂኝ ውስጥ የሚኖሩት የአህዴድ፣ ብአዴን ተላላኪ ሹማምንት ብቻ ሳይሆኑ የገዢው ፓርቲ አስኳል የህወሀት አለቆች ሳይቀሩ ስደት ላይ ያነጣጠሩ መሆናቸውን ያመላከታል። የኦሮሚያ ፕሬዛዳንቶች የነ ሀሰን ዓሊ፣ የነጁናዲን ሳዶ . . የነ አልማዝ መኮ፣ የነ ዮናታን ደቢሣ . . . ወዘተ አሳዳጆች ጭምር የሚሠደዱባት ሀገር - ኢትዮጵያ።

ዛሬ የተለያዩ ባለሰልጣናት ነፍሰ ጡር ሚስቶቻቸውን አሜሪካና አውሮፓ እየሄዱ እንዲወልዱ የሚያደርጉት ለልጆቻቸው ሌላ የስደት አገር ፍለጋ መሆኑ ሊሸሽግ የሚችል አይደለም። ፖርቹጋላዊው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝ ከሰሞኑ ከተሰናበቱ በኋላ ‹ለዜጎቻችን ቅድሚያ ይሰጣል› በተባለው መስፈርት ተተኪ የሆኑት ዮሀንስ ሳህሌ (የቀድሞው የራስ ሆቴልና የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋች) ዜግነት አሜሪካዊ ሆኖ መገኘቱንም እንዳትዘነጉ።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር ተስፋዬ መሪሣን ስደት ይዘግቡ የነበሩ፣ የስራቱን ቅጥ ያጣ አምባገነንነት፣ የአፈናውን ልክና የዜጎችን ሰቆቃ እየተከታተሉ በጽናት ሲያጋልጡ የቆዩ የነጻው ፕሬስ ህትመቶች በተራቸው የስርዓቱ አፈና ሰለባ ሆነዋል። የአዲስ አበባ ጎዳናዎች ከስርዓቱ ደጋፊ ጋዜጣና መጽሄቶች በቀር ነጻ ፕሬስ እንደናፈቃቸው እንዲቀሩ ተደርገው ጭር ብለዋል። የነጻ ፕሬስ ህትመቶች ይዘጋጁባቸው የነበሩ ቢሮዎች በይፋ በመንግስት ትዕዛዝ ሲታሸጉ፣ የስርዓቱ ቀላጤ ፍ/ቤቶችም የፖለቲካ ህትመት አሳታሚ ድርጅቶች ንብረት ተወርሶ ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲሰጥ ማለትም በመንግስት እንዲወረስ ማድረጋቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በተለያዩ ጊዚያት በዚሁ በጋዜጠኝነታቸው ምክንያት የዓመታት እስር እየተበየነባቸው ሲታሰሩና ሲፈቱ የዘለቁ ጋዜጠኞች የደህንነት ኃይሉን አፈናና ማሰቃየት ተቋቁመው ሀሳብን በነጻነት የመግለጽና የፕሬስ መብት እንዲከበር ቢተጉም ቀጣዩ ዕጣ ፈንታቸው በጸረ ሽብር ህጉ እየተከሰሱ ቋሚ ኑሯቸውን በወህኒ እንዲያደርጉት መታቀዱን አስተማማኝ መረጃ በማግኘታቸው ለመሰደድ ተገደዋል።

❋ ❋ ❋

ኤፕሪል 19 ቀን 2015ዓ.ም. በነእያሱ ይኩኑአምላክ፣ ባልቻ በለጠ . . . ወዘተ ላይ ‹ኢስላሚክ ስቴት ኢን ኢራቅ ኤንድ ዘ ሌቫንት› እየተባለ የሚጠራው ቡድን የሊቢያ ቅርንጫፍ የፈጸመው ኢሰብዓዊና ዘግናኝ ግድያ ይፋ ተለቆ ትኩረት ሳቢ መሆኑ እንጂ ባለፉት ዓመታት ዜጎቻችን ከስደት ጋር በተገናኘ ፍዳቸውን ሲቆጥሩ ነው የኖሩት። ዕድል ቀንቷቸው አውሮፓ የደረሱ ወንድም እህቶቻችን በሰሀራ በርሀ እያለፏቸው የመጡ አስከሬኖቻችና በሜድትራንያን ባህር ሰምጠው የቀሩ ወገኖቻችን ሁኔታ የአዕምሮ ሰላም እንደነሳቸው ይገልጻሉ። ይሁንና አገር ቤት የቀሩ ወንድም እህቶች፤ ወዳጅና ዘመዶች በዚሁ መንገድ ሲሰደዱ "ይቅርባችሁ" ለማለት አይደፍሩም። ካገር ያስወጣቸውን መከራ ልክ ያስታውሳሉና። አትሞክሩት ቢሉም የሚሰማቸው እንደማይኖር ያምናሉ። እነሱም መሰል የሰቆቃ ታሪኮችን እየሰሙ ነበርና ያንን አስከፊ የስደት መንገድ ያቋረጡት።

በአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት በሚታይ ሁኔታ ከተመዘገበ የስደተኞችን ከአገር የመኰብለል ሂደት መቀነስ እንደሚቻል በጉዳዩ ዙርያ ጥናት ያደረጉ ኤክስፐርቶች የሚገልጹት ነው። ከኢትዮጵያ አንጻር ግን አገዛዙና አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማት "ተመዝግቧል" የሚሉት ዕድገት የተሰዳጆችን ቁጥር ከቶም ሲቀንስ አይታይም። በአገሪቱ የታየው የኢኮኖሚ ዕድገት (ቢጋነንም) ፈጽሞ ፍትሀዊ ክፍፍል የማይታይበት መሆኑ በህዝቡ ህይወት ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥ ያላስመዘገበ መሆኑን የሚገልጹ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች በሚነካ ህንጻ ብቻ ዕድገት እንደማይለካ ይጠቅሱና በኢትዮጵያም ሰብዓዊ ዕድገት ላይ ያተኮረ መሻሻል ባለመታየቱ ተስፋ የቆረጡ ዜጎች በገፍ እንዲሰደዱ ያደረገ መሆኑን ያብራራሉ።

በኢትዮጵያ ጉዳይ በርካታ የጥናት ጽሁፎች በማቅረብ የሚታወቁት የሚኒሶታ ሴንት ሜሪ ዩንቨርሲቲ መምህር ፕሮፌሰር ሀሰን ሁሴን "የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራምና የኦክስፎርድ ዩንቨርሲቲ የድርጊትና ሰብዓዊ ልማት ኢኒሼቲቭ" የተለያዩ መስፈርቶችን አቅርበው ባካሄዱት ምርምር ሀገሪቱ ከአፍሪካ ሁለተኛዋ ውራ (ኒጀር ብቻ ትከተላታለች) መሆኗን ማሳየቱን አጣቅሰው " . . . በነዚህ ጥናቶች መሰረት አገሪቱ በማህበረ ኢኮኖሚ፣ በመልካም አስተዳደርና በሰብዓዊ ልማት ያስመዘገበችው ውጤት ከስራ አጥነትና መንግስት ከሚከተለው እኩልነትን ከሚያሳጣ ጎሳ ተኮር አካሄድ ጋር ተደማምሮ (በከፊል) የጅምላ ስደቱ እንዲጧጧፍ አግዟል" የሚል አመለካከት ያቀርባሉ።

የሀገሪቱ ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሄድ ከስራ ፈትነቱ ጋር ተዳምሮ የበረከተው (በሶሺዮሎጂስቶች ቋንቋ "ዘ ሬስትለስ ጀኔሬሽን" የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል መልካም አስተዳደር ያሰፍናሉ በሚባሉ ሀገራት እንኳ ከቁጥጥር ውጪ ሊሆኑ የሚችሉባቸው ዕድሎች ከፍተኛ መሆናቸውን የሚጠቅሱ ምሁራን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አንባገነን አገዛዞች ስር ይህን መሰሉ ቀውስ ከስደተኞች ቁጥር መበራከት ባለፈ ለወደፊት ሀገራዊ ህልውና ጭምር አሥጊ እንደሚሆን ይገልጻሉ። ለስደት ማቀጣጠያ የሚሆኑ በርካታ ሁኔታዎች ባሉበት ሀገር መንግስት የፖለቲካ ምህዳሩን እያጠበበ በሚጓዝበት እርምጃው ሲቀጥል ስደቱም በዚያው ልክ እያሻቀበ እንደሚሄድ የጠቆሙት ፕሮፌሰር ተኮላ ሀጎስ ደግሞ " . . . ተስፋውን የተነጠቀ፣ ተስፋው የተሟጠጠ ዜጋ ምንም የሚያስፈራው ነገር አይኖርም።" ይላሉ።

የፕሮፌሰር ተኮላን ሀሳብ የሚያጠናክረው አንድ ዕውነት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ለስደት በወጡበት አንገታቸው በሰይፍ መቀላቱን ከሰሙ በኋላ ሳይቀር ዜጎቻችን "አስፈሪውን ነገር ከመፍራት" ውጪ ሆነው ዛሬም ከሰማይ እሳት ወደሚዘንብባት የመን እና

ከአሸባሪዎች እጅ ወዳልወጣችው ሊቢያ መጓዛቸውን አለማቆማቸው ነው። የአልጀዚራ ዘጋቢ በ‹እስላማዊ መንግስት› የተገደሉ ወጣቶችን ቤተሰብ ሀዘን ለመዘገብ ወደ ጨርቆስ ጎራ ባለችበት ወቅት ያነጋገረቻቸው ወጣቶች "ጓደኞቻችን ዕጣ ፈንታቸው ሆኖ በአሰቃቂ ሁኔታ ቢገደሉም ሌሎች ብዙ የምናውቃቸው ሰዎች ግን ሊቢያን አቋርጠው እንግሊዝና ጀርመን መግባታቸውን በማረጋገጣችን እኛም ከቀናት በኋላ ጉዟችንን እንቀጥላለን" ማለታቸውን መርሳት አይቻልም። ይህም በአገሩ ተስፋው ሙሉ ለሙሉ የተሟጠጠበት ሰው ጥቂትም ቢሆን የመትረፍ ተስፋ አይጥፋ ይሆናል በሚል የሞት መላዕከት የሚያንዣብቡበትን የስደት ጉዞ እስከመምረጥ መድረሱን የሚያሳብቅ መሪር ዕውነት ነው።

ኢትዮጵያውያን ዛሬም በመተማ በኩል የሱዳንን ምድር ረግጠው በሠሀራ በርሀ በኩል የ3,700 ኪ.ሜ. አስቸጋሪ ጉዞን በማድረግ ከሊቢያ ርዕሰ መድና ትሪፖሊ ለመድረስ ጉዟቸውን ቀጥለዋል። በለስ ቀንቷቸው እዚያ ቢደርሱ እንኳን ደላላዎች የሚያቀርቡላቸውን የደከሙ ጀልባዎችን ተጠቅሞ የሜዲትራንያን ባህርን ማቋረጥ ይጠበቅባቸዋል። በረሀው የሞት ጥላ ያጠላበት፣ ባህሩም የሞት መንፈስ ያረበበት መሆኑ አልጠፋቸውም። ሀገር ውስጥ ከነገሰው ተስፋ ቢስነት ግን ይሻላል ባይ ሆነዋል።

በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት የተመሰረተ የወጣቶች ማህበር አመራር የሆነው ባህሩ ለማ ለአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ስለዚሁ ሁኔታ የተናገረውን መጥቀሱ በሀገሩ የተማረረውን "ፍርሀት አልባ" ትውልድ አቋም ያንጸባርቃል። ባህሩ እንዲህ ነበር ያለው፡-

". . . ለበርካታ ወጣቶች ጉዞው አደገኛ መሆኑን፣ እዚሁ አገር ውስጥ ሰርቶ መለወጥ እንደሚችሉ ብነግራቸውም አይሰሙኝም። ከሞቱም ሰማዕት መሆናቸው እንዲታወቅላቸው ሲነግሩኝ መጽሀፍ ቅዱስ ሠጥቼ እሸኛቸዋለሁ። አንዳንዶቹ ዕጣ ፈንታችንን እንሞክራለን እያሉ ነው የሚጓዙት።"

የስደትን አስከፊ ቀውስ ለመፍታት የሚያስችለው ቁልፍ - ስልጣን በያዘው አገዛዝ እጅ የሚገኝ መሆኑን በጉዳዩ ዙርያ ጥናት ያደረጉ ኤክስፐርቶችና ምሁራን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እያሳሰቡ ነው፤ ሰሚ ጆሮ ባያገኙም። ስደተኛ ወገኖቻችንን ከቦንድ ግዢ ባለፈ እንደዜጋ በቁም ነገር የማያስባቸው፣ በአገራቸው ተስፋ አጥተው ለአስከፊ ስደት እንዲበቁ ዓይነታ ምክንያት የሆናቸው አገዛዝ፤ በጊዚያዊ ሆይሆይታ፣ ለቅሶ በመድረስና ደላሎችን በማወዝ ችግሩን እንደማይፈታው ህዝቡ ጠንቅቆ የተረዳው መሆኑን ሊያውቀው ይገባል። ይህን መሰሉ መሰረታዊ ቀውስ ባንድ ሰሞን ‹ሆያ ሆዬ› ሊድበሰበስ እንደማይችል፣ ይልቅስ በብሄራዊ ደረጃ መፍትሄ ሊበጅለት እንደሚገባ የሚጠቁሙ እንደ ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ ያሉ ምሁራን የሚያቀርቧቸውን ሀሳቦች የሚያጤን መንግስት ሊኖረን ይገባል። ዜጎችን ከሰቆቃ ለመታደግ።

የኢትዮጵያውያን አሳሳቢና አስጨናቂ ስደት ሕገ መንግስታዊ ከለላ ማግኘት እንደሚኖርበት የሚያስረዱት ምሁራን ይህ ጉዳይ በተለያዩ ምክንያቶች የፖሊሲ ጥያቄ ሆኖ መስፈር እንዳለበት ያሳስባሉ። በቅድሚያ ዜጎች በሀገራቸው ሠርቶ የመኖር፣ በልቶ፣ጠጥቶ የማደር . . . መብታቸው መከበር እንደሚኖርበት፣ መንግስትም ይህን የማክበር ግዴታ እንዳለበት በሕገ መንግስት ደረጃ መጠቀሱ ለችግሩ መፍቻ አንድ መንደርደርያ ሊሆን እንደሚችል ፤ ይህን ማሳካት የማይችል መንግስት ደግሞ ሥልጣን ላይ የመቆየት ሕገ መንግስታዊ መብት ሊኖረው እንደማይችል ይተነትናሉ። ጉዳዩ የገዘፈ መሆኑ ታውቆ በህገ መንግስት ደረጃ ከለላ ከተሰጠው በኋላ ደግሞ መንግስት ኢትዮጵያውያንን ከስደት ለመታደግ የሚያስችሉ፣ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሳይሆን ምድር ላይ ባለው ሀቅ ዜጎች በሀገራቸው ሰርተው መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ መቸገር ይኖርበታል። ምሁራን ይህን በመፍትሄ ሀሳብነት ይጠቁሙ እንጂ የህገ መንግስት አንቀጾችና በየምዕራፉ የሚያወጣቸውን የራሱን አዋጆች ሳይቀር በጠመንጃ መደፍጠጡ ልዩ መገለጫው የሆነ እንደ ኢህአዲግ አይነት አገዛዝ ይህን የመስማትም ሆነ የማሳካት ፍላጎት አይኖረውም። መፍትሄው የሚገኘው ህገ መንግስት የሚያከብር፣ በዜጎቹ ላይ ሳይሆን ለዜጎቹ የሚቆም መንግስት ሲኖረን ብቻ ነው። ለዚያ ያብቃን።


◇ ◇ ◇



# AL ANDALAS CAFE

እድሳቱን አጠናቆ በተለመደው ቅልጥፍናና ትህትና
ደንበኞቹን ሊያስተናግድ ተዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል!!!



የኢትዮጵያ ቡና ፤ ሽሮና የተለያዩ
ቅመማቅመሞች አሉን!
ምርጥ እንጀራም ያገኛሉ!

**127 HALDON ST,**
**LAKEMAB**
**TELE (02) 97589078**


በየመን ፤ በደቡብ አፍሪካና በሊቢያ በግፍ ህይወታቸውን ያጡ ወገኖቻችንን ነፍስ
በቀኙ ያስቀምጥልን!